# የይሖዋ ምስክሮችና

# አስተምህሮአቸው

## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

በተስፋዬ ሮበሌ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
Ethiopian Evangelical
Baptist Church
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

ራዕይ አሳታሚ
የመጀመሪያ እትም 1991 ዓ.ም.
ሁለተኛ እትም 1995

# የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው

## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን – ተስፋዬ ሮበሌ

# The Teachings of Jehovah's Witnesses

## as Evaluated/Judged by The Word Of God – Tesfaye Rohele

የዘመን አቆጣጠሩ እ. ኢት. አ. (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር) ካልተባለ በስተቀር በጎርጎርዮሳውያን አቆጣጠር ማለት ነው።

የተለየ መግለጫ ካልቀረበ በስተቀር በመጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች በ1954 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

የሽፋን ሥዕል – ሠዓሊ እንየሁ ጸጋዬ ናቸው።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። (Copyright C 1999 – Raey Publishers) ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነ ክፍሉን በተለያዩ መንገዶች ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም ዓይነት መልኩ መረጃዎችን ለመውሰድ ከተፈለገ በትክክል ምርጫውን ጠብቆ ሊጠቀስ፥ በእግርጌ ማስታወሻዎች ሊመላከት ይገባዋል።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ. 101539
አዲስ አበባ

RP.04 2M

## ምስጋና [Acknowledgments]

ፍጹም ልሠራ በማልችልበት ጊዜ ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ ያስቻለኝና የረዳኝን ልዑል እግዚአብሔርን ከልብ አመሰግናለሁ።

የከበረ ጊዜውን መሥዋዕት በማድረግ ሆሄያቱን በማረም፥ ሰዋሰውን በማስተካከል፥ የረዳኝን ወንድም ምኒልክ አሰፋውን እጅግ በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ።

እንዲሁም በጸሎትም ሆነ የሚያስፈልገኝን ሁሉ በመርዳት ከጎኔ ለቆሙት፦ ወንድም አሰፋው ታደሰና ባለቤቱ እመቤት ዓለሙ፤ የመጽሐፉን የሽፋን ሥዕል ውብ አድርጎ ያዘጋጀውን ሠዓሊ እንየው ጸጋዬን፤ በርዕስ ጉዳዩ ላይ መጽሐፍ እንድጽፍ ያበረታታኝን ወንድም ደስታ ደምሴን እንዲሁም የመጽሐፉን ረቂቅ በኮንፒውተር አሳምራ የተየበችውን እኅት መሠረት ዳምጠውን፥ አንዳንድ ጠቃሚ መጻሕፍትን ፎቶ ኮፒ አድርጎ የሰጠኝን ዶክተር አንድሬው ኖክ [Dr. Andrew Noch]ን፥ የይሖዋ ምስክሮች በኢትዮጵያ የሚሰውን ጽሑፍ እንድጠቀምበት የፈቀደልኝን ዶክተር ስቲቨ ስትራውስ [Dr. Steve Strauss]ን እግዚአብሔር ይባርካችሁ ለማለት እወዳለሁ። ለሁሉም ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ!

## የመጽሐፉ መታሰቢያነት

ክርስቶስን የሕይወቱና የሐሳቤ አልፋና ዖሜጋ እንዳደርግ ለአስተማሩኝ፥ በቃልም በተግባርም ምሳሌ ለሆኑኝ አስተማሪዎቼ፡-

- አቶ ዮሴፍ መንግሥቱ
- አቶ ምኒልክ አስፋው
- ሚስተር ጆን እና ሚስስ ሜሪ ካርፔንተር
- ሚስተር እና ሚስስ አርተር ማክሌን
- አቶ ለዐከ ታፈሰ
- ዶክተር ብራይን ሆልት

እንዲሁም ብዙ የተማርኩባቸው፥ በክርስቶስ ፍቅር ዘወትር በልቤ ለሚኖሩት የኮልፌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት፥ የአገልግሎት ሥልጠናና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት (1988 ዓ.ም.–1990 ዓ.ም.) ተማሪዎቼ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

## Dedication

**This book is dedicated to my teachers who have taught me that Christ is the ALPHA and OMEGA of thought and life:-**

- **Ato Yosef Mengestu**
- **Ato Menelik Asfaw**
- **Mr. John and Mary Carpenter**
- **Mr. And Mrs. Arthur Mac Lean**
- **Ato Leake Tafesse**
- **Dr. Brian Holt**

**Finally, I would also like to dedicated this book to all of my students from whom I have learned much: Kolfe KHC Bible School (1996-1998) students, in the catechism and Ministry Classes.**

## መቅድም

“የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን” የተባለው ይህ መጽሐፍ ክርስቲያኖች መሠረተ እምነታቸው ከእግዚአብሔር ቃል የተቀዳና በአመክንዩ የተደገፈ ለመሆኑ ቃለ እግዚአብሔርን ዋቢ በማድረግ ከመናፍቃን ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማስቻል ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን የይሖዋ ምስክሮችም ይህን መጽሐፍ በጥሞና እንዲመለከቱት አሳስባለሁ።

*የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር* (Watchtower Bible and Tract Society) የሚባለው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት በ1994 ዓ.ም. “ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር” በሚል ርዕስ 445 ገጽ ያለው መጽሐፍ ለንባብ አብቅቶአል። ይህ መጽሐፍ እንደማንኛውም *‘የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ’* የድርጅቱን መሠረተ እምነት “ከአደጋ” ለመጠበቅ እንዲሁም የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለመቃወም እንዲያስችል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። መጽሐፉ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት እንዴት መቃወም እንደሚቻል፥ ኢየሱስ ፍጡር ነው ለሚለው የድርጅቱ ትምህርት “ማስረጃ” የሚያቀርብ፥ መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንዳልሆነ፥ አካላዊ ህልውና እንደሌለው፥ የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን ይልቁንም ትምህርቱ ከአረማውያን መድበለ አማልክት እንደተወሰደ በተጨማሪም ይህንና ይህን የመሳሰሉ ሌሎች መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮዎችን የሚቃወሙ ርዕሶችን ያካተተ ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች ለእንደዚህ ዓይነቱ የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት መልስ ለመስጠት የሚያስችል ዕውቀት የላቸውም። ለዚህም ነው በመናፍቃን ላይ ለብዙ ዓመት የሠራው የሥነ–መለኮት ምሁር፥ ዶክተር ዋልተር ማርቲን “ለአሥራ አምስት ቀናት በይሖዋ ምስክሮች የተማረ ሰው በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ የአማካይ [average] ክርስቲያንን እምነት ሊያናጋ ይችላል” የሚለው። ይህ አባባል ለብዙ ዓመት የይሖዋ ምስክሮች ንቁ ተሳታፊ አባል የነበረን የአንድ ሰው ምስክርነት ያስታውሰኛል፡-

> “የይሖዋ ምስክሮች በሚያስተምሩበት ማንኛውም ትምህርት ላይ ‘ማስረጃ’ ይሆናሉ የሚሉአቸውን ጥቅሶች ከእግዚአብሔር ቃል ላይ ይጠቅሳሉ። በዚህም መንገድ ምንም በማያውቀው ለጋ አእምሮዬ ውስጥ *‘የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት’* አስተምህሮን ጠቀጠቁበት። የይሖዋ ምስክር ከመሆኔ በፊት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የማውቀው ነገር አልነበረኝም። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ

‘ብዙ ሰለ አወቅሁ’ ለመስክ አገልግሎት ከአስጠኝዬ (ከአስተማሪዬ) ጋር ወጣሁ። በመጀመሪያም ቀን የመስክ አገልግሎቴ ሁለት የባፕቲስት፣ አንድ የሉተራን እንዲሁም ሦስት የፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አባላትን እምነት አናጋሁ። ብዙ ክርስቲያናችም ለቃለ እግዚአብሔር መሃይማን የመሆናቸው ጉዳይ እጅግ አስደነቀኝ” [Don Nelson, “That Hideous Strength: The Watchtower Society”, Christian Research Newsletter, March/April 1991, p.1]

የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮአቸውን በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ ይረዱናል የሚሉአቸውን ጥቅሶች አጥንተው ነው በራችንን የሚያንኳኩት። ከዚህም በተጨማሪ “ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር” የሚለው *‘የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ’* ውስጥ የይሖዋ ምስክሮች ለመስክ አገልግሎት ወጥተው የሚያገኙአቸውን ሰዎች እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው፣ ውይይት ቀስቃሽ የሆኑ ርዕሶችን በማቅረብ በመረጡት ርዕስ ጉዳይ ላይ ምን ምን መናገር እንደሚጠበቅባቸው በሰፊት ያስተምራል። ይህ ብቻም አይደለም መጽሐፉ፡- “ፍላጎት የለኝም”፣ “ስሃይማኖት ግድ የለኝም”፣ “የይሖዋ ምስክሮችን አልፈልግም”፣ “የራሴ ሃይማኖት አለኝ”፣ “እኛ ክርስቲያኖች ነን”፣ “ሥራ አለብኝ”፣ “አዘውትራችሁ የምትመጡት ስምንድን ነው?”፣ “የእናንተን ሃይማኖት በሚገባ አውቀዋለሁ”፣ “ገንዘብ የለንም”፣ “ቡዲስት ነኝ የሚል ሰው ቢያጋጥም”፣ “ ‘ሂንዱ ነኝ’ የሚል ሰው ቢያጋጥም”፣ “ ‘አይሁዳዊ ነኝ’ የሚል ሰው ቢያጋጥም”፣ “ ‘እስላም ነኝ’ የሚል ሰው ቢያጋጥም” ምን ዓይነት መልስ መስጠት እንዳለባቸው ይተነትናል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተቀናጅቶ የመጣውን የመናፍቃን እንቅስቃሴ ጤናማ በሆነ አስተምህሮ ለመገደብ እንዲያስችል ነው፡- *“የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን”* የተባለው ይህ መጽሐፍ የተጻፈው።

ዛሬ በዓለማችን ከ5.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት የይሖዋ ምስክሮች በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ከአንድ ቢሊዮን ሰዓት በላይ በመጠቀም፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ሳይሆን ፍጡር ነው፤ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና የለውም፣ አምላክም አይደለም ወዘተ የሚለውን አስተምህሮ በሃቢቱና በየመንገድ ዳሩ በትጋት ይናገራሉ። ይህንንም ትምህርት በሰፊት የሚያትቱትን ጽሑፎች ያሠራጫሉ። በዓለም ዙሪያ በአንድ ደቂቃ 45 ሰኮንድ ውስጥ አንድ ሰው የይሖዋ ምስክር አባል ይሆናል። በእንዲህ ዓይነት ፍጥነት በመስፋፋት ቤተ ክርስቲያንን አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያደረሳትን መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ስመግታት እንዲያግዝ ጭምር ነው ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው።

የክርስቶስን ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ የመስበክ ኀላፊነት የተሰጠው ለማን ነው? ዛሬ ለይሖዋ ምስክሮች የምሥራቹን ቃል የሚናገር ማነው? የይሖዋ ምስክሮች ክርስቲያኖችን ጨምሮ በየቀኑ የብዙ ሰዎችን ቤት ያንኳኳሉ፣ ከብዙ ሰዎችም ጋር ይገናኛሉ። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች ለይሖዋ ምስክሮች የሚሰጡት መልስ እጅግ አሳዛኝ ነው። እንዲህም በማለት ያባርሩአቸዋል፡- “አዝናለሁ፣ ከእናንተ ጋር ለመወያየት ፈቃደኛ አይደለሁም”፣ “እእእ. . . እናንተ ናችሁ አውቃችኋለሁ”፣ “እኔ ክርስቲያን ነኝ”፣ “ጊዜ የለኝም” ወዘተ። እኛ ክርስቲያኖች ወንጌላውያንን ወይም ሚሲዮናውያንን ራቅ ወዳሉ አገሮች እንልካለን የሚሄዱበትንም አገር ወይም አካባቢ ቋንቋና ባህል እንዲለምዱ አስቸጋሪና ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ትምህርቶችንና ሥልጠናዎችን እንሰጣለን። ነገር ግን በራችንን ለሚያንኳኩ፣ ዘውትር በየመንገዱ ዳር ለምናገኛቸው፣ ደኅንነት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጊዜና ሸክም እንዴት አጣን? በእርግጥ በመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉትን ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት የማምጣት ኀላፊነት አለብን። ለይሖዋ ምስክሮች በክርስቶስ የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ለመናገር ፍላጎቱ እያለን አቀራረቡና ዕውቀቱ ለቸገረን ይህ መጽሐፍ መፍትሔ አለው። መጽሐፉንም ሆነ ትምህርቱን አስመልክቶ ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሂስ ካልዎት በሚከተለው አድራሻ ቢጽፉልኝ ይደርሰኛል፡-

ተስፋ የወንጌላውያን ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመ. ሳ. ቁጥር 70295
አዲስ አበባ

**TESFA Evangelical Society For Apologetics,**
**P. O. Box 70295**
**Addis Ahaba, Ethiopia**

ተስፋዬ ሮበሌ
ታኅሣሥ 1991 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# መግቢያና የምልክቶች መፍቻ

ይህ መጽሐፍ አራት ምዕራፎች አሉት። ምዕራፍ አንድና ምዕራፍ አራት ለክርስትና እምነት መናፍቃን ሁሉ ሊያገለግሉ የሚችሉ መሠረታዊ መርሆችን ያካተተ ነው። መቼም ከፀሐይ በታች ያሉትን መናፍቃን ሁሉ እናጥና ብንል ጊዜውም፥ ትልበቱም ሊኖረን አይችልም። ነገር ግን ዋና ዋና መናፍቃንን [Major Cults] ጊዜ ሰጥተን በማጥናት በተጓዳኝ ደግሞ ሁሉም መናፍቃን ያላቸውን ተመሳሳይ ባሕርይ፥ መናፍቃን ነፍቀዋል የምንለው ከየት ክልል ሲወጡ እንደሆነ፥ ለሰ መናፍቃን ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት፥ የመናፍቃን ለኬታማነት ምክንያት ምን እንደሆነ፥ የእግዚአብሔርን መንጋ ከመናፍቃን እንቅስቃሴ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን የምንመለከትበት ክፍል ነው።

ምዕራፍ ሁለት የይሖዋ ምስክሮች በዓለም ዙሪያና በኢትዮጵያ ያላቸውን አጠቃሳይ እንቅስቃሴና ታሪክ በስፋት የምንማርበት ቦታ ነው።

በምዕራፍ ሦስት በጥልቀት የምንመለከተው የይሖዋ ምስክሮችን አስተምህሮ ነው። ለአስተምህሮቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ የምንሰጠው በዚሁ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። በእያንዳንዱም ክፍል መጀመሪያ ላይ የሚከተሉትን ምልክቶች እናገኛለን፡—



ይህ ምልክት የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ትጹስና የትራክት ማኅበር ዓርማ ነው። ይህ ምልክት ባለበት ርዕስ ሥር የምንመለከተው የይሖዋ ምስክሮችን አስተምህሮ የራሳቸውን ጽሑፍ በዋቢነት በማቅረብ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስና የሚዛን ምልክት ባለበት ስፍራ ስላይ የተመለከትነውን የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር እንመዝነዋለን።



የመጽሐፍ ቅዱስ ስዕል ባለበት ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ በርዕስ ጉዳዩ ላይ የሚያስተምረውን ትምህርት በአጭሩ የምንከልስበት ስፍራ ይሆናል።



በጥያቄ ምልክት ሥር ደግሞ የይሖዋ ምስክሮች ሊጠየቁት የሚገባቸውን ጥያቄዎች አስፍረናል።

የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው ላይ ሂስ የሚሰነዝሩትን፡— "ተቃዋሚዎች" እንዲሁም እምነቱን ጥለው የወጡትን፡— "አፈንጋጮች" ይሉአቸዋል። ከእነዚህም ሰዎች ጋር መነጋገርም ሆነ ጽሑፎቻቸውን ማንበብ በጥብቅ የተከለከለ ነው። እንዲያውም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት እነዚህን ጽሑፎች፡— "መንፈሳዊ የዘሙት ስዕሎች" ይላቸዋል። "በሰይጣን ጠረጴዛ ላይ ማዕድ መብላት" እንደሆነም አድርጎ ያስተምራል።

በድርጅቱ ትምህርት መሠረት የይሖዋ ምስክሮች ከ"አፈንጋጮች" ወይም ከ"ተቃዋሚዎች" ጎራ ፈርጀውን ከእኛ ጋር ያላቸውን ውይይት እንዳያቆሙ ቁልፍ የሆኑ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የአስተምህሮአቸውን ከንቱነትና የድርጅቱን ስህተት ልናሳያቸው እንችላለን።

ጥያቄዎቹ በተለይ ያነጣጠሩት የድርጅቱን ሐሰተኝነት በማጋለጥ ላይ ነው። ምክንያቱም የይሖዋ ምስክሮች የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ላይ ያላቸው እምነት እጅግ ከፍተኛ ነው። እንደ ይሖዋ ምስክሮች እምነት እግዚአብሔር መንፈሳዊ ምግብ ለሥጋ ለባሽ ሁሉ የሚያወርደው በዚህ ድርጅት አማካኝነት ብቻ ነው። በእግዚአብሔር የሚመራና የእግዚአብሔር ብቸኛ የሆነ ምድራዊ ወኪል ይኸው ድርጅት ነው። እንዲያውም በዚህ ድርጅት ጥላ ሥር ካልተጠለሉ በስተቀር እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደኅንነት አይሰጥም። የድርጅቱን ጽሑፍ በእማኝነት በማቅረብ የድርጅቱን ሐሰተኝነት ለተከታዮቹ ማሳየት ስብዙ አቅጣጫ ጠቀሜታው ታላቅ ነው።

# ማውጫ

## ምዕራፍ አንድ፦ ቅኝት

1.1 ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው?..........3
1.2 ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?..........6
1.3 የመናፍቃን ሥነ-መለኮታዊ ባሕርይ..........7

## ምዕራፍ ሁለት፦ የይሖዋ ምስክሮች አነሣሥና እድገት

2.1 በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ?..........16
2.2 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በዓለም አቀፍ ደረጃ..........19
2.3 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያ..........21
2.4 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲካዊ
ዘገባ በኤርትራና በኢትዮጵያ..........22
2.5 የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ..........25
2.6 የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ..........36

## ምዕራፍ ሦስት፦ የይሖው ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን?..........50
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም..........60
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ..........74
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ..........92
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ..........104
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥
በነፍስና በሲኦል ላይ..........123
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት..........132

## ምዕራፍ አራት፦ ሰዎችን ከመናፍቃን እንዴት እንጠብቅ?

4.1 ሰዎች መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ?..........151
4.2 ሰዎች መናፍቃንን እንዳይከተሉ
እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን?..........155
4.3 የይሖዋ ምስክሮችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት
ተመካሪ አቀራረብ..........160

# ምዕራፍ አንድ

## ቅኝት

1.1 ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው?..........3
1.2 ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?..........5
1.3 የመናፍቃን ሥነ-መለኮታዊ ባሕርይ..........7

## 1.1 ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው?

"ብአንድ ርዕስ ነገር ላይ ውይይት ከመጀመራችን በፊት ልናስተላልፈው የምንፈልገውን ሐሳብ በትክክል ሊወክሉልን በሚችሉት ቃላት ላይ ተመሳሳይ እይታ እንዲኖረን በቃሉ ትርጉም እንስማማ።" የሚለውን የጥንት ግሪካውያን አነጋገር በእርግጥ ዘመን የማይሽረው፣ ብልህነት የተሞላበት አባባል ነው። ታዲያ እነዚያ የጥንት ግሪክ ሊቃውንት በዚህ እውነታ ላይ ተንተርሰው በሳይንሱ መስክ ያፈለቋቸው ፅንሰሃሳቦች፥ ያደረጓቸው ጥናቶችና ምርምሮች፣ የሰነዘሯቸው መላምቶች፣ ያቀረቡአቸው ንድፈ ሐሳቦች ለዘመናችን ሳይንሳዊ ዕውቀትና ግኝት ፈር ቀዳጅና ፋና ወጊ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። እኛም ኑፋቄ የሚለውን ቃል በመፍታት ትምህርታችንን ብንጀምር ከብዙ አቅጣጫ ጠቀሜታው ታላቅ ነው።

ከቋንቋ አጠቃቀም የምንግረው አብዛኛውን ጊዜ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጉም እንዳለው ነው። ነገር ግን የቃሉን እማራጭ ትርጉም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኑፋቄ የሚለው ቃል የወከለው ትርጉም ምን እንደሆነ ቀጥለን እንመስከቃለን።

### የቃሉ ጥሬ ትርጉም

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ፣ <u>የዐማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፣ ኑፋቄ የሚለውን ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ይፈታዋል (ገጽ 662)፦

- ነፈቀ – ዐመትን ዕለትን ወርን ከፈለ፥ ለየ፥ ወይም አንድ ሙሉ የኾነ ነገርን ከኹለት ከፈለ፥ ወይም የብርቱካንን፥ የሎሚን አካል ከፍልፍሎች በእየከፍላቸው ለየ። [በዚህ ትርጉም መሠረት ነፈቀ ማለት አንድን ነገር ከሁለት ከፈለ፥ ለየ፥ መደበ ማለት ነው።]

- ነፈቀ – ከሃይማኖት ወጣ፥ ተጠራጠረ፥ መናፈቅን፥ ከሀዲን ኾነ ነፈቀ። [በዚህ ትርጉም መሠረት ነፈቀ ማስት ከትክክለኛው የእምነት መንገድ ወጣ፥ ሳተ ወይም ትክክለኛውን እምነት ካደ፥ ተጠራጠረ ማስት ነው።]

ኪዳነወልድ ክፍሌ፣ <u>መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዘገበ ቃላት ሐዲስ</u>፣ ደግሞ ኑፋቄ የሚለውን ቃል እንዲህ ይተረጉመዋል (ገጽ 645–646)

- መናፍቅ (ቃት ቀን) ናፋቂ አናፋቂ፤ የማጠራጠር የሚያጠራጥር፤ ጠርጣሪ አጠራጣሪ፤ ሃይማኖቱ ሕጹጽ የሆነ፣ ሞሉ እና ፍፁም ትክክል ያይደለ፤ መንፈቁን እምኖ መንፈቁን የሚክድ። [በዚህ ትርጉም መሠረት መናፍቅ ማለት እምነቱ ትክክል ያልሆነ፣ ግማሹ እውነት ግማሹ ደግሞ ሐሰት የሆነ እምነት ያለው ማለት ነው።]

- ነፈቀ — መንፈቅ፣ መሠንጠቅ፣ አስተካክሎ መክፈል መለየት። [በዚህ ትርጉም መሠረት ነፈቀ ማለት እኩል ለእኩል ለየ፣ ከፈለ ማለት ነው።]

- ኑፋቄ — በቁሙ፤ መክፈል መካፈል፤ ክፍያ አከፋፈል። ጥርጥር፣ ጥርጠራ፤ ምንታዌ።

ይህ እንግዲህ ነፈቀ ወይም ኑፋቄ ለሚለው የግዕዝ ቃል የቋንቋው ምሁራን ለቃሉ የሰጡት ፍቺ ነው። ይህን ፍቺ መሠረት በማድረግ ነፈቀ፣ ኑፋቄ፣ መናፍቅ የሚሉት ቃላት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የወከሉት ትርጉም ቀጥሎ በጥቅሉ የተባለውን ይመስላል። *መናፍቅ (ነፈቀ/ኑፋቄ) ማለት ትክክለኛውን እምነት የተወ፣ የካደ፣ የጣለ፤ ከትክክለኛው እምነት ግማሹን አምኖ ግማሹን የካደ፤ ትክክለኛውን እምነት የሚጠራጠር፣ ልቡና አሳቡ የሚዋዥቅ፣ የሚዋል ማለት ነው።*

## የቃሉ ሥነመለኮታዊ አጠቃቀም

ኑፋቄ ወይም ነፈቀ ለሚለው የግዕዝ ቃል የእንግሊዝኛ አቻ ትርጉሙ ክልት [CULT] እና ሔረሲ [HERESY] የሚሉት ቃላት ናቸው። ክልት የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ክልተስ ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም፡— "ለመለኮት አምልኮን አቀረበ ወይም ክብርን ሰጠ" ማለት ነው። የላቲን ቩልጌት ትርጉም ቃሉን የሚጠቀምበት ለእውነተኛው አምላክም ሆነ *ለጣዖታት* የሚቀርበውን አምልኮ በሚያሳይ መልኩ ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 17፥23 የአቴና ሰዎች ያመልኩአቸው ለነበሩት ጣዖታት ይቀርብላቸው የነበረውን አምልኮ ሲያሳይ፤ በቁጥር 25 ላይ ደግሞ "ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ" ለሚሰጠው ልዑል እግዚአብሔር የሚሰጠውን አምልኮና ክብር ለማሳየት ቃሉ ጥቅም ላይ ውሎአል[1]።

---

1. Alan W. Gomes, Unmasking the Cults. (Grand Rapids: Zondervan, 1995), ገጽ 7



ሔረሲ የሚለው ቃል "ሔረሲስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተወረሰ ሲሆን፤ ትርጉሙም "ምርጫ" ወይም "የተመረጠ ነገር" ማለት ነው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ግሪክ ሔረሲ የሚለው ቃል በአብዛኛው ጥቅም ላይ የዋለው "ክፍፍል" ወይም ልዩነት በሚለው ትርጉሙ ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን *ሔረሲ የሚለውን ቃል* ትጠቀምበት። የነበረው መሠረታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንደሚክድ ትምህርት አድርጋ ነበር (የሐዋ. 24፥14)[2]

በዘመናችን ያሉ ብዙ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ኑፋቄ ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጉም (ግላዊ) የተለያየ ቢሆንም፤ ብዙዎቹ የሚስማሙበት ከዚህ የሚከተለውን ነው፡— *የክርስትና እምነት መናፍቃን እራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፤ በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዓት የሚከተሉ፤ ይህም አስተምህሮ ከስልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ጽሑፎች የተቀዳውን የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን መናፍቃን ብለን እንጠራቸዋለን*[3]። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መናፍቅ የሚለውን ቃል የምንጠቀምበት በሥነ መለኮታዊ አጠቃቀሙ ነው።

## 1.2 ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?

መጽሐፍ ቅዱስ ለመናፍቃንና ለትምህርታቸው ትልቅ ትኩረት ሰጥቶአል። የሥነመለኮት ሊቃውንት እንደሚሉት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንድ ሦስተኛው ያተኮረው በመናፍቃንና በትምህርቶቻቸው ላይ ነው። ይህ እውነታ የሚያስገነዝበን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመናፍቃንና ለትምህርታቸው ምን ያህል ትኩረት እንደሰጡና እኛም ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ማጥናት እንዳለብን የሚያስተምረን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት በርዕስ ጉዳዩ ላይ ለፊ አስተያየት ለጥተዋል በማለት ብቻ ፍሬ ነገሩን በደፈናው ማለፍ አግባብ ስለማይሆን በእኛ እምነት ዋና ዋና የምንላቸውን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ጥቅሶች ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል።

- ሐሰተኛ እረኞች፣

ኢሳ. 66፥10–12፤ ኤር. 23፥2፤ 50፥6፤ ሕዝ. 34፥2–3፤ ዮሐ. 10፥12

◆ ሐሰተኛ ነቢያት

ዘዳ. 13፥5፤ 18፥22፤ ኢሳ. 9፥15፤ ኤር. 2፥6፤ 5፥31፤ 14፥14፤ 23፥16፤ ሕዝ. 13፥2፤ 22፥28፤ ሆሴ. 9፥7፤ ሚክ. 3፥5፤ ሰፎ. 3፥4፤ ዘካ. 13፥3፤ ማቴ. 7፥15፤ 24፥11፤ ማር. 13፥22

◆ ሐሰተኛ አስተማሪዎች

ማቴ. 5፥19፤ 15፥9፤ 1ጢሞ. 1፥7፤ 4፥2፤ 6፥3፤ 2ጢሞ. 1፥11፤ 2ጴጥ. 2፥1

ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎቱ ዘመን ከሐሰተኛ አስተማሪዎችና እረኞች ጋር በመፋጠጥ ብዙ ጊዜውን አሳልፎአል። በመጨረሻም ለሞት አልፎ የተሰጠው በእነዚህ ሰዎች ነበር።

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል መስበክ ብቻ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱ ሊገጥማቸው ያለውን ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ መከራ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። እንደ ጌታ ትምህርት ከእነዚህ መከራዎች ሁሉ እጅግ የከፋው ብዙዎችን በማሳት በእርሱ ስም የሚመጡት የሐሰተኛ ነቢያት፣ እረኞች፣ አስተማሪዎችና የሐሰተኛ ክርስቶሶች ተግዳሮት ነው (ማቴ. 24፥15፤ 7፥15-23)። የመጀመሪያዎቹን አምስት መቶ ዓመታት የሥነ መለኮት ታሪክ ስንመረምር እነዚህ የክርስቶስ ትንቢታዊ ቃሎች እውን ሆነው እናገኛቸዋለን።

ስመገመት በሚያስቸግር ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ያለውን የመናፍቃንን እንቅስቃሴ ጤናማ በሆነ አስተምህሮ ስመግታት የመናፍቃንን ባሕርይ፣ ታሪክና አስተምህሮ ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያት ከመናፍቃንና ከትምህርታቸው እንድንጠነቀቅ ቢያሳስቡንም የኑፋቄ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ መታየቱ አልቀረም። እንዲያውም አሁን በእኛ ዘመን ከክርስትና እምነት ተከታዮች በላይ በጣም እየተስፋፋ ቤተ ክርስቲያንን አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያደረሳት የመናፍቃን ከፍተኛ እድገት ነው ("የመናፍቃን ስታቲስቲክ" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል)። ለዚህ ነው ቲም ጃክብሰን የተባሉት የእግዚአብሔር ሰው "ዓለማችን በመሲህ ነን ባዮች መጥለቅለቋ ለማንም ሰው ግልጽ ሆኖ የሚታየው እውነት ነው" ያሉት።

2. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 17
3. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 7



ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመጠበቅ ኃላፊነቱአን እንድትወጣ እንዲሁም በመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ለማምጣት የመናፍቃንን ትምህርትና አሠራር ማወቅ ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ የመስበክ ኃላፊነት አለበት። ኃላፊነት ደግሞ አንድ ቀን ያስጠይቃል። ስለዚህ በመናፍቃን ዓለም ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቸል ልንላቸው አይገባም። አንዳንድ ክርስቲያኖች የመናፍቃንን መንፈቅ (መላት) በማወቃቸውና እንቅስቃሴውንም በመኮነን ብቻ ይረካሉ። መናፍቃንን ኮንናቸውም አልኮነናቸው የሚያመጣው ምንም ሰውጥ የለም። በመሠረቱ ሰዎችን በመኮነን የሚሠራ ምንም ሥራ የለም። ከዚህ ይልቅ ግን ሰዎች የሚሉትን ነገር በትክክል ተረድቶ ልክ አለመሆናቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ዋቢ አድርጎ በመጥቀስ ማሳየት ያስፈልጋል።

መናፍቃን እንደ ማንኛውም ሰው መዳን ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም እነርሱ እንደ ሌሎች ሰዎች ጠፍተዋል። ወደ ጠፉ ሰዎች መሄድ ደግሞ የክርስቲያኖች ሁሉ ኃላፊነት ነው። እግዚአብሔር ዐደራ ሰጥቶናል። ያም ዐደራ ለሰዎች ሁሉ እውነተኛውን የምሥራች ቃል መንገር ነው።

## 1.3 የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ ባሕርይ[1]

### 1.3.1 "የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ ባሕርይ" ስንል ምን ማለታችን ነው?

በዚህ ክፍል የምንመለከተው የመናፍቃንን ሥነ መለኮታዊ ባሕርይ ነው። ይኸውም ከሃይማኖታዊ አስተምህሮአቸው በመጀመር የአስተምህሮአቸውን ከንቱነት እንዴት አድርገን መለየት እንደምንችል በእርጋት እንመለከታለን። የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ አቋም ከልምምዳቸው ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፤ ነገር ግን በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው ልምምዳቸውን ሳይሆን ሥነመለኮታዊ አቋማቸውን ነው።

ከዚህ በታች በዝርዝር የምናየው የመናፍቃንን አስተምህሮ ሲሆን ሁሉም መናፍቃን ሁሉንም ባሕርይ ያሳያሉ ማሰት ግን አይደለም። ሆኖም አብዛኞቹ መናፍቃን ባሕርያቱን በተወሰነ መጠን ያሳያሉ።

1. ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው፡- Alan W. Gomes. Un masking the Cults. (Grand Rapids: Zondervan, 1995) ገጽ 24-46 በሚል ርዕስ ከጻፈው መጽሐፍ ላይ ነው።

እነዚህ ባሕርያት መሠረታዊ ልዩነት ይፈጥራሉና [ለምሳሌ፡- አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ያለመቀበል ወዘተ]።

አንድ ሰው መናፍቅ የሚባለው ከመሠረታዊው የክርስትና አስተምህሮ ሲያፈነግጥና ይህንንም አስተምህሮ ሲክድ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከመሠረታዊ እምነታቸው ይልቅ ለልምምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ። እንዲሁም እንዳንድ ክርስቲያናዊ ተቋሞች የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ዘዴን ይከተላሉ። ይህ አካሄዳቸው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት እስካልተቃረነ ድረስ ሰዎቹን መናፍቅ ሊያሰኛቸው አይችልም።

## 1.3.2 የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ ባሕርይ

### 1. አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ

መናፍቃን እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የክርስትና አስተምህሮ በአንዱ የእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ ሦስት ዘላለማዊ አካላት ይኸውም፡- አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንዳሉ አያምኑም። ምናልባትም ሁሉም መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ይክዳሉ ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም። እንዲያውም አንዳንዶች ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች የሥላሴን አስተምህሮ ከአረማውያን የመድበል አማልክት አስተሳሰብ ጋር ያመሳስሉታል፤ ይህ አስተምህሮ ከአረማውያን የተቀዳ ነው ብለው በድፍረት ይናገራሉ። አንዳንድ መናፍቃን ደግሞ ሥላሴን እናምናለን ይላሉ። ነገር ግን ሥላሴ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራሩበት መንገድ ፍጹም የተሳሳተና ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት እጅግ የራቀ ነው።

### 2. ደኅንነት በእምነት አማካይነት በጸጋ መሆኑን ይክዳሉ

ቫን ባለን እንደሚለው የሁሉም መናፍቃን የመጨረሻ ትምህርት ድምዳሜ "ራስህን ማዳን አለብህ"[2] የሚል ነው። ለእግዚአብሔር ጸጋ የከንፈር አገልግሎት ብቻ እንዲሰጡ ያደረጋቸው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያከናወነው የደኅንነት ሥራን ስለሚያቃልሉ ነው። የክርስቶስ የደኅንነት ሥራ በራሱ ሙሉ በሙሉ የማያድን ከሆነ የጎደለውን በሥራ ማካካስ ወይም መሙላት አይቀሬ ነው።

2. J. K. Van Baalen, The Chaos of the Cults (Grand Rapids: Eerdmans, 1962), 359, cited in Alan W. Gomes ገጽ. 26



እንዲያውም አንዳንዶች የክርስቶስ የማዳን ሥራ አንድ ሰው ወደ እምነት ከመምጣቱ በፊት ያሰበትን ኃጢአት የማጠብ ኃይል አለው። ነገር ግን ወደ እምነት ከመጣ በኋላ ራሱን ማዳን ያለበት በሥራ እንደሆነ አጠንክረው ያስተምራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የክርስቶስ የማዳን ሥራ ትንንሽ ኃጢአቶችን እንጂ ትልልቅ የሚባሉ ኃጢአቶችን እንደማያካትት ይናገራሉ።

ሌሎች ደግሞ የክርስቶስ የደኅንነት ሥራ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደሚሆን ነገር ግን እርሱ የጀመረውን እነርሱ ከዳር እንደሚያደርሱት ያውጃሉ።

### 3. የአካል ትንሣኤን ይክዳሉ

የክርስቶስ የአካል ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው (1ቆሮ. 15) ። መናፍቃን ደግሞ መሠረታዊ የሚባሉ የክርስትናን አስተምህሮ ማጣመም ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። እጅግ የታወቀውና የትንሣኤን አስተምህሮ የሚያጣምመው ትምህርት ትንሣኤን መንፈሳዊ የሚያደርገው ነው። ስለዚህም ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው በመንፈስ ነው ይላሉ (ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች)። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ስመሆኑ በግልጽ ይናገራል ["የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ" የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል] (ሉቃ. 24፥39፤ ዮሐ. 2፥19–21፤ ቆላ. 2፥9)

### 4. የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊት ይክዳሉ

አንዳንድ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስ በስህተት እንደተሞላ ይናገራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሥልጣናዊ ቃልነቱን በመቀነስ "አሮጌው ብርሃን" በማለት ይጠሩታል። ይህም "አዲሱ ብርሃን" ከሚባለው ከእነርሱ አስተምህሮ ማነሱን ያመለክታል።

ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደሆነ ቢናገሩም መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲስማማ አድርገው "ይተረጉሙታል"። አንዳንዶች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት የሚያቃልሉት ከእነርሱ አስተምህሮ ጋር የሚስማሙ ሌሎች ጽሑፎችን በማዘጋጀት ነው። እነዚህ ጽሑፎች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ይታያሉ።

## 5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ በመተርጎም አዲስ ትንታኔ ይሰጣሉ

መናፍቃን አብዛኛውን ጊዜ ለክርስቲያናዊ ቃላት አዲስ ትርጓሜ መስጠት ይወዳሉ። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ2ቆሮ. 11፥4 ላይ ሐዋርያት ከሰበኩት የተለየ (ገላ. 1፥6–9) ሌላ ክርስቶስ፥ ሌላ መንፈስ፥ ሌላ ወንጌል የሚለውን አጠቃቀም የሚጠቀመው። መናፍቃን ስለ ክርስቶስ፥ ስለ ወንጌል፥ ስለ ደኅንነት አብዝተው ይናገራሉ፤ ነገር ግን ቃሉን የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን በተጠቀመበት መንገድ አይደለም። [ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች ክርስቶስ ፈጣሪ ነው ይላሉ፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ የአብ የመጀመሪያ ፍጥረት ነው። እንግዲህ ክርስቶስ ለይሖዋ ምስክሮች ፈጣሪም ተፈጣሪም ነው ማለት ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ክርስቶስ ግን፡- ጅማሬ የሌለው፥ ፍጻሜ የሌለው፥ ፍጹም አምላክና በባሕሪው ከአብ ጋር ፍጹም ትክክል የሆነ ነው]። ስለዚህ አንድ መናፍቅ እኔ በክርስቶስ አምናለሁ ቢል፤ ክርስቶስን ምን ብሎ እንደሚያምነው (ፍጹም አምላክ ወይስ ፍጡር) ልንጠይቀው ይገባል። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፡- "ብዙውን ጊዜ ከመናፍቃን ጋር የምናደርገው ውይይት ፍሬ አልባ የሚሆነው ለምንወያይባቸው ጉዳዮች ትክክለኛውን ትርጉም (ግላዊ) ባለመስጠታችንና እነርሱም ምን ማለታቸው እንደሆነ እንዲያብራሩልን ስለማንጠይቃቸው ነው"[3]። ስለዚህ ለመናፍቃን ከመመስከራችን በፊት መናፍቃኑ ቁልፍ የሆኑ ቃላትን እንዴት አድርገው እንደሚጠቀሙባቸው ወይም እንደሚተረጉሙአቸው አስቀድመን ማወቅ ምስክርነታችንንም ሆነ ውይይታችንን ፍሬያማ እንዲሆን ያደርገዋል።[4]

## 6. ድርጅቶቻቸውና መሪዎቻቸው የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደራሴዎች እንደሆኑ ይናገራሉ

የብዙ መናፍቃን መሪዎች የእግዚአብሔር ብቻኛ ወኪሎች፥ ድርጅታቸውም በአምላክ የሚመራ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባቸው መንገዶች፥ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ መገለጥ ተቀባዮች አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ።

3. Martin. Kingdom of the Cults. ገጽ 19. Cited in Alan W. Gomes. ገጽ .31
4. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 24



በዚህ ጉዳይ ላይ እንደ አብነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" [The Watchtower Bihle and Tract Society] በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው የአምላክ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት እንደሆነ ይናገራሉ። የድርጅቱም ሥልጣናዊ መዋቅር "ታማኝና ልባም በሆኑ ባሪያዎች" እንደተሞላ፥ እነዚህም ባሪያዎች ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ በወቅቱ እንደሚያወርዱ የእግዚአብሔር እንደራሲዎች[5] ይታያሉ።

## 7. ከአስተምህሮአቸው ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶችን ዘለው ያልፋሉ [Compartmentalization]

በርካታ መናፍቃን ከአዋጃቸው ጋር የሚቃረኑ እውነታዎችን ትኩረት አይሰጡአቸውም ወይም አቃለው ይመለከቱአቸዋል። ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች ብዙ እውነት ሲሆኑ ያልታዩ የሐሰት ትንቢቶችን ተንብየዋል፤ ነገር ግን ይህንን አስተምህሮ እንዲገነቡ ያደረጋቸውን ትንቢታዊ መጽሐፍትን አተረጓጎም ዘዴ አሁንም አልቀየሩም። የአርማጌዶን ጦርነት በ1914 ዓ.ም. ይሆናል ተብሎ ነበር በዚህ ወቅት ሊሆን ሳይችል ሲቀር ቀኑ ወደ 1915 ዓ.ም. ከዚያም 1975 እና 1981 ተሸጋገረ[6]። ነገር ግን ይህን ትንቢት የተናገረው ድርጅት አሁንም ራሱን ከአምላክ ትንቢታዊ እውነት ተቀባይ አድርጎ ይቆጥራል።

## 8. የዘላለምን ቅጣት ይክዳሉ

ብዙ መናፍቃን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዘላለም ቅጣት የሚያስተምረውን ትምህርት አይቀበሉም። አንዳንዶች ለምሳሌ የሁለንታዊ [Universalism] ትምህርት አራማጆች የሰው ልጆች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ ሲያስተምሩ፤ ሌሎች ደግሞ አምላክ ኃጢአተኞችን ወደ አለመኖር [Annihilation] ደረጃ ያመጣቸዋል እንጂ ለዘላለም በገሃነም አይቀጣቸውም የሚል እምነት አላቸው። ለምሳሌ ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ[7] በድፍረት "የዚህ [የዘላለም ቅጣት] እግዚአብሔርን የማያከብር አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው። ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳያነቡ ለማስፈራራትና እግዚአብሔርን እንዲጠሉ ለማድረግ ነው"[8] ብሎአል።

5. በምድር በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ (1991)። ገጽ 191–195 እንዲሁም፡- ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 280–283
6. The Watchtower (1 April 1972).
7. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሁለተኛ ፕሬዝዳንት የነበረ ነው።
8. Rutherford, Let God Be True. ገጽ 79 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

## 9. ከአስተምህሮአቸው ይልቅ ለልምምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ

አንዳንድ መናፍቃን ከእውነት ይልቅ ለስሜት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ። በዚህ መሰሉ የመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ሰዎች አስተምህሮአችን ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ነው ወይ? ለሚለው ጥያቄ ሳይሆን ጥሩ ስሜት ተሰምቶኛል ወይ? ከቀድሞው ልምምዴ ጋር ይስማማል ወይ? ለሚለው ትኩረት ይሰጣሉ። ስሜትና የግል ልምምድ መጥፎ ነው ለማለት አይደለም። ነገር ግን ስሜትም ሆነ ልምምድ ተገቢ የሆነውን ስፍራ መያዝ አለባቸው። የእግዚአብሔር ቃል "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ሐሳብህ [Mind] ውደድ" ይላል (ዘዳ. 6፥5፤ ማቴ. 22፥37፤ ማር. 12፥30፤ ሉቃ. 10፥27)። ይህም ዓይነቱ አምልኮ እውነትን ከስሜት ጋር አጣምሮ የያዘ ነው። እንዲህ ቢባልም የክርስቲያኖች እምነት በእውነታ ላይ የተመሠረተ መሆኑን መዘንጋት አይገባም። በእርግጥ እውነት እንደፈረሰ፥ ስሜት ደግሞ እንደጋሪ ተከታትለው ሊሄዱ ይገባል።

## 10. ከእግዚአብሔር በቀጥታ ተቀበልናቸው ለሚሉአቸው መገለጦችና ራእዮች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ

መናፍቃን በተለይም የእንቅስቃሴው መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ቀጥተኛ ግንኙነት የተነሣ ራእይ እና መገስጥ እንደሚወርድላቸውና እግዚአብሔርም ለሕዝቡ የሚሆነውን መንፈሳዊ ምግብ የሚሰጠው በእነርሱ በኩል ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። አብዛኛውን ጊዜ መገለጦቻቸውና ራእዮቻቸው የሚያተኩሩት የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ ሊሆን በዚያን ጊዜ የእነርሱ ዕጣ ፈንታ ምን እንደሆነ የሚናገሩ ናቸው። ቃለ እግዚአብሔር "ሁሉንም መርምሩ መልካሙን ያዙ" (1ተሰ. 5፥21) ይሰናል ትንቢቱ እንደተነገረው ካልተፈጸመ ትንቢቱም ሆነ ነቢዩ ከእግዚአብሔር አይደሉም ማለት ነው (ዘዳ. 18፥22)። የአንድ ትንቢት ትክክለኛነት የሚረጋገጠው ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማቱ ነው (ኢሳ. 8፥20)።

## 11. ለተአምራቶችና ለምልክቶች ከፍተኛ ስፍራ ይሰጣሉ

እግዚአብሔር በእውነተኛ ክርስቲያኖች በኩል ድንቅና ተአምር ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የሚክዱ ሰዎች ድንቅና ተአምር ሊያደርጉ አይችሉም (ዘዳ.



18፥22፤ ኢሳ. 8፥20)። እነዚህ ሰዎች ተአምራትን ካደረጉ ያደረጉት ተአምራት ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰይጣን ነው (2ተሰ. 2፥9)።

## 12. ሥነፍጻሜን በተመለከተ የጊዜ ሰሌዳ አላቸው

ብዙ መናፍቃን ሥነፍጻሜን በተመለከተ ቋሚ የጊዜ ሰሌዳ አላቸው። ያስቀመጡትንም ቀን የእግዚአብሔር ቃል እንዲደግፍላቸው የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ዘዴን ይጠቀማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥነፍጻሜ የሚሰጠውን ትምህርት ማወቅ ለዚህ ጊዜ ይጠቅማል። በተለይ የክርስቶስን አዳኝነት ለማይቀበሉ የፍርድ ቀን እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ማቴ. 25፥31-46፤ ዕብ. 9፥27፤ ራእ. 20፥12-15)። የወቅቱን ሁኔታ ተመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንተና ለመስጠት መሞከር ጨርሶ ትክክል አይደለም። ለምሳሌ፦ በባሕር ለላጤው ጦርነት ጊዜ ፕሬዝዳንት ሳዳም ሁሴንን እንደ ክርስቶስ ተቃዋሚ (Antichrist) ሁኔታውን ደግሞ እንደ ዓለም መጨረሻ አድርገው ያስተማሩ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመፍታት የሞከሩት ከወቅቱ ሁኔታ ተነሥተው በመሆኑ ወደ ተሳሳተ መደምደሚያ ደርሰዋል። ለዚህ ሁሉ ያበቃቸው መጽሐፍ ቅዱስን ስመተርጎምና ለመፍታት የተጠቀሙበት ስልት ነው።

## 13. የአማኞችን የክህነት አገልግሎት ይክዳሉ

መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ሁሉ ካህናት እንደሆኑ ያስተምራል (1ጴጥ. 2፥4-10፤ ራእ. 1፥6፤ 5፥10)። ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ በቀጥታ ከጌታ ጋር መገናኘት ይችላል ማለት ነው።

የበርካታ መናፍቃን መሪዎች፥ ተከታዮቻቸው ለድርጅቶቻቸውና ለትምህርቶቻቸው እንዲገዙ ለማድረግ የአማኞች የክህነት አገልግሎት ይክዳሉ (1ዮሐ. 2፥26-27)።

## 14. ትክክለኛ የሆነውን የቅዱሳት መጽሐፍት አፈታት መንገድ አይከተሉም

መናፍቃን ትምህርታችን ልክ ነው ለማለት የሚሞክሩት የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ዘዴን በመጠቀም ነው። ይኸውም አንድን ጥቅስ ወይም ቃል ከዐውደ ንባቡ አላቀው ይተረጉሙታል። ለሰዋሰው አወቃቀሩም ሆነ ለክፍሉ ታሪካዊ ዳራ እንዲሁም ለክፍሉ ሥነ

ጽሑፋዊ ቅርጽ ቦታ አይሰጡም። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ራሳቸው የተሳሳተ የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት ዘዴን የሚጠቀሙበት ወቅት አለ። ድርጊቱ የሚወገዝ ቢሆንም እንኳ ይህ አጠቃቀማቸው ከመሠረታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር እስካልተጋጨ ድረስ መናፍቃን ልንላቸው አንችልም።

### 15. ለደቃቅ አስተምህሮዎች ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ

ብዙ መናፍቃን ለመሠረታዊው አስተምህሮ ከሚሰጡት ስፍራ ይልቅ ለትናንሽ ትምህርቶች የሚሰጡት ስፍራ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ለምሳሌ፦ ለአለባበስ፥ ለአምልኮ ቀናት፥ ለክብረ በዓላትና፥ ለልደት ቀናት ወዘተ የሚሰጡት ቦታ እጅግ የላቀ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

# የይሖዋ ምስክሮች አነሣሥና እድገት


2.1 በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ?..........16
2.2 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በዓለም አቀፍ ደረጃ.....19
2.3 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያ.............21
2.4 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲካዊ
ዘገባ በኤርትራና በኢትዮጵያ .................................22
2.5 የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ...............................25
2.6 የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ.........................................36

## 2.1 በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ?

ይህን ጥያቄ በትክክል ለመመለስ አዳጋች የሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ምክንያት ትክክለኛ ስታቲስቲካዊ ዘገባ አለማግኘት ነው። በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚያስገነዝቡን በአሁኑ ወቅት ወደ 30 ሚሊዮን የሚደርሱ መናፍቃን በዓለማችን ይገኛሉ። የመናፍቃኑ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ በትክክል እንዳይታወቅ ያደረገው ምክንያት ድርጅቶቹ የተከታዮቻቸውን ቁጥር በትክክል አለማወቃቸው ነው። ሁለተኛው ምክንያት የሥነ መለኮት ምሁራን "ኑፋቄ" ለሚለው ቃል የሚሰጡት ግላዊ አንድ ወጥ አለመሆኑና ይህ ቃል እንማንን በቃሉ ትርጉም ሥር እንደሚያካትት ከአንድ ተመሳሳይ አቋም ላይ አለመደረሱ ነው። ለማንኛውም በተለያዩ አጋጣሚዎች ይፋ የሆኑ ስታቲስቲካዊ ዘገባዎችን መሠረት በማድረግ የመናፍቃኑ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። አሁን የይሖዋ ምስክሮችን አጠቃላይ ስታቲስቲክ ወደ መመልከቱ እንዝለቅ።

### በዓለማችን ላይ ምን ያህል የይሖዋ ምስክሮች አሉ?

### 1. የአባላት ብዛት

እንደ ጎርጎርዮሳውያን የዘመን አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. በ232 አገሮች በተደረገው ቆጠራ ንቁ የይሖዋ ምስክር ተሳታፊ አባላት ቁጥር 5,599.931 ሲሆን ይህ ቁጥር በ1998 ዓ.ም. ወደ 6 ሚሊዮን ያሻቅባል ተብሎ ይገመታል። በ1997 ዓ.ም. በተደረገው የ"መታሰቢያ" አገልግሎት ["Memorial" Service] (የይሖዋ ምስክሮች የጌታን እራት የሚያስቡበት ቀን የመታሰቢያ አገልግሎት ብለው ይጠሩታል) 14,322,226 ሰዎች ፕሮግራሙን ተካፍለዋል[1]። ይህ የሚያሳየን የይሖዋ ምስክሮች ከንቁ ተሳታፊ አባሎቻቸው እጥፍ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ አወንታዊ ተጋቦት እንዳላቸው የሚያመላክት ነው። በዓለም ዙሪያ በአንድ ደቂቃ 45 ሴኮንድ ውስጥ አንድ ሰው የይሖዋ ምስክር አባል ይሆናል[2]። በዓለማችን 73,070 የይሖዋ ምስክር ጉባዔዎች ይገኛሉ[3]። (የይሖዋ ምስክሮች ስብሰባቸውን "ጉባዔ" ብለው ይጠሩታል)።

---

1. "1998 Year hookook of Jehovah's Witnesses", ገጽ.31
2. Alan W. Gomes, Unmasking the Cults. ገጽ.22
3. ዝኒ ከማሁ።



### 2. የእድገት መጠን

የይሖዋ ምስክሮች የእድገት ፍጥነት እጅግ አስደንጋጭ ነው። በ1965 ዓ.ም. 1.1 ሚሊዮን የነበረው ንቁ ተሳታፊ ሕባላት ቁጥር በ1980 ዓ.ም. ወደ 2.2 ሚሊዮን፣ በ1992 ደግሞ ወደ 4.4 ሚሊዮን አሻቅቦአል። በ1994 ዓ.ም.፥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፥ በሶቬየት ኅብረት ብቻ 27,000 ሰዎችን አጥምቀዋል[4]። በዓለም ዙሪያ በየዓመቱ 50 አዳዲስ ጉባዔዎች ይቋቋማሉ[5]።

### 3. ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ

የይሖዋ ምስክሮች በ1997 ዓ.ም. ብቻ ለመስክ ምስክርነት 1,179,735,841 ሰዓታትን ተጠቅመዋል[6]። ይህን ቁጥር ለንቁ ተሳታፊ አባሎቻቸው ቁጥር ስናካፍለው እያንዳንዱ አባል ለመስክ ምስክርነት በዓመት ከ200 ሰዓታት በላይ ተጠቅሞአል ማለት ነው። በ1997 ዓ.ም. የተከታዮቻቸውን ልጆች ቁጥር ጨምሮ 375,923 ሰዎችን አጥምቀዋል[7]። ይህ የሚያሳየን የይሖዋ ምስክሮች ለአንድ ሰው በአማካኝ 3,500 ሰዓታትን መጠቀማቸውን ነው[8]። አንድ ንቁ የይሖዋ ምስክር ተሳታፊ አባል በአማካይ በአንድ ወር 16 ሰዓታትን ለመስክ ምስክርነት ያውላል[9]። በ1970 ዓ.ም. አንድ ንቁ አባል በዓመት ለመስክ አገልግሎት ("የመስክ አገልግሎት" የሚባለው በየመንገድ ዳሩና በየቤቱ የመጠበቂያ ግንብ ወንጌልና ጽሑፎችን ማሠራጨት ነው) 150 ሰዓታትን ያውል የነበረ ሲሆን በ1992 ዓ.ም. ይህን ሰዓት በማሻሻል አንድ አባል በዓመት 236 ሰዓታትን በመስክ ምስክርነት ላይ ያሳልፋል[10]።

---

4. Christian Reasearch Institute, "Cult Growth Statistics," citing the watchtower (1 January 1993):ገጽ 15,26.
5. ዝኒ ከማሁ። the Watchtower Society Video, Jehovah's Witnesses: the Organization Behind the maire (1990) ጠቅሶ እንደጻፈው።
6. "1998 Yearbook of Jehovah's Witnesses" ገጽ.31
7. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 31
8. Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Withnesses. (Grand Rapids: Zon., 1995) ገጽ.14
9. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 15
15. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 16

## 4. የጽሑፍ ሥርጭትና የመገናኛ ብዙሃን

ከማንኛውም መናፍቃን ይልቅ የጽሑፍ ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀሙት የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። የይሖዋ ምስክሮች በዓለም ዙሪያ 33 ታላላቅ ማተሚያ ቤቶች አሏቸው። "ቤቴል" በመባል የሚታወቀው ትልቁ ማተሚያ ቤታቸው ብቻ በቀን ርዝመቱ 1,000 ማይል (1, 609 ኪሎ ሜትር) የሚያህል ወረቀት ወይም 61 ሚሊዮን ገጽ ወረቀት ያትማል[11]። ከዚህ በተጨማሪ በወር 3ሚሊዮን የአዲሲቱን ዓለም ትርጉም (የይሖዋ ምስክሮች "የአዲሲቱን ዓለም ትርጉም" ከመጀመሪያው ቅጂ ላይ የተተረጎመ ነው ቢሉም ትርጉሙ ግን ከትምህርታቸው ጋር እንዲስማማ ተደርጎ የተሠራ መጽሐፍ ነው) እያተመ ያወጣል። በ1991 ዓ.ም. በእነዚህ ማተሚያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ 11,000 የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ነበሩ[12]።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጽሑፎቹን በ210 ቋንቋዎች ይተረጎማል። "መጠበቂያ ግንብ" በሚል ርዕስ የሚታተመው መጽሔት በብዛት ከሚታተሙት መጽሔቶች ውስጥ ዋንኛው ነው፤ መጽሔቱ በወር ሁለት ጊዜ የሚታተም ሲሆን በእያንዳንዱ እትም 16 ሚሊዮን ቅጂዎች ይባዛሉ፤ በ120 ቋንቋዎችም ይተረጎማሉ። አሥራ አምለት ሚሊዮን የሚያህለው ቅጂ የሚታተመው በእንግሊዝኛ ነው። ሥርጭቱም ሪደርስ ዳጀስትና ቲቪ ጋይድ ከሚባሉት መጽሔቶች ካላቸው ሥርጭት ጋር የሚስተካከልና፤ ሽያጩም ከታይምስ፥ ከኒውስዊክ፥ ከዮኤስ ኒውስና፥ ከወርልድ ሪፖርት ጋር ይወዳደራል[13]። "ንቁ" በመባል የሚታወቀው የድርጅቱ መጽሔት በ13 ሚሊዮን ቅጂዎች ሲባዛ በ75 ቋንቋዎች ይተረጎማል[14]።

የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም በ1990 ዓ.ም. ብቻ በ67 ሚሊዮን ቅጂዎች የተባዛ ሲሆን በ14 ቋንቋዎች ተባዝቶ ለንባብ በቅቶአል። በአሁኑ ጊዜ ይህ መጽሐፍ ከ16 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል[15]።

"ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት" በሚለው ለያሜ ተጽፎ የታተመው መጽሐፍ በ1968 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ሊታተም በሥርጭት ደረጃ ቀዳሚውን ስፍራ ከያዙት አምስት መጻሕፍት መካከል አንዱ ሊሆን በቅቶአል[16]።

11. CRI "Cult Growth Statistics", citing the watchtower (1 Jan. 1993): 19 h
12. David A. Reed, Jehovah's Withness Literature: a Critical Guide to Watchtower Publications (Grand Rapids: Baker, 1993) ገጽ. 9
13. Alan W.Gomes, Unmasking the Cults, ገጽ. 23
14. Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses, ገጽ. 15
15. Alan W. Gomes, Unmasking the Cults, ገጽ.23
16. Bowman, ገጽ. 15



## 2.2 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በዓለም አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ እንቅስቃሴ[1] ከ1991–1997[2] ዓ.ም.

ድርጅቱ የሚንቀሳቀስባቸው አገሮች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 211 | 229 | 231 | 232 | 232 | 233 | 232 |

የጉባዔዎች ብዛት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 66,207 | 69,558 | 73,070 | 75,573 | 78,620 | 81, 908 | 85,256 |

በመታሰቢያ ቀን የተገኙ ሰዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 10,650,158 | 11,431,171 | 11,865,765 | 12,288,917 | 13,147,201 | 12,921,933 | 14,322,226 |

የመታሰቢያ ቀን ተካፋዮች[3]

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 8,850 | 8,683 | 8,693 | 8,617 | 8,645 | 8,757 | 8,795 |

በመንግሥት አገልግሎት የተገኙ ንቁ ተሳታፊ አባላት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 4,278,820 | 4,289,737 | 4,709,889 | 4,914,094 | 5,199,895 | 5,413,769 | 5,599,931 |

1. የግርጌ ማስታወሻ ካልተደረገበት በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት "Yearbook of Jehovah's Witnesses" በሚል ስም ድርጅቱ በየዓመቱ እያሳተ ከሚያወጣው መጽሐፍ ላይ ነው።
2. የዘመን አቆጣጥሩ እ. ኢት. አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርዮሳውያን መሠረት ነው።
3. ኅብስቱንና ጽዋውን የወሰዱ የመቶ አርባ አራት ሺው አካላት ("ቅቡዓን")

### በመስክ ምስክርነት በየወሩ የሚካፈሉ

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 4,071,954 | 4,289,737 | 4,483,900 | 4,695,111 | 4,950,334 | 5,413,769 | 5,335,078 |

### የእድገት መጠን በመቶኛ

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 5.9 | 5.3 | 4.5 | 5 | 5 | 4.4 | 3.6 |

### የየዓመቱ ተጠማቂያን

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1992 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 300,945 | 301,002 | 296,004 | 314,818 | 338,491 | 366,579 | 375,923 |

### ለመስክ አገልግሎት የዋለው ሰዓት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 951,870,021 | 1,278,127,000 | 1,057,341,972 | 1,096,065,354 | 1,150,353,44 | 1,140,621,714 | 1,179,735,841 |

### በየወሩ በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 3,947,261 | 4,278,127 | 4,515,587 | 4,701,357 | 4,865,060 | 8,855,030 | 4,552,589 |

### ለልዩ አቅኚዎች፥ ለሚሲዮናውያን ክፍያ እንዲሁም ለመስክ አገልግሎት የመጓጓዣ ወጪ በዶላር

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 40,219,589.01 | 45,218,257.59 | 48,857,112.38 | 50,126,004.05 | 57,955,025.64 | 60,932,324.26 | 63,914,602.00 |

### ዋና ቢሮዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 97 | 98 | 100 | 100 | 101 | 104 | 104 |



## 2.3 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያ[1] ከ1991–1997[2] ዓ.ም.

### ንቁ ተሳታፊ አባላት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 3,020 | 3,887 | 3,884 | 4,446 | 4,895 | 5,206 | 5,649 |

### ንጥጥር! አንድ የይሖዋ ምስክር ለ ________ ሰው

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 16,391 | 13,121 | 12,358 | 12,371 | 11,236 | 10,565 | 9,736 |

### ለመስክ አገልግሎት የሚወጡ አስፋፊዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 2,730 | 3,533 | 3,525 | 4,144 | 4,626 | 5,036 | 5,292 |

### የእድገት መጠን በመቶኛ

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 13 | 29 | 19 | 18 | 12 | 9 | 5 |

### የየዓመቱ ተጠማቂያን

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 502 | 665 | 449 | 794 | 619 | 581 | 548 |

### የአቅኚዎች ቁጥር[3] (ave. Pio. Pubs.)

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 483 | 770 | 799 | 983 | 1,113 | 985 | 916 |

---

1. የግርጌ ማስታወሻ ካልተደረገበት በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት "Yearbook of Jehovah's Witnesses" በሚል ስም ድርጅቱ በየዓመቱ እያሳተመ ከሚያወጣው መጽሐፍ ላይ ነው።
2. የዘመን አቆጣጠሩ እ. ኢት. አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርድሳውያን መሠረት ነው።
3. አቅኚ የሚባሉት የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ናቸው።

### የጉባዔዎች ብዛት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 54 | 54 | 48 | 48 | 72 | 76 | 79 |

### ለመስክ አገልግሎት የዋለው ሰዓት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 862,403 | 1,269,513 | 1,289,350 | 1,550,349 | 1,688,752 | 1,654,474 | 1,570,141 |

### በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 3,726 | 4,778 | 4,677 | 4,834 | 4,866 | 4,402 | 3,674 |

### በመታሰቢያ ቀን የተገኙ ሰዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 7,192 | 10,980 | 11,932 | 13,246 | 13,742 | 14,677 | 15,716 |

## 2.4 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲካዊ ዘገባ በኤርትራና በኢትዮጵያ[1] ከ1951–1990[2] ዓ.ም.

### ንቁ ተሳታፊ አባላት

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 18 | 32 | 51 | 67 | 81 | 103 | 119 |

| ዓ. ም. | 1958 | 1959 | 1960 | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 128 | 109 | 105 | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | 253 | 313 | 384 |

1. የግርጌ ማስታወሻ ካልተደረገበት በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት "Yearbook of Jehovah's Witnesses" በሚል ስም ድርጅቱ በየዓመቱ እያሳተመ ከሚያወጣው መጽሐፍ ላይ ነው።
2. የዘመን አቆጣጠሩ እ. ኢት. አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርዮሳውያን መሠረት ነው።



| ዓ. ም. | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 | 1976 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 498 | 596 | 829 | 931 | 1,844 | 1,637 | 1,903 |

| ዓ. ም. | 1977 | 1978 | 1979 | 1980[3] | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 1,824 | 1,593 | 1,475 | 596 | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | 2,413 |

### ንቁ ተሳታፊ አባላት በአማካይ

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | 21 | 40 | 57 | 63 | 80 | 104 |

| ዓ. ም. | 1958 | 1959 | 1960 | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 117 | 104 | 89 | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | | 275 | 275 | 437 |

| ዓ. ም. | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 | 1976 | 1977 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 528 | 711 | 860 | 1,185 | 1,537 | 1,809 | 1,811 |

| ዓ. ም. | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 1,466 | 1,180 | | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | 2,413 |

### የየዓመቱ ተጠማቂያን

| ዓ. ም. | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 19 | 142 | 50 | 269 | 322 | 368 | 370 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 350 | 85 | 84 | 44 | | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | |

### አቅኚዎች

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 | 1958 | 1959 | 1960 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | 13 | 10 | 11 | 14 | 19 | 12 | 10 | 3 |

3. 1981 መረጃ የተገኘው ከ Barrett 1982, 286. ላይ ነው።

| ዓ. ም. | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | | 5 | 9 | 18 | 42 | 58 | 65 | 101 | 155 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 144 | 136 | 101 | 8 | | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | |

የጉባዔዎች ብዛት

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 | 1958 | 1959 | 1960 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | 4 | 5 | 5 | 6 | 7 | 8 | 10 | 10 |

| ዓ. ም. | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | | 4 | 4 | 6 | 8 | 10 | 14 | 26 | 44 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 49 | 50 | 50 | 41 | 8 | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | |

በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 | 1958 | 1959 | 1960 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | 107 | 130 | 140 | 192 | 263 | 271 | 118 | 123 |

| ዓ. ም. | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | | 509 | 2,309 | 800 | 989 | 1,105 | 1,159 | 1,607 | 2,309 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 2,719 | 2,174 | 4,316 | 1,076 | | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | |

በመታሰቢያ ቀን የተገኙ ሰዎች

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 4,732 | 4,974 | 4,316 | 3,815 | | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | |



## 2.5 የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ[1]

የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ ከመሥራቾቹና ከመሪዎቹ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ የእነዚህን ግለሰቦች ታሪክ ማጥናት የድርጅቱን ታሪካዊና ሥነ-መለኮታዊ መሠረት አጥርቶ ለማየት ይረዳል።



“መጋቢ” ቻርልስ ታዝ ራስል (1852–1916)

“መጋቢ” ቻርልስ ታዝ ራስል በቀድሞ አልገኒ አሁን የፒትስበርግ አካል የሆነችው ፔንስልቫኒያ በየካቲት 16 ቀን 1952 ዓ.ም. የፕሮስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አባል፥ የእስኮትላንድና የአየርላንድ ዝርያ ከነበራቸው ቤተሰብ ተወለደ። ራስል በ15 ዓመቱ ከአባቱ ጋር በአክስዮን የልብስ መሸጫ ሱቅ ከፈተ። በዚህንም ጊዜ ነው የፕሮስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያንን በመተው የማኅበረ ምዕመናን ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው።

ይሁን እንጂ ራስል በዚህም ቤተ ክርስቲያን ይሰጡ ከነበሩት አስተምህሮዎች፥ በተለይ የዘላለም ቅጣትና በቅድመ ምዳቤ ትምህርቶች እጅግ ተቸገረ፤ በዚህም ምክንያት በ17 ዓመቱ ወደ ክህደትና መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አለመቀበል ደረጃ ደረሰ። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ራስል በራሱ ቃል እንዲህ ብሎ ነበር፦

---

1. ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው፦ A.A. Hoekema. Jehovah's Witnesses (Eerdmans, 1963) ገጽ. 9-20 Qualified to be Ministers (Brookelyn, 1955), ገጽ 297-312 እና Jehovah's Witnesses in the Divine Purpose (Brooklyn, 1959) ገጽ 14-63 ከተባሉት የድርጅቱ መጻሕፍት ላይ ጠቅሶ ከጻፈው ጽሑፍ ላይ ነው

> “በፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮአዊ ቀኖና ሥር ያደኩ ሰው ብሆንም በተፈጥሮዬ የሚጠይቅ አእምሮ ስለነበረኝ በአመክንዩ እውነታ ትምህርቶቹን መዘንኩአቸው፤ በዚህም ምክንያት የእምነቴ ታንኳ በእግዚአብሔርና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተሰበረ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዝግጅትና ምሪት ጉዳዩ ወደ በጎ ጎዳና ሔራኝ። ይልቁንም በሰዎች የሃይማኖት መግለጫ ሁሉና በቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ላይ የነበረኝ ተአማኒነት ተሰበረ”[2]

በ1870 ዓ.ም፡—

> “ለመጀመሪያ ጊዜ ከጆናስ ዊንደል ስለ አድቬንቲስቶች ሰማሁ። የዚህ ሰው ቃለ እግዚአብሔር አተረጓጎም ሙሉ በሙሉ እኛ፥ አሁን እየተደሰትንበት ባለው መልኩ ግልጽ ባይሆንም ከእግዚአብሔር በታች በቂ ነበር። ይህም ነበር በመዋዥቅ ላይ የነበረውን እምነቴን በእግዚአብሔር አስትንፋሳዊ ቃል ያበረታው”[3]

ከዚያም ራስል በፒትስበርግ ስድስት ሰዎች የሚገኙበትንና በየጊዜው ስመገናኘት የወሰነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ከ1870 ዓ.ም. — 1875 ዓ.ም. አደራጅቶ መራ። ራስልና ጓደኞቹ ክርስቶስ በሥጋ ዳግም ይመጣል የሚለው ትምህርት ስላልተዋጠላቸው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መንፈሳዊና የማይታይ መሆኑን ለማሳመን ራስል “ዘ ኦብጀክት ኤንድ ማነር ኦፍ ዘሎርድስ ሪተርን” በሚል ርዕስ 50ሺ ቅጂ በራሪ ወረቀቶችን አባዛ።

በ1878 ዓ.ም. ራስል ከሮቸስተሩ ኤን ኤች ባርባር ጋር ተገናኘ፤ ባርቦር ከአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ያፈነገጡ ሰዎች መሪ ነበር። ያፈነገጡበትም ምክንያት ራስል የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መንፈሳዊ (የማይታይ) ነው በሚለው ትምህርቱ በማመናቸው ነበር። ከዚያም ራስል ይመራው የነበረው የፔትስበርግ ኅብረትና ባርቦር ይመራው የነበረው የሮቸበተር ኅብረት ተቀላቀለ። በዚህም ግንኙነት ምክንያት “ዘ ሄራልድ ኦፍ ዘ ሞርኒንግ” መጽሔት የመውጣት ምክንያት ሆነ። ይህ መጽሔት በፊት በባርቦር ነበር የሚታተመው። በ1877 ዓ.ም. ባርቦር

2. Watchtower magazine, 1916, ገጽ. 170-171 ከJehovah's Witnesses in the Divine Purpose, ገጽ. 14 ላይ ጠቅሶ ከወሰደው። ለምን ግን “በሁሉም” የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ የነበረው ተአማኒነት ተሰበረ?

3. Jehovah's Witness in the Divine Purpose, ገጽ. 14



እና ራስል በኅብረት 184 ገጽ ያለውን መጽሐፍ፡— “ስሪ ወርድስ ኦር ፕላን ኦፍ ሪደምሽን” አሳተሙ።

> “ይህ መጽሐፍ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1874 ዓ.ም. የተፈጸመ ሲሆን ምጽአቱም ሳይታይ በመንፈስ ነው የሚለውን እምነታቸውን ገሃድ አደረገው። ከዚያም በትክክል በሚያስደንቅም ሁኔታ የአሕዛብ ዘመን በ1814 ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ ጠቆመ”[4]

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ራስልከባርቦር ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋረጠ። ምክንያቱም ራስል የክርስቶስ የማዳን ሥራ አዳምንና የእርሱን ዝርያዎች ይጨምራል ብሎ ስለሚያምን ነበር። ከዚያም ራስል፡— “ዛየንስ ዋች ታወር ኤንድ ሄራልድ ኦፍ ክራይስትስ ፕረዘንስ” የሚለውን መጽሔት ማሳተም ጀመረ። የመጀመሪያው ኅትም በሐምሌ 1 ቀን 1879 ዓ.ም. ነበር ለንባብ የበቃው።

አዲሱ መጽሔት ለእንቅስቃሴው መስፋፋት ታላቅ ሚና ተጫውቶአል። ለምሳሌ፡— በ1880 ዓ.ም. በሰባት የአሜሪካን ክፍላተ አገራት 30 ጉባዔዎች ተቋቁመው ነበር። በ1881 ዓ.ም. “የመጠበቂያ ግንብ የትራክት ማኅበር” በራስል አስተዳዳሪነት ተመሠረተ። ይህ ስም በ1888 ዓ.ም. “የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር” በሚለው ስያሜ ተለወጠ። በታኅሣሥ 13 ቀን 1884 ዓ.ም. ይህ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብ በማውጣት በኮርፖሬሽን መልክ ተዋቀረ። ምን አልባት ይህን ቀን የድርጅቱ ሕጋዊ ጅማሬ ልንለው እንችላለን። ምንም እንኳ ድርጅቱ በዚህ ስም ሕጋዊነትን ቢያገኝም 1896 ዓ.ም. የድርጅቱ ስም “የፔንሲልቫኒያው የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር” የሚል አዲስ ስያሜ አገኘ[5]። በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ II ላይ እንደተጠቀሰው የድርጅቱ ዓላማ “የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በተለያዩ ቋንቋዎች በበራሪ ጽሑፎችና መጽሔቶች ወረቀቶች እንዲሁም ሕጋዊነት ባላቸው መንገዶች ሁሉ ማሠራጨት ነው”[6]

ከዚህ ዓላማ ጋር በተዛመደ መልኩ ራስል 7 ቅጽ ተከታታይ የአስተምህሮ መጽሐፍትን ጽፎአል። የመጀመሪያው ቅጽ የታየው በ1888 ዓ.ም. ሲሆን የመጽሐፉም ርዕስ “ዘ ዲቫይን ፕላን ኦፍ ዘ ኤጅ” የሚል ነበር። ሰባቱም ቅጽ መጻሕፍት በመጀመሪያ የተሰየሙት “ሚሊኒያል ዳውን” በሚል ስያሜ ሲሆን፤ በኋላም “ስተዲስ ኢን ዘ እስክሪብቸርስ” ተባሉ። እነዚህ መጻሕፍት ከፍተኛ ሥርጭት የነበራቸው ሲሆን የመጀመሪያው ቅጽ ከ8 ሚሊዮን ቅጂ በላይ ታትሞ ተሠራጭቶአል።

4. Qualified to be Ministers, ገጽ. 300

5. Qualified to be Ministers, ገጽ. 303

6. ዝኒ ከማሁ ገጽ 304

በ1999 ዓ.ም. ድርጅቱ በአልገኒ ፔንስልቫኒያ ሕንፃ አገኘ። ይህም ለ20 ዓመታት የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ሆኖ አገልግሎአል። በ1891 ዓ.ም. ራስል የመጀመሪያ ጉዞውን በለንደን በማድረግ በ1900 ዓ.ም. በለንደን ቢሮ ከፈተ። ወዲያው መጻሕፍትና በራሪ ጽሑፎች (እንግሊዝኛን ጨምሮ) በተለያዩ ቋንቋዎች መታተም ጀመሩ። በ1903 ዓ.ም. ራስል ሁለተኛውን የአውሮፓ ጉዞ ወደ ጀርመን በማድረግ የድርጅቱን ቅርንጫፍ ከፈተ። በ1904 ዓ.ም. በአውስትራሊያ ሌላ ቢሮ ተቋቋመ።

በ1909 ዓ.ም. በድርጅቱ የሕግ አማካሪ በሆነው ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ አዲስ የመስፋፋት ምዕራፍ ተከፈተ። ሮዘርፎርድ ለድርጅቱ አንዳንድ ዕቃዎች በብሮክሊን ኒውዮርክ ስለገዛ ዕቃዎቹን በይዞታነት ለማቆየት ድርጅቱ ሌላ ኮርፖሬሽን አዋቀረ። በዚህም ምክንያት "ፒውፐልስ ፑልፒት ኮንሶሴሽን ኦፍ ኒውዮርክ" ተቋቋመ። በ1958 ዓ.ም. የዚህ ኮርፖሬሽን ስም "የኒውዮርኩ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" ተባለ።

በአንድ ወቅት ራስል በመጽሔቱ "ታምረኛው ስንዴ" አንዱን ፓውንድ በአንድ ዶላር ሊሸመት እንደሚችል ይህም ስንዴ ከመደበኛው ስንዴ በአምስት እጥፍ እንደሚያድግ አስተዋውቆ [Advertise] ነበር። በዚህም ምክንያት የ"ብሮክሊን ዴይሊ ኢግል" መጽሔት "ፓስተሩና" "ተአምረኛው ስንዴ" በሚል፥ አስቂኝ የካርቶን ስዕል አውጥቶበት ነበር። በዚህም ምክንያት ራስል የመጽሔቱን አዘጋጅ በፍርድ ቤት ስለከሰሰው መንግሥት ስንዴውን ለማስመርመር ተገዶ ነበር። ነገር ግን እውነታው የተገላበጠ ሆነ። ይኸውም "ታምረኛው ስንዴ" ከሌሎች ስንዴዎች አምስት እጥፍ የተሻለ ሳይሆን ከሌሎቹ በጥቂት ያነሰ ሆኖ ተገኘ። ከዚህም የተነሣ የኢግል መጽሔት አዘጋጅ ክሱን ረታ። ፍርድ ቤቱም በነጻ አሰናበተው[7]።

ራስል በ1979 ዓ.ም. ሚሪያ ፍራንሲስ አክሊን አገባ። በዚህ ጋብቻ ራስል ልጅ አልወለደም። ሚስስ ራስል ለብዙ ዓመት በመጠበቂያ ማኅበር ገንዘብ ያዥና ጸሐፊ፥ የ"መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ረዳት አዘጋጅ ሆነው ሠርተዋል። በ1897 ዓ.ም. ራስልና ወይዘሮዋ ተፋቱ።

7. Walter R. Martin እና Norman H. Klaan Jehovah of the Watchtower, rev. ed. (Grand Rapids: Zondervan, 1959) ገጽ 15-77 ከኅዳር 1 ቀን 1916 ዓ.ም. ከወጣው Daily Eagel ላይ ጠቅሰው እንደጻፉት።



በ1913 ዓ.ም. ሚስስ ራስል "ባላቸው ያደረግባቸው ስለነበረው ጭቆና፥ ከሌሎች ሴቶች ጋር የነበረው አላስፈላጊ ግንኙነት" በመጥቀስ ራስልን ከሰሱ[8]።


ራስል የጻፋቸውን የአስተምህሮ መጻሕፍት ቃለ እግዚአብሔርን ለመረዳት ብቸኛ አማራጮች እንደሆኑ እንዲያውም ያለ እነርሱ አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ መረዳት ስለማይችል በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ እንደሚቆይ በድፍረት የተናገረ ሰው ነው። ቃል በቃል የራስልን አባባል እናቅርብ፦

> "የተረዳነው ነገር አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ መለኮታዊውን ዕቅድ ማወቅ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ጥቂት እንኳን ተጠቅሞባቸው የኔን መጽሐፍ ማቆም [ወደ ጎን ማድረግ] ትውስታቸውን ወይንም ትምህርታቸውን በመርሳት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መመለስ በሁለት ዓመት ውስጥ ጨለማ ውስጥ እንደሚያስገባ ነው፤ ከልምምዳችን የተረዳነው። በሌላ አነጋገር አንድ ሰው "እስክሪብቸርስ እስተዲስ" [የራስል 7 ቅጽ መጻሕፍት] ብቻ ከነማጣቀሻቸው ያነበበ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ባያነብ እንኳን፥ በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ብርሃን ይወጣል። ምክንያቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ብርሃን በእጁ አለና"[9]

በአንድ ወቅት ለራስል "የግሪክ ፊደላትን ታውቃለህ?" የሚል ጥያቄ ሮስ ላውየር ከተባለ ሰው ቀርቦለት ነበር። ራስልም፦ "እንዴታ! በደንብ አውቃለሁ እንጂ" የሚል መልስ ሰጠ። በኋላም የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ተሰጥቶት ከላይ ያሉትን ፊደላት እንዲጠራቸው ቢጋበዝ ሊጠራቸው ስላልቻለ የግሪክ ቋንቋን ያለመቻሉን አምኖ ነበር[10]።

ራስል በጥቅምት 31 ቀን 1916 ዓ.ም. በቴክሳስ ክፍለ አገር ሞተ። ይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ራስል በሕይወቱ ዘመን አንድ ሺ ማይሎችን በመሄድ 30ሺ ስብከቶችን የሰበከ በድምሩ ከ50ሺ ገጽ በላይ ወረቀቶችን የጻፈ ሰው ነበር[11]።

8. Bruce M. Metzger, "The Jehovah's Witnesses and Jesus Christ" Theology Today, April, 1953, ገጽ. 65-66 ዶ/ር ሜትዜገር ለአንባቢያቸው የጠቀሱት ከ Herbert H. Stroup's. The Jehovah's Witnesses (New York: Columbia University press, 1945), ገጽ 9-11 ላይ ነው።
9. Watchtower, Sept. 15,1910 ገጽ. 298 እንዲሁም ይህ ክፍል በ July, 9157 Watchtower ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። በትንፍ ያለውን አይጨምርም።
10. Russel – Vs – Ross transoript on file in the Brooklyn headquarters of the Watchtower Society. Martin & Klann ገጽ. 18 ላይ ጠቅሰው እንደጻፉት።
11. Qualified to be Ministers, ገጽ. 310



## "ዳኛው" ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ (1869–1942)

በራስል የአስተዳደር ዘመን የድርጅቱ የሕግ አማካሪ የነበረው ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት ሆነ። ሮዘርፎርድ በኅዳር 8 ቀን 1869 ዓ.ም. የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አባል ከነበሩ ቤተሰብ በቦንቪል ሚዞሪ ተወለደ። የ16 ዓመት ልጅ ሳለ የሕግ ትምህርት ለመማር ኮሌጅ ገባ። በ22 ዓመቱ በፍርድ ቤት በዳኝነት መሥራት ጀመረ። በቦንቪል ፍርድ ቤት ለአራት ዓመት ከሠራ በኋላ ዋናው ዳኛ በሚታመምበት ጊዜ እንደ ዋና ዳኛ ሆኖ አገልግሎአል። ለዚህም ነው ሮዘርፎርድ "ዳኛው" የተባለው። ሮዘርፎርድ ከመጠበቂያ ግንብ ባለሥልጣናት ጋር ግንኙነት የጀመረው በ1894 ዓ.ም. ነበር። ወደ እንቅስቃሴው የገባው በ1806 ዓ.ም. ቢሆን፤ የድርጅቱ የሕግ አማካሪ የሆነው በ1807 ዓ.ም. ነው።

ሮዘርፎርድ የፕሬዝዳንትነቱን ወንበር እንደያዘ የብሮክሊኑን ቢሮ የአስተዳደር መዋቅር በመቀየር የድርጅቱ አባላት ወደ መስክ አገልግሎት እንዲያተኩሩ አደረገ። ነገር ግን ራስል በሞተ ማግስት በድርጅቱ ባለሥልጣናት መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ የችግሩ ምክንያት ናችሁ የተባሉትም ሰዎች ከሥልጣናቸው ተባረሩ።

በሐምሌ 1917 ዓ.ም. ከራስል 7 ቅጽ ተከታታይ መጻሕፍት መካከል የመጨረሻው ጥራዝ "ዘ ፊኒሽድ ሚስትሪ" በሚል ርዕስ ታተመ። ይህ መጽሐፍ ራስል በሕይወት ዘመኑ በራእይና በሕዝቅኤል መጻሕፍት ላይ የጻፋቸውን ማብራሪያዎች በማሰባሰብ በመጠበቂያ ግንብ ዋና አዘጋጆች ሰኅትመት የቀረበ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ "ዘ ፎል ኦፍ ባቢሎን" ["የባቢሎን ውድቀት"] በሚል ርዕስ በአራት ገጽ የተጻፈው በበራሪ



ጽሑፍ መልክ በብዛት በመታተም ከታኅሣሥ 30 ቀን 1917 ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን አባላት ተሠራጨ። እንደዚህ በራሪ ጽሑፍ ካቶሊክና የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት የዘመኑ ባቢሎን ስለሆኑ በትልቅ መጠላት ውስጥ እንደሚያልፉ "የተነበየ" ነበር።

በየካቲት 1918 የካናዳ መንግሥት የራስልን መጻሕፍት በአገሪቱ ውስጥ እንዳይሠራጩ እገዳ አወጣ፡ ይህ የሆነው መጻሕፍቱ ውትድርናን አጥብቀው ስለሚከለክሉ ነበር። በግንቦት 1918 ዓ.ም. የአሜሪካን መንግሥት ሮዘርፎርድን ጨምሮ ስምንት የድርጅቱን ባለሥልጣናት የአሜሪካንን የጦርና የባሕር ሥራ አናንቃችኋል፥ ተቃውማችኋል በሚል አሠራቸው[12]።

በሰኔ 20 ቀን ያስቻለው ፍርድ ቤት ስምንቱ ሰዎች ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኛቸው በአትላንታ ጆርጅያ በ20 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ በየነ[13]።

በዚህም ምክንያት የብሮክሊኑ ዋና መሥሪያ ቤት ሥራ ስላቆመ ድርጅቱ ሥራውን ከፒትስበርግ ማንቀሳቀስ ጀመረ። ጦርነቱ በ1918 ዓ.ም. ሲጠናቀቅ [አንደኛው የዓለም ጦርነት] የድርጅቱ አባላት የፓርላማ አባላትንና የአመራር አካላት፥ የመጠበቂያ ግንብ መሪዎች እንዲፈቱ ጠየቁ። በግንቦት 14 ቀን 1919 ዓ.ም. ስምንቱም መሪዎች በምሕረት ተለቀቁ[14]።

የብሮክሊኑ ቢሮ ዳግም ተከፈተ። በዚህም ዓመት ሁለተኛው መጽሔት "ዘ ጎልደን ኤጅ" ["ወርቃማው ዘመን"] በሚል ርዕስ ወጣ። ይህ መጽሔት በ1837 ዓ.ም. ኮንሶሌሽን መጽናናት በ1948 ዓ.ም. "አዌክ" ["ንቁ"] ተባለ።

የድርጅቱ የኅትመት ሥራ እየተስፋፋ በመምጣቱ ድርጅቱ የኅትመት ሥራዎች ሁሉ በድርጅቱ ማተሚያ ቤት እንዲታተም ወሰነ። በ1921 ዓ.ም. የሮዘርፎርድ የመጀመሪያ መጽሐፍ "ዘ ሃርፕ ኦፍ ጎድ" ["የእግዚአብሔር በገና"] ወጣ። ሮዘርፎርድ ከራስልም ይልቅ ብዙ መጻሕፍትን የጻፈ ሰው ነበር። ወዲያው የራስልን መጻሕፍት የሚተኩ፥ በድርጅቱ አስተምህሮ ላይ የተመሠረቱ የአስተምህሮ መጻሕፍትን ጻፈ።

12. Qualified to be Ministers, ገጽ. 315.
13. ዝኒ ከማሁ
14. ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 316

በ1920 የድርጅቱ አባላት በሙሉ የመስክ ምስክርነታቸውን በተመለከተ ሳምንታዊ ሪፖርት እንዲያደርጉ ተወሰነ። "ለ30 ዓመት የይሖዋ ምስክሮች ባሪያ ነበርኩ" የሚለውን መጽሐፍ የጻፈው ዊሊያም ሽነል የእንቅስቃሴውን ውስጣዊ ሥራ እንዲህ በማለት ገልጦት ነበር፦ የሮዘርፎርድ ፖሊሲ በድርጅቱ መሠረታዊ ለውጥ አምጥቶ ነበር። በራስል የአስተዳደር ዘመን ድርጅቱ ትኩረት የሚሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፥ በባሕርይ እድገት፥ በመንፈስ ፍሬዎች ላይ ነበር። አሁን ይህ ሁሉ ቀርቶ የድርጅቱን ጽሑፎች በማሠራጨትና ለዋናው መሥሪያ ቤት ስለ ሥርጭቱ የየቀን ውሎ ሪፖርት ወደ ማድረግ ተለወጠ። ሦስት አራተኛ የሚሆኑት "የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች" [ከ1931 ዓ.ም. በፊት የነበሩት የይሖዋ ምስክሮች "የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች" ይባሉ ነበር] በዚህ ምክንያት ድርጅቱን ለቀቁ።

በ1931 ዓ.ም. በኮሎምቦስ ኦሀዩ በተደረገው ስብሰባ የድርጅቱ አባላት "የይሖዋ ምስክሮች" ተባሉ። ይህ ስያሜ የተወሰደው ከኢሳ. 43፥10 ላይ ነው "እናንተ የመረጥሁት ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር"[15]

ከ1940 ዓ.ም. ጀምሮ "መጠበቂያ ግንብ" እና "መጽናናት" የሚባሉት መጽሔቶች በየመንገድ ዳሩ በአባላቱ መሠራጨት ጀመሩ። ይህ የማሠራጨት ፖሊሲ እስከ አሁን እንዳለ ነው [ለዚህም ነው የይሖዋ ምስክሮችን በየቤቶቻችን በሮች ላይ እና በየመንገድ ዳር የምናያቸው]።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ድርጅቱ ያወጣውን የገለልተኝነት ፖሊሲ በ1917 ዓ.ም. ዳግም አጸናው። ከዚህም የተነሣ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በጦር ኃይሉ ውስጥ አናገለግልም በማለታቸው ወኅኒ ተጣሉ።

ሮዘርፎርድ ድርጅቱን ለ25 ዓመት ከመራ በኋላ በጥር 6 1942 ዓ.ም. ሞተ። ድርጅቱ እንደሚለው በሮዘርፎርድ የፕሬዝዳንትነት ዘመን ድርጅቱ ከዲሞክራሲያዊ አስተዳደር በ"እግዚአብሔር ወደሚመራ" ["ቴዎክራቲክ" (Theocratic)] ድርጅት ተሸጋግሮአል። ይህም ማለት የአጥቢያ ጉባዔ ዳሬክተሮች የሚመረጡት በአጥቢያ ጉባዔዎች ሳይሆን ብሮክሊን በሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የአመራር አካላት ይሾማሉ1 ማለት ነው።

15. Jehovah's Witnesses in the Divine Purpose, ገጽ. 125-126





## ናታን ሆመር ኖር
## (1905–1977)

ናታን ሆመር ኖር በጥር 13 ቀን 1942 ዓ.ም. የድርጅቱ ሦስተኛ ፕሬዝዴንት ሆኖ ተመረጠ። ኖር በ1905 ዓ.ም. በቤትልሔም ፒንስልቫንያ ተወለደ። በ16 ዓመቱ የተሃድሶ ቤተ ክርስቲያን አባልነቱን በመተው አሊንቶን ፒንስልቫኒያ ወደ ሚገኘው የይሖዋ ምስክሮች ጉባዔ ተቀላቀለ። በ18 ዓመቱ የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሰባኪ እንዲሁም ብሮክሊን በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት አባል ሆነ። በ1932 ዓ.ም. የድርጅቱ የኅትመት እንቅስቃሴዎች ሁሉ አስተባባሪ እንዲሁም የኅትመት ቢሮ አስተዳዳሪ ሆነ፤ በ1934 ዓ.ም. የኒውዮርክ ኮርፖሬሽን ዳሬክተር፤ 1940 ዓ.ም. የፔንስልቫኒያው ኮርፖሬሽን ምክትል ዳሬክተር ሆነ።

ኖር ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ፕሬዝዴንቶች ዕውቅ አልነበረም። ከአሜሪካን ውጪ ያሉ አንዳንድ የድርጅቱ አባላት ስሙን እንኳ አያውቁም ነበር። በሥልጣን በነበረበት ጊዜ ዓላማው አድርጎ የተንቀሳቀሰው የትምህርት ፕሮግራሞችን ማሳደግ ነበር። ይህም እውን የሆነው የ"ጊልአድ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት" በ1943 ዓ.ም. ሲቆረቆር ነው። ሌላው የአጥቢያ ጉባዔ የሥልጠና ፕሮግራሞችን የሚያግዝ ሦስት የመማሪያ መጻሕፍትን በ10 ዓመታት ውስጥ ማዘጋጀት ነው። እነዚህ መጻሕፍት ያካተቱት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች፥ የመመስከር ዘዴና ታሪክን ነው። እነዚህም መጻሕፍት፦ "ቴዎክራቲክ ኤይድ ቱ ኪንግደም ፐፕሊሸርስ" (በ1945 ዓ.ም.) "ኢኩዮፕድ ፎር ኤቨሪ ጉድ ወርክ" (በ1946 ዓ.ም.) እንዲሁም "ኳሊፋይድ ቱ ቢ ሚኒስተርስ" (1955 ዓ.ም.) የሚባሉት ናቸው።

እነዚህ መጻሕፍት ሌላ በኖር የፕሬዝዴንትነት ዘመን አዲስ የአለተምህሮ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ከዚህም በፊት እንደነበሩት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች እነዚህ መጻሕፍት በአንድ ግለሰብ የተጻፉ አልነበሩም በመሠረቱ እነዚህ መጻሕፍት በሚስተር ኖር ተጽፈው ከኅትመት በፊት የተለያዩ ሰዎች አይተዋቸዋል። ከዚያም የጽሐፊው ስም ሳይኖር ለኅትመት በቁ[10]። እነዚህ መጻሕፍት ራስልና ሮዘርፎርድ የጻፉአቸውን የአስተምህሮ መጻሕፍት የተኩ ነበሩ። ከእነዚህም መካከል በ1943 ዓ.ም. የታተመው "እውነት አርነት ያወጣሃል" እንዲሁም በ50 ቋንቋዎች 17 ሚሊየን ቅጂ ተባዝቶአል የሚባለው "እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን" የሚለው ይገኙበታል።

በኖር የፕሬዝዴንትነት ዘመን ከተሠሩት ሥራዎች መካከል ወደ እንግሊዝኛ ተተርጎመ የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ መጽሐፍ በመጀመሪያው የታየው 1950 ዓ.ም. ሲሆን "ዘ ኒው ወርልድ ትራንስሌሽን እፍ ዘ ክርስቲያን ግሪክ እስክሪብቸር" [የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም] በመባል ይጠራል። የብሉይ ኪዳን ኅትሙ የወጣው ቀስ በቀስ ነበር። የመጀመሪያው ጥራዝ የታተመው በ1953 ዓ.ም.፥ ሁለተኛው በ1955 ዓ.ም.፥ ሦስተኛው በ1957 ዓ.ም.፥ አራተኛው በ1958 ዓ.ም.፥ አምስተኛው በ1960 ዓ.ም. ነበር። "የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም" ሙሉ ጥራዝ ለመጀመሪያ የታየው በ1961 ዓ.ም. ነበር። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ አባላት እነማን እንደሆኑ፥ ከመጀመሪያው ቅጂ (በኩረ-ጽሑፍ) ወደ እንግሊዝኛ የመተርጎም አቅማቸውና ዕውቀታቸው ምን ያህል እንደሆነ እስከ ዛሬ በድርጅቱ የተሰጠ ማብራሪያ የለም። ነገር ግን ዕብራይስጥና የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ትርጉሙን በአንድ ድምፅ ኮንነውታል።

---

10. ይህ መረጃ የተገኘው የሚስተር ኖር ጸሐፊ ከነበሩት ሚስተር አሊሰ ቪ ግላበ ብሮክሊን በሚገኘው ዋና ጽሕፈት ቤት በሐምሌ 6 ቀን 1962 ዓ.ም. ቃለ መጠይቅ ተደርገው መሆኑን A.A Hoekema, Jehovah's Witnesses በሚለው መጽሐፍ ገጽ 18 ላይ ጠቅሶ ጽፎአል።





ፍሬድሪክ ዊሊያም ፍራንዝ
(1893–1992)

ናታን ሆመር ኖር በ1977 ዓ.ም. ሲሞት በእርሱ የፕሬዝዴንትነት ዘመን እንደ ትልቅ የሥነ-መለኮት ምሁር ይቆጠር የነበረው ፍሬድሪክ ዊሊያም ፍራንዝ ሥነ-መለኮትን በአግባቡ የተማረ ባይሆንም ከእርሱ በፊት ከነበሩት የድርጅቱ ፕሬዝዴንቶች ይልቅ የሥነ-መለኮት ዕውቀት የነበረው ሰው ነበር። በዚህ ሰው የአስተዳደርም ዘመን ነው የይሖዋ ምስክሮች ስትምህርታቸው ማስረጃ የሚሉአቸውን ጥቅሶች መጥቀስ የጀመሩት።

ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ድርጅቱ ታላቅ ቀውስ ውስጥ ስለ ወደቀ ብዙ የአስተዳደር አካላት የፍራንዝ የወንድም ልጅ፥ ሬምንድ ፍራንዝን ጨምሮ ለድርጅቱ ታማኝ አይደላችሁም በሚል ከሥራ ተባረሩ። ነገር ግን ነውጡን ያስከተሉት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ የድርጅቱ መሠረታዊ አስተምህሮቶች ጥያቄ ውስጥ የመውደቃቸው ጉዳይ ዋነኛው ነበር። ለምሳሌ፦ ድርጅቱ ሥነ-ፍጻሜን በተመለከተ ያወጣቸው አሀዛዊ ትንቢት [አርማጌዶን ጦርነት በ1975 ዓ.ም. ይሆናል] በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ፥ ዳግም ልደት ለ144ሺዎች ("ለቅቡዓን") ብቻ እንጂ ለበጎች አያስፈልግም የሚለውን ትምህርት ጥቂት የአመራር አካላት፥ ሬይ ፍራንዝን ጨምሮ፥ ማውገዛቸው ይገኝበታል[17]።

ፍራንዝ በ1992 ዓ.ም. ሲሞት አሁን የእርሱን የፕሬዝዴንትነት ቦታ ተክቶ ያለው በፍራንዝ የአስተዳዳሪነት ዘመን የአመራር አካል የነበረው ሚልተን ጂ ሔንሼ ነው።

---

17. Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses. P 12.

## 2.6 የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ

### ሀ. ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ቅኝት

"ሁሉም የይሖዋ ምስክር ይሰብካል" የሚለው የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ[1] ሽማግሌ አነጋገር የይሖዋ ምስክር መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ የሚገልጽ የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገር ነው። አንድ ሰው የይሖዋ ምስክሮች ንቁ ተሳታፊ አባል የሚሆነው የይሖዋ ምስክርችን መልእክት "ሲያሰፋፋ" ["Publishing"] ብቻ ነው። ለዚህም ነው ንቁ ተሳታፊ አባል "አስፋፊ" ["Publisher"] በሚል ለያሜ የሚጠራው።

አንድ ንቁ የይሖዋ ምስክር በወር 18 በዓመት 236 ሰዓታትን "በመስክ አገልግሎት"[2] ላይ ያሳልፋል[3]። ይህ ሰዓት አንድ ንቁ አባል "ጉባዔ"[4] የሚካፈልበትን የድርጅቱን ጽሑፍ የሚያነብበትን፣ አዳዲስ አባሎችን የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን[5] አስተምህሮ የሚያስተምርበትን ጊዜ ሳይጨምር ነው። ሙሉ ጊዜያቸውን በመስክ አገልግሎትና በድርጅቱ ሥራ ላይ የሚያሳልፉት "አቅኚዎች" ["pioneers"] ይባላሉ። አስፋፊዎች ምንም ዓይነት ክፍያ ከድርጅቱ አይከፈላቸውም። አቅኚዎች ግን "መጠነኛ" ክፍያ ያገኛሉ። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ተከታዮቹን አቅኚና አስፋፊ ብሎ ይከፈላቸው እንጂ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ ነው ቢባል አብለት አይሆንም።

ዓለማቀፋዊ የሆነው የሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ የሚደራጀው ብሮክሊን በሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት በኩል ነው። በእያንዳንዱ የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ውስጥ ሁለት ሣጥኖች ይገኛሉ። አንዱ ሣጥን በየአገሩ ለሚገኙ አጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ግንባታ የሚውል ስጦታ የሚለጥበት ሲሆን ሁለተኛው ሣጥን ደግሞ ዓለማቀፋዊ የሆነውን ሚሲዮናዊ ሥራ የሚደግፍ ስጦታ የሚጨመርበት ነው። የይሖዋ ምስክሮች ስጦታቸውን በእነዚህ ሣጥኖች ውስጥ እንዲጨምሩ ድርጅቱ ያበረታታል[6]።

---

1. የይሖዋ ምስክሮች የመሰብሰቢያ ስፍራቸውን "የመንግሥት አዳራሽ" [Kingdom Hall] ብለው ይጠሩታል።
2. "የመስክ አገልግሎት" የሚባለው በየመንገድ ዳሩና በየቤቱ የመጠበቂያ ግንብ ወንጌልን መሰበክና ጽሑፉን ማሠራጨት ነው።
3. Robert M. Bowman Jr. Jehovah's Witnesses. (Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1995) ገጽ. 14
4. የሰንበት ስብሰባ "ጉባዔ" በመባል ይታወቃል።
5. የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፦ "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል ይታወቃል።
6. ለዚህ ጽሑፍ ዝግጅት ዶ/ር ስቲቭ ስትራውስ ቃለ መጠይቅ ያደረጋቸው በአሜሪካን አገር የሚገኙ የአጥቢያ ሽማግሌ እንደሚሉት፦ በአብዛኛው አጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ድርጅቱን የሚረዳው ለሚሲዮናውያን የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ነው።



በየሳምንቱ እያንዳንዱ የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ሳምንታዊ "የአገልግሎት ስብሰባ" [Service Meeting] ይኖረዋል። በዚህ የስብሰባ ጊዜ በየአገሩ ያሉት የይሖዋ ምስክሮች የሥራ ዜና ያዳምጣል። "የመንግሥታችን አገልግሎት" [Our Kingdnm Ministry] ከሚባለው ጋዜጣ "ቴዎክራሲያዊ ዜና" [Theocrtic News] የሚባለው አምድ ይነበባል። በየሳምንቱ እያንዳንዱ የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ተመሳሳይ ርዕስ ያጠናል። ስለዚህም እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር በየአገሩ የይሖዋ ምስክሮች የሥራ እንቅስቃሴ እንዲያውቅ ይረዳዋል።

እያንዳንዱ ሚሲዮናዊ ከመጣበት የአጥቢያ ጉባዔ ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላል። ነገር ግን ይህ ግንኙነት ሕጋዊ አይደለም። ሕጋዊ የሆነው ግንኙነት ከዋናው ጽሕፈት ቤት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ብቻ ነው። የሚሲዮናውያንን የሥራ ሪፖርት የሚያሠራጨው ዋና ጽሕፈት ቤቱ ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ሚሲዮናዊ ሆነው በሌላ አገር እንዲሠሩ አይገደዱም። በግለሰቡ ፍላጎት እንዲሁም "በልቡ መነሣሣት" ብቻ ነው። አንድ የይሖዋ ምስክር ወደ ሌላ አገር ሄዶ ማገልገል ቢፈልግ የሚስዮናዊ ማመልከቻ ቅጹን በመሙላት ብሮክሊን ወደሚገኘው የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ይልካል። ድርጅቱ ግለሰቡን ከተቀበለው በሚሲዮናዊነት ወደ ሌላ አገር ከመሄዱ በፊት ጊልአድ በሚባለው የድርጅቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለአምስት ወራት ይሰለጥናል።

የጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በ1943 ዓ.ም. ሲከፈት ዓላማ ያደረገው "የሙሉ ጊዜ አቅኚ አገልጋዮችን በውጪ አገር ሚሲዮናዊ ሆነው እንዲያገለግሉ ለመርዳት ነው"[7]። የጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቢሆንም የሰብከት ዘዴንና የድርጅቱን ድርጅታዊ አወቃቀር በተጓዳኝነት ያስተምራል። ትምህርቱን ለአምስት ወራት ተከታትለው የጨረሱትን ዋናው መሥሪያ ቤት በሚሲዮናዊነት ወደተለያዩ አገሮች ይልካቸዋል።

ጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በአንድ ጊዜ 50 ተማሪዎችን ተቀብሎ የማስተማር አቅም አለው። የበለጠ ሚሲዮናውያንን ለማሠልጠን በኒውዮርክ ፓተርሰን ፋርም በሚባለው አካባቢ አዲስ ሕንፃ እየገነባ ነው።

---

7. Doing God's Will (1986) ገጽ. 22

አብዛኛውን ጊዜ ሚሲዮናውያኑ የሚችሉትን ቋንቋ በሚናገሩበት አካባቢ ይመደባሉ። ነገር ግን ቋንቋውን በማይችሉበት አካባቢ የተመደቡት ሚሲዮናውያን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ቋንቋ ይማራሉ። የሚሲዮናውያኑን የመጓጓዣ ወጪ፥ የቤት ክራይ፥ የምግብና አንዳንድ የተለያዩ ወጪዎችን የሚሸፍነው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ነው። ሚሲዮናውያኑ በወር 140 ሰዓታትን በመስክ አገልግሎትና መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ማሳለፍ ይጠበቅባቸዋል[8]። የሁሉም የይሖዋ ምስክሮች የመስክ አገልግሎት ትኩረት ያደረገው የይሖዋ ምስክር ባልሆነ ማንኛውም ግለሰብ ላይ ነው[9]። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሚሲዮናውያኑ ሥራቸውን የዕድሜ ልክ እንዲያደርጉት ያደፋፍራል።

## ለ. የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ በኢትዮጵያ[10]

### የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር ነው የሚባለው ኪሪኮር አታዛኮርታዚያን [Krikor Hatzakortazian] ነው። አታዛኮርታዚያን አርሜኒያዊ ይሁን እንጂ ከየት እንደመጣ፥ እንዴት የይሖዋ ምስክር እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም። አታዛኮርታዚያን በ1935 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር ቢሆንም ብሮክሊን ከሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የተላከ የድርጅቱ ሚሲዮናዊ አልነበረም። ይህ ሰው የአርሜኒያ፥ የግሪክና የፈረንሳይ ቋንቋ ተናጋሪ ነበር። "የማስፋፋት" ሥራውን እንደ ጀመረ ነበር "ስደት" የገጠመው። በኅዳር 1 ቀን 1935 ዓ.ም. በወጣው "መጠበቂያ ግንብ" በመባል በሚታወቀው የድርጅቱ መጽሔት ላይ የመጀመሪያውን ይመስክ አገልግሎት እንዲህ አድርጎ ገልጾት ነበር፡-

"ከሥራ ወደ ቤቴ ስመለስ ከሰይጣን ወኪሎች አንዱ ከተደበቀበት ስፍራ በድንገት በመውጣት ጭንቅላቴን በትልቅ በትር ሁለቴ መታኝ። የመታኝም እጠንክሮ ስለነበር በትሩ ለሁለት ተሰበረ። ነገር ግን በጌታ እርዳታ፥ ለጎረቤቶቼም መደነቅ ቁስሌ ሥር የሰደደ አልነበረም። በአልጋ ላይ የቆየሁት ለሁለት ቀናት ብቻ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ የጠላት ወኪል በጩቤ አጠቃኝ። ነገር ግን ሊወጋኝ ባለበት ቅጽበት ባልታወቀ ኃይል ጩቤውን በመወርወር ብቻዬን ተወኝ"።

8. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 23
9. ይህ የሆነበት ምክንያት ይሖዋ ምስክር ሆኖ በመጠበቂያ ግንብ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር ካልተጠለለ የዘላለም ሕይወት የለውም የሚል ጽኑ እምነት ስላላቸው ነው።
10. አብዛኛውን መረጃ የወሰድነው ዶ/ር ሰቲቨ ስትራውስ "የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በ1993 ዓ.ም. ከጻፈው ያልታተመ የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ላይ ነው። ይህ ታሪክ በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሺዮን የነበረችውን ኤርትራን የሚጨምር ነው።



"ነገር ግን አሁንም ስደታቸውን ገፍተውበት ነበር። በዚህ ጊዜ ደግሞ በሐሰት ወንጅለውኝ በእጼው ፊት ስመቅረብ ወደ መዲናዋ፥ አዲስ አበባ ልከውኝ ነበር። በከተማዋ በቆየሁባቸው ጊዜያት (አራት ወር) በተለያዩ ስፍራዎች በመዘዋወር በየቤቱ፥ በየሆቴል ቤቶችና በየካፍቴሪያዎች አገልግሎት እሰጥ ነበር። በመጨረሻም በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረብኩ፤ ካዳመጡኝም በኋላ ጥፋት ስላላገኙብኝ ወደ ቤት እንድሄድ በማዘዝ በነፃ አሰናበቱኝ። ስለዚህ ድል ጌታ ይመስገን!"[11]

በመጠበቂያ ግንብ ዋና መሥሪያ ቤት ተልከው፥ አገራቸውን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን ኢትዮጵያ የደረሱት በ1950 ዓ.ም. ነበር። "እንደ እናንተ ይናገራል ስለሚባለው የድሬዳዋ ሰው አንዳንድ ወሬ ሰሙ" ፡ ከሚሲዮናውያኑም አንዱ፡- ሃይውርድ ዋርድ [Haywood ward] ወደ ድሬዳዋ ተጓዘ እዚያም "እንግሊዝኛ መናገር የማይችል አንድ ሽማግሌ ሰው አገኘ። ሚሲዮናዊ እንደመሆኑ መጠን ራሱን አስተዋወቀ። ሽማግሌው እንባቸውን እንዥረዥሩት፤ ወደ ሰማይ አንጋጠው በአርሜኒያ ቋንቋ አጉተመተሙ። በንግግራቸው መካከል ጆሆቫ የሚለው ስም ነበር። ይህ ሰው ወንድም አታዛኮርታዚያን ነበር"[12]። ለሚሲዮናዊውም በእጃቸው የቀሩትን የመጠበቂያ ግንብ መጽሔት የጥንት ቅጂ አሳዩት። ሚሲዮናዊው ዳግም ወደ ድሬዳዋ ከመመለሱ በፊት ነበር አታዛኮርታዚያን የሞቱት። ከዚህም የተነሣ አታዛኮርታዚያን እንዴት የይሖዋ ምስክር እንደሆኑ፥ እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ሳይታወቅ ቀረ። ነገር ግን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት በኢትዮጵያ የነበሩ የይሖዋ ምስክር አታዛኮርታዚያን ናቸው[13]።

### በቅንጅት የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ

ሚሲዮናዊነትን ዓላማቸው አድርገው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የመጀመሪያዎቹ የይሖዋ ምስክሮች በጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተማሩ ሦስት ያላገቡ ሚሲዮናውያን ነበሩ። ዲን ሆብት እና የይውድ ዋርድ በመስከረም 14 ቀን 1950 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ

11. Year book 1992. ገጽ. 82
12. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 81
13. ዝኒ ከማሁ ገጽ 80-82

በመምጣት[14] የመጠበቂያ ግንብን ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ ጀመሩ[15]። እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ሚሲዮናውያን ዓላማ አድርገው መንቀሳቀስ የጀመሩት "አንድ ሰው አንድ ያግኝ" በሚል ነበር። በአንድ ዓመት ውስጥም ስድስት ኢትዮጵያውያን ንቁ ተሳታፊ አባል በመሆን ተመዘገቡ። በዓመቱም ማለቂያ አካባቢ ቁጥራቸው ወደ አሥራ ስድስት ደረሰ ነበር[16]።

የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አስፋፊ ከሚሲዮናውያኑ አንዱ በመንገድ ዳር ያገኘው ወጣት ነበር። የይሖዋ ምስክሮቹ ሚሲዮናውያን እንደሆኑ ለጓወቀ እርሱ ራሱ ጌታዬ እባክህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ንገረኝ አለው። ሚሲዮናዊውም ወደ ቤቱ ወስዶት "ሌት ጎድ ቢ ትሩ" [እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን] የሚለውን መጽሐፍ አስጠናው። በማግስቱም፣ በነበራቸው የጥናት ጊዜ ኢትዮጵያዊው አንድ ጓደኛውን ይዞ መጣ። በየዓመቱም መጨረሻ ላይ እነዚህ ሁለት ሰዎች ቅንዓት የነበራቸው ንቁ የይሖዋ ምስክር ሆኑ። እያንዳንዳቸውም በሚመሩት ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ከ20 ሰዎች በላይ ተካፋዮች ነበሩ[17]።

በቅንጅት የተጀመረውም ሚሲዮናዊ ሥራ ተቃውሞ የነበረበት ነበር። ሚሲዮናውያኑ እንዲህ በማለት ሪፖርት አድርገው ነበር፡-

> "ሳምንታዊውና ጠንካራው የኢትዮጵያ ሚሲዮናዊው ድርጅት፣ ሱዳን ኢንቲሪየር ሚሽን ምን አልባት የኛ ጠንካራው ተቃዋሚ ነው። ነገር ግን ድርጊቱ ምስክሮችን አፍርቶ ነበር። ሚሲዮኑ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤት ነበረው። በሳምንቱ ውስጥ ሚሲዮናውያንን በማሠልጠን እሁድ ከሰዓት በኋላ ልሱዳን ሚሽን እንዲሰብኩ ይልካቸዋል። ለስብከትም የሚልካቸው ወደ ሚሲዮናውያኑ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን ቤት እውነትን ለመማር ወደመጡት ሰዎች ነው። ከእነርሱም ውስጥ አንዱ ለእውነት ባለው አቋም ከኤስ አይ ኤም ሚሲዮን ተባረረ። ደስተኛም ስለነበር በመጀመሪያው ወር አገልግሎቱ 40 ሰዓት ሪፖርት አድርጓል"[18]።

14. Year book 1992, ገጽ 95-96
15. Awake . 1960, ገጽ. 21
16. Year book 1952. ገጽ. 65
17. ዝኒ ከማሁ።
18. Year book 1952 ገጽ 66 የይሖዋ ምስክሮች በመስክ ያሳለፉትን ሰዓት ለዋናው መሥሪያ ቤት ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል።



በርከት ያሉ ሰዎች ወደ ሚሲዮናውያኑ ቤት መምጣት ጀመሩ። የዓመቱንም ሚሲዮናዊ ሥራ በሚያበረታታ ሁኔታ አጠናቀቁ። ሚሲዮናውያኑ የዓመቱን ሪፖርት "ተግባራችን እስከ አርማጌዶን ድረስ እዚሁ ይቀጥል"[19] በሚል ጸሉት ደመደሙት።

ከጅማሬው አስደናቂ የሆነው ምላሽ የመጀመሪያው የመንግሥት አዳራሽ በ1953 ዓ.ም. ሲከፈትም ቀጥሎ ነበር። ሚሲዮናውያኑ፡- ኢትዮጵያውያን ለትምህርት ያላቸው ጥማትና የተማሩትንም ለማካፈል ያላቸው ፍላጎት አስደንቆናል የሚል ሪፖርት ለዋናው መሥሪያ ቤት አድርገው ነበር።

በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የኢትዮጵያው ንጉሥ ነገሥት፣ ኃይለ ሥላሴ በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ሚሲዮናውያን ሁሉ በመላው ኢትዮጵያ ትምህርት እንዲጀምሩ ፈቃድ ሰጡ። ይህ ጥሪ ይሖዋ ምስክሮችንም ያካተተ ነበር። የይሖዋ ምስክሮች አዲስ አበባ በሚገኘው የንግድ ሥራ ኮሌጅ ለማስተማር መፈለጋቸው ወደ አገሪቱ የመግባት ምክንያት ሆን ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከነበረው "መደበኛ ፖሊሲ የተለየ"[20] ነበር። የንግድ ሥራ ኮሌጁ ታይፕ፣ የሂሳብ መዝገብ አያያዝና እንግሊዝኛ መጠነኛ ክፍያ በማስከፈል ማስተማር ጀመረ። በዚህን ወቅት ከ125-13 ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ይማሩ ነበር። በ1952 ዓ.ም. ከጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተመረቁ አዲስ ሚሲዮናውያን ወደ አገሪቱ ገቡ[21]። ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የሁለት ቀን ስብሰባ አደረጉ[22]። ዚሚራማን [Zimmermans] የተባሉት ባልና ሚስቶች ወዲያው በንግድ ሥራ ኮሌጅ ውስጥ ማስተማር ጀመሩ። ሌሎች ሁለት ባልና ሚስቶች፣ ብሩመሊ [Brumleys] እና ሉክ [Lucks] ወደ ሐረር ክፍለ ሀገር በመሄድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፈቱ ከሚሲዮናውያኑ ውስጥ ሁለት ያላገቡ ወንዶች በድሬዳዋ ተመሳሳይ ትምህርት ቤት ከፈቱ። ድሬዳዋ ኪሪኮር አታዛኮርታዚያን ይኖርበት የነበርች ከተማ ነች። ሁሉም ሚሲዮናውያን እምነቱን ለማስፋፋት የተጠቀሙበት ዘዴ በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሰበካ ማካሄድ ሳይሆን ከትምህርት ክፍለ ጊዜ በኋላ ፈቃደኛ ተማሪዎችን ወደ ቤታቸው በመጋበዝ ስለ እምነታቸው ማስተማር ነበር[23]።

19. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 67
20. Awake, 1960, 21
21. Awake, 1957a, 17
22. Year book 1953. ገጽ.74
23. Year book 1992. ገጽ. 94

በ1953 ዓ.ም. ሚሲዮናውያኑ ይከተሉት የነበረውን እምነቱን የማስፋፋት ዘዴ በመቀየር በየመንገድ ዳር የተገኘውን ሰው ብቻ ሳይሆን የሰዎችንም ቤት ማንኳኳት ጀመሩ። የይሖዋ ምስክር ለመሆን ካልወሰኑ ሰዎች ጋርም የሚደረገው ጥናት እንዳይራዘም ወሰኑ።

ቤት በማንኳኳት በተካሄደ የመስክ አገልግሎት የተገኙት የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት በ1953 ዓ.ም. ተጠመቁ። በዚህ ጊዜ ነበር የወቅቱ የይሖዋ ምስክሮች ፕሬዝዴንት፥ ናታን ሆመር ኖር ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት[24]።

የይሖዋ ምስክሮች በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቁ፥ በሚያማምሩ ስዕሎች የተሞሉ ጽሑፎችን አዳዲስ አባሎችንም ሆነ ነባሮችን ለማስተማር ይጠቀሙ። በ1955 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በአጥቢያ ሚሲዮናውያን የአማርኛ ጽሑፎች ተዘጋጁ። እነዚህ አነስ ባለ መጽሐፍ የተዘጋጁት የመጀመሪያ ጽሑፎች “የእግዚአብሔር መንገድ ፍቅር ነው”. እና “ይህ የመንግሥት መልካም ዜና” የሚባሉት ናቸው[25]። እነዚህ ጽሑፎች በሚሲዮናውያኑ መልዕክት በተደሰቱ ሰዎች ቤት ይቀመጡ ነበር።

ከጽሑፎቹ በተጨማሪ ሰዎችን ወደ እምነቱ ለመሳብ የተደረገው ሌላው ሙከራ፦ “አዲሱ ማኅበረሰብ በድርጊት ላይ” [“The New World Society in Action] የሚሰውን ፊልም በአገሪቱ ትልቅ ሲኒማ ቤት ውስጥ ማሳየት ነበር። ማስታወቂያዎች በየሰፍራው ስለተሰጡ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩት ሰዎች ከሲኒማ ቤቱ አቅም በላይ ስለነበሩ አብዛኞቹ ፊልሙን የተከታተሉት ቆመው ነበር። ከፊልሙም በኋላ ለእያንዳንዱ ታዳሚ በራሪ ጽሑፎች ተሠራጩ። የአካባቢውን ፀጥታ ለማስጠበቅ የመጡት ፖሊሶች ጭምር ጽሑፎቹን በማሠራጨት ተባብረዋል[26]። ፊልሙ በጎንደር፥ በደሴና በአስመራ ለዕይታ ቀርቦአል[27]።

24. Year book 1952. ገጽ. 149
25. Year book 1992. ገጽ. 98-100
26. Year book 1957. ገጽ 140-141
27. Year book 1992. ገጽ. 100



በ1950ዎቹ መካከል ላይ የመጠበቂያ ግንብ ሚሲዮናውያን ከአዲስ አበባ ውጪም ሆነ ትምህርት ቤት ባቋቋሙባቸው ከተሞች እንዳይሰብኩ ተከለከሉ። ብሮክሊን የሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት ኢትዮጵያውያኑን በአቅኚነት እያሰለጠነ ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ሰፍራዎች በተነ። በ1954 ዓ.ም. መጨረሻ አሥራ ዘጠኝ አስፋፊዎች በአሥራ ሦስት ከተሞችና መንደሮች ይሰብኩ ነበር። ከስድስት ሳምንት ስብከት በኋላ በአንድ ከተማ ውስጥ ሁለት ኢትዮጵያውያን አቅኚዎች አሥራ ሦስት የቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ያካሂዱ ነበር። አሥር ሰዎችም በመስክ አገልግሎት ጊዜ አብረዋቸው በመሆን ያስፋፉ ነበር። በ1954 ዓ.ም. አዲስ ጉባዔ ተቆረቆረ[28]። እነዚህ አስፋፊዎች ወደ አዲስ አበባ በመላክ አዲስ አበባ ለሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት የሥራ ሪፖርት ይጽፉ ነበር። የነዋሪው ሕዝብ 15000 በሚደርሳቸው ከተሞች ቢያንስ ሰምንት ንቁ ተሳታፊ አባላት የሚገኙባቸው ጉባዔዎች ተቋቋሙ። በዚህ አካባቢ የሚገኝ የፕሮቴስታንት ሚሰዮናዊ አንድ የይሖዋ ምስክር አቅኚ አግኝቶ እምነቱ የተሳሳተ አዲስ ሃይማኖት እንደሆነ ነገረው። አቅኚውም፡ የይሖዋ ምስክሮች አዲስ አይደሉም አቤል ራሱ የይሖዋ ምስክር ነበር አለው። ሚሲዮናዊው ለአቅኚው እምነቱ ራስልና ሮዘርፎርድ የሚባሉ የሁለት ግለሰቦች እምነት እንደሆነ ነገረው። አቅኚው እነዚህን ሰዎች ፈጽሞውኑ ሰምቶ እንደማያውቅ ገለጸለት። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናዊ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥቶ ነበር “ምንም እንኳ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን ታሪክ በቅጡ ባያውቅም እምነቱ የተመሠረተበትን የእግዚአብሔር ቃል ያውቅ ነበር”[29]።

በ1950ዎቹ መካከል አዲስ መስፋፋት ከተደረገባቸው አካባቢዎች አንዱ ኤርትራ ነው [በወቅቱ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴራሲዮን ነበረች]። ሁለት አስፋፊዎች በጤና ችግር ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ በመሄድ የመጀመሪያ ሥራቸውን ጀመሩ። በ1956 ዓ.ም. አዲስ ጉባዔ ተቆረቆረ 50 ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈሉ ነበር። በ1956 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናዊ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ በመሄድ ሚሲዮናዊ ሥራ ጀመረ፥ ጽሑፎችንም ለማሠራጨት ፈቃድ አገኘ[31]።

28. Year book 1955. ገጽ 143 and Year book 1957. ገጽ. 141
29. Year book 1956. ገጽ. 141-142
30. Year bonk 1955. ገጽ. 143 & Year book 1957. ገጽ 36-37
31. Awake 1960. ገጽ. 21-26

በመጀመሪያዎቹ ስምንት ዓመት በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ የተደረጉ ሚሲዮናዊ ሥራዎች ፈጣን እድገት የሌለባቸው ነገር ግን ብዙ ያደከሙ ነበሩ። በ1958 ዓ.ም. 128 ንቁ ተሳታፊ አባላት በስምንት ጉባዔዎች ውስጥ ይገኙ ነበር። ጉባዔዎቹ ከምዕራቡ ዓለም በመጡ ሚሲዮናውያን ሳይሆን በኢትዮጵያውያን የሚመሩ ነበሩ[32]።

## የመጀመሪያው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች በመጀመሪያ ስደት ደረሰብን የሚሉት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በ1954 ዓ.ም. የይሖዋ ምስክሮች ከመንግሥት ጥቂት ተቃውሞ ገጥሞአቸው ነበር። በዚህ ዓመት ብዙ የመጠበቂያ ግንብ ሚሲዮናውያን ወደ አገር ለመግባት ጠይቀው ጥያቄያቸው ውድቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ሚሲዮናውያን የመቆየት ሕልም አጨልሞ ነበር። ከመንግሥት የደረሰባቸውን ተቃውሞ የጠነሠሱት ከመንግሥት ጋር ይሠሩ የነበሩ ሌሎች ሚሲዮናውያን ናቸው የሚል እምነት አላቸው[32]።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከውጪ የሚመጡትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ብትቃወምም፤ የይሖዋ ምስክሮች የሥላሴን አስተምህሮ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት፥ የመንፈስ ቅዱስን ሰብእና እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑትን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮቶች ስለማይቀበሉ ከሌሎቹ ሚሲዮናውያን ይልቅ የይሖዋ ምስክሮችን አጥብቃ ትቃወም ነበር። በ1957 ዓ.ም. ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ አገር አቀፍ የሆነ ተቃውሞ አስነሥታ ነበር። በሚያዝያ ወር 1957 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያኒቱ ዲያቆን በሰንበት ቀን ወደ ደብረ ማርቆስ ከተማ ዋና አደባባይ በመሄድ የይሖዋ ምስክሮችን አወግዞ ነበር[33]። "እነዚህ ሰዎች የማሪያም ጠላቶች ናቸው። የአሪዮስ ተከታዮች ከአገራችን ይውጡ" እያለ ጽሑፋቸውን "በእግሩ በመርገጥ" ነበር ተቃውሞውን የገለጸው። ሕዝቡም በቁጣ በመነሣሣት የይሖዋ ምስክሮች በሚሰበሰቡበት ጉባዔ ሄዶ ተቃውሞ ነበር። በዚህም ችግር ምክንያት የይሖዋ ምስክሮች በፖሊስ ጥበቃ እያሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ኮሚቴ በማዋቀር የይሖዋ ምስክሮችን አስተምህሮ መረመረ። በግንቦት 28 ቀን 1957 ዓ.ም. [ኮሚቴው የኮሚቴው ስም፡- "የኢትዮጵያ ሕዝቦች ደኅንነት ባለሥልጣን" ይባላል] የሚከተለውን ትእዛዝ አወጣ፡-

32. <u>Awake</u> 1957a, ገጽ. 28 32. <u>Year book 1955</u>, ገጽ.143
33. <u>Year book 1992</u>, ገጽ. 100



> "የመጠበቂያ ግንብ ሚሲዮን ለሕዝቦች ደኅንነት አደገኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ የዚህ ድርጅት የውጪ ሚሲዮናውያን ሁሉ እስከ ሰኔ 10 ቀን አገር ለቀው እንዲወጡ። በድርጅቱ የሚካሄዱ ማንኛውም እንቅስቃሴዎች ከላይ እስከ ተጠቀሰበት ጊዜ ድረስ እንዲያቆሙ "[34]።

አንድ መቶ ሃያ ስምንት የሚሆኑ የንግድ ሥራ ኮሌጅ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ ለአገሪቱ ትልቅ ጥቅም ስለሚሰጥ ተጨማሪ አስተማሪዎች እንዲመደቡ ለትምህርት ሚኒስቴር አመለከቱ። ተማሪዎቹ ከመንግሥትም ጋር በርካታ ስብሰባዎችን አደረጉ። የተማሪዎቹ አቤቱታ፡- በ1955 ዓ.ም. የወጣው ሕገ መንግሥት ለሃይማኖቶች ሁሉ እኩል መብት ስለሚሰጥ የይሖዋ ምስክሮች ከአገር መባረር የለባቸውም የሚል ነው። የሃይማኖት ነጻነቱን አስመልክቶ አንድ ምክትል ሚኒስቴር እንዲህ አሉ፡- "የሃይማኖት ነጻነት እንደ ምላጭ ነው። ጎልማሳ ሰው ተጠንቅቆ ይጠቀምበታል፤ ነገር ግን ሕፃናት ሰውነታቸውን ይተለትሉበታል።" የሚኒስቴሩ ምሳሌ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሃይማኖት ነጻነት ዝግጁ ያለመሆኑን የሚያመለክት ነበር። የይሖዋ ምስክሮች ግፊቱ የመጣው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው ባዮች ናቸው[35]። ትእዛዙ ሊሻሻል ስላልቻለ ሁሉም የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን አገር ለቀው እንዲወጡ ተደረገ[36]።

ነገር ግን ሚሲዮናውያኑ በኤርትራ የመቆየት ፈቃድ ተሰጥቶአቸው ነበር። በአዲስ አበባ የነበረው ዋና መሥሪያ ቤት ስለተዘጋ ብሮክሊን የሚገኘው ዋና ጽሕፈት ቤት በኤርትራ የነበረውን ሥራ ይቆጣጠር ጀመር። "ሕይወት በአዲስ ዓለም" የሚባለው የትግርኛ በራሪ ጽሑፍ በ1957 ዓ.ም. ታተመ። ከ1958 ዓ.ም. ጀምሮ "መጠበቂያ ግንብ" የተባለው መጽሔት በትግርኛ ቋንቋ እየታተመ መውጣት ጀመረ። ጥቂት አቅኚዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከአስመራ ከተማ ወደ ገጠር አካባቢዎች ተላኩ። በ1958 ዓ.ም. አራት ጉባዔዎች በገጠር ተቋቁመው ነበር። የይሖዋ ምስክሮች በኤርትራ የገጠማቸው ችግር ስደት ሳይሆን ሰዎች ለእምነቱ የነበራቸው ፍላጎት ሥር የሠደደ ያለመሆኑ ነው[37]።

በ1959 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ የሚገኙትን የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲሁም በኢትዮጵያ ያወጣው እገዳ በኤርትራም ተግባራዊ እንዲሆን አደረገ። በ1960 ዓ.ም. ሁሉም የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን አገር ለቀው ወጡ[38]።

34. <u>Awake</u> 1957b, ገጽ. 17
35. <u>Awake</u> 1957 b, ገጽ.18-19
36. <u>Year book 1992</u>, ገጽ. 101
37. <u>Year book 1958</u>, ገጽ 77-78 & Year book 1959, ገጽ. 82-83
38. <u>Awake</u> 1960, ገጽ 21-26

ምንም እንኳ ከኤርትራም ሆነ ከኢትዮጵያ ምዕራባውያኑ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን ከአገር ቢባረሩም በ1957 ዓ.ም. ከነበረው የአባላት ቁጥር በ1956 ዓ.ም. የዘጠኝ ሰዎች እድገት አሳይቶ ነበር[39]። ነገር ግን ይህ ቁጥር 1962 ዓ.ም. ወደ 76 [ከ129 ወደ 76] አሽቆልቁሎ ነበር[40]። በ1962 ዓ.ም. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ፌዴሬሽን ስለተጠናቀቀ ኤርትራ የኢትዮጵያ ክፍለ አገር ሆነች። ይህም በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው የሠላሳ አሥርተ ዓመታት ጦርነት አስከተለ። ይህ ነው እንግዲህ ለይሖዋ ምስክሮች የአባላት መመናመን ምክንያት የሆነው ከ1961 ዓ.ም. እስከ 1966 ዓ.ም. ምንም ዓይነት "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት በአማርኛ ቋንቋ አልታተመም። ዓመታዊ መጽሐፍም በኢትዮጵያ የነበሩትን የይሖዋ ምስክሮች ቁጥር አልገለጸም[41]። በ1964 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ከነበረው ችግር የተነሣ በኢትዮጵያ የነበረው ጉባኤዎችን የመቆጣጠር ሥራ ወደ ኬንያው ቢሮ ተዛወረ።

ከ1960ዎቹ መካከል ጀምሮ የይሖዋ ምስክሮች አንጻራዊ ነጻነት ስላገኙ በየመንገድ ዳርም ሆነ የሰዎችን በር በማንኳኳት እምነታቸውን መስበክ ጀመሩ። በ1961 ዓ.ም. "እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን" [Let God Be True] በ1973 ዓ.ም. "ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት" እንዲሁም "እውነተኛ ሰላምና ጥበቃ–ምንጭ የቱ ነው?" [True Peace and Security – From What Source?] የሚባሉት መጽሐፍት በአማርኛ ታተሙ። በትግረኛ ቋንቋ ደግሞ "የመንግሥት አደረጃጀት – በብከትና ደቀ መዛሙርት ማፍራት" [Organization for Kingdom – Preaching and Disciple – Making] የሚባለው መጽሐፍ ተዘጋጀ።

ኢትዮጵያውያን የይሖዋ ምስክሮች ዓለማቀፋዊ ስብሰባዎችን የመካፈል ዕድል አገኙ። በ1969ዓ.ም ሠላሳ ሦስት የኢትዮጵያ ተወካዮች ፡– "ሰላም በምድር" [Peace on Earth] የተባለውን ጉባኤ በኒውዮርክና በለንደን ተካፈሉ[42]። በ1973 ዓ.ም. በኬኒያ "መለኮታዊ ድል" [Divine victory] የተባለውን ዓለማቀፋዊ ስብሰባ ጥቂት ኢትዮጵያውያን እንዲካፈሉ ተፈቀደላቸው። በአጠቃላይ አንጻራዊ ሰላሙ የይሖዋ ምስክሮች የመስክ አገልግሎት እንዲያካሂዱ፣ ጽሑፎቻቸውንና መጽሔቶቻቸውን እንዲያሠራጩ፣ ዓለማቀፋዊ ስብሰባዎችን እንዲካፈሉ ረድቶአቸዋል።

39. "የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያና በኤርትራ ከ1951–1990" የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል
40. Year book 1964, ገጽ 277-
41. "የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ" የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል።
42. Year book 1970, ገጽ. 197



እነዚህ ዓመታት ለይሖዋ ምስክሮች ፍጹም የተመቹ ነበሩ ማለት አይቻልም። በአንዳንድ አካባቢዎች የይሖዋ ምስክሮች እንዳይሰብኩ በፖሊስ ታግደው ነበር። አንዳንዶች እገዳውን ቸል በማለት ለመስበክ በመሞከራቸው በወኅኒ ተጥለዋል። እሁድ ነሐሴ 27 ቀን 1972 ዓ.ም. ፖሊስ በአንዳንድ ጉባዔዎች በመሄድ 208 የይሖዋ ምስክሮችን አሠረ። ከእነዚህ ውስጥ 96ቱ ስድስት ወር ወኅኒ እንዲወርዱ ተፈረደባቸው። ነገር ግን አሥራቱ በገንዘብ ስስተለወጠ ገንዘቡን ከፍለው ተፈቱ። በ1971 ዓ.ም. በመንግሥት ባለሥልጣኖች ትእዛዝ በአስመራ የነበረው አጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ተዘጋ[43]።

አብዛኞቹ ችግሮች የተፈጠሩት በይሖዋ ምስክሮችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስነበረው ችግር ነበር። በ1974 ዓ.ም. ብዙ የይሖዋ ምስክሮች ወኅኒ የወረዱት በስብከታቸው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ስለ ነኮታተሉ ነበር[44]። "ንቁ" በመባል የሚታወቀው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሔት በወቅቱ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አሠራጭቶ ነበር፡– በቤተክርስቲያኒቱ መሬት ላይ ያለው አርሶ አደር ለመሬቱ ክራይ ቢከፍልም በከፍተኛ ሁኔታ በርሀብ እየተሰቃየ ነው[45]። በጊዜ የነበረውን ርሀብ ደግሞ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ፍጻሜ ተመልክቶ ነበር[46]።

ምንም እንኳ እስከ አሁን ያየነው የይሖዋ ምስክሮች በውጭ የተነሣባቸውን ችግር ቢሆንም፤ ውስጣዊ አለመግባባቶችም ተፈጥረውባቸው ነበር። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት (የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት) የነበረው የጴንጤቆስጤ ልምምድ ወደ አጥቢያ የይሖዋ ምስክሮች ጉባዔም ደርሶ ነበር። ስለዚህም አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች ሰማያዊ ተስፋ ተቀብለናል ማለት ጀመሩ [እንደ መጠበቂያ ግንብ ማኅበር አስተምህሮ ለማያዊ ተስፋ የተቀበሉት "ቅቡዓን" ብቻ ናቸው]። ናይሮቢ ከሚገኘው ቢሮ ዊሊያ ኒስበት [William Nisbet] የተባለው ሚሲዮናዊ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ችግሩን ለመቅረፍ ቢሞክርም አንዳድ የይሖዋ ምስክሮች በአቋማቸው ስለጸኑ ከድርጅቱ ተባረዋል[47]።

43. Year book 1970 ገጽ.129-130
44. Year book 1975 ገጽ. 7-8
45. Awake 1974b, ገጽ. 30
46. Awake 1974a, ገጽ 7-8
47. Year book 1992, ገጽ. 130

### ሁለተኛው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች ይጋጠማቸው ሌላው ስደት ከማርኪሲስታዊው መንግሥት ነው። በመስከረም 1974 ዓ.ም. በመፈንቅለ መንግሥት ደርግ ሥልጣን ጨበጠ። አገሪቱም በማርኪሲዝም – ሌኒኒዝም ሪእተ – ዓለም መተዳደር ጀመረች። በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት፣ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ታላቅ የሆነ ስደት ደረሰባቸው። እንደ 1980ዎቹ ከ1980 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. በዓመታዊ መጽሐፉም ሆነ "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ምንም ዓይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው[48]። እንደ 1992 ዓ.ም. ዓመታዊ መጽሐፍ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል[49]።

### ማጠቃለያ

የከሪኮር ኢታዛኮርታዚያን ወራሾች ከ1991 ዓ.ም. ወዲህ ባሉት ዓመታት የየዓመቱ የእድገት መጠናቸው በአማካይ 15 በመቶ መሆኑ የሚያመለክተን እጅግ ስኬታማ መሆናቸውን ነው። በየዓመቱም አዲስ አበባ በሚገኘው የስፖርት መጫወቻ ሜዳ [ስታዲየም] አገር አቀፍ ስብሰባቸውን ያደርጋሉ። በ1997 ዓ.ም. ስታቲስቲክ መሠረት፡– 5,849 ንቁ ተሳታፊ አባላት፣ 5,292 ለመስክ 918 አቅኚዎች፣ 97 ጉባዔዎች፣ ለመስክ አገልግሎት 1,570 141 ሰዓት፣ 3,874 በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አሉአቸው።

ለይሖዋ ምስክሮች እድገት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት መካከል በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፣ ሊለብ የሚችሉና ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጁት ጽሑፎቻቸው፣ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረት እምነቱን ማወቁ፣ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው[50]።

---

48. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ የሚለውን ርዕስ ይመልከቷል።
49. 1992 ዓመታዊ መጽሐፍ በደርግ ዘመን ስለ እምነታቸው የተገደሉትን ሰዎች ስምና ፎቶግራፍ አውጥቶአል።
50. አባላቱ የመጠበቂያ ግንብን አስተምህሮ የሚያስተምሩት እንዲሁም የድርጅቱን ጽሑፎች የሚያሠራጩት "የመስክ አገልግሎት" ለደኅንነታቸው አስፈላጊ (እንገብጋቢ) ስለሆነም ጭምር ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን? ... 50
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም ... 60
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ ... 74
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ... 92
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ ... 104
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፣ በነፍስና በሲኦል ላይ ... 123
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ... 132

## 3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን?

እንደ ይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ አንድ እውነተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ ድርጅት ብቻ አለ[1]። ይህም ድርጅት "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" ነው። ይህ የሃይማኖት ድርጅት "የክርስቲያኖች ዓለማቀፋዊ ማኅበር ሲሆን የይሖዋ አምላክንና ለሰዎች ያለውን የእርሱን ዓላማ በንቁነት የሚመሰክር"[2] ነው።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች እምነት የመጠበቂያ ግንብ እግዚአብሔር ራሱ የእርሱ ወኪል እንዲሆን የመሠረተው ድርጅት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ቃሉን የሚያስተምረው በዚህ ብቸኛ ድርጅት በኩል ብቻ ነው። ካለ ድርጅቱና በድርጅቱ እየታተሙ ከሚወጡ ጽሑፎች በስተቀር ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን አንብበው እውነተኛ ትርጉሙን ሊያገኙ በፍጹም አይችሉም። "መጠበቂያ ግንብ" በሚል ርዕስ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡ መጽሔቶች እንዲህ ይላሉ፦

- "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የዓለማችን ትልቁ ኩባንያ [Corporation] ነው፤ ምክንያቱም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ጌታ ምሥራቹን ያስታወቀው በድርጅቱ አማካኝነት ነውና"።[3]
- "ከመከር ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተከታታይ እግዚአብሔር እውነቱን ለማሠራጨት የተጠቀመው አንዱና ብቸኛው ድልድይ በሆነው በመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በኩል አይደለምን?"[4]
- "የጆሆቫ [ የይሖዋ] የሚታይ ምድራዊ ድርጅት በእርሱ የሚመራና እርሱን የሚወክል ነው"[5]

1. የድርጅቱን አስተምህሮ በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ። (1991) ገጽ 191–195፣ ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፣ (1994) ገጽ 280–284 ይመለከቷል።
2. Reasoning from the scriptures (1989) ገጽ. 199
3. The Watchtower, 15 January 1917, ገጽ. 6033
4. The Watchtower, 1 April 1919, ገጽ. 6414



- "እግዚአብሔር የራሱን ድርጅት እየመራ እንዳለ ልብ ልናደርግ ይገባናል"[6]
- "በምድር ሁሉ ላይ የጆሆቫ ድርጅት በእግዚአብሔር መንፈስ ወይም ንቁ ኃይል የሚመራ ብቸኛ ድርጅት ነው"[7]

እንደ ይሖዋ ምስክሮች ዐዋጅ ከላይ ያየናቸው ዐረፍተ ነገሮች ሁሉ እውነት ከሆኑ ከእነርሱ በስተቀር ሌላ ክርስቲያናዊ ድርጅት በእግዚአብሔር የማይመራ ሰይጣናዊ ድርጅት ነው ማለት ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ሁሉ ለዚህ እውነተኛ ለሆነ ብቸኛ ድርጅት መገዛት አለባቸው። ምክንያቱም ድርጅቱ የእግዚአብሔር እውነት መገለጫ ብቸኛው ምድራዊ ድርጅት ነውና። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅቱን እንደ እግዚአብሔር ድምፅ እንዲታዘዙት ይጠበቅባቸዋል[8]። ይህ ብቻ አይደለም ድርጅቱ ስለ ራሱ እንዲህ ይላል፦ "ጆሆቫ አምላክን ብቻ አይደለም እንደ አባትነት ልናውቀው የሚገባን ነገር ግን የእርሱን ድርጅት እንደ እናትም ጭምር እንጂ"[9]።

የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በቂ ላለመሆኑ ድርጅቱ እንዲህም የሚል ትምህርት አለው፦ "እግዚአብሔር ከሚጠቀምበት ከዚህ [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር] ድልድይ ጋር ግንኙነት ከሌለን፥ ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብም በሕይወት ጎዳና እርምጃ ልናሳይ አንችልም"[10]።

"በመጠበቂያ ግንብ [መጽሔት] አምድ ጆሆቫ በቀጣይነት ለሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር አዘጋጅቶአል"[11] ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች "ለልባምና ታማኝ ባሪያዎች" [መንፈሳዊ ምግብ የሚያወርዱ ይህንንም ድርጅቱ በሚያሳትማቸው ጽሑፎች በኩል የሚያስተላልፍ "ቅቡዓን"፥ "ልባምና ታማኝ ባሪያ" በመባል ይታወቃሉ] እንዲሁም ለጽሑፎቻቸው መገዛት አለባቸው። በመጠበቂያ ግንብ ውስጥ ያሉ ቅቡዓ አማኞች የሚወክሉት "መንፈሳዊ ምክሮች ሁሉ የሚመጡበት

5. The Watchtower, 1 May 1938, ገጽ. 169 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
6. ዝኒ ከማሁ
7. The Watchtower, 1 June 1985, ገጽ. 19
8. The Watchtower, 15 June 1957, ገጽ. 370
9. The Watchtower, 1 May 1957, ገጽ. 274
10. The Watchtower, 1 December 1981, ገጽ. 27 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
11. The Watchtower, 1 May 1964, ገጽ. 277 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

ብቸኛ የሆነ የሚታይ [የአምላክ] ድልድይ"[12] ስለሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር ለድርጅቱ፥ ለድርጅቱ ጽሑፍና ለጽሑፍ ጸሐፊያን መገዛት አለበት። የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ "የልባምና ታማኝ ባሪያዎችን ሹመት ስለሚያውቁና ስለሚቀበሉ ይገዛሉ"[13]።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

ከላይ የተመለከትናቸውን የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለማስደገፍ ድርጅቱ የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው፤–

አንድ እውነተኛ ድርጅት ብቻ አለ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ "አንድ እምነት ብቻ" እንዳለ ያስተምረናል (ኤፌ. 4፥5)። ይህም አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ "አንድ መንጋ" የተባለው ነው (ዮሐ. 10፥16)።

ዛሬ በተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ ያለው መከፋፈል የሚያሳየን እነዚህ መንፈሳዊ ድርጅቶች ከእግዚአብሔር ድርጅት ጋር ኅብረት ያለመፍጠራቸውን ነው (1ቆሮ. 1፥10)።

አማኞች ለዚህ ብቸኛ የአምላክ ድርጅት መገዛት አለባቸው። አማኞች መንፈሳዊ ምግብ የሚያወርዱላቸው "ልባምና ታማኝ ባሪያ" ያስፈልጋቸዋል (ማቴ. 24፥45–47)። በዚህ ክፍል በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ባሪያ" ከሚለው ቃል ፊት ያለው የተወሰነ መስተዓምር [The] የሚያመለክተው ሁሉንም "ባሪያዎች" ሳይሆን የተወሰኑትን ብቻ ነው። ይህም "ባሪያ" የተወሰነ የክርስቲያን ስብሰብ ነው። ይህም ባሪያ የሚያሳየው የይሖዋ ምስክሮችን "የቅቡዓን" ክፍል ነው። እነዚህ ባሪያዎች አስተማሪ እንደመሆናቸውም መጠን ዋና

12. Marina Bodine. Christian Research Newsletter, "Bible Answer Man" Column, May 1 June 1992, ገጽ.3 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

13. Robert M. Bowman, Understanding Jehovah's Witnesses (Grand Rapids: Baker House, 1991), ገጽ. 119



ሥራቸው መንፈሳዊ ምግብንና አስተምህሮአዊ መረጃዎችን ለተቀሩት የይሖዋ ምስክሮች ማውረድ ነው። ሁሉም የይሖዋ ምስክሮች "ለባሪያዎቹ" ትምህርት በየባምንቱ ሊገዙና ከአምላክም የሚመጣውን ማንኛውም ትምህርት በሙሉ ልብ መቀበል አለባቸው።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ ያለው የኢየሩሳሌም ስብሰባ ይህን አቀራረብ እንድንከተል ያስተምረናል። እያንዳንዱ ጉባዔ ብቻውን ምንም ዓይነት ሥራ ሊሠራ አይችልም። ነገር ግን በኢየሩሳሌም ለሚገኙት "የሽማግሌ" አካላት ብቻ ሌሎች ይገዛሉ። በአሜሪካን አገር ብሮክሊን በሚባለው ሰፍራ የሚገኙት የድርጅቱ የአመራር አካላት እንደ ኢየሩሳሌሙ ጉባዔ የሽማግሌዎች ስብስብ ናቸው። የድርጅቱን ሥራ የሚያከናውኑት እነዚህ "ልባምና ታማኝ ባሪያዎች" ናቸው።

ስለዚህ ሁሉም የይሖዋ ምስክሮች ከአመራር አካላት የሚመጣውን ማንኛውም ዓይነት አዲስ ትምህርት፥ ከበፊቱ አስተምህሮት ጋር እንኳ ቢጋጭ ያለምንም ጥያቄ መቀበል አለባቸው።

በተጨማሪም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሐዋ. 8፥30–31 እና 2ጴጥ. 1፥20–21 መደገፊያ በማድረግ ማንኛውም የይሖዋ ምስክር መጽሐፍ ቅዱስን በግል አጥንቶ ያጠናውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማብራራት እንደሌለበት፤ እንዲያውም ሊሞክረው እንኳን እንደማይገባ፤ ነገር ግን በመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የመጽሐፍ ቅዱስ ትንተና ሊደገፍ እንደሚያስፈልገው የሚያስተምሩት የድርጅቱ ጽሑፎች እንዲህ ይላሉ፡–

- "እግዚአብሔር ቃሉን ያዘጋጀው በነጠላ ሰዎችን ለመናገር አይደለም ወይም የሕይወትን እውነታ በራሱ እንዲያንፀባርቅ ብሎ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ብርሃንን ያዘጋጀው በድርጅቱ በኩል ነው"[14]
- "የነጠላ አስተሳሰብን ሆነ . . . እግዚአብሔር በሚታየው ድርጅት ያዘጋጀውን ምክር ያለመቀበል አስወግዱ"[15]
- "የነጠላ ሕሳቦትን ተዋጉ"[16]
- "ጥገኛ ያልሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሳይሆን ጥገኛ የሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ፈልጉ"[17]

14. The Watchtower, 1 May 1957, ገጽ. 274

15. The Watchtower, 15 January 1983, ገጽ. 22

16. ዝኒ ከማሁ ገጽ 27

17. The Watchtower, 15 September 1911, ገጽ. 4885

- “ከጆሆቫ የማይታይ ላይ ልባችንን ካላደረግን በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል መረዳት አንችልም”[18]
- “ጆሆቫንም ሆነ የድርጅቱን ሰዎች የምናፈቅር ከሆነ ተጠራጣሪዎች አንሆንም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው የመጠበቂያ ድርጅት የሚያመጣውን ‘ሁሉ ነገር ማመን ነው’ ”[19]
- “[እግዚአብሔር] ከሚታየው ድርጅቱ በስተቀር መንፈስ ቅዱስን ሆነ ቃሉን መረዳትንና ማድነቅን አይሰጥም”[20]



## የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን የአምላክ ድርጅት ነውን?



የይሖዋ ምስክሮች ከኤፌ. 4፥5 “አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት” በሚለው ጥቅስ ላይ በመደገፍ “አንድ እውነተኛ የሃይማኖት ድርጅት ብቻ አለ” የሚለው ትምህርት ፍጹም ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ክፍሉ “አንድ ሃይማኖት” አለ እንጂ “አንድ ድርጅት ብቻ አለ” አላለም። ሰዎች ባጥቃቅን አስተምህሮዎች ላይ የተለያየ አመለካከት ስላላቸው በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ አሉ (ሮሜ 14)። ነገር ግን በመሠረታዊው የቃለ እግዚአብሔር አስተምህሮት ላይ ተመሳሳይ የእምነት አቋም አላቸው።

እርግጥ ነው ዮሐ. 10፥16 “አንድ መንጋ” አለ ይላል። ነገር ግን “አንድ መንጋ” አለ ማለት አንድ “የሃይማኖት ድርጅት ብቻ አለ” ማለት በፍጹም አይደለም። ከክፍሉ ዐውደ ንባብ የምንግማረው ነገር ይህ “መንጋ” የእረኛውን፥ የክርስቶስን ድምፅ የሚሰማ፥ እርሱ የሚያውቃቸው፥ እነርሱም የሚያውቁት ማለት ነው (ቁ. 7–9, 11, 14–15, 26–27) እንጂ “አንድ መንጋ” ማለት በአንድ የሰበአዊያን ድርጅት የታቀፈ ማለት አይደለም።

---

18. <u>The Watchtower</u>, 1 October 1967, ገጽ. 587
19. <u>Qualified to the Ministers</u>, (1955), ገጽ. 156
20. <u>The Watchtower</u>, 1 July 1965, ገጽ. 391 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም



በአንደኛ ቆሮ. 1፥10 በመመሥረት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት “ዛሬ የሚታየው የሃይማኖት መከፋፈል ድርጅቶቹ ሐሰተኛነታቸውን የሚያሳይ ነው” የሚለው ትምህርቱን ለማስደገፍ ብቻ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ጥቅስ እንጂ የክፍሉን ትምህርት የሚያንጸባርቅ አይደለም። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ክርስቲያኖች ጠንካራ ኅብረት መፍጠር እንዳለባቸው ያስተምራል እንጂ ያለመግባባታቸው ወይም መለያየታቸው ከትክክለኛው መሠረተ እምነት መውጣታቸውን ወይም ሐሰተኛ ሃይማኖት መከተላቸውን ለማሳየት በፍጹም እይደለም። ምንም እንኳ በመካከላቸው “እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ” የሚል መለያየት ቢኖራቸውም ጳውሎስ ግን እነዚህን ሰዎች “ወንድሞች” (1ቆሮ. 1፥2) ነበር የሚላቸው እንጂ “በልባምና ታማኝ ባሪያ” የሚመራ ሃይማኖታዊ ድርጅት ይኑራችሁ በፍጹም አላለም።

ከላይ እንደተመለከትነው የይሖዋ ምስክሮች በማቴ. 24፥46–47 “ልባምና ታማኝ ባሪያ” የሚለው አገላለጽ ክርስቲያንን በአጠቃላይ የሚያሳይ ሳይሆን ድርጅቱ የክርስቶስ ቅቡዓ ተከታዮች [ የ144 ሺው] በድርጅት ደረጃ የተሰበሰቡትን ብቻ የሚያሳይ ነው። እነዚህም የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤት የአመራር አካላት ናቸው የሚል የእምነት አቋም አላቸው።

ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ክፍል ላይ የሚናገረው ለተለዩ ወይም ለተወሰኑ “ባሮች” ሳይሆን በአጠቃላይ ለታማኝ ባሮችና ታማኝ ላልሆኑ ባሮች ጭምር ነው። “ባሪያ” ከሚለው ቃል ፊት ያለው የተወሰነ መስተፃምር ለተወሰነ ወይም ለተለየ ባሪያ የተጠቀሰ ነው የሚለው የድርጅቱ ትንታኔ ከእንግሊዝኛም ሆነ ከግሪክ ሰዋሰው እውነት እጅግ የራቀ ነው። በእንግሊዝኛም ሆነ በግሪክ ሰዋስው ነጠላ ቁጥር በሚያሳይ ስም ፊት የተወሰነ መስተፃምር መኖር አጠቃላይ የሆነ ነገር ሊያመለክት ይችላል [ለአብነት ያህል አንድ የእንግሊዝኛ ዐረፍተ ነገር እንመልከት፡– The Wise person plans ahead. በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ብልኀ [Wise] የሚለው ቃል የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። ከእርሱ ፊት ያለው የተወሰነ መስተፃምር [the] ብልኀ [Wise] የሚለውን ቃል የተወሰነ ብልኀ ብቻ እንዲያመለክት አላደረገውም፤ ነገር ግን ብልኀ የሚለው ነጠላ ስም አስቀድሞ የሚያቅድን ማንኛውንም ብልኀ ሰው የሚያመለክት ነው።]

የክፍሉም ዐውድ የሚያመለክተው በአጠቃላይ ታማኝ ስለሆኑና ታማኝነት ስለጎደላቸው ባሮች ነው። ጌታ እየተናገረ ያለው እርሱ

የሚናገረውን ሁሉ ስለሚያደርግ ወይም ስለሚጠብቅ ባሪያ አይደለም፤ ራሱን "ልባምና ታማኝ ባሪያ" ብሎ ስለለየመ ለአንድ የሃይማኖት ድርጅት የአመራር አካላት አይደለም።

በየሐዋ. 15 ላይ የምናነበው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ለብለባ የማንኛውንም የሃይማኖት ድርጅት የሚወክል አይደለም። እንደ ይሖዋ ምስክሮች ትምህርት የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ በአሜሪካን አገር የሚገኘውን የድርጅቱን የአመራር አካላት በፍጹም ሊወክል አይችልም። ምክንያቱም የኢየሩሳሌሙ ስብሰባ በበጉ (በኢየሱስ) ሐዋርያት ብቻ የተካሄደ ነበር። የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ በመካከላቸው ሐዋርያት እንደሌሉ በበርካታ ጽሑፎቻቸው ገልጸዋል። አሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት እስከሌሉ ድረስ የትኛውም ሃይማኖታዊ ስብሰባ ይህን የኢየሩሳሌሙን ስብሰባ ሊወክል ወይም በእርሱ ሊመሰል አይችልም።

"ቃለ እግዚአብሔርን ለመረዳት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት አስፈላጊ ነው" ስሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት የተጠቀሰው ከየሐዋ. 8፥30–31 ላይ ነው። ፊሊጶስ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ". . . በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" አለው። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም፡– ". . . የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" አለው። ፊሊጶስም ጃንደረባውን ያስተምረው ዘንድ ተቀመጠ። "ዮር ዊል ቢ ዳን ኦን ኧርዝ" ["ፈቃድህ በምድር ይሁን"] በሚል ርዕስ የታተመው የመጠበቂያ ድርጅት መጽሐፍ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡– "የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳትም ሆነ ፈቃዱን ለማወቅ የተቀናጁና ራሳቸውን ለእርሱ [ለእግዚአብሔር] የሰጡ ሰዎች ያስፈልጋሉ። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም የተገነዘበው ይህንኑ ነው"[21]።

በእርግጥ የይሖዋ ምስክሮች ቃለ እግዚአብሔርን የሚያነቡት በክፍሉ ውስጥ የሌለውን ነገር እየጨመሩ ነው የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት አነጋገር ትክክል ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲረዱ ሰዎች ሊመሯቸው እንደሚያስፈልግ ክፍሉ ማስተማሩ እሙን ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንኳን አንዳንድ የጳውሎስ መልእክቶች ለመረዳት አስቸጋሪ እንደሆኑ ተናግሮአል (2ጴጥ. 3፥18)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ስላሉ ነው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎችን የሰጠው (ኤፌ. 4፥11)።

---

21. <u>Your Will Be Done On Earth.</u> (1958) ገጽ. 362 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።



ክፍሉ የእግዚአብሔር እውነተኛ ተከታዮች ሁሉ ሊቀበሉት የሚገባ ሥልጣናዊ ቃል ስለሚያስተላልፍ ድርጅት አይናገርም። ፊሊጶስ ደግሞ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እየጠቀሰ አስተማረው እንጂ በድርጅት በተጻፉ ተጨማሪ ጽሑፎች ረዳትነት አልነበረም። ይህም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ተጠመቀ (የሐዋ. 8፥34–48)።

"ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፥ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና።" (የሐዋ. 8፥38) ይህ ክፍል ፊሊጶስና ጃንደረባው ዳግም እንዳልተገናኙ ነገር ግን ጃንደረባው በአዳኙ እየተደሰተ መንገዱን እንደቀጠለ ነው የሚናገረው እንጂ ራሱን ለአንድ ድርጅት እንዳስገዛ የድርጅቱንም ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስንም ለመረዳት ተጠቀመበት አይለንም።

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር መጽሐፍ ቅዱስ በግል ተጠንቶ መብራራት እንደሌለበት ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ማብራራት የድርጅቱ ሥራ ብቻ እንደሆነ ለሚያስተምረው ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ከሚጠቅሰው ጥቅስ መካከል አንዱ (2ጴጥ. 1፥20–21) ነው። ክፍሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዴት መተርጎም እንዳለብን ሳይሆን የሚያስተምረው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት እንደተጻፉ ነው። ቁ. 20–21 "ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጎም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ"። "ሊተረጉም" የሚለው ቃል ትንቢት የመጣው በነቢያቶቹ ፍላጎት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን የሚያሳይ ነው። "ተነድተው" የሚለው ቃል ከድሮ መርከብ አነዳድ የተወሰደ ሥዕላዊ አገላለጽ ነው። የጥንት መርከቦች ሞተር ስላልነበራቸው የሚሄዱት በነፋስ ኃይል ነበር። ነፋሱ በበረታ ጊዜ የመርከቧ ሾፌር መቆጣጠር ስለማይችል ነፋሱ ወደፈለገበት ቦታ ነድቶ መርከቡን ይወስዳል። ሉቃስ ይህን ቃል በሐዋርያት ሥራ ላይ ተጠቅሞበታል (የሐዋ. 27፥15, 17)። እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊያንን መርቶአቸዋል፥ የጽሑፋቸውም የበላይ ተቆጣጣሪ እርሱ ነበር።

ይህ የሚያሳየን 2ጴጥ. 1፥20–21 መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተገኘ ያስተምራል እንጂ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም አይደለም። ከመጠበቂያ ግንብ ጋር በተቃረነ መልኩ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ዓይነት ትምህርት፥ የግለሰቦችንም ሆነ

የሃይማኖት ድርጅቶችን መመርመር እንዳለባቸው አስተምሮአል (1ተሰ. 5፥21) የቤርያ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ዓይነት ትምህርት፥ የጳውሎስን ትምህርት እንኳ ጨምረው ይመረምሩ ነበር (የሐዋ. 17፥11)። እግዚአብሔር እምነታችንን እንድንመረምር ይፈልጋል።

የተለያዩ ትምህርቶችን የምንመረምረው ቃለ እግዚአብሔር ምን እንደሚል አጥንተንና ቲረድተን ነው። እግዚአብሔር ያለምንም ጥያቄ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፍን እንድንቀበል አይፈቅድም "በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ. . ." (2ቆሮ. 13፥5)።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ቀኖናዊና እንከን አልባ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል (ማቴ. 5፥17–18፤ ዮሐ. 10፥34–35)። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈው፤ አስተምህሮዎችና የእምነት አንቀጾች የሚመዘኑበት፥ የስበአዊያን ልምምዶችና አካሄዶች የሚገሩበት የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ነው (2ጢሞ. 3፥16፤ 2ጴጥ. 1፥20–21)። እንደዚሁም ማንኛውም ዓይነት ትምህርቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ሊመዘኑ ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም እንከን የሌለበት የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህም የሐዋርያትንም ሆነ (የሐዋ. 17፥11) የነቢያትን (2ጴጥ. 2፥1) ትምህርት ጨምሮ ማለት ነው። ጳውሎስ ለገላቲያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች አዲስ ወንጌልን መቀበል በፍጹም እንደሌለባቸው ይመክራል (ገላ. 1፥8)።

## የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን አስመልክቶ ጥይቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. ቅቡዓ አማኞች በድርጅት መልክ ተዋቅረው "ልባምና ታማኝ ባሪያ" የተባሉት በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሆነ፥ እነዚህም ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን ለመረዳት ብቸኛ መንገድ ከሆኑ ለአንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ዓመታት እግዚአብሔር በምድር ላይ እውነተኛ ወኪል የለውም ነበር ማለት ነው? በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ይረዱ ነበር?
2. እግዚአብሔር በነዚህ ዘመናት የነበሩ ሰዎች ቅዱስ ቃሉን እንዲረዱ አይፈልግም ነበር ማለት ነው?
3. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከመቆርቆሩ በፊት ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን እንዴት ይረዱ ነበር?



4. መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች አንገብጋቢ ከሆኑ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶ የመረጃውን መንገድ የከለከለው እግዚአብሔር ምን ዓይነት ነው?
5. ሰዎች በሃይማኖት ድርጅት ሥር መጠለል እንዳለባቸውና ለድርጅቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንተና መገዛት እንደሚገባቸው የሚያስተምረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የት ጋ ነው የሚገኘው? [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የሚጠቅሰው ጥቅስ የፊሊጶስንና የኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ታሪክ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ፊሊጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ዳግም እንዳልተገናኙ ይናገራል]።
6. ፊሊጶስ ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጋር የተወያየው በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነበር ወይስ ተጨማሪ መጻሕፍትንና መጽሔቶችን ተጠቅሞ ነበር?
7. ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባና ለፊሊጶስ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በቂ ከሆነ ለእኛስ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፥ ያለተጨማሪ ጽሑፎች በቂ መሆን አይችልም?
8. ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል"። (2ጢሞ. 3፥15) ይለዋል። ለጢሞቴዎስ መጽሐፍ ቅዱስን *ብቻ* ማወቁ ለደኅንነት በቂ ከሆነ ለእኛ በቂ የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?
9. የቤርያ ሰዎች የጳውሎስን ትምህርት የመፈተን መብት ነበራቸው (የሐዋ. 17፥11)። ጳውሎስ ራሱ ሁሉን ነገር መመርመር እንዳለብን ይናገራል (1ተሰ. 5፥21)። የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህንን ትዕዛዝ መከተል የለባቸውምን? እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘን እንዳለብን ካዘዘን፥ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ጽሑፎች ሁሉ በቃለ እግዚአብሔር ልንመዝናቸው ይገባል ማለት ነው። እርሶ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ለመመዘን ፈቃደኛ ነዎት?
10. በርካታ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ከአምላክ ቃል ጋር በቀጥታ የሚቃረኑ ከሆነ ምን ያደርጋሉ?
11. በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዘንድ የነበረው መለያየት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ክርስቲያን አይደሉም እንድንል ያደርገናልን? (1ቆሮ. 1፥2 ይመለከቷል)
12. 1ቆሮ. 1፥10 በሃይማኖት ድርጅቶች መካከል ስላለው መለያየት ይናገራልን?
13. 1ቆሮ. 1፥10 የክርስቲያኖች ኅብረት የሚታየው በአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለላቸው ነው ይላል?

14. "ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ፥ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው፥ የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል"። (ሮሜ 14፥2–5) በዚህ ክፍል መሠረት ክርስቲያኖች በአንዳንድ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ላይ የተለያየ አቋም መያዛቸው ተቀባይነት ያለው አይመስልዎትም?

## 3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም



ሐምሌ 26 ቀን 1931 ዓ.ም. በኮሎንበስ ኦሀዮ በተደገው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የአባላት ስብሰባ ላይ የድርጅቱ ሁስተኛ ፕሬዚዴንት፥ ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ ለድርጅቱ ተከታዮች "የይሖዋ ምስክሮች" የሚል ስያሜ አወጣ[1]። በዚህ አዲስ ስያሜ ብዙ የድርጅቱ አባላት ደስ ከመሰኘታቸውም በላይ አዲሱን ስያሜ ተቀብለውታል። ምክንያቱም አዲሱ ስያሜ የድርጅቱ ተከታዮች ቀድሞ ይጠሩባቸው የነበሩትን የተለያዩ ቅጽል ስሞች ስለሚያስቀር ነው። እነዚህ ቅጽል ስሞች፥ " 'ራስላውያን፥ ሮዘርፎርድውያን'፥ 'የመጠበቂያ ግንብ ስሞች'፥ 'የሺ ዓመት ንጋቶች' "[2] የሚባሉት ነበሩ።

ይህ ለድርጅቱ ተከታዮች መጠሪያ እንዲሆን የተሰጠው አዲስ ስም የተወሰደው ከኢሳይያስ 43፥10–12 ሲሆን፤ እንደ ድርጅቱም እምነት የአምላክ ብቸኛ መጠሪያ ስም ጆሆቫ ነው[3]። ይህንንም ስም የግድ ልንጠቀምበት ያስፈልገናል ባዮች ናቸው[4]።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ይህን የተቀደሰ የአምላክ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያስወገዱት የዕብራውያን ጣኦት አምላኪ ጸሐፍት ናቸው። ነገር ግን ልንጨነቅ አይገባንም! ምክንያቱም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት "የአዲሲቱ ዓለም የቅዱሳን ጽሑፎች ትርጉም" ["አው ወርልድ ትራንስሌሽን ኦፍ ዘ ሆሊ ስክሪብቸርስ"] በሚል ስያሜ ያሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክን ስም "በታማኝነት" በማደስ YHWH [YHWH - ቴትራግራማቶን በመባል ይታወቃል] በመባል

1. The 1975 Year book of Jehovah's Witnesses, ገጽ. 149
2. The Watchtower, Feb. 15,1962. ገጽ. 119
3. Make sure of All Things Hold Fast to What Is Fine. ገጽ. 264
4. ዝኒ ከማሁ



የሚታወቀው የእግዚአብሔር ስም በሚገኝበት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ሁሉ ላይ ጆሆቫ የሚለውን ቃል መልሶአል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ጆሆቫ የሚለው የአምላክ ስም ድርጅቱ ባሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ሁሉ ላይ ይገኛል። የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] የተርጓሚዎች ኮሚቴ የአብን ስም ያሳያሉ በሚባሉ ቦታዎች ሁሉ ላይ ስሙን አስገብቶአል።

በየቤታችን በር ላይም ሆነ በየመንገድ ዳር የምናገኛቸው የይሖዋ ምስክሮች ጆሆቫ የሚለውን የአምላክ ስም መጠቀም እጅግ አንገብጋቢ፥ እንደያውም የሞትና የሕይወት ጉዳይ እንደሆነ ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] ሮሜ 10፥33 "የጆሆቫን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና" እና ሕዝቅኤል 39፥6 "እኔም ጆሆቫ እንደሆንኩ ሕዝቦች ማወቅ አለባቸው" የሚለውን በመጥቀስ ይሞግቱናል።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች የሥነ–መለኮት አቋም ኢየሱስ ክርስቶስ ጆሆቫ ሳይሆን ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው። ይህን ትምህርት አስመልክቶ ከድርጅቱ የሚወጡ ጽሑፎች እንዲህ ይላሉ፡– "ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማይን ከመተው በፊትና ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ ሚካኤል የሚለው ስም የኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አለ"[5]። "ሚካኤል ታላቅ መልአክ ነው፤ ይህም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ አይደለም"[6]። እንደ መጠበቂያግንብ አስተምህሮ ኢየሱስ ኃያል አምላክ ነው። ነገር ግን እንደ ጆሆቫ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም[7]።

አብ ብቻ ጆሆቫ ስለመሆኑ የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቅሱት ጥቅስ ሉቃ. 4፥8 ነው። ክፍሉ በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] እንዲህ ይነበባል "ልታመልኩት የሚገባችሁ አምላካችሁ ጆሆቫ ነው፤ ለእርሱም ብቻ ነው የተቀደሰ አገልግሎት መስጠት የሚገባችሁ"። ይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ጆሆቫ ከሆነ ኢየሱስ ጆሆቫ አይደለም ማለት ነው ይሉናል።

የይሖዋ ምስክሮች ጆሆቫ ስለሚለው የአምላክ ስም ያላቸውን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ ከሚጠቅሱአቸው ጥቅሶች መካከል፡– ዘጸ. 3፥15 እና ማቴ. 6፥9 ዋንኞቹ ናቸው። ጥቅሶቹን አስመልክቶ ከድርጅቱ የሚወጡ የድርጅቱ አንድምታዎች

5. The Watchtower, 15, May 1969, ገጽ. 307
6. The watchtower, 15, December 1984, ገጽ.29
7. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ. 150

እንዲህ ይላሉ፡— ዘጸ. 3፥15 — ጆሆቫ የሚለው ስም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ስም ነው። ሙሴ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በጠየቀው ጊዜ እግዚአብሔር የመለሰለት፡— “ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው፤ ጆሆቫ እግዚአብሔር የአባታችሁ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅ አምላክ እና የያዕቆብ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ፤ ይህም ከትውልድ ትውልድ የመታሰቢያ ስሜ ነው” [የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም NWT]።

እምላክ ለዘላለም ሊጠራበት የሚገባው ስም ጆሆቫ ነው። “በሃያኛው ክፍለ ዘመን ላለው ትውልድም ሆነ ለኛ ከ1914 ጀምሮ ላለው ትውልድ የዘላለሙ አምላክ መጠሪያ ስም ጆሆቫ ነው። ይህ ለዘላለም ለእርሱ መታሰቢያ መጠሪያ ስም ነው። ለዘላለምም እኛ እርሱን የምናስበው በዚህ ስም ነው። ይህ የእርሱ የማይለወጥ ስም ነው። ከሰው ፍጥረት ጀምሮ እስከ ሙሴ ዘመን ይህ [ስም] አልተለወጠም ከሙሴ ጀምሮ 1914 እንዲሁም እስከ አሁን ይህ ስም [ጆሆቫ] አልተለወጠም። በእነዚህ ሺ ዓመታት ውስጥ ያልተለወጠውን ስም በአግባቡ መጠቀም ይገባናል”[8]።

በማቴ. 6፥9 የተባለነው “ስለዚህ በዚህ መልኩ ልትጸልዩ ይገባችኋል፡— በሰማይ የምትኖር አባታችን፥ ስምህ ይቀደስ” [NWT]። እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ የእግዚአብሔር ስም የሚቀደስበት ብቸኛው መንገድ አምላክን በእውነተኛ ስሙ[ጆሆቫ] ስንጠራው ነው[9]። ጸሎታችን በእርግጥ እንዲሰማልን ከፈለግን እግዚአብሔርን በዚህ ስም እየጠራ ነው ልንጸልይ ይገባል። እግዚአብሔርን በሌላ ስም መጥራት አምላክን ያስማክበር ነው[10]።

እንደ መጠበቂያ ግንብ ማኅበር አስተምህሮ የተቀደሰውን የአምላክ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያስወገዱት ጣኦት ያመልኩ የነበሩት ዕብራውያን ጸሐፍት ናቸው። እንደዚሁም በዚህ ዘመን ያሉ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ጆሆቫ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም በመተው ስውን እያሳሳቱ ናቸው። በ1961 ዓ.ም. የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ከማቴ. 6፥9 በመዋስ “ስምህ ይቀደስ” [“ሊት ዮር ኔም ቢ ሳንቲፋይድ”] በሚሰው ርዕስ ያሳተመው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡—

---

8. “Let your Name Be Sanetified” ገጽ. 88። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
9. Let Gad Be True ገጽ. 28
10. Let Your Name Be Sanctified



“መጽሐፍን [መጽሐፍ ቅዱስን] በተለያዩ ቋንቋዎችና የአነጋገር ዘዬዎች የመተርጎሙ ሂደት ቀጥሎአል። ይህ መጽሐፍ ለብዙ ሰዎች መዳረሱ የዘላለም ሕይወታቸውን በአደጋ ላይ ይጥለዋል። ምክንያቱም ከነዚህ ትርጉሞች የፈጣሪያችንን ስም መማር ስለማንችል ነው። ከስሙ ይልቅ ሌላ ቃል ወይም ስም ነው የሚጠቀሙት። በነዚህ ትርጉሞች ስሙ [የአምላክ ስም] አልተከበረም ወይም አልተቀደሰም፤ ከአንባቢዎቹ ለደኅንነታቸው የሚሆናቸውን ስም እንዳያውቁት ተደብቆባቸዋል”[11]።

ለደኅንነት ይጠቅማል የተባለው “ስም” እንዴት ሊታወቅ እንደቻለ ይኸው የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ እንዲህ በማለት ያብራራል፡— “በልባችን የራሳችን የሆነ ዘላለማዊ ፍላጎት ካለን፥ ራሳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተዋወቅ የምንጓጓ ከሆነ፥ ብዙ የክርስቲያን ድርጅቶች በተሳሳተ መልኩ እንዳቀረቡት ሳይሆን እርሱን እንደ እርሱነቱ ለማወቅ የስሙን መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና በማጥናት ወደ ትክክለኛው መረዳት መድረስ እንችላለን፤ እንዲሁም ራሳችንን ከተፈተነው ከእርሱ የሚታይ ድርጅት፥ ‘ለእርሱ ስም በሆኑ ሰዎች’፥ ቅሬታ ከሆኑ ቅቡዓ ምስክሮች፥ ልባምና ታማኝ ባሪያዎች ጋር ፍጹም መተባበር ነው”[12]።

በአጠቃላይ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚያምኑት እኛ ብቻ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ስም በትክክል ስለምንጠራ የአምላክ እውነተኛ ተከታዮች እኛ ነን። በእኛ የሃይማኖታዊ ድርጅት ጥላ ሥር ያልተጠለለ ሁሉ የሰይጣን እንደራሴ ነው ባዮች ናቸው።



## የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም
## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



ሃያ ሰባቱም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነው። የመጀመሪያ ቅጂ ጸሐፊያን ጌታ፥ አምላክ ወይም እግዚአብሔር ለሚሉት ስሞች የተጠቀሙበት ቃል፡— ጌታ [በግሪክ፡— “ኩሪዮስ”]፥ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [በግሪክ፡— ቴዎስ] የሚለውን ስም ነው። እነዚህ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊያን ጆሆቫ ወይም ያህዌ የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል አንድም ጊዜ በጽሑፎቻቸው

---

11. ዝኒ ከማሁ ገጽ 12። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
12. ዝኒ ከማሁ ገጽ 374–375

አልተጠቀሙም። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊያን ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን ጠቅሰው ጽፈዋል። ነገር ግን ይህን ስም ቴዎስ [አምላክ] ወይም ኩሪዮስ [ጌታ] በሚሉት የግሪክ ቃላት ነበር የተኩት።

የጥንት ዕብራውያን ያህዌ [YHWH] የሚለውን የእግዚአብሔር ስም መጥራት ስለሚፈሩ በዚህ ስም ፈንታ አዶናይ [Adonai] የሚለውን የአምላክ ስም ይጠቀሙ ነበር። ይህን የአምላክ ስም መጥራት እንዲፈሩ ያደረጋቸው የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን፥ ከአሥርቱ ትዕዛዛት ሦስተኛውን ሕግ እንዳያፈርሱ በመጠንቀቅ ያህዌ [YHWH] ከሚለው ስም ይልቅ አዶናይ [Adonai] የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ይጠቀሙ ነበር።

የጥንት ዕብራውያን ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን [Consonants] ብቻ በመጻፍ በሚያነቡበት ጊዜ ብቻ ድምፅ ሰጪ ፊደላትን [Vowels] እያስገቡ ጽሑፋቸውን ያነቡ ነበር። በኋላ የዕብራይስጥ ቋንቋ እያደገ ስለመጣ ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን [Consonants] ከድምፅ ሰጪ ፊደላት [Vowels] ጋር አብሮ መጻፍ ተጀመረ። ነገር ግን ዕብራውያን ያህዌ [YHWH] የሚለውን ስም እግዚአብሔርን ከመፍራትና ስሙን ከማክበር የተነሣ ስለማይጠሩት ቋንቋው ሲያድግ የቀድሞው ትክክለኛ አነባበብ [Pronunciation] አዲሱ ትውልድ ሳያውቀው ቀረ። ይህን ችግር ለመቅረፍ ዕብራውያን አጀናይ በሚለው ስም ላይ የሚገኙትን ድምፅ ሰጪ ፊደላት ማስተም፡– “ ‘A’፥ ‘O’፥ ‘A’ ”ን YHWH በሚለው ድምፅ ተቀባይ ፊደላት ውስጥ በመጨመር Yahowah ተብሎ እንዲነበብ አደረጉ [YHWH የሚለውን ቃል ምንም ብስን ማንበብ አንችልም። ምክንያቱም ድምፅ ተቀባይ ብቻ ስለሆነ። ስማንበብ የግድ ድምፅ ሰጪ ፊደል ያስፈልጋል]። ስዚህም ነው ያህዌ የሚለው ስም ሰው ሠራሽ ስም ነው የሚባለው። ይህን እውነት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ይቀበለዋል[13]። በአጠቃላይ ያህዌ የሚለው ስም ቴትራግራማቶን [YHWH] ሊነበብበት ከሚችለው ከብዙ አማራጮች አንደኛው ነው። ነገር ግን ጆሆቫ የሚለው አነባበብ ሊሆን ከሚችሉ የተለያዩ የአነባበብ አማራጮች እጅግ የራቀ ነው። ስዚህም ነው የተለያዩ መድበለ ዕውቀቶች [Encyclopedias] ጆሆቫ የሚለው አጠራር እጅግ የተሳሳተ ነው የሚሉት። አንዳንዶቹን ለአብነት ያህል ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል[14]፡–

13. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፤ ገጽ 195

14.. Personal Freedom Outreach – Why the Name Jehovah's Witnesses? በሚል ስያሜ ካሳተመው ትራክት ላይ የተወሰደ ነው



- ጆሆቫ፡– “ስብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስም ትክክል ያልሆነ ቅምር ነው”[15]
- ጆሆቫ፡– “ስእስራኤል አምላክ የተሳሳተ ስም”[16]
- ጆሆቫ፡– “ስእግዚአብሔር መጠሪያ YHWH ስሚለው የዕብራይስጥ ስም የተሳሳተ አነባበብ ነው። በስዋሰው ሕግ ይህ ንበት ፍጹም የማያስኬድ ነው”[17]
- ጆሆቫ፡– “ባዕድ ከሆነ ድምፅ ሰጪ ፊደላት ተዋቅሮ ጆሆቫ በመባል በስህተት የተነበበ”[18]
- ጆሆቫ፡– “ሰው ሠራሽ”[19]
- ጆሆቫ፡– “ለእስራኤል የቃል ኪዳን አምላክ የተሳሳተ መለኮታዊ ስም”[20]
- ጆሆቫ፡– “ያህዌ ስሚለው መለኮታዊ ስም የተሳሳተ መጠሪያ”[21]
- ጆሆቫ፡– “የቴትራግራማቶን የተሳሳተ ንበት”[22]

ጆሆቫ የሚለው ቃል በኪንግ ጀምስ ትርጉም ላይ በአራት ቦታዎች ላይ ተጠቅሶአል (ዘጸ. 6፥3፤ መዝ. 83፥18፤ ኢሳ. 12፥2፤ 26፥4)። እንዲሁም በኒው ኢንግሊሽ ባይብል ሁለት ጊዜ፥ (ዘጸ. 3፥15፤ 6፥3)። የተርጓሚዎቹ ኮሚቴ ቃሉን የተጠቀመበት YHWH የሚለውን የቃል ንበት ማንም በትክክል ስለማያውቀው ነገር ግን በሰፊት እየተሠራበት ያለው ቃል ጆሆቫ ስለሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች የአምላክን ስም በትክክል የምናውቅ እኛ ብቻ ነን ሊሉ በፍጹም አይገባቸውም። ይህን የአምላክ ስም ማንም አያውቀውም።

ዘጸ. 3፥15 እግዚአብሔር በጣም ብዙ ስሞች እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ጆሆቫ ከሚለውም ስም ሌላ እግዚአብሔር በሌላ ስም ተጠርቶአል። ስምሳሌ በዚሁ ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር “የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅ አምላክ፥ የያዕቆብ አምላክ” ተብሎአል። ይህም ስም

15. Merits Student Encyclopedia (Volume 10, 1973 Edition)
16. Encyclopedia Americana (Volume 16, 1976 Edition)
17. The Jewish Encyclopedia (Volume 7, 1964 Edition)
18. Encyclopedia International (Volume 9, 1974 Edition)
19. The Interpreters Dictionary of the bible (Volume 2,1969 Edition)
20. The New schaff – Herog Encyclopedia (Volume 6, 1910 Edition)
21. The New Catholic Encyclopedia (Volume 7, 1967 Edition)
22. The Universal Jewish Encyclopedia (Volume 6, 1948 Edition)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ ተጠቅሶአል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ያህዌ በሚለው ስም ቢጠራም በዚህ ስም ብቻ አይደለም የሚታወቀው። ስለዚህ ዘጸ. 3፥15ን በመጥቀስ እግዚአብሔር የሚጠራበት ብቸኛ ስም ያህዌ ነው ማለት በፍጹም አንችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን ያህዌ ብሎ ጠርቶት አያውቅም። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር አብ ይሖዋ በሚለው ስም ብቻ መጠራት ካለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ይህንን ስም ባለመጥራት ከመስመር ውጪ ነው ማለት ነው [የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም (NWT) ተርጓሚዎች 237 ጊዜ ያህል ጆሆቫ የሚለውን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጨምረዋል]። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያት በጽሑፎቻቸው ውስጥ አንድም ጊዜ ጆሆቫ የሚለውን ቃል አልተጠቀሙም። ድርጅቱ ለአምላክ ስም ተቆርቋሪ ነኝ በሚል ሽፋን ያለምንም መሠረት ይህንን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ 237 ጊዜ መጨመሩ የድርጅቱ አባላት የአዲሲቱ ዓለም ትርጉምን አንብበው የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንዳያውቁ አድርጓቸዋል። በኋላ ይህንን ጉዳይ በስፋት እንመለከተዋለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጸሎት ሲያስተምር "ጆሆቫ አምላክ ሆይ በሰማይ የምትኖር" ብሎ አልጀመረም። ነገር ግን አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ብሎ ነው ያስተማረው (ማቴ. 6፥9)። ኢየሱስ ክርስቶስ በሌላም ጊዜ ጸሎቱን በዚህ ሁኔታ ነው ያቀረበው (ማቴ. 11፥25፤ 26፥39–42፤ ማር. 14፥36፤ ሉቃ. 10፥21፤ 22፥42፤ 23፥34)። ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን እርሱ በጸለየበት መልኩ "አባታችን ሆይ" ብለው እንዲጸልዩ ነው ያስተማራቸው። በእርግጥ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ እግዚአብሔርንም፦ "አባ አባት" ብለን ልንጠራው እንችላለን! ሮሜ 8፥15፤ ገላ. 4፥8። እግዚአብሔርን አባ አባት ብለን መጥራት የምንችል ከሆነ ዘጸ. 3፥15ን በመጥቀስ እግዚአብሔር ሊጠራበት የሚገባው ስም ያህዌ ብቻ ነው ልንል አንችልም።

እንደ አዲስ ኪዳን የግሪክ መጻሕፍት ያህዌ የሚለው ስም አንድም ጊዜ በአዲስ ኪዳን 27ቱም መጻሕፍት ውስጥ አይገኝም። ያህዌ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር መጠሪያ ለትውልድ ሁሉ ብቸኛ ስም ከሆነ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ መጠቀስ ነበረበት።

ዘጸ. 3፥15 የሚለው ምንድን ነው? ያህዌ የሚለው ስም ከዕብራይስጡ ረዳት ግሥ [Verb "to be"] ጋር የተያያዘ ነው። ይህን ስም በመጀመሪያ የሚገኘው በዘጸ. 3 ላይ ሙሴ እግዚአብሔር በምን ስም እንደሚጠራ በጠየቀበት ጊዜ ነው። እግዚአብሔርም "ያለና የሚኖር 'እኔ ነኝ' [I



**AM WHO I AM" "እኔ [I AM] ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ" (ቁ. 14) አለው። "እኔ" ["I AM" ] የሚለው ቃል ያህዌ የሚለው ቃል አይደለም። ነገር ግን "እኔ" (ቁ. 14) እና "ያህዌ" (ቁ. 15) የሚሉት ቃላት ውልደተ-ቃላቸው ከአንድ ዓይነት ግሥ [Verb "to be"] ነው። በቁጥር 14 ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ የገለጸለት "እኔ እኔ ነኝ [*I AM WHO I AM*]" የሚለው ስም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ባሕርይ የሚያሳይ ነው። ይህ ቃል ነው በቁጥር 15 ላይ ያህዌ የተባለው። የሁለቱም ቃላት ውልደተ-ቃል አንድ ነው በተለዋዋጭነትም አገልግለዋል።**

በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ባሕሪን፥ ሥራንና ተፈጥሮን ያሳያል። የአንድ ሰው ወይም ነገርን ስም ማወቅ ባሕሪውን፥ ሥራውንና ተፈጥሮውን ማወቅ ነው። ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ስምና ባሕሪይ በተለዋዋጭነት ተጽፎ የምናገኘው። ለምሳሌ ያህል መዝሙር ዳዊትን ብንወስድ ይህን እውነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፦ "አቤቱ፥ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ *አመሰግንሃለሁ፥ ለስምህም እዘምራለሁ*" (መዝ. 18፥49)። "*ለእግዚአብሔር ተቀኙ ለስሙም ዘምሩ፤ ወደ ምድረ በዳ ስወጣም መንገድ አድርጉ፤ ስሙ እግዚአብሔር ነው*" (መዝ. 68፥4)። "ይህን ፍጥረትህን አስብ ጠላት *እግዚአብሔርን ተሳደበ፥ ሰነፍ ሕዝብም ስሙን አስቆጣ*" (መዝ. 74፥18)። "አቤቱ *አምላኬ ሆይ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥ ለዘላለምም ስምህን* አከብራለሁ" (መዝ. 66፥12)። ከመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የምናየው ነገር እግዚአብሔርና ስሙ እንደማይነጣጠሉ ነው። አንዱን ማወቅ ሌላውን ማወቅ ነው።

የሥነ- መለኮት ሊቃውንት እንደሚያስገነዝቡት ያህዌ የሚለው የእግዚአብሔር ስም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነትና ሉዓላዊነት ያሳያል። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሙሴ፦ "ይህ ለዘላለሙ ስሜ ነው፥ እስከ ልጅ ልጅ ድረስም መታሰቢያዬ ይህ ነው" (ዘጸ. 3፥15) ሲለው ለሙሴ የነገረው ለሙን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ማንነቱን ለትውልድ ሁሉ ነው ያስታወቀው። በዚህ ስም ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ማንነት ዘላለማዊነቱና ሉዓላዊነቱ ነው። ከዚህም የተነሣ ትውልድ ሁሉ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነትና ሉዓላዊነት በማወቅ እንደ ማንነቱ ያከብረዋል።

ስለዚህ ዘጸ. 3፥15 ትኩረት የሚሰጠው ውጫዊ በሆነው በእግዚአብሔር ስም ላይ ሳይሆን ከስሙ በስተጀርባ ያለው፥ ትውልድ ሁሉ ሊያውቀው፥ ክብር ሊሰጠው በሚያስፈልገው የእግዚአብሔር ባሕሪይ ላይ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ትውልድ ሁሉ እንዲያውቀው የሚፈልገው ዘላለማዊ የሆነውን ባሕሪውን ነው። ይኸውም ሉዓላዊነቱንና ዘላለማዊነቱን።

እስከ አሁን ከቃለ እግዚአብሔር የተማርነውን ጠቅለል ስናደርገው፦ *አንደኛ፥* እግዚአብሔር አምላክ ያህዌ የሚባል ስም አለው። *ሁለተኛ፥*

ይሆን የእግዚአብሔር ስም ትክክለኛ አነባበብ ማንም ሰው አያውቀውም። ምስተኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያህዌ በሚለው ስም ጠርቶት አያውቅም። ኢየሱስ እግዚአብሔርን የጠራው አባ፥ አባቴ ብሎ ነው። ራተኛ፥ አማኞች እግዚአብሔርን "አባታችን" ብለው የመጥራት መብት ተሰጥቶአቸዋል። ሳምስተኛ፥ ያህዌ የሚል ስም በአንድም የአዲስ ኪዳን የግሪክ ቅጂዎች ውስጥ አይገኝም። ሰድስተኛ፥ ዘጸ. 3፥15 ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው በእግዚአብሔር ስም ላይ ሳይሆን ትውልድ ሁሉ ሊያውቀው በሚገባው ከስሙ በስተጀርባ ባለው የእግዚአብሔር ባሕርይ፥ ሉዓላዊነቱና ዘላለማዊነቱ ላይ ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ጆሆቫ የሚለውን ስም ከብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ ቅጂዎች ላይ ያስወገዱት ጣኦት አምላኪ የነበሩ ዕብራውያን ጸሐፍት ናቸው የሚሰው አነጋገራቸው ፍጹም ሐስት ነው። እነዚህ ጸሐፊዎች ብሉይ ኪዳንን ሲገለብጡ የማይፈልጉትን ትምህርት እንደዚህ የሚቀንሱ ከሆነ ዛሬ በእጃችን ያሉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ አይወድቅም?

በመናፍቃን ትምህርት ላይ ብዙ ጥናት ያደረጉ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ይሖዋ (ጆሆቫ) የሚለውን ቃል በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] ውስጥ 237 ጊዜ ያህል ማስገባቱ ይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስን ከአብ አሳንሰው እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል ለምሳሌ እነዚህን ጥቅሶች ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ይመልከቱ (የሐዋ. 2፥1፤ ሮሜ 10፥13፤ ማቴ. 11፥27፤ ዮሐ. 20፥28። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ዐውዳቸውን ይመልከቱ)።

ፊሊ. 2፥9-11 ከስም ሁሉ በላይ ስም የተሰጠው ለዚህም ስም "በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው"። ይህ ጥቅስ ከብሉይ ኪዳን ስለእግዚአብሔር ተሰጥቶ ከነበረው ጥቅስ ጳውሎስ በቀጥታ የወሰደው ነው ኢሳ. 45፥23 "ቃል ከአፌ በጽድቅ ወጥቶአል፥ አትመለስም፦ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ"። እውነቱ ይህ ከሆነ ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚያስተምረን ስለእግዚአብሔር እውነት የሆነው ሁሉ ስክርስቶስም እውነት መሆኑን ነው።

የአዲስ ኪዳን አማኞች የአብ ምስክር እንዲሆኑ ሳይሆን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር እንዲሆኑ ነው የተጠሩት። የሐዋ. 1፥8 "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ"።



ማቴ. 6፥9 አምላክን በእውነተኛው ስሙ ጆሆቫ [ይሖዋ] ብለን ስንጠራው ነው ስሙ የሚቀደሰው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የለውም። ከላይ ስም ባሕርይንና ማንነትን እንደሚያሳይ ተመልክተናል። የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ ወይም ማክበር ማለት በዚያ ስም የሚጠራውን እግዚአብሔር ማክበር ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ የተቀደሰ ነው። ስምህ ይቀደስ ብሎ መጸለይ እግዚአብሔር በሕዝቡ ዘንድ መከበር እንደሚገባው እንዲከበር መሻታችንን መግለጻችን ነው (ዘጸ. 20፥8፤ ዘሌ. 19፥2፥ 32፤ ሕዝ. 36፥23፤ 1ጴጥ. 1፥15)። እግዚአብሔር የሚከበረው ጆሆቫ! ጆሆቫ! ወይም ይሖዋ! ይሖዋ! እያልን አሥሬ ስለጠራነው አይደለም። ስሙን አሥሬ ጠርተን በምግባራችንና በባሕርያችን ላናስከብረው እንችላለን።

## ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎአል



የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ በሚባለው ስም አልተጠራም ባዮች ናቸው። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ በሚለው አምላካዊ ስም ተጠርቶአል።

ያህዌ የሚለው ስም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እንደማይገኝ፥ ይህ ስም ቴዎስ (እግዚአብሔር ወይም አምላክ) እንዲሁም ኩሪዮስ (ጌታ) በሚሉት የግሪክ ስሞች እንደተተካ ከላይ ተመልክተናል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ነው የሚለውን ትምህርት ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ከአዲስ ኪዳን ጋር በመቀናጀት ያስተምሩናል።

በብሉይ ኪዳን ስለ ያህዌ የተነገረው በአዲስ ኪዳን በቀጥታ ለክርስቶስ ተሰጥቶአል። ለምሳሌ፦ ኢሳ. 40፥3 "የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን [ያህዌ] መንገድ በምድረበዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም [ኤሎሒም] ጎዳና በበረሀ አስተካክሉ"። ወንጌላት የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት መጥበቁ ዮሐንስ ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ በማስተካከሉ እንደተፈጸመ ይናገራሉ (ማር. 1፥2-4፤ ማቴ. 3፥3)። በብሉይ ኪዳን መንገድ ጥረጉልኝ ያለው ያህዌ በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ሆኖ እናገኘዋለን።

ያህዌ መልእክተኛውን እንደሚልክ ፊት ፊቱም በመሄድ መንገዱን እንደሚያስተካክልለት በነቢያት ትንቢት ተናግሮ ነበር "እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል የምትወድዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" (ሚል. 3፥1) አዲስ ኪዳን በያህዌ ፊት ፊት በመሄድ መንገድ ያስተካከለው መጥመቁ ዮሐንስ እንደነበር ያስተምረናል "ደግሞ አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ

መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና" (ሉቃ. 1፥76)። "እነሆ፥ መንገድን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኞን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና" (ማቴ. 11፥10)። መንገድ ከተስተካከለስት በኋላ የመጣው ብሉይ ኪዳን ያህዌ ነው ሲለው አዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታ (በግሪኩ፦ ኩሪዮስ ይለዋል) ነው። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ።

በብሉይ ኪዳን የይህዌ ድምፅ "እንደ ብዙ ውኖች ይተምም ነበር" (ሕዝ. 43፥2) ይለናል። በአዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ተመሳሳይ ነገር እናነባለን፦ "ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበር" (ራእ. 1፥15)። በብሉይ ኪዳን ስያህዌ እውነት የሆነው ሁሉ ስኢየሱስም እውነት መሆኑ ምን ያስተምረናል? ዴቪድ ዌልስ "የክርስቶስ ማንነት" በተባለው መጽሐፍ ከዚህ የበለጠ ትይዮዎችን በክርስቶስና በያህዌ መካከል መኖሩን ያሳያል፦ "ያህዌ" ቀዳሻችን (ዘጸ. 31፥13)፥ በሁሉ ቦታ የሚገኝ (መዝ. 139፥7–10)፥ ሰላማችን (መሳ. 6፥24)፥ ጽድቃችን (ኤር. 23፥6)፥ ድላችን (ዘጸ. 17፥6–16)፥ ፈውሳችን (ዘጸ. 15፥26) እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም እንደዚያው ነው (1ቆሮ. 1፥30፤ ቆላ. 1፥27፤ ኤፌ. 2፥14)። ወንጌል የእግዚአብሔር እንደሆነ (1ተሰ. 2፥2፤ 6–9፤ ገላ. 3፥6) ሁሉ፤ የክርስቶስም ነው (1ተሰ. 3፥2፤ ተሳ. 1፥7)። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር እንደሆነች ሁሉ (ገላ. 1፥13፤ 1ቆሮ. 15፥9) ያችው ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ነች (ሮሜ 16፥16)። የእግዚአብሔር መንግሥት (1ተሰ. 2፥12) የክርስቶስ መንግሥት ነው (ኤፌ. 5፥5)። የእግዚአብሔር ፍቅር (ኤፌ. 1፥3–5)፥ የክርስቶስ ፍቅር ነው (ሮሜ 8፥35)። የእግዚአብሔር ቃል (ቆላ. 1፥25፤ 1ተሰ. 2፥13)፥ የክርስቶስ ቃል ነው (1ተሰ. 1፥8፤ 4፥15)። የእግዚአብሔር መንፈስ (1ተሰ. 4፥6)፥ የክርስቶስም ነው (ፊል. 1፥19)። የእግዚአብሔር ሰላም (ገላ. 5፥22፤ ፊል. 4፥9)፥ የክርስቶስም ነው (ቆላ. 13፥15፤ ፊል. 1፥2፤ 4፥7)። የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን (ኢሳ. 13፥6) የክርስቶስም ነው (ፊል. 1፥6፤ 10፤ 2፥16፤ 1ቆሮ. 1፥8)። የእግዚአብሔር ጸጋ (ኤፌ. 2፥6–9፤ ቆላ. 1፥6፤ ገላ. 1፥15)፥ የክርስቶስ ጸጋ ነው (1ተሰ. 5፥26፤ ገላ. 1፥6፤ 6፥16)።

የእግዚአብሔር ማዳን (ቆላ. 1፥13) የክርስቶስም ማዳን ነው (1ተሰ. 1፥10)። የእግዚአብሔር ፈቃድ (ኤፌ. 1፥11፤ 1ተሰ. 4፥3፤ ገላ. 1፥4) የክርስቶስ ፈቃድ ነው (ኤፌ. 5፥17፤ 1ተሰ. 5፥16)። ስለዚህም ነበር ጳውሎስ የእግዚአብሔር ባሪያ (ሮሜ 1፥19) እንደሆነ ሁሉ የክርስቶስም ባሪያ ነኝ (ሮሜ 1፥1፤ ገላ. 1፥10) ይል የነበረው። ኑሮውም ስእግዚአብሔር ክብር እንደሆነ ሁሉ (ሮሜ 5፥2፤ ገላ. 1፥24)፥ ለክርስቶስም ክብር ነበር (2ቆሮ. 6፥19፥ 23፤ 4፥6)። እምነቱ በእግዚአብሔር ላይ እንደሆነ ሁሉ (1ተሰ. 1፥6–9፤ ሮሜ 4፥1–5)፥ በክርስቶስ ኢየሱስም ላይ ነበር (ገላ. 4፥6፤ 1ተሰ. 4፥5)፥ ክርስቶስንም አውቆታል (2ቆሮ. 4፥6)[23]።

23. David F. Wells, The Person of Christ (West chester, IL: Cross way Books, 1984), ገጽ. 64-65.



## እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ ክርስቶስ



| አምላካዊ ስምና አምላካዊ ባህሪይ | ለእግዚአብሔር አብ | ለኢየሱስ ክርስቶስ |
|---|---|---|
| ያህዌ (ጃሆቫ) ["I AM"] | ዘጸ. 3፥14፤ ዘዳ. 32፥39፤ ኢሳ. 43፥10 | ዮሐ. 8፥24፤ 8፥58፤ 18፥4–6 |
| እግዚአብሔር ወይም አምላክ | ዘፍ. 1፥1፤ ዘዳ. 6፥4፤ መዝ. 45፥6–7 | ኢሳ. 9፥6፤ 1ዮሐ. 5፥20–21፤ ዮሐ. 1፥1፤ 2ጴጥ. 1፥1፤ ዮሐ. 20፥28፤ የሐዋ. 18፥25–26፤ 20፥28 ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8 |
| አልፋና ዖሜጋ (መጀመሪያና መጨረሻ) | ኢሳ. 41፥4፤ 48፥12፤ ራእ. 1፥8 | ራእ. 1፥17–18፤ 2፥8፤ 22፥12–16 |
| ጌታ | ኢሳ. 45፥23 | ማቴ. 12፥8፤ የሐዋ. 7፥59–60፤ 10፥36፤ ሮሜ 10፥12፤ 1ቆሮ. 2፥8፤ 12፥3፤ ፊል. 2፥10–11 |
| አዳኝ | ኢሳ. 43፥3፤ 43፥11፤ 63፥8፤ ሉቃ. 1፥47፤ 1ጢሞ. 4፥10 | ማቴ. 1፥21፤ ዕብ. 5፥9፤ ሉቃ. 2፥11፤ ዮሐ. 1፥29፤ ዮሐ. 4፥42፤ ቲቶ 2፥18 |
| ንጉሥ | መዝ. 95፥3፤ ኢሳ. 43፥15፤ 1ጢሞ. 6፥14–16 | ራእ. 17፥14፤ 19፥16 |
| ፈራጅ | ዘፍ. 18፥25፤ መዝ. 50፥4,6፤ መዝ. 96፥13፤ ሮሜ 14፥10 | ዮሐ. 5፥22፤ 2ቆሮ. 5፥10፤ 2ጢሞ. 4፥1 |
| ብርሃን | 2ሳሙ. 22፥29፤ መዝ. 27፥1፤ ኢሳ. 42፥6 | ዮሐ. 1፥4, 9፤ 3፥19፤ 8፥12፤ 9፥5 |
| አለት | ዘዳ. 32፥3–4፤ 2ሳሙ. 22፥32፤ መዝ. 89፥26 | ሮሜ 9፥33፤ 1ቆሮ. 10፥3–4፤ 1ጴጥ. 2፥4–8 |
| ቤዛ አዳኝ | መዝ. 130፥7–8፤ ኢሳ. 48፥17፤ 54፥5፤ ኢሳ. 63፥9 | የሐዋ. 20፥28፤ ኤፌ. 1፥7፤ ዕብ. 9፥12 |
| ጽድቃችን | ኢሳ. 45፥25 | ኤር. 23፥6፤ ሮሜ 3፥21–22 |
| ባል | ኢሳ. 54፥5፤ ሆሴ. 2፥16 | ማቴ. 25፥1፤ ማር. 2፥18–19፤ 2ቆሮ. 11፥2፤ ኤፌ. 5፥25–32፤ ራእ. 21፥2, 9 |
| እረኛ | ዘፍ. 49፥24፤ መዝ. 23፥1፤ መዝ. 80፥1 | ዮሐ. 10፥11, 16፤ ዕብ. 13፥20፤ 1ጴጥ. 2፥25፤ 5፥4 |
| ፈጣሪ | ዘፍ. 1፥1፤ ኢዮ. 33፥4፤ መዝ. 96፥5–6፤ 102፥25–26፤ ኢሳ. 40፥28 | ዮሐ. 1፥2–3, 10፤ ቆላ. 1፥15–18፤ ዕብ. 1፥1–3, 10 |
| ሕይወት ሰጪ | ዘፍ. 2፥7፤ ዘዳ. 32፥39፤ 1ሳሙ. 2፥6፤ መዝ. 36፥9 | ዮሐ. 5፥21፤ 10፥28፤ 11፥25 |
| ኃጢአትን ይቅር ባይ | ዘጸ. 34፥6–7፤ ነህ. 9፥17፤ ዳን. 9፥9፤ ዮና. 4፥2 | ማር. 2፥1–12፤ የሐዋ. 26፥18፤ ቆላ. 2፥13፤ 3፥13 |
| ፈዋሽ እግዚአብሔር | ዘጸ. 15፥26 | የሐዋ. 9፥34 |
| በሁሉ ቦታ የሚገኝ | መዝ. 139፥7–12፤ ምሳ. 15፥3 | ማቴ. 18፥20፤ 28፥20፤ ኤፌ. 3፥17፤ 4፥16 |
| ሁሉን የሚያውቅ | 1ነገ. 8፥39፤ ኤር. 17፥9–10, 16 | ማቴ. 11፥20–28፤ ሉቃ. 5፥4–8፤ ዮሐ. 2፥26፤ 16፥30፤ 21፥17፤ የሐዋ. 1፥24 |
| ሁሉን ቻይ | ኢሳ. 40፥31፤ 45፥5–13 | ማቴ. 28፥18፤ ማር. 1፥29–34፤ ዮሐ. 10፥18፤ ይሁ. 24 |
| ዘላለማዊ | መዝ. 102፥25–27፤ ዕብ. 9፥6 | ኢሳ. 9፥6፤ ሚክ. 5፥2፤ ዮሐ. 8፥58 |
| የማይለወጥ | ኢሳ. 46፥9, 10፤ ሚል. 3፥6፤ ያዕ. 1፥17 | ዕብ. 13፥8 |
| የሚመለክ (ስግደትን የሚቀበል) | ማቴ. 4፥10፤ ዮሐ. 4፥24፤ ራእ. 5፥14፤ 7፥11፤ 11፥16 | ማቴ. 14፥33፤ 28፥9፤ ዮሐ. 9፥38፤ ፊል. 2፥10–11፤ ዕብ. 1፥6 |

## የአምላክን ስም አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. በዘ. 3፥15 እግዚአብሔር ያህዌ የሚለው ስም ሳይጨመርበት "የአባቶቻችሁ አምላክ የአብርሃም አምላክ፤ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ" ተብሎ ከተጠራ እግዚአብሔር ያህዌ በሚለው ስም ብቻ መጠራት ያለበት ለምንድን ነው?
2. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያህዌ በሚለው ስም ፈጽሞ ካልጠራው "አባት" ብሎ ግን መጥራቱ እግዚአብሔር ሊጠራበት የሚገባው ስም ያህዌ ብቻ ነው እንድንል ያደርገናል?
3. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሐፍ ቅዱስ ለህትመት የሔለበት መጽሐፍ ነው እያለ በአንጻሩ የዕብራውያን ጣኦት አምላኪ ጸሐፍት ጆሆቫ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አስወግደውታል ማለቱ የቃለ እግዚአብሔርን ተአማኒነት በጥያቄ ውስጥ አይጥለውምን?
4. አዲስ ኪዳን ከአብ ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከፍ እንደሚያደርግ አውቀዋልን? ከዚህ በታች የሚከተሉትን ሁሉ በማን ስም የሚከናወኑ ናቸው?
    - በማን ስም ነው መሰብሰብ ያለብን (ማቴ. 18፥20፤ 1ቆሮ. 5፥4)?
    - አጋንት የሚታዘዙት በማን ስም ነው (ሉቃ. 10፥17፤ የሐዋ. 16፥16)?
    - ንስሐና የኃጢአት ይቅርታ የሚሰበከው በማን ስም ነው (ሉቃ. 24፥47)?
    - የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት በማን ስም ነው ያመነው (ዮሐ. 1፥12፤ 3፥16፤ የሐዋ. 10፥43፤ 1ዮሐ. 3፥23፤ 5፥13)?
    - በማን ስም ብቻ ነው ደኅንነት የሚገኘው (የሐዋ. 4፥12)?
    - ጸሎታችንን መጸለይ ያለብን በማን ስም ነው (ዮሐ. 14፥13–14፤ 15፥16፤ 16፥23–24)?
    - መንፈስ ቅዱስ የተላከው በማን ስም ነው (ዮሐ. 14፥26)?



    - ጳውሎስ የማንን ስም ነው እንድንጠራ ያስተማረን (1ቆሮ. 1፥2)?
    - በማን ስም ሥልጣን ነበር ደቀ መዛሙርት በሽተኛን የፈወሱት፥ ሽባን የተረተሩት (የሐዋ. 3፥16፤ 4፥7–10, 30)?
    - የማን ስም ነው ከሁሉ በላይ የሆነው ስም (ኤፌ. 1፥21፤ ፊል. 2፥9–11)?
5. መልሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከሆነ፤ የይሖዋ ምስክሮች አዲስ ኪዳን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይልቅ የአብን ስም ይሆን ያህል ማወደሱን የሚያመለክቱ ጥቅሶች ማቅረብ ይችላሉን?
6. የይሖዋ ምስክሮች የይሖዋ ምስክር ነን እንደሚሉት ሁሉ ክሙሉ ልባቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ነን ማለት ይችላሉ (የሐዋ. 1፥6)?
7. እንደ የሐዋ. 1፥8 የማን ምስክሮች ነው መሆን ያለብን?
8. የይሖዋ ምስክሮች የእግዚአብሔር እውነተኛና ብቸኛ ምስክሮች ከሆኑ፤ ድርጅታቸው፥ የመጠበቂያ ግንብ የተፈጠረው በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሆነ [የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ] እግዚአብሔር ለአንድ ሺ ስምንት መቶ ዓመታት ያለ ምስክር ነበር ማለት ነው? እግዚአብሔር በነዚህ ዘመናት ውስጥ የነበሩ ሰዎች እርሱን እንዲያውቁት አይፈልግም ነበር ማለት ነው? ሰሰዎች አይገደውም?
9. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ *ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ*" (የሐዋ. 1፥8)። ከዚህ በኋላ አዲስ ኪዳንን ስንመረምር ደቀመዛሙርት የአብ ወይም የያህዌ ምስክር ሳይሆን የኢየሱስ ምስክር ነው የሆኑት። ምስክርነታቸውም መሠረት ያደረገው ኢየሱስ በአካል ከሙታን መነሣቱን ነበር። ይህም አስተምህሮ የወንጌል መሠረት ነው (1ቆሮ. 15፥1–4)። ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስ ትንሣኤ የደኅንነት መሠረት እንደሆነ አስተምሮአል (ሮሜ 10፥9–10)። ነገር ግን የይሖዋ ምስክሮች የኢየሱስ ክርስቶስን የአካል ትንሣኤ አይቀበሉም ["የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል]።

ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር እንጂ የይሖዋ ምስክር አልነበሩም። የሚከተሉትን የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ይመልከቱ፡—

- "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ስዚህም ነገር እኛ *ሁላችን ምስክሮች ነን*" (የሐዋ. 2፥32)
- "የሕይወትን ራስ ገደላችሁት እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥ ለዚህም ነገር እኛ *ምስክሮች ነን*" (የሐዋ. 3፥15)
- "ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል *ይመሰክሩ ነበር!* በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው" (የሐዋ. 4፥33)
- "እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው በሕዝብም ዘንድ *ምስክሮቹ ስሆኑት* ከእርሱ ጋር ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለወጡት ብዙ ቀን *ታያቸው*" (የሐዋ. 13፥30–31) በእነዚህ ጥቅሶች *መሠረት* የጥንት ክርስቲያኖች የይሖዋ ምስክሮች ነበሩ ወይስ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች?

## 3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ



የይሖዋ ምስክሮች በሥላሴ አስተምህሮ አያምኑም። የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በሚል ስያሜ የሚታወቀው ድርጅታቸው "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" በሚል ርዕስ ያስተመው ጽሑፍ እንዲህ በማለት ይጠይቃል "ሰዎች ስለ ሥላሴ በቅድሚያ የሚያውቁት ነገር ሳይኖር መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር ቢያነቡት ካነበቡት ነገር የሥላሴን ጽንሰ ሐሳብ ሊያገኙ ይችላሉን? በፍጹም አይችሉም"[1]። "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር " በሚለው መጽሐፋቸው ደግሞ "የሥላሴ ትምህርትም ሆነ ስለ አምላክ ያላቸው ፅንሰ ሐሳብ [የሥላሴ አማኞች] ከአረማውያን ምንጮች የተቀዳና መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ካለቀ ከአያሌ መቶ ዘመናት በኋላ የአሁኑን ቅርጽ እንዲይዝ የተደረገ ነው"[2] ይላል።
የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ ክርስቶስ የሥላሴን ትምህርት ፈጽሞ አላስተማረም ባይ ነው። "ሌት ጎድ ቢ ትሩ" [እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን] የሚለው የድርጅቱ መጽሐፍ እንዲህ ይላል "ይህ እንግዳ የሆነና የተወሳሰበ አደናጋሪ አስተምህሮ በክርስቶስ ኢየሱስ

1. በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993) ገጽ 2
2. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (Booklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1994 ገጽ 204–205 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።



*ምንም ትኩረት አልተሰጠውም፤ አላብራራውም፥ አላስተማረውም*"[3] ይኸው መጽሐፍ ስዚህ አጸመ የሚያቀርበው አመክንዮአዊ ማስረጃ ደግሞ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀን በቆየበት ጊዜ ዓለማትን የሚያስተዳድረው ማን ነበር። ይህ ነው መሠረታዊው ጥያቄ. . . ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ከሆነ ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ እግዚአብሔርም በመቃብር ውስጥ ሞቶ ነበር ማለት ነው። ዓለማትን በሙላት ለመቆጣጠር ለሰይጣን እንዴት ዓይነት አስደናቂ አጋጣሚ ነው! . . . ኢየሱስ ክርስቶስ የማይሞት እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ መሞት አይችልም ነበር"[4]።

ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በዘመናት ሁሉ የሥላሴን አስተምህሮ በሰዎች እንዲወገዝና ምክንያታዊ አቀራረብ ስማስያዝ ሲል የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሥላሴን መሠረተ እምነት ከምታምንበት መንገድ ውጪ አጣሞ እንዲህ ሲል ያቀርበዋል፦ "ይህ ሦስት እግዚአብሔሮች በአንድ እግዚአብሔር የሚለው አስተምህሮ. . . ከሰይጣን ጨለማዊ ምስጢሮች አንዱ፥ በጳጳሱ በኩል ቃሉንና የእግዚአብሔርን ዓላማ ያጨለመበት ነው" [5] [ልብ ይበሉ የክርስትና እምነት ስለ ሥላሴ ያለው አስተምህሮ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ በአንድ በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት [Godhead] ሦስት እኩል የሆኑ አካላት [Persons] አሉ የሚል እንጂ "ሦስት እግዚአብሔሮች በአንድ እግዚአብሔር" የሚል ትምህርት አይደለም]። ይህ ብቻ አይደለም ይኸው የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ፦ "ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢአመክንዮአዊ የሆነው የሥላሴ አስተምህሮ ሦስት አምላኮች በአንድ አካል [One Person]"[6] ይላል። [የሥላሴ አማኞች ግን የሚያምኑት "ሦስት እግዚአብሔሮች በአንድ እግዚአብሔር" የሚል ሳይሆን አንድ እግዚአብሔር አስ፤ በአንዱም በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት ሦስት እኩል የሆኑ አካላት አሉ የሚል ነው]።

"ሪኮንስሊዬሽን" የሚለው የድርጅቱ መጽሐፍ፦ "እንደ ሥላሴ የሚያታልልና የተስፋፋ አስተምህሮ የለም። ይህም አስተምህሮ የተጠነሰሰው በአንድ አእምሮ ነው፤ ይህውም በሰይጣን ዲያቢሎስ ነው"[7] ይላል።

3. "Let God Be True " (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1952) ገጽ. 200
4. ዝኒ ከማሁ ገጽ 109
5. Studies in the scriptures, Vol 5 (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1899), ገጽ. 60-61
6. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 76
7. Reconciliation (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1928), ገጽ. 101

"ሪችስ" የሚለው መጽሐፍ ደግሞ፡- "የእግዚአብሔርን ስም ለማጕደፍና ሰዎችን ከእግዚአብሔር ለማሸሽ በሰይጣን የተሠራውና የተነገረው ሌላው ውሸት 'ሥላሴ' ነው"[8] ይላል።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴ አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው ባይ ብቻ ሳይሆን የሥላሴ ትምህርት ጽንሰ ሐሳብ የተቀዳው ከአረማውያን መድበለ ኣማልክት ነው የሚልም አስተያየት አለው። በሥላሴ ማመን ተገቢ እንዳልሆነ ለማሳሰብ በዚሁ በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የወጣው ጽሑፍ፥ "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" "ዘ ፖጋኒዝም ኢንአወር ክርስቲያኒቲ" ["አረማዊነት በክርስትናችን ውስጥ"] የተሰኘውን መጽሐፍ በመጥቀስ "[የሥላሴ] እምነት የመጣው ሙሉ በሙሉ ከአረማውያን ነው"[9] ይላል።

በተጨማሪም ይኸው የድርጅቱ ጽሑፍ የሥላሴን አስተምህሮ እንዲህም እያለ ያጣጥለዋል "[የሥላሴ] እምነት የመነጨው ሙሉ በሙሉ ከአረማውያን ነው። . . . ለምሳሌ በሕንዳውያን ሃይማኖት ውስጥ ብራህማ፥ ሲቫ እና ሲስኑ የተባሉት የሦስት አማልክት ጥምረት፥ በግብፃውያን ሃይማኖት ደግሞ ኦሲሪስ፥ አይሲስ እና ሆረስ የተባሉ የሦስት አማልክት ጥምረት እናገኛለን. . . አምላክ ሥላሴ እንደሆነ የሚታመነው በታሪክ በታወቁ ሃይማኖቶች ብቻ አይደለም"[10] በአጠቃላይ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴን አስተምህሮ እንዲህ ሲል ይደመድመዋል፡- "እግዚአብሔር የዚህ አስተምህሮ ጠንሳሽ አይደለም"[11]

በአጠቃላይ "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት ስለ ሥላሴ ያለው አስተምህሮ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡- ይሖዋ አምላክ በአንድ አካል [Person] ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ሥላሴ አይደለም። በክርስትና የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ እንደ ሠፈረው በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት ውስጥ ሦስት እኩል የሆኑ አካላት የሉም።

8. Riches (Brooklyn: Watchtower bible and Tract Society, 1936), ገጽ. 185
9. በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ገጽ 3። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
10. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 11። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም
11. "Let God Be True" ገጽ. 101



ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም። ኢየሱስ በቅድመ-ሰብእናው ጊዜ በእግዚአብሔር በቀጥታ የተፈጠረ ብቸኛ ፍጡር ነው - ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎችን ፍጥረታት እንዲፈጥር በእግዚአብሔር አምላክ ኃይል ተሰጥቶታል። ክርስቶስ አሁን የሚኖረው መለኮት መሰል ሥልጣኑን እንደያዘ ነው። እንደያውም ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ከይሖዋ አምላክ ጥቅማጥቅሞችንና ኃይልን በማግኘት በይሖዋ ሥር ሆኖ መላውን ዓለም እያስተዳደረ ነው።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እኔነት [Personality] የለውም በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚባል ሦስተኛ አካል የለም። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እኔነት የሌለው የአምላክ ፈጣን ኃይል ነው። እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡ እንዲታዘዘው ለማድረግ ሲፈልግ ለሕዝቡ የሚሰጠው ኃይል ነው።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች



የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴን አስተምህሮ ላለመቀበልና ትምህርቱም ከአረማውያን መድበለ አማልክታዊ እሳቤ የተቀዳ ነው ብሎ ለመደምደም ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸው "ማስረጃዎች" የሚከተሉት ናቸው[12]።

የሥላሴ ትምህርት ያቆጠቆጠውና በስፋት ይታመንበት የጀመረው ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ሥላሴ" ወይም "ሦስት አካላት አንድ እግዚአብሔር" የሚለውን ቃላት አይጠቀምም። የብዙ ሊቃውንቶች ሥራ እንደሚያረጋግጠው የሥላሴ ትምህርት የመነጨው ወይም መሠረታዊ እሳቤው መንጸባረቅ የጀመረው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ነው።

12. በግርጌ ማስታወሻ ካልተመለከተ በስተቀር የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርቶች የተወሰዱት፡- በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (1993) እንዲሁም ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 197-198፥ 212-218፥ 406-428 ከተሰኙት መጻሕፍት ላይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ትምህርት የሚያስተምረው ምንም ነገር የለም። እንደ ማቴ. 28፥19 ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሥላሴን ትምህርት ለማስተማር ብቁ አይደሉም። ክፍሉ የሚያሳየን አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተወሰነ ኅብረት እንዳላቸው እንጂ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ሦስት እኩል የሆኑ አካላት ለስመኖራቸው አይደለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም። ፍጥረታት "አማልክት" ["gods"] ተብለዋል። ዕብራውያን 2፥7 የተጠቀለው ከመዝ. 8፥5 ላይ ሲሆን "መልአክ" የሚለው ቃል ከዕብራይስጡ "ኤሎሒም" ከሚለው ቃል የተመለለ ነው። ስለዚህ መዝሙር 8፥5 ላይ የሚገኘው "ኤሎሒም" የሚለው ቃል "አማልክት" ወይም "እግዚአብሔር መሰል" ["godlike Ones"] [NWT] ተብሎ መተርጎም አለበት። መዝ. 82፥1 8፤ ዮሐ. 10፥34 የእስራኤል ፈራጆች "አማልክት" ተብለዋል። በዚህ ክፍል ላይ "አማልክት" የሚለው ቃል የገባው እግዚአብሔርን በሚወክል መልኩ ነው። ምክንያቱም ፈራጆቹ የእግዚአብሔር ወኪሎች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው መከላከያ ጥቅስ መዝ. 82፥8 ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የሚያንስ አምላክ [a god] ነው እንጂ "ሁሉን ቻይ አምላክ" አይደለም። በኢሳ. 9፥6 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ "ኃያል አምላክ" ተባለ እንጂ "ሁሉን ቻይ አምላክ" አልተባለም። ዮሐ. 1፥1 እግዚአብሔር ከሚለው የግሪክ ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር [The] ካለ ቃሉ በአብዛኛው መተርጎም ያለበት እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው። ነገር ግን ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ እንደ ሚገኝበት ዐውድ ስለሚወሰን የቃሉን ፍቺ የሚወስኑት ተርጓሚዎቹ ናቸው። በዚህ ክፍል ግን "ቃል" የተባለው ክርስቶስ "በእግዚአብሔር ዘንድ" ስለነበር እርሱ ራሱ እግዚአብሔር [God] ሊሆን አይችልም። ይህንንም ዐውድ ራሱ ግልጽ ያደርገዋል። ምክንያቱም ማንም ከራሱ ጋር ["ዘንድ"] አብሮ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ የዮሐ. 1፥1 ትክክለኛ ትርጉም [a god] የሚለው ነው።

እንደ ሥላሴ አማኞች ትምህርት በዮሐ. 5፥18 ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ "ከእግዚአብሔር ጋር እኩል" እንደ ሆነ ነው። ነገር ግን ዮሐንስ የዘገበልን ዕብራውያኑ የኢየሱስ አነጋገር የገባቸው ኢየሱስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳስተካከለ ነው። ስለዚህ ሰንበትን ሽረሃል የሚሰው የዕብራውያኑ አነጋገር ሐሰት እንደሆነ ሁሉ፤ ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለሃል የሚለውም ሐሰት ነው።



በዮሐ. 20፥28 ቶማስ ኢየሱስ ክርስቶስ "አማላኩ" [God] መሆኑን ማመኑ ኢየሱስ ከእርሱ በላይ ኃያል መሆኑን መቀበሉን የሚያመለክት ነው። ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ሆኖ በማየቱ ወደ እግዚአብሔር አምላክ በመደነቅ መጮሁን የሚያሳይ ነው። ይህ ክፍል ቶማስ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ሁሉን ቻይ አምላክ ማመኑን የሚያስተምር አይደለም። ዮሐ. 20፥17 የሚያስተምረን እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይ መሆኑን ነው። እንዲሁም ዮሐ. 20፥31 የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው። ምሳ. 8፥22 "እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ በቀድሞ ሥራው መጀምሪያ" ክፍሉ ስለ ጥበብ ነው የሚያወራው። ስለ እግዚአብሔር ጥበብ አይደለም ምክንያቱም እግዚአብሔር የራሱን ጥበብ ሊፈጥር አይደልም። ስለዚህ ክፍሉ ስለ ሌላ ጥበብ ነው የሚናገረው። በ1ኛ ቆሮ. 1፥24 ክርስቶስ ጥበብ ተብሎአል ስለዚህ ምሳ. 8 የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ነው። ይህም የሚያሳየው ክርስቶስ እንደተፈጠረ ነው።

በቆላ. 1፥15 "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው" ይላል። በኩር የሚለው ቃል የሚያሳየን በመወለድ ሂደት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ መሆኑን ነው። ይህም የሚያረጋግጥልን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሖዋ አምላክ እንደተፈጠረ ነው። ራእ. 3፥14 ኢየሱስ ክርስቶስ ለ"እግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው" ከዚህ ዐረፍተ ነገር በቀላሉ የምንማረው ኢየሱስ ክርስቶስ ይሖዋ አምላክ ከፈጠራቸው ፍጥረታት የመጀመሪያው መሆኑን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ በላይ የሆነ አምላክ አለው። ኢየሱስ አባቱን እግዚአብሔር ብሎአል ኢየሱስ ይህንን ያለው ከትንሣኤው በኋላ ሰማያዊ በሆነው ክብሩ ሳለ ነው (ዮሐ. 20፥17፤ ራእ. 3፥12)። ኢየሱስ ከእርሱ በላይ የሆነ አምላክ ካለው ሁሉን ቻይ አምላክ ሊሆን አይችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ በሰማይ ከእግዚአብሔር በታች ሆኖ ነው ያለው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ለእግዚአብሔር እየተገዛ እንዳለ ያስተምረናል። ይህም በምድር በነበረበት ጊዜ እንደተገዛው ማለት ነው (ዮሐ. 14፥28፤ 1ቆሮ. 11፥3፤ 15፥28)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው። በዳንኤል 10፥13 ላይ ሚካኤል "ከዋንኞቹ አለቆች አንዱ" ነው። ዳን. 12፥1 ላይ "በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል.

.”። የሚለው ትንቢት የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ (ሚካኤል) በሰማይ እንደ ንጉሥ ሆኖ በ1914 በነገሠበት ጊዜ ነው[13]። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድመ ሕልውናውም ሆነ በደኅረ ሕልውናው ጊዜ ሚካኤል እንደሆነ ነው።

1ተሰ. 4፥16 “ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ”። “ጌታ ራሱ” ነው “በመላእክት አለቃ ድምፅ” የሚናገረው። ይህም ኢየሱስ ሚካኤል እንደሆነ ያሳያል “ሚካኤል ብቻ ነው ‘ሊቀ መልአክ’ የተባለው፤ ይህም ማለት ‘የመላእክት ዋንኛ’ ወይም ‘የመላእክት ገዥ’ ማለት ነው። ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በነጠላ ቁጥር ነው። ይህም እግዚአብሔር ለመላእክት አንድ አለቃ ብቻ እንዲኖራቸው ያደረገ ይመስላል። በ1ተሰ. 4፥16 የትንሣኤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ በሊቀ መልአክ ሚካኤል ድምፅ ተገልጽዋል፤ ይህ የሚያመለክተን በእርግጥ ራሱ ሊቀ መልአክ እንደሆነ ነው”[14]።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና (Personality) የለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንደሌለው ተደርጎ ነው የተገለጸው። በማር. 1፥10 መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል ነው የታየው። በማቴ. 3፥11፤ በሉቃ. 3፥16 መንፈስ ቅዱስ ከእሳት ጋር ተነጻጽሮአል። በኤፌ. 5፥18 መንፈስ ቅዱስን መሞላት በወይን ጠጅ ከመስከር ጋር ተነጻጽሮአል። አካላዊ ህልውና ባለው ነገር መሞላት ሞኝነት ነው። መንፈስ ቅዱስ በሰውኛ አገላለጽ ቀርቦአል። ስለዚህ አካላዊ ህልውና ሊኖረው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መንፈስ አካላዊ ህልውና እንዳለው አቅርቦታል፤ ነገር ግን በሰውኛ አገላለጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዴ አካላዊ ህልውና የሌላቸውንም ነገሮች በሰውኛ አገላለጽ አቅርቦአቸዋል። ለምሳሌ፡- ጥበብ ልጅ እንዳለው (ሉቃ. 7፥35)። ኃጢአትና ሞት እንደ ንጉሥ እንደነገሡ (ሮሜ 5፥14,21)። ውኃና ደም ከመንፈሱ ጋር እንደሚመስክሩ (1ዮሐ. 5፥8)።

---

13. "Your Will Be Done On Earth" (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1944), ገጽ. 259
14. Aid to Bible Understanding (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1971), ገጽ.1152





## የይሖዋ ምስክሮች
## የሥላሴ ትምህርት
## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



የሥላሴ ትምህርት የተቀዳው የእግዚአብሔር ስልጣናዊ ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። እንደ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ሁሉ የሥላሴ ትምህርት ሥርዓታዊ ትንተናን ተከትሎ የቀረበው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ለተነሣው የመናፍቃን እንቅስቃሴ መልስ ለመስጠት እንዲያስችላት ነው። የምሁራን ማስረጃ የሚረጋግጠው ይህንኑ እውነታ እንጂ የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ሰፊ ትምህርት አለው። አስተምህሮተ ሥላሴ የተመሠረተው በማቴ. 28፥19 ላይ ብቻ አይደለም። የበሰለ የሥላሴ አማኝ የሥላሴ ትምህርት ያረፈው በዚህ ክፍል ላይ ብቻ ነው አይልም። ክፍሉ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንዳላቸው ጥርት አድርጎ ያሳያል። አብና ወልድ አካላዊ ህልውና ካላቸው ከእነርሱ ጋር አብሮ የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና የለውም የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? በሦስቱም ስም መጠመቃችን ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለሦስቱም ሥልጣን ማስገዛታችንን የሚያሳይ ነው። ይህም እኩል የሆነ ሥልጣን እንዳላቸው ያሳያል።

በአዲስ ኪዳን ብቻ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር፥ የዘላለም ሕይወትን በመስጠት፥ እንዲሁም በክርስትና ሕይወታችን ላይ ተሳትፎ ሲያደርጉ እናያለን። ይህ የሚያሳየን የሥላሴ አስተምህሮ ቀዳማዊ አመንጪው ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው። የእግዚአብሔርንና የአማልክትን [gods] የትርጉም አጠቃቀም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለውን ነጠላ ቃል የሚጠቀመው ያህዌን ለማመልከት ነው። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር [በግሪኩ ቴዎስ] የሚለው ነጠላ ቃል በአዲስ ኪዳን 1400 ጊዜ ተጠቅሶአል። ሐሰተኛ አማልክትን ወይም ጣኦታትን ለማሳየት ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ስድስት ጊዜ ብቻ ነው። ይህም ቃሉ ለሐሰተኛ አማልክት ስለ መዋሉ ዐውዱ ያሳየናል (የሐዋ. 7፥43፤ 12፥22፤ 28፥6፤ 2ቆሮ. 4፥4፤ ፊል. 3፥19፤ 2ተሰ. 2፥7)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል በነጠላ **ቁጥር ሲጠቀምበት**

[በዕብራይስጥ ‘ኤል’ ወይም ‘ኤሎሂም’። በግሪክ ‘ቴዎስ’] የሚያመለክተው ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ነው። ስለዚህ ይህ ወጥነት ያለውና አንድ ዓይነት የቃል አጠቃቀም በግልጽ የሚያሳየን ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቃሉን የተጠቀሙበት እውነተኛውን አምላክ እንዲያመለክት አድርገው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ይናገራል (ለምሳሌ፡- ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6–6፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19፤ 1ዮሐ. 5፥20)። በአንጻሩም አማልክት [gods] ተብለው የተጠሩት ሁሉ ሐሰተኛ አምላክ ናቸው (1ቆሮ. 6፥5፤ ዘዳ. 32፥21፤ መዝ. 96፥5፤ ኢሳ. 41፥23–24)። እውነቱ ይህ ከሆነ የይሖዋ ምስክሮች በዮሐንስ 1፥1 እና 20፥26 ላይ ቴዎስ የሚለው ነጠላ ቃል ለክርስቶስ ለምን እንደተሰጠ መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ?

መዝ. 62፥1 ላይ ሰዎች አማልክት (gods) ተብለዋል፤ ይህም በውክልና ደረጃ ብቻ ነው። ቃሉንም የሚጠቀምበት በምፀት [ironical] ነው። በክፍሉ ላይ “አማልክት” እያለ የሚጠራቸው አድሎአዊ ፍርድ የሚበይኑትን ሐሰተኛ ፈራጆች ነው። ምክንያቱም ራሳቸውን እንደ አማልክት አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው። ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ ይላቸዋል (ቁ. 6, 7)። ጌታ ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ እያስተማረ ያለው (ዮሐ. 10፥34) “የእግዚአብሔር ቃል አይሻርም” ለእነርሱ በምፀት የመጣው ቃል ለእኔ በቀጥታ መዋል አለበት የሚል ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል ነውና (ቁ. 27–30, 36)።

በኢሳ. 9፥6 መሲሑ “ኃያል አምላክ” እንደተባለ ሁሉ፤ በዚያው ዐውድ ውስጥ የያዕቆብ አምላክ “ኃያል አምላክ” ተብሎአል (ኢሳ. 10፥21)። ይህ ክፍል “ኃያል አምላክ” የሚለውን ቃል ለአብ እንደሰጠ ሁሉ ለወልድም መስጠቱ የወልድን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።

ዮሐ. 1፥1 ቴዎስ [እግዚአብሔር] የሚለው የግሪክ ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚተረጎመው እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ ነው። ቃሉ በዚህ መልኩ የሚተረጎመው ከቃሉ ፊት የተወሰነ መስተፃምር ሲኖርም ሳይኖርም ነው። በግሪክ፥ በእንግሊዝኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች የተወሰነ መስተፃምር [the] መኖርም ሆነ አለመኖር በስም [Noun] ላይ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም። በተለይ ቴዎስ የሚለውን የግሪክ ቃል አስመልክቶ ያለው የተወሰነ መስተፃምር ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ግሪክ የትርጉም ለውጥ አያስከትልም። ለምሳሌ፡- ሰይጣን “የዚህ ዓለም አምላክ” (2ቆሮ. 4፥4) ተብሎአል። ነገር ግን ቴዎስ [አምላክ] ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር መኖሩ ቃሉ እውነተኛውን አምላክ እንዲያሳይ አላደረገውም።



በአጠቃላይ ቴዎስ ከሚለው ነጠላ ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር ቢኖርም ባይኖርም ቃሉ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል። ነገር ግን ዐውዱ እውነተኛውን አምላክ የማያመለክት ከሆነ በእንግሊዝኛው (god) ተብሎ ይተረጎማል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው የተተረጎመው (ዮሐ. 1፥1, 12, 13, 16)። በዮሐ. 1፥1ላይ “ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር” እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር አለ። የትርጉም ይዘቱን ሳይቀይር ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው በሚቀጥለው ሐረግ ውስጥ ተጠቅሶአል፥ “ቃልም እግዚአብሔር ነበር”። የተወሰነ መስተፃምር ከቴዎስ ፊት መኖርም ሆነ አለመኖር የትርጉም ለውጥ እንደማያመጣ የሚከተሉትን ጥቅሶች በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም እንኳን ማየት ይቻላል (ዮሐ. 3፥2፤ 13፥3፤ ሮሜ 1፥21፤ 1ተስ. 1፥6፤ ዕብ. 9፥14፤ 1ጴጥ. 4፥11–12)[15]።

“ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር” የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያሳየን ቃል የተባለው ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አብሮ እንዳለና [“ዘንድ”] ቃልም ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ህልውና [personality] እንዳለው የሚያስተምረን ነው። በዚህ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ይስማማሉ [ነገር ግን “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” አብም ወልድም አንድ ህላዌ አላቸው ከሚለው ትምህርታቸው ጋር ይህን ጥቅስ እንዴት ያስታርቁት ይሆን?] ቀጣዩ ዐረፍተ ነገር “ቃልም እግዚአብሔር ነበር” ሲል ቃል የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው የሚያሳይ ነው እንጂ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር መለወጡን ለማሳየት ተፈልጎ አይደለም። በአጠቃላይ በዮሐ. 1፥1 ላይ ለማለት የተፈለገው ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበር። እንዲሁም ቃል ራሱ የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው ነው። ዮሐንስ እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር (“ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር”) በማድረግ እግዚአብሔር አብን ለማመልከት እንደፈለገ ሁሉ ለወልድም፥ “ቃልም እግዚአብሔር ነበር” የተወሰነ መስተፃምር ቢጠቀም ኖሮ “ቃል” የተባለው ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር። ዮሐንስ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ክርስቶስ ከአብ የተለየ ህላዌ እንዳለው ያሳየው ዐረፍተ ነገሩን ያለ መስተፃምር በመገንባት ነው።

---

15. ለበለጠ መረጃ Robert M. Bowman, Jr., Jesus Christ, and the Gospel of John. (Grand Rapids: Baker, 1989) እንዲሁም Murray J. Harris, Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus (Grand Rapids: Baker, 1992) ይመልከቷል።

በዮሐ. 5፥18 ላይ ዮሐንስ ዕብራውያን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር እኩል ነኝ ማለቱ ነው ብለው መረዳታቸውን መዘገቡ እውነት ነው። እንዲሁም ሰንበትን ሽረሃል የሚለው የዕብራውያን ክስ ትክክል ያለመሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ እኔ ከአብ ጋር እኩል ነኝ አላለም የሚለውን ትምህርታቸው አያመለክትም። በሌላ ዐውድ ኢየሱስ ዕብራውያንን የሰንበትን መንፈስ በመሻራቸው ሲቃወማቸው እናያለን (ማቴ. 12፥9–14)። ነገር ግን በዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ የሰንበት ጌታ መሆኑን እያስተማረ ነው። በዮሐ. 5፥17 ላይ ኢየሱስ ሰንበትን እየተቸ ሳይሆን ሕጉ እርሱን እንደማይወክል፥ ሕጉ በሰበአዊያን ላይ ብቻ ተግባራዊ እንደሚሆን እያስተማረ ነው። ስለዚህ ዕብራውያን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ማድረጉ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከሉ ነው በማለታቸው አልተሳሳቱም። ጌታ በሚቀጥሉት ጥቅሶች እያለ ያለው እግዚአብሔር መሆኑን እየካደ ሳይሆን የልጁ ሥልጣን በአባቱ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እያስረገጠ ነው።

ዮሐ. 20፥28 ኢየሱስ ሕያው ሆኖ ከሙታን በመነሣቱ ቶማስ በመደነቅ ወደ እግዚአብሔር "ኦ አምላኪ!" ብሎ መጮኹ ነው የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ከክፍሉ ዐውድ ጋር ብቻ ሳይሆን ከታሪካዊ ዳራውም ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበሩ ዕብራውያን የእግዚአብሔር ስም በንዝህላልነት በዚህ መልኩ አይጠቀሙበትም ነበር[16]። ከክፍሉ የምንመለከተው ነገር ቶማስ በቀጥታ ለኢየሱስ መልስ እየሰጠ እንዳለ ነው፡– "ቶማስም ጌታዬ አምላኬ ብሎ መለሰለት"።

የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው ለሚለው ትምህርታቸው ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሱአቸው ጥቅሶች፥ (ምሳ. 8፥22፤ ቆላ. 1፥15፤ ራእ. 3፥14) በፍጹም ትምህርታቸውን የሚደግፉ አይደሉም። ይልቁንም ድርጅታቸው የአምላክን ቃል እንዴት እንደሚያጣምም እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቃል ያለው ዕውቀት ደካማ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

ምሳ. 8፥22 በምሳሌ መጽሐፍ ከምዕራፍ 1–9 ባሉት ክፍሎች ሁሉ ጥበብ በሰውኛ አነጋገር ጥቅም ላይ ውሎአል። ስለዚህ ምሳ. 8፥22–31 ስለ ክርስቶስ ይናገራል ማለት ትክክል አይደለም። የምሳሌ መጽሐፍ ፍጹም ቅኔያዊ በመሆኑ ከ1ቆሮ. 1፥24 30 ጋር በማያያዝ ክፍሉ ስለ

16. David Reed, Jehovah's Withnesses Answered Verse by Verse (Grand Rapids: Baker Book House, 1992), ገጽ .84



ክርስቶስ ይናገራል ማለት አግባብ አይደለም። የምሳሌ መጽሐፍ የቅኔ መጽሐፍ ነው፤ ሥነ–ጽሑፋዊ ቅርጹም ቅኔያዊ ነው። በምሳ. 1–9 ባሉት ክፍሎች ጥበብ በሰውኛ (personification) አገላለጽ ነው የተጠቀሰችው ዳዊት መሰንቆንና በገናን ተነሡ እንደሚለው ማለት ነው፥ "በገና ሆይ፥ ተነሥ፥ መሰንቆም፤ እኔም ማልጄ እነሣለሁ" (መዝ. 108፥2)። ክፍሉ ስለ ጥበብ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ነው የሚናገረው ካልን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልናነሣ እንችላለን፡–

- ክፍሉ ጥበብን በአንስታይ [feminine] ነው የሚጠራት (ቁጥር 1, 2, 3, 11) ክርስቶስ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው "አንቺ" [she] የተባለው?
- ምሳሌ 8 የሚናገረው ስለ ጥበብ ብቻ ሳይሆን ስለ ማስተዋልም ጭምር ነው (ቁ.1)። 1ቆሮ. 1፥24, 30 በመጥቀስ ክርስቶስ ጥበብ ነው ካልን ማስተዋልስ ደግሞ ማነው?
- "ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሶሶችዋን አቆመች" (9፥1) ሲል ምን ማለቱ ነው?
- ስለምን ስለ ክርስቶስ የመናገር ከሆነ "በውኑ ጥበብ አትጮኽምን? ማስተዋልስ ድምፅዋን አትሰጥምን? " በማለት ሰውኛ አገላለጽ መጠቀም ለምን አስፈለገው?
- ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ከሆነ፤ የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ክርስቶስ ነውና (1ቆሮ. 1፥24) እግዚአብሔር ክርስቶስን ከመፍጠሩ በፊት ኃይልና ጥበብ የለውም ነበር ማለት ነው?
- በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ጥበብ እንደሚገዛ ንብረት ነው የቀረበችው (1፥5፤ 4፥5፤ 15፥32፤ 18፥16፤ 17፥16፤ 18፥15፤ 19፥8፤ 20፥14፤ 23፥23) ይህስ ምን ያስተምረናል?

በእርግጥ የምሳሌ መጽሐፍ የጥበብን [Wisdom] አስፈላጊነት እንጂ ስለ ክርስቶስ አያወራም።

ቆላ. 1፥15 "በኩር" የሚለው ቃል በመወሰድ ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ማለት ሳይሆን ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ወራሽና ባለቤት መሆኑን የሚያስተምር ነው። "በኩር" ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል [ፕሮቶቶኮስ] የሚያመለክተው በጊዜ ቅደም ተከተል የመጀመሪያ መሆንን ሳይሆን ታላቅነትንና ክብርን የሚያሳይ ቃል ነው። ንጉሥ ዳዊት የእሴይ የመጨረሻ ልጅ ነው። በንግሥና ከሄድን ከዳዊት በፊት ንጉሥ ሳኦል 40 ዓመት ነግሦአል። ነገር ግን እግዚአብሔር ዳዊትን

በኩር ይለዋል መዝ. 88፥27። ይህ የሚያሳየን የዳዊትን ክብር እንጂ የጊዜ ብልጫን አይደለም። የዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ ምናሴ ሆኖ ሳለ (ዘፍ. 41፥50–51) ኤፍሬም "በኩር" ተብሎአል (ኤር. 31፥8)። ያዕቆብ የኤሳውን ብኩርና ወስደ ስንል ክብሩን ወሰደ ማለታችንም አይደል? ጳውሎስ በቆላ. 1፥15 ላይ የኢየሱስን ፍጡር መሆን ለማመልከት ቢፈልግ ኖሮ "ፕሮቶቶክስ" ከሚለው የግሪክ ቃል ይልቅ "ፕሮቶኪቲሲስ" የሚለውን ቃል ይጠቀም ነበር[17]። በአዲስ ኪዳን ግሪክ "ፕሮቶኪቲሲስ" የሚለው ቃል አንድም ጊዜ ክርስቶስን ለማሳየት በጥቅም ላይ አልዋለም[18] የይሖዋ ምስክሮች በቆላ. 1፥15 ላይ አራት ጊዜ ሌሎች [other] የሚለውን ቃል በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ላይ ጨምረዋል። ነገር ግን የግሪክ አዲስ ኪዳን ሌሎች [other] የሚል ቃል የለውም። ይህን ቃል በክፍሉ ውስጥ አራት ጊዜ መጨመራቸው ኢየሱስን ፍጡር አድርጎ እንዴት እንዳቀረበው ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ይመልከቱ።

ራእ. 3፥14 የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት "አርኪ" የሚለውን የግሪክ ቃል "ከተፈጠሩት ነገሮች የመጀመሪያ" አድርጎ ተርጉመውታል። ቃሉ በአዲስ ኪዳን የጊዜን መጀመሪያ ለማሳየትም ሆነ ( ዮሐ. 1፥1, 2፤ 6፥64፤ 8፥25, 44፤ 15፥27፤ 16፥4፤ 1ዮሐ. 1፥1፤ 2፥7, 13, 14, 24፤ 3፥8 11፤ 2ዮሐ. 5, 6) መገኛ ወይም ምንጭ በሚለው ትርጉሙ በብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ ተተርጉሞአል (ሉቃ. 12፥11፤ ሮሜ 8፥38፤ 1ቆሮ. 15፥24፤ ኤፌ. 1፥21፤ 3፥10፤ 6፥12፤ ቆላ. 1፥16፤ 2፥10, 15፤ ቲቶ 3፥1) ። በራእይ መጽሐፍ ቃሉ እግዚአብሔርን ለማመልከት ገብቶአል ወይም ጥቅም ላይ ውሎአል (ራእ. 21፥6፤ 22፥13)። በነዚህ ክፍሎች ውስጥ ቃሉ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ስማሳየት ከገባ የክርስቶስን ዘላለማዊነት የማያሳይበት ምንም ምክንያት የለም። ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም በስተቀር በየትኛውም የእንግሊዝኛም ሆነ የአማርኛ ትርጉሞች ላይ ቃሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው አይልም። ነገር ግን የፍጥረት መገኛ ወይም መጀመሪያ ተብሎ ነው የተተረጎመው [የ1860 ዓ.ም. የአማርኛ ትርጉም ከ1954 ዓ.ም. ትርጉም ጋር ያወዳድሩ]።

ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን አምላኪ ብሎአል። ምክንያቱም ኢየሱስ የፍጡሩን ቦታ ለኛ ለኃጢአተኞች ሲል ስለወሰደ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብ በሰማይ እንኳ ተገዝቶለት ነው ያለው። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ ከአብ ያንሳል ማለት ግን በፍጹም አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው (የሐዋ. 17፥31፤ 1ጢሞ. 2፥5) ስለዚህ የክርስቶስ መገዛት በምድር በነበረበት ጊዜ ብቻ አይደለም።

17. F.F Bruce in Inerrany, ed. Norman L. Geisler (Grand Rapids: Zondervan, 1979)
18. J.B Light foot, Paul's Epistles to the colossians and to philemon. (Grand Rapids: Zondervan, 1979), ገጽ. 147



ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል አይደለም። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ ሚካኤል ነው ለማለት የሚጠቅሰው ጥቅስ ዳን. 10፥13 ፍጹም የሚያስኬደው አይደለም። ምክንያቱም ሚካኤል "ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ" እንደሆነ እንጂ ኢየሱስ ሚካኤል ነው የሚል ዐረፍተ ነገርም ሆነ ቃል በክፍሉ ውስጥ አልተጠቀሰም። በራእ. 19፥16 ኢየሱስ "የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ" ነው እንጂ ከብዙ አለቆች መካከል አንዱ አይደለም ከመላእክት አንድም እንኳ የእግዚአብሔር ልጅ ካልተባለ (ዕብ. 1፥5) ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክት ሊሆን አይችልም የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት በላይ (1፥1–4)፥ ከመላእክት በላይ (1፥5–2፥8)፥ ከሙሴ በላይ (3፥1–6) እንደሆነ ያስተምረናል። ከተዘረዘሩትም በላይ መሆኑ የታየው የእግዚአብሔር የመጨረሻ መገለጥ (1፥1)፥ የዓለማት ፈጣሪና የዓለማት ደጋፊ መሆኑ (1፥3) እንዲሁም የእግዚአብሔር ባሕርይ (1፥3) ስላለው ነው። ይህ ብቻ 'አይደለም በዕብ. 1፥6 ላይ መላእክት ለኢየሱስ ይሰግዱለታል [በግሪክ ፕሮስኩኖ]። መልአክ ከሆነ እንዴት መላእክት ሰገዱለት? መላእክት ዓለማትን መግዛት ካልቻሉ (ዕብ. 2፥5) የዓለማት ገዥ ኢየሱስ በፍጹም መልአክ ሊሆን አይችልም (ዘፍ. 49፥10፤ 2ሳሙ. 17፥18፤ መዝ. 2፥8፤ ዳን. 7፥13–14፤ ሉቃ. 1፥32–33፤ ማቴ. 2፥1–2፤ 8፥35፤ ራእ. 19፥16)።

1ተሰ. 4፥16 "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና" ክፍሉ ኢየሱስ በታላቅ እጀብ እንደሚመጣ የሚያስተምረን ክፍል እንጂ ኢየሱስ ራሱ በመልአክ ድምፅ ይናገራል አይልም።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና [personality] አለው። ብዙውን ጊዜ አካላዊ ህልውና ማለት መጨበጥ፥ መታየት ወዘተ ማለት የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ህልውና አለው ሲባል የራሱ ማንነት ይኸውም ስሜት፥ እውቀትና ፈቃድ አለው ማለት ነው። ይዳሰሳል፥ ይታያል ወዘተ ማለት አይደለም። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና በሌላቸው ነገሮች መመሰሉ አካላዊ ህልውና እንደሌለው ያመለክታል የሚለው ትምህርት ፍጹም የተሳሳተ ነው። (ማር. 1፥10) መንፈስ ቅዱስ በርግብ መመሰሉ አካላዊ ህልውና የለውም እንድንል አያደርገንም። አብ ራሱ በቁጥቋጦ እንደሚነድ እሳት ሆኖ ነው ሙሴን የተገናኘው (ዘጸ. 3፥2–4)። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር አብ ህልውና የለውም ማለት አይደለም።

በማቴ. 3፥11፤ ሉቃ. 3፥16 መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉ አካላዊ ሀልውና የሰውም እንድንል አያደርገንም። መጽሐፍ ቅዱስ በተምሳሌታዊ አገላለጽ እግዚአብሔር እሳት ነው ይለናል (ዘዳ. 4፥24፤ 9፥3፤ ዕብ. 12፥29)።

ኤፌ. 5፥18 በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ የሚለው የመልእክት ክፍል በእግዚአብሔርም (3፥19) እንዲሁም በክርስቶስ (4፥10) ተሞሉ ይለናል። አብና ወልድ አካላዊ ሀልውና እያላቸው የሚሞሉን ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ቢሞላብን አካላዊ ሀልውና የሰውም የሚያስኘው ለምንድን ነው?

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ምን ይላል



የሥላሴ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ (ኢሳ. 43፥10፤ 44፥8-8፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19 1ዮሐ. 5፥20)። አብ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. 17፥3፤ 1ቆሮ. 8፥8)። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው (ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 1፥1፤ 20፥28፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1)። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. 5፥3-4፤ 2ቆሮ. 3፥17)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ተብሎአል (ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 1፥1፤ 20፥28፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1)። ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎአል (ሮሜ 10፥9-13፤ ፊል. 2፥9-11፤ ዕብ. 1፥10-12፤ 1ጴጥ. 2፥3፤ 3፥15)። የእግዚአብሔር ባሕሪያት ሁሉ አሉት (ቆላ. 1፥15፤ 2፥9፤ ዕብ. 1፥3)። ይኸውም፦ አይለወጥም (ዕብ. 1፥11-12፤ 13፥8)። ዘላለማዊ ነው (ዮሐ. 1፥1-2፤ 8፥58፤ 17፥5፤ ቆላ. 1፥17፤ ዕብ. 1፥2 12)። የኃይል ሁሉ ባለቤት ነው (ማቴ. 28፥8፤ ኤፌ. 1፥21)። ሁሉን ያውቃል (ዮሐ. 18፥30)። በሁሉ ቦታ ይገኛል (ማቴ. 18፥20፤ 28፥30፤ ኤፌ. 1፥23፤ ኤፌ. 4፥10፤ ቆላ. 3፥11)። ከስዎች ግምት በላይ ነው (ማቴ. 11፥27። ተፈርቶአል ኤፌ. 5፥21)። ከምንም ከማንም በላይ በፍጹምነት ተፈቅሮአል (ማቴ. 10፥37)። በፍጹም ልብ ታምኖአል [እግዚአብሔርን እንደምናምነው] (ዮሐ. 3፥18፤ 14፥1)። ስግደትን




ተቀብሎአል ወይም ተመልኮአል (ማቴ. 28፥17፤ ዕብ. 1፥6፤ ራእ. 22፥3)። የስበአውያንን ጸሎት ያዳምጣል (ዮሐ. 14፥14፤ ሮሜ 10፥12-13፤ 1ቆሮ. 1፥2)።

መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሀልውና አለው። የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎአል [እርኩሳን መናፍስት መንፈስ እንደተባሉት ማለት ነው] መንፈስ ቅዱስ ስም አለው (ማቴ. 28፥19)። አጽናኝ ተብሎአል (ዮሐ. 14፥18) [ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ (በግሪኩ ቅጂ ላይ) አካላዊ ሀልውና ላለው አካል ብቻ የሚሰጥ ነው]። በኢየሱስ ክርስቶስ ተልኮአል፤ ይኸውም ለማስተማር፥ ለመስከር ወዘተ። ይህም ከራሱ ሳይሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ ወስዶ ነው (ዮሐ. 14፥28፤ 15፥26-27፤ 18፥7 13-14)። ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ተነጻጽሮአል (ማር. 3፥28-30፤ 1ጢሞ, 4፥1፤ 1ዮሐ. 3፥24-4፥8)። ለደቀ መዛሙርት ፈቃዱን ተናግሮአል፤ ወደ አገልግሎትም መርቶአቸዋል (የሐዋ. 8፥29፤ 10፥19-20፤ 18፥7)። ስዎችን ወደ ልዩ ልዩ አገልግሎት ጠርቶአል (የሐዋ. 13፥2፤ 20፥28)። እርሱ ራሱ እንደፈቀደ ለክርስቲያኖች ስጦታን ይሰጣል (1ቆሮ. 12፥11)። ከእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (የሐዋ. 1፥18፤ 28፥25፤ ዕብ. 3፥7)። ሊዋሽ ይችላል፤ ማለትም ስዎች ሊዋሹት ይችላሉ [ነገር ግን አምላክ ስለሆነ ያውቃል] (የሐዋ. 5፥3)።

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። ያህዌ ተብሎአል (ዘጸ. 34፥34 ይህን ጥቅስ ከ2ቆሮ. 3፥17-18 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ተብሎአል (የሐዋ. 6፥3-4)። የእግዚአብሔር ባሕርያት አሉት። ዘላለማዊ ነው (ዕብ. 9፥14)። ሁሉን ያውቃል (1ቆሮ. 2፥10)። በሁሉ ቦታ ይገኛል (መዝ. 139፥7)።

## አስተምህሮተ ሥላሴን አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች



1. ባቢሎናውያንም ሆኑ አሶራውያን መድበስ አማልክት [polytheism] አምላኪዎች ነበሩ። የሥላሴ አስተምህሮ ዳግም፦ "አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ [monotheism]፤ በአንዱ የእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት [Godhead] ውስጥ ሦስት አካላት [persons] አሉ" የሚል ነው። ታዲያ የሥላሴ አስተምህሮ የአረማውያን ፅንሰ ሐሳብ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ትክክል ነውን?

2. "ሥላሴ" የሚሰው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ ብቻ ትምህርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ማለት ይቻላልን? [የይሖዋ ምስክሮች ድርጅታቸው በአምላክ የሚመራ ነው ስለሚሉ "ቴዎክራቲክ" ("በአምላክ የሚመራ") የሚሰውን ቃል ይጠቀማሉ። ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። እንዲያውም ቃሉ የመጣው ከአረማውያን ነው፤ የሮም ቄሳሮችም ሆኑ የግብፅ ፈርዖኖች አምላክ ነን ይሉ ስለነበር፣ አስተዳደራቸውን "ቴዎክራቲክ" ብለው ይጠሩታል። ቴዎክራቲክ የሚለው ቃል የመጣው ከአረማውያን ስለሆነ ቃሉን መጠቀም የለብንም ማለት እንችልም፤ ምክንያቱም ፅንስ ሐሳቡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኝ]።
3. ለበአውያን ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔርን ሊረዱ አይችሉም (ኢሳ. 55፥6–9፤ ሮሜ 11፥33፤ 1ቆሮ. 13፥12)። "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" የሚባለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሐፍ በገጽ 148 ላይ "አምላክ መጀመሪያ የልውም ማለት ምክንያታዊ ነውን? ይህን ጉዳይ አእምሮአችን ሙሉ በሙሉ ሊረዳው አይችልም። ለመረዳት አለመቻላችን ግን ይህን ሐቅ ላለመቀበል ምክንያት አይሆንንም" ይላል። የሥላሴን አስተምህሮ አእምሮአችን ሙሉ በሙሉ ሰላልተረዳው አንቀበልም ማለት ምክንያታዊ ነውን?
4.

| ባሕሪ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| በሁሉ ቦታ መገኘት | 1ነገ. 8፥27 | ማቴ. 28፥20 | መዝ. 139፥7 |
| ሁሉን ማወቅ | መዝ. 147፥5 | ዮሐ. 16፥30 | 1ቆሮ. 2፥10 |
| ሁሉን መቻል | መዝ. 135፥6 | ማቴ. 28፥18 | ሮሜ 15፥19 |
| ቅድስና | ራእ. 15፥4 | የሐዋ. 3፥14 | ሮሜ 1፥4 |
| ዘላለማዊነት | መዝ. 90፥2 | ሚኪ. 5፥2፤ ዮሐ. 1፥2፤ ራእ. 1፥8,17 | ዕብ. 9፥14 |

አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ዓይነት ባሕርይ ካላቸው በሥላሴ ማመን ያልተገባን ለምንድን ነው?

5. አልፋና ዖሜጋ እግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ (ኢሳ. 44፥6) ኢየሱስ ክርስቶስም አልፋና ዖሜጋ ነው (ራእ. 22፥12–13)። አልፋና ዖሜጋ የሆነው አብ ጀማሬ ከሌለው፤ አልፋና ዖሜጋ የሆነው ኢየሱስ እንዴት ጅማሬ ሊኖረው ይችላል?
6. በዳን. 10፥12 ኢየሱስ ክርስቶስ ሚካኤል ነው የሚል ግልጽ ዐረፍተ ነገር ወይም ቃል አለ?
7. ከመልአክት እግዚአብሔር ልጄ ያለው ከሌለ (ዕብ. 1፥5) ኢየሱስ ልጄ ካለው እንዴት ኢየሱስ መልአክ ሊሆን ይችላል?



6. ከመልአክት ዓለምን የሚመራ ከሌለ (ዕብ. 2፥5) ነገር ግን ኢየሱስ ዓለምን ከመራ (ሉቃ. 1፥32–33፤ ራእ. 19፥16) እንዴት መልአክት ነው ልንለው ቻልን?
9. ሊቀ መልአክ ሚካኤል ሰይጣንን "ጌታ ይገሥጽህ" (ይሁዳ 9) ካለው ኢየሱስ ግን በሥልጣኑ ሰይጣንን መገሠጹ (ማቴ. 4፥10፤ 16፥23፤ ማር. 8፥33) ምን ያስተምረናል?
10. መንፈስ ቅዱስ እውቀት (ሮሜ 8፥27፤ 1ቆሮ. 2፥10–11)፥ ስሜት (ኤፌ. 4፥30፤ 2ቆሮ. 2፥2, 5) እንዲሁም ፈቃድ (1ቆሮ. 12፥11፤ ያዕ. 1፥18) ካለው "ኃይል" ብቻ እንጂ አካላዊ ህልውና የለውም ከሚለው የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ትምህርት ጋር እንዴት ይታረቃል? ኃይል ዕውቀት፥ ስሜት፥ ፈቃድ ሊኖረው ይችላል?
11. መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክር (ዮሐ. 15፥26)፥ ትእዛዝ የሚሰጥ (የሐዋ. 8፥29፤ 13፥2) ከሆነ እንዴት የመጠበቂያ ግንብ ኃይል ብቻ ነው አለው? ኃይል አካላዊ ህልውና ያላቸው አካላት የሚሠሩትን እንዲህ ዓይነት ሥራ ሊሠራ ይችላልን?
12. ኃይል ሊያዝን፥ ሊሰደብ፥ ሊዋሽ፥ ሊታዘዙት እንዲሁም ሊላክ ይችላልን? [መንፈስ ቅዱስ ግን ሊያዝን (ኤፌ. 4፥30)፥ ሊሰደብ (ማቴ. 12፥32)፥ ሊዋሽ (የሐዋ. 5፥3–4)፥ ሊታዘዙት (የሐዋ. 13፥2) እንዲሁም ሊላክ (ዮሐ. 14፥26) ይችላል]።
13. መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት አዝውትሮ በዋቢነት የሚጠቅሳቸው የግሪክ ቋንቋ ምሁራን መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንዳለው እንደሚያምኑ ያውቃሉ? [F.F Bruce, A.T Robertson, John N. Darby, R.C Trench, J.H Thayer, Marvin R. Vincent, W.E Vine, እንዲሁም R.Young[19]]
14. ኢየሱስ ክርስቶስ አካላዊ ህልውና እንዳለው እየታመነ ሰዎችን "የሚሞላ" ከሆነ (ኤፌ. 4፥10፤ 1፥23)፤ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን መሙላቱ (ኤፌ. 5፥16) አካላዊ ህልውና የለውም ያሰኘዋል?

---

19. ለምሳሌ፡- Richard Trench, Synonyms of the New Testament (Grand Rapids: Eerdman, 1953), ገጽ 357-361. A.T Robertson Word Pictures in the New Testament, Vol. 5 (Nashviii Broad-man Press, 1932, ገጽ. 253 W.E Vine, An Expository Dictionary of New Testament Words, Vol. 4 (old Tappan, N.J: Revell, 1966), ገጽ .64

## 3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

የይሖዋ ምስክሮችና የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ነው። የክርስቶስ ሰብአዊ አካል ከሙታን አልተነሣም፡ ነገር ግን የክርስቶስ ሰብአዊ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል ወይም ወደ አለመኖር ደረጃ ሄዶአል የሚል አስተምህሮት አለው። ይህን አስመልክቶ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡ ጽሑፎች እንዲህ ይላሉ፡-

- "ንጉሥ ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ ሞቶ የማይታይ ፍጥረት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል"[1]
- "በትንሣኤው ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሰው አልሆነም ነገር ግን መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ተነሣ"[2]
  ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የክርስቶስን ትንሣኤ በተመለከተ እንዲህም የሚል ግምት አለው፡-
- የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል
- ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ መታሰቢያነት አንድ ሥፍራ ተጠብቆ ነው ያለው[3]

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች[4]

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በመንፈስ ነበር ለሚለው ትምህርታቸው የይሖዋ ምስክሮችና ድርጅታቸው የሚከተሉትን ጥቅሶች እንደ ቃለ እግዚአብሔር ማስረጃነት ይጠቀሙባቸዋል።

1. Let God Be True (1946) ገጽ. 22
2. The Kingdom is at Hand. ገጽ. 258 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም
3. Studies in the Scripture. ገጽ. 129 Vol 2
4. Reasoning from the Scriptures, ገጽ. 217,334-335 እና Insight on the Scriptures. ገጽ. 785-86



ክርስቶስ ኢየሱስ አካሉን ዳግም ካስነሣ ለኃጢአት የከፈለውን ክፍያ መልሶ ወስዶታል ማለት ነው (ማቴ. 20፥28)።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ እንደተነሣ ይናገራል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 15፥45 ኢየሱስ በትንሣኤው የመንፈስ ትንሣኤ እንዳደረገ ወይም መንፈስ ሆኖ እንደተነሣ መግለጽ ያስተምራል። በ1ጴጥ. 3፥18 ላይ "በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት መንፈስ ሆኖ ተነሣ ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ቀመስ ባሕርይና ክብር ስላለው ከሙታን የተነሣው ከሰብአዊያን በላይ ሆኖ ነው። የኢየሱስ አምላክ ቀመስ ባሕሪው እግዚአብሔርን እንዲወክል አድርጎታል (ቆላ. 2፥9፤ ዕብ. 1፥3) ስለዚህም መንፈስ መሆን የግድ ያስፈልገዋል (ዮሐ. 4፥24)።

ኢየሱስ ሰው ሆኖ ስለው ልጆች ስላደረገው በጎ ሥራ አምላክ መለኮታዊ መንፈስ ሸልሞታል ወይም ክብር ሰጥቶታል (ዮሐ. 17፥5)። መንፈስም ሆኖ ከሙታን በመነሣቱ ሥጋና ደም የማይወርሰውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ኢየሱስ ወርሶአል (1ቆሮ. 15፥50)። ይህም መለኮት የመሆን ሽልማት ኢየሱስን በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባት አስችሎታል (ዮሐ. 20፥19)። ይህ ብቻም አይደለም በድንገት መታየትም ሆነ መሠወር ይችል ነበር (ሉቃ. 24፥30-36)።

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ያስመታየቱ መንፈስ ሆኖ መነሣቱን ያረጋግጣል። ዓለም ኢየሱስን በፍጹም አያይም (ዮሐ. 14፥19)። ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስ ማንም አላየውም፥ ሊያየውም አይችልም (1ጢሞ. 6፥16)።

ደቀ መዛሙርት ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስን ያወቁት በአካል ሳይሆን በምግባሩ ብቻ መሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርት የታያቸው በተለየ አካል መሆኑን ያሳየናል። የኤማሁስ መንገደኞች ኢየሱስን ያወቁት ዳቦውን ቆርሶ፥ ባርኮ ሲሰጣቸው ነው (ሉቃ. 24፥13-31)። ማሪያም ኢየሱስን ያወቀችው ስሟን ከጠራ በኋላ ነው (ዮሐ. 20፥10-17)። ዮሐንስ ኢየሱስን ያወቀው ሌሎች ዓሣ እያጠመዱ ነው (ዮሐ. 21፥1-7)።

## የኢየሱስ ትንሣኤን በተመለከተ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለኃጢአታችን ክፍያ እንዳዋለ ያስተምረናል (ማቴ. 20፥28)። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በአካል ሊነሣ አይችልም አላለም።

እርግጥ ነው (1ቆሮ. 15፥45) ኢየሱስን መንፈስ ነው ይለዋል፤ ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነበር ማለት እይደለም። ይህን ክፍል ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነበር ብለን የምንተረጉመው ከሆነ አዳምም "ሕያው ነፍስ" ብቻ የሆነ፥ ቁሳዊ የሆነ አካል የሌለው ነበር ማለት ነው። ክፍሉ አዳምን ነፍስ፥ ኢየሱስን ደግሞ መንፈስ አድርጎ ማነጻጸሩ፥ አዳም ሰው ኢየሱስ መንፈስ ነው ስማለት ፈልጎ እይደለም። ነገር ግን ጳውሎስ የሚያነጻጽረው የአዳም ሕይወት ምድራዊና ተፈጥሮአዊ ነበር፤ የክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት ግን መንፈሳዊና ከማያዊ ነበር። እዳም ሕይወት ያገኘው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ሲባልበት ነው፤ ኢየሱስ ግን ሕይወት ሰጪ ነው፤ ስለዚህም የሕይወትን መንፈስ እፍ እስብን። ይህንን ነው ጳውሎስ በንጽጽር ሲያሳየን የፈለገው።

1ኛ ጴጥ. 3፥18 "በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማስት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት እንደሚለው መንፈስ ሆኖ ተነሣ ማለት እይደለም። ነገር ግን "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማስት በሥጋ ቢሞትም መንፈስ ቅዱስ ግን እስነሣው ለማለት ነው ["Made alive by the Spirit" NIV]። ስለዚህ ክፍሉ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ተነሣ ሳይሆን የሚለው መንፈስ ቅዱስ ነው ያስነሣው ማስቱ ነው (ሮሜ 8፥11 ይመለከቷል)።

ስመ ጥር የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ክፍሉ ኢየሱስ በሞተበት ዓርብና በትንሣኤ በተነሣበት እሑድ መካከል ስለነበረው የሽግግር ወቅት የሚተርክ እንጂ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚናገር እይደለም ባዮች ናቸው። ክፍሉ ስለ ትንሣኤ በፍጹም አያወራም። በሞቱና በትንሣኤው መካከል የነበረውን ወቅት የሚያሳይ ነው። ይህ ትንተና ከክፍሉ ዐውድ ጋር የሚስማማ ነው። ቀጣዩ ቁጥር (ቁጥር 19)



"በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው" ይህም በሞቱ ድል መንሣቱን ለማወጅ ነው። ድል የነሣውም እርኩሳን መናፍስትንና በኖኅ ዘመን የነበሩትን ኃጢአተኞች ነው (ቁጥር 20፤ ዘፍ. 6፥1-4፤ 2ጴጥ. 2፥4-5፤ ይሁ. 5-6፤ ቆላ. 2፥15) ይህ ትንተና ከዐውዱ ጋር መስማማቱ ብቻ ሳይሆን የክፍሉን የሐሳብ ፍሰት የተከተለ ነው። ቁጥር 18 ስለ ክርስቶስ ሞት፤ ቁጥር 19 እና 20 በሞቱና በትንሣኤው መካከል ስለነበረው ጊዜ፤ ቁጥር 21 ትንሣኤ፤ ቁጥር 22 ዕርገት።

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከትነው የሥነ መለኮት ሊቃውንት ክፍሉን አስመልክቶ ሁለት የተለያየ አመስካከት አላቸው። "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት በሥጋው ሲሞት መንፈስ ቅዱስ አስነሣው የሚለው አንደኛው ትንታኔ ሲሆን፤ ክፍሉ ስለ ትንሣኤ ሳይሆን በሞቱና በትንሣኤው መካከል ስለነበረው ጊዜ የሚናገር ነው የሚለው ትንተና ሁለተኛው ነው። ነገር ግን በየትኛውም መንገድ ክፍሉ የይሖዋ ምስክሮች "ክርስቶስ መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ነው የተነሣው" ለሚለው ትምህርታቸው ድጋፍ ሊሆን በፍጹም አይችልም። ጴጥሮስ ክርስቶስ በሥጋዊ አካል እንደተነሣ እልካደም፤ ምክንያቱም በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ክርስቶስ በአካል እንደተነሣ ይመሰክራሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደሆነ ያስተምረናል። የይሖዋ ምስክሮች "ኢየሱስ መለኮት ቀመስ" ትምህርታቸው ምን ማለት ነው? ኢየሱስ አባቱን ድሮ በነበረኝ ክብር አክብረኝ (ዮሐ. 17፥5) ማለቱ ወደ ቀድሞ ክብሩ እንደሚመለስ እንጂ ሰዋዊነቱን ለመተው መፈለጉን አያሳይም። የኢየሱስ የትንሣኤ አካል እኛ ከለበስነው ሥጋና ደም የሚለየው የኢየሱስ የትንሣኤ አካል የማይሞት፥ የማይበሰብስ፥ እጅግ የከበረ፥ ወዘተ መሆኑ ብቻ ነው (1ቆሮ. 15፥50)።

ልክ ነው ኢየሱስ በተዘጋ ቤት ውስጥ ገብቶአል (ዮሐ. 20፥19፤ 26)። በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንገት መታየትም ሆነ መሠወር ይችል ነበር (ሉቃ. 24፥30-38)። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ ከሙታን የተነሣው መንፈስ ሆኖ ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በፊሊጶስ ተመሳሳይ ነገር አድርጓል (የሐዋ. 8፥38-40) ነገር ግን ፊሊጶስ መንፈስ አልነበረም። ኢየሱስ ከትንሣኤው በፊት በውሃ ላይ የሄደው (ማቴ. 14፥25-27፤ ማር. 6፥42-50፤ ዮሐ. 6፥6-20) በአካል መሆኑ ከታመነ ከትንሣኤው በኋላ በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባቱም ሆነ መሠወሩ መንፈስ ነው እንዴት ያስኘዋል?

በእርግጥ ኢየሱስን ዓለም ዳግም አያየውም (ዮሐ. 14፥19)። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ነው የተነሣው ማለት አይደለም። ከትንሣኤው በፊት እንደሚያደርገው በሕዝብ ፊት አይመላለስም ለማለት ነበር እንጂ። እግዚአብሔር ኢየሱስን እንዲያዩ የፈቀደላቸው ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች ሰዎች ኢየሱስን አይተውታል (የሐዋ. 10፥39–41)።

አንደኛ ጢሞ. 6፥16 ሰው ኢየሱስን በመለኮታዊ ክብሩ ፍጹም ማየት እንደማይችል ያስተምራል። ነገር ግን ጳውሎስና ሌሎች ጥቂት ሰዎች በክብሩም እንኳ ቢሆን አይተውታል። ከፍሎ ኢየሱስ በአካል ስላልተነሣ ማንም ሊያየው አይችልም አይልም። ሉቃ. 24፥13–31 ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ያላወቁት "እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር" (ቁጥር 16) ይላል። እግዚአብሔር ዓይናቸውን ሲከፍትላቸው (ቁጥር 31) አወቁት። ስለዚህ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ዘግይተው ማወቃቸው ኢየሱስ መንፈስ ስለሆነ ሳይሆን ዓይናቸው ስለተያዘ ነው።

ዮሐ. 20፥10–17 በዚህ ክፍል ላይ ማሪያም ኢየሱስን በመጀመሪያ ያላወቀችው *አንደኛ* ጨለማ ስለ ነበር (ቁጥር 1)። *ሁለተኛ* ብዙ አልቅሳ ስለ ነበር ዓይኗ በእንባ ስለተሞላ (ቁጥር 11፤ 13፤ 15)። *ሦስተኛ* ኢየሱስ እስኪጠራት ጊዜ ድረስ ወደ እርሱ ስላልዞረች ነበር (ቁጥር 16)። እንጂ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ስለተነሣ አይደለም።

በዮሐ. 21፥1–7 ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ያላወቁት፡– *አንደኛ* ጊዜው "ንጋት" ላይ ስለ ነበር (ቁጥር 4)። ሁለተኛ፥ ታንኳይቱ ኢየሱስ ከነበረበት *ሥፍራ* "ሁለት መቶ ክንድ" [(Hundred Yards) የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳን የሚያህል] (ቁጥር 8) ያህል ርቃ ስለነበር ነው እንጂ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ስለተነሣ አልነበረም።

## *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምን ይላል?*



የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አስተምህሮ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡– "ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት" በተጨማሪም ጳውሎስ



"ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ" (1ቆሮ. 15፥14፤ 17)። የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ አስመልክቶ ያለው እውነተኛ ትምህርት የአንድን ሰው ዘላለማዊ ሕይወት ጉዳይ ይወስናል "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና" (ሮሜ 10፥9)።

## 1. ትንሣኤ የሚለው ቃል ቁሳዊ የሆነ አካልን ብቻ የሚያሳይ ነው

በመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ትንሣኤ የሚለው ቃል ቁሳዊ አካልን ብቻ የሚያመለክት ነው። ዕብራውያን በተለይ በፈሪሳውያን ዘንድ የጻድቃን የወደፊት ሁኔታን አስመልክቶ የተለያየ አመለካከት ቢኖራቸውም፥ ሁሉም ግን ትንሣኤን ቁሳዊ አካል በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከመነሣት ጋር ብቻ ነበር የሚያያይዙት[5]።

ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈሪሳውያን ግብዝነት ደስተኛ ባይሆንም፥ ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤን ባለመቀበላቸው ቢነቅፋቸውም፥ ትንሣኤ በሚለው የቃል ፍቺ ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው (ማቴ. 22፥23–32)።

ጳውሎስ ቀድሞውኑ ፈሪሳዊ ስለነበር ስቃይ የደረሰብኝ በሙታን ትንሣኤ በማመኔ ነው ብሎ ነበር (የሐዋ. 23፥6–8)።

በአጠቃላይ ትንሣኤ የሚለው ቃል ያለው ትርጉም የሞተ ሰው አካል በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት ሕይወት ማግኘት ማለት ነው።

## 2. ኢየሱስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው

በአብ ቀኝ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ልጅ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው (የሐዋ. 17፥31፤ 1ቆሮ. 15፥47፤ 1ጢሞ. 2፥5)።

5. Norman L. Geisler, The Battle for the Resurrection (Nashville: Thomas Nelson, 1990), ገጽ. 179-181

በሐዋ. 17 ጳውሎስ ስለ ሙታን ትንሣኤ እያስተማረ (ቁጥር 32) ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ ሰው ሆኖ እንዳለ ይናገር ነበር (ቁጥር 31)። በ1ኛ ቆሮ. 15፥47 ጳውሎስ ስለ ሁለት ሰዎች እየተናገረ ነው ያለው። የአንደኛው ሕይወት ሰማያዊ ነው፤ የሌላው ደግሞ ምድራዊ ነው። ይህ የሚያመለክተን አሁን እንኳ ኢየሱስ ሰው ሆኖ እንዳለ ነው እንጂ በአንድ ወቅት ሰው የነበረና አሁን ሰውነቱን የተወ ማለት አይደለም። 1ጢሞ. 2፥5 በዚህ ክፍል ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜም እንኳ ሰው ባይሆን ኖሮ "ሰው" ማለት ባላስፈለገው ነበር። ኢየሱስን አማላጅ እንዲሆን ያደረገው የኛን ደምና ሥጋ መውሰዱ ነበር። ኢየሱስ የኛን ደምና ሥጋ ቀይሮ መንፈስ ሆኖ ካለ አማላጅነቱ እምኑ ላይ ነው?

## 3. ኢየሱስ ራሱ እኔ መንፈስ አይደለሁም ብሎአል

በሉቃ. 24፥39 ኢየሱስ መንፈስ እንዳልሆነ ለማስረገጥ የእጁንና የእግሩን ችንካር በማሳየት እኔው ራሴ ነኝ ብሎአል። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ኢየሱስ ሥጋና ደም አለኝ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ዳሱኝ ያለው የደቀ መዛሙርቱን እምነት ለማገዝ በመነሣቱ እንዲያምኑ ነበር የሚለው ትንተና ፍጹም ከእውነት የወጣ ነው። እንዴት ደቀ መዛሙርቱን እያታለለ እምነታቸውን ያጠናክራል?

## 4. ወንጌላት የኢየሱስ አካል ሕያው እንደሆነ ይናገራሉ

መላእክት የኢየሱስ አካል በመቃብሩ ሥፍራ ያለመገኘቱን ማብሠራቸው ኢየሱስ በአካል መነሣቱን ያሳያል (ማቴ. 28፥6፤ ማር. 16፥6)።

የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል በስቅላቱ ጊዜ በእጆቹ፥ በእግሮቹና በጎኑ የነበሩት ቁስሎች ወይም ጠባሳዎች ነበሩበት (ሉቃ. 24፥39–40፤ ዮሐ. 20፥20፤ 25፥27)።

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ በልቶአል (ሉቃ. 24፥41–43፤ የሐዋ. 1፥4፤ ዮሐ. 21፥12–15)።

## 5. ኢየሱስ ሰብአዊ ሕይወቱን በትንሣኤ መልሶአል

ኢየሱስ አካላዊ ሕይወቱን የሰጠው (ያኖረው) ለዘላለም ሊተወው ሳይሆን በከበረ ሁኔታ ዳግም ሊያስነሣው ነው (ዮሐ. 10፥17–18)። "ነፍሴን ደግሞ እንሣት ዘንድ እኖራለሁና" (ቁጥር 17) የሚለው ገለጻ



የሚያመለክተን ነፍሱን የሚያኖርበት ምክንያት ለማስነሣት ነው። (በዚህ ክፍል "ሒና" የሚለው የግሪክ ቃል ምክንያትን የሚያሳይ ነው)።

የሐዋ. 2፥24–32 "እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና" (ቁጥር 24) ይላል እንጂ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከእንደገና መንፈስ አድርጎ ሠራው አይልም። "ሞት ይይዘው ዘንድ" ካልቻለ የይሖዋ ምስክሮች ለምን ሞቶ ቀረ ይሉናል?

ጴጥሮስ በመዝ. 16፥8–11 ያለውን ቃል ከክርስቶስ ጋር ያያይዘዋል (የሐዋ. 2፥25፤ 29–30) ". . . ደግሞ ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና . . ." (ቁጥር 28–27)። የሞተው የክርስቶስ አካል በሲኦል እንደማይቀር "ተስፋ" ያደርጋል። በዚህ ቦታ "ነፍስ" የሚለው ቃል ሰብአዊ የሆነውን ሕይወቱን የሚያሳይ ነው [እነዚህን ጥቅሶች ይመለከቷል (ማቴ. 20፥28፤ ማር. 10፥45፤ ዮሐ. 10፥17–18) በእነዚህ ክፍሎች ላይ ነፍስ (በግሪኩ ሱቼ) የሚለው ቃል የክርስቶስን ሥጋዊ ሕይወት የሚያሳይ ነው]።

## 6. የሞተው አካል ነው ከሙታን የተነሣው

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሞተውን አካሉን ከሙታን እንደሚያስነሣ በዮሐ. 2፥19–22 ላይ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ቁጥር 19 ላይ "ይህን" የሚለው አመልካች ቃል የሚያሳየው ኢየሱስ "ቤተ መቅደስ" ብሎ ስለሚጠራው አካሉ ነው። ይህም በሚናገርበት ጊዜ የነበረው። ኢየሱስ "አፍርሱት" (ቁጥር 19) ያለውን ነው ያስነሣው። የፈረሰው መንፈሳዊ አካል ወይም ቤተ ክርስቲያንን አይደለም። ነገር ግን አካሉን ነበር እንጂ [የይሖዋ ምስክሮች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች አስነሣለሁ ያለው ቤተ ክርስቲያንን ነው የሚል አቋም አላቸው። ነገር ግን ኢየሱስ አስነሣለሁ ያለው የፈረሰውን፥ በሦስተኛውም ቀን የተነሣውን ነው]።

ኢየሱስ "በሦስት ቀን" ያስነሣው አካሉን ነበር እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አልነበረም። "ቤተ መቅደስ" የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ምድራዊ ሕንፃ ነው።

## 7. በአንደኛ ቆሮንቶስ 15 ጳውሎስ ስለ አካል ትንሣኤ አስተምሮአል

1ኛ ቆር. ምዕራፍ 15 ስለ ክርስቶስም ሆነ ስለ አማኞች ያለውን የአካል ትንሣኤ በስፋት የሚያስተምር ስለሆነ ትኩረት ሰጥተን ልናጠናው ይገባል።

### ሀ. "... ከእናንተ አንዳንዶቹ፦ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ?" (ቁጥር 12)

ጳውሎስ ይህን መልዕክት የጻፈው ከአቴና ትንሽ ኪሎ ሜትር ወረድ ብላ ለምትገኘው ቆሮንቶስ ነው። በዚያ የሞቱ ሰዎች ደግሞ ሕይወት ያገኛሉ የሚለው ትምህርት ተረት ነበር (የሐዋ. 17፥32)። አንድ ግሪካዊ ሰው ወደፊት ሕይወት በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ይቀጥላል የሚለው ትምህርት የሚቀበለው እንጂ የሚስናከልበት ጉዳይ አይደለም፤ ግሪካውያንን የሚያስናክላቸው የአካል ትንሣኤ ወይም በዚሁ አካል ዳግም ሕይወት ያገኛል የሚለው ትምህርት ነው[6]።

### ለ. "...የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም..." (ቁጥር 37)

የዘር ፍሬ ከሚበቅለው ፍሬ እንደሚለይ የትንሣኤ አካል ከሚሞተው አካል የተለየ ነው። ነገር ግን በተዘራው (በሞተው) ዘር እና በበቀለው ዘር መካከል በክፍለ - ህዋስ ወይም በመሠረታዊው ተፈጥሮአቸውም ሆነ በታሪካቸው ልዩነት እንደሌላቸው ሁሉ የትንሣኤ አካል ከሞተው አካል ያለው አንድነት እንደዚሁ ነው።

### ሐ. "የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።" (ቁጥር 42–44)

በክፍሉ ዐራት ጥንድ ነገሮች አብረው ተነጻጽረዋል። በመበስበስ፥ ባለመበስበስ፤ በውርደት፥ በክብር፤ በድካም፥ በኃይል፤ ፍጥረታዊ፥ መንፈሳዊ። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥንዶች ስለሚሞተው አካል

6. F.F. Bruce The Acts of the Apostles. The Greek Text with Introduction and commentary 2d ed. (Grand Rapids: Eerdmans, 1952) ገጽ. 340 (on Acts 17፥32)



የተሰጡት አሉታዊ ገለጻዎች ናቸው። መበስበስ፥ ውርደት፥ ድካም ከመጀመሪያው አዳም የተወረሱ መጥፎ ነገሮች ናቸው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥንዶች ውስጥ ስለ ትንሣኤ አካል የቀረቡት ገለጻዎች የሚጠቁሙት አሉታዊ የሆኑት የውድቀት ውጤቶች እንደሚለወጡ ነው። በክፍሉ ላይ የቀረቡት የጳውሎስ ማስረጃዎች የሐሳብ ፍሰታቸው ወጥነት ያለው ነው። አራተኛው ጥንድ እንደ ሌሎቹ አብረው የተነጻጸሩ ናቸው። ይኸውም ለውድቀት መንስኤ ለሆነው አካልና ከውድቀት ለመነሣት ምክንያት ስለሆነው አካል ነው። "ፍጥረታዊ አካል" የተባለው የኃጢአት አሉታዊ ውጤት የሆነው ነው። በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከምድር አፈር እንዳበጀው፥ ይህንንም አካል "መልካም ነው" እንዳለ እንመለከታለን (ዘፍ. 1፥26–31)።

1ኛ ቆሮ. 2፥14–15 ስለ "መንፈሳዊ ሰው" ይናገራል። "መንፈሳዊ ሰው" ማለት ግን ቁስአዊ አካል የሌለው መንፈስ ብቻ የሆነ ማለት አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ያለ ማለት ነው።

በአጠቃላይ "ፍጥረታዊ አካል" በእግዚአብሔር ቢፈጠርም፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ "መልካም ነው" ቢለውም እንኳ በኃጢአት አማካኝነት ግን ይህ አካል ተበላሽቶአል።

### መ. "እንዲሁ ደግሞ፦ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።" (ቁጥር 45)

በዚህ ክፍል ላይ የተነጻጸሩት ነፍስ (በግሪክ፦ ሱኺ) እና መንፈስ (በግሪክ፦ ኒውማ) መፈታት ያለባቸው ከቁጥር 44 አንጻር ነው። ስለዚህ በቁጥር 44 ላይ ያለው ንጽጽር በሚሞተው አካል [ለኃጢአትና ለውጤቱ ስለባ (ተጠቂ) የሆነው] እና በትንሣኤ አካል [ከኃጢአት ተጽዕኖ ውጪ የሆነው] መካከል ነው በቁጥር 45 ላይም የምናገኘው ንጽጽር ይህንኑ ነው። አዳም በሚፈጠርበት ጊዜ ኃጢአተኛ ስላልነበር የኃጢአትም ጥቃት አልደረሰበትም። ነገር ግን በኃጢአት በመውደቁ ተበላሸ፥ ረከሰ፥ ደከመ፥ ሟች ሆነ።

### ሠ. "የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው።" (ቁጥር 47)

ይህ ክፍል ኢየሱስን ሰው ይለዋል። ለኃጢአት ክፍያ ኢየሱስ ሰበአዊነቱን ትቶአል ከሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ጋር ቀጥታ ይጋጫል።

የትንሣኤ አካል አፈር ብቻ አይደለም ነገር ግን ለሕይወት ብቁ እንዲሆን የተለወጠ ነው (ቁጥር 48)

### ረ. "... ሥጋና ደም የእግዚአብሔር መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።" (ቁጥር 50)

የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር መጥቀስ ይወዳሉ። ነገር ግን ተከታዩ ዐረፍተ ነገር ግልጽ ያደርገዋል። የሚሞተው አካላችን ችግሩ ቁሳዊ አካል መሆኑ ሳይሆን ስለተበላሸ፥ በስባሽ ስለሆነ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ "ሥጋና ደም" የሚለውን አገላለጽ በምድር ብቻ የተወሰነ መሆንን፥ ድካምን የሚገልጽ ስዕላዊ ቋንቋ ነው (ማቴ. 16፥17፤ ገላ. 1፥16፤ ኤፌ. 6፥12፤ ዕብ. 2፥14)።

"የእግዚአብሔርን መንግሥት" ያስመውረሳችን ምክንያት ከሥነ-ምግባራዊ ውድቀት የተነሣ ነው (1ቆሮ. 6፥9–10፤ ገላ. 5፥21)። ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ቁሳዊ አካልን መተው ሳይሆን (1ቆሮ. 15፥50) የተበላሸውን ሁኔታችንን የሚያድስና የሚያስተካክል የመንፈስ ቅዱስ ሰማያዊ ሕይወት ማግኘት ነው (1ጴጥ. 1፥4)።

### ሰ. "... ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋል።" (ቁጥር 52–53)

ጳውሎስ በዚህ ክፍል እያጠናከረ ያለው ትምህርት ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ መለወጥ የግድ እንደሚያስፈልገው ነው። እሱን በማጥፋት መንፈሳዊ በሆነው አካል (ኢቁሳዊ አካል) በመቀየር አለፈላጊ አይደለም። ይህ የተበላሸው፥ ሟች የሆነው ሰብአዊነት የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን መልበስ ያስፈልገዋል።



አሁን ያለን ይህ አካላችን ቀጣይነት ይኖረዋል፤ ነገር ግን የሚበሰብሰው ክፍል ሊለወጥ ይገባዋል።

### ሸ. "... በዚያን ጊዜ፦ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።" (ቁጥር 54)

ትንሣኤ ሞትን ድል የሚያደርገው የሚሞተው በሕይወት ሲታደስ ነው።

### በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ላይ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. አሁን በአብ ቀኝ ተቀምጦ ያለው የእግዚአብሔር ልጅ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ እንዳለ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይናገራሉ (የሐዋ. 17፥31፤ 1ቆሮ. 15፥47፤ 1ጢሞ. 2፥5)። ኢየሱስ አሁን እንኳ ሰው ሆኖ ካለ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ኢየሱስ በመንፈስ ነው የተነሣው ለምን ይላል?
2. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ከተነሣ፥ ጌታ ወደ ሰማይ ካረገ፥ ከ30 ዓመት በኋላ ጳውሎስ ኢየሱስ በአካል ይኖራል ለምን አለ (ቆላ. 2፥9)?
3. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ከተነሣ አካሉ የት ሄደ? (ግምት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ይስጡን)
4. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከተነሣ ለምን ደቀ መዛሙርቱን "እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው" (ሉቃ. 24፥16፤ 31)?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከተነሣ የኤማሁስ መንገደኞች "ተይዞ" የነበረው ዓይናቸው ሲከፈት እንዴት ሊያውቁት ቻሉ (ሉቃ. 24፥61፤ 31)?
6. መላእክት የኢየሱስ አካል በመቃብሩ ሥፍራ ያለመገኘቱን ማብሠራቸው (ማቴ. 26፥6፤ ማር. 16፥6) ኢየሱስ በአካል መነሣቱን እንዴት አያሳይም? [ደብቀውት ነበር በውሸት ተነሥቶአል ያሉት?]
7. የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል በስቅላቱ ጊዜ በእጆቹ፥ በእግሮቹና በጎኑ የነበሩት ቁስሎች ወይም ችንካሮች በመስቀል ላይ የነበረው አካል መነሣቱን እንዴት አያመለክትም (ሉቃ. 24፥39–40፤ ዮሐ. 20፥20፤ 25፤ 27)?

8. ዮሐ. 2፥19–22 "ይህን" የሚለው ቃል የሚያሳየው ኢየሱስ "ቤተ መቅደስ" ብሎ ስለሚጠራው አካሉ አልነበረምን? (አዎ ሊሉ ይገባል) ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው "አፍርሱት" (ቁጥር 19) ያለውን ከሆነ፤ የፈረሰው ኢየሱስ ከሦስት ቀን በኋላ ያስነሣው አካሉን አልነበረምን? እውነቱ ይህ ከሆነ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ነው የተነሣው ለምን ይላል?
9. ዮሐ. 2፥18–22 ኢየሱስ የሥልጣኑን ምልክት አካሉን ማስነሣቱ እንደሆነ ከተናገረ የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ በአካል አልተነሣም ለምን ይሉናል?
10. ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ነው ከሙታን የተነሣው ለሚለው እምነታቸው የይሖዋ ምስክሮች ከቃለ እግዚአብሔር አንድ ጥቅስ ሊጠቅሱልን ይችላሉ?

## ማጠቃለያ

ዛሬ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በስህተት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን በመከተል ላይ ላሉ እውነት ፈላጊ የይሖዋ ምስክሮች የራሱን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ትደግማለች፡– ". . . ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሰሳችሁ እዩ. . ." (ሉቃ. 24፥38–39)።

## 3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ



የይሖዋ ምስክሮች ደኅንነት የሚገኘው በሥራ እንደሆነ ያምናሉ። ደኅንነት በጸጋና ክርስቶስ በማመን ይገኛል ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚሰጡት የአንደር አገልግሎት ብቻ ነው። ደኅንነት ለይሖዋ ምስክሮች፡– ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ በሙሉ መገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ ከመሆን ውጪ የሚታሰብ አይደለም። መሠረታዊ የሆነውን የመጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡት ጽሑፎች እንዲህ ይገልጹታል፡–



- "ደኅንነት ለማግኘት ወደ ይሖዋ ድርጅት [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር] ይምጡ"[1]
- "እግዚአብሔር የግንኙነት ድልድይ አድርጎ ከሚጠቀምበት [የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት] ጋር ግንኙነት ከሌለን የቱንም ያህል መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብ በሕይወት ጎዳና ልናድግ አንችልም"[2]
- "በምድረ ገነት ዘላለማዊ ሕይወት ለማግኘት ያንን ድርጅት [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር] በመለየት የእርሱ አካል ሆኖ እግዚአብሔርን ማገልገል ነው"[3]
- "የዘላለምን ሕይወት ለመሸለም ጠንክረን መሥራት አለብን"[4]
- "አንድ ሰው በሕይወት መጽሐፍት ላይ ስሙ እንዲጻፍለት በሥራው ሊደገፍ ይገባዋል"[5]

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች በማንበብ የይሖዋ ምስክሮች እንዴት የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊረዱ ይችላሉ? እንደ መጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ጸጋ ማለት ደኅንነትን ለመሥራት የሥራ ዕድል ማግኘት ማለት እንጂ! ጸጋ የደኅንነት ነፃ ስጦታ ነው ማለት በፍጹም አይደለም።

የይሖዋ ምስክሮች ለመዳን የጸጋን አስፈላጊነትና በክርስቶስ የማመንን አንገብጋቢነት ይናገራሉ። ደኅንነትም "ነፃ ስጦታ" ነው ባዮች ናቸው። ነገር ግን እንደ መጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ጸጋና እምነት በራሳቸው በቂ አይደሉም። ደኅንነትም በእምነት ብቻ የሚገኝ ነፃ ስጦታ አይደለም።

እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች በዚህ ሕይወት ደኅንነት ይኑራቸው አይኑራቸው በፍጹም እርግጠኞች አይደሉም[6]።

አንድ የይሖዋ ምስክር ከኃጢአት ሊርቅና እግዚአብሔርን ፈጽሞ ሊታዘዝ ይገባዋል። በሺው ዓመትም ጊዜ የሚገጥመውን ፈተና ካላለፈ ወደ አለመኖር ደረጃ ይሄዳል። በሺው ዓመት ጊዜ እግዚአብሔርን በታማኝነት ያገለገለ የዘላለም ሕይወት ይሰጠዋል።

1. The watchtower, 15 November 1983, ገጽ. 21 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
2. The watchtower, 1 December 1981, ገጽ. 27 በቅንፍ ያለውም አይጨምርም።
3. The watchtower, 15 February 1983, ገጽ 12-13 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
4. The watchtower, 15 August 1972, ገጽ. 491
5. The watchtower, 1 April 1947, ገጽ. 204
6. Life Everlasting – In Freedom of the sons of God, ገጽ. 398.

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የደኅንነት አስተምህሮ ክርስቲያኖችን በሁለት ጎራ ይከፍላቸዋል። ይኸውም፡- “ቅቡዓን” እና “ታላቁ መንጋ” በማለት ነው። “ቅቡዓን” የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጅ ሆነው ወደ ሰማይ ይሄዳሉ። እነዚህም ሰዎች በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩና ከ1935 ዓ.ም. በፊት ድርጅቱን የተቀላቀሉ ናቸው። የ“ታላቁ መንጋ” አባላት ትንሣኤን ካገኙ በኋላ በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራሉ 1935። ይህ “ታላቅ መንጋ” ሰማይ ከሞላ በኋላ የመጣ ሲሆን [ሰማይ ሞላ የተባለው በ1935 ዓ.ም. ላይ ነው] እስከ አሁን ድረስ በምድር ላይ እየኖሩ ያሉት ናቸው። “ቅቡዓን” ሆነው ዛሬ በምድር ላይ ያሉት “ቅሬታዎች” በመባል ይታወቃሉ። ደኅንነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመንና ተግቶ በመሥራት ነው። እንደመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ደኅንነት የሚገኘው ሕይወትን በመቀየር ለአምላክ መንግሥት ብቁ መሆንን በማረጋገጥ ነው።

አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ [144 ሺ ናቸው የሚባሉት “ቅቡዓን” ናቸው] ብቻ ናቸው ዳግም የተወለዱት። “ቅቡዓን” ዳግሞ የሚወለዱት በሰማይ መንፈስ ሆኖ ለመኖር የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ብቻ እንጂ ለደኅንነት አንገብጋቢ ስለሆነ አይደለም።

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከላይ የተመለከትነውን የደኅንነት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

ክርስቲያኖች በሁለት ጎራ (ቡድን) ይከፈላሉ[7]። በራእ. 7፥2-6 “ቅቡዓን” ወይም 144ሺዎቹ አንደኛው ጎራ ሲሆኑ፤ በራእ. 7፥9-17 ደግሞ “ታላቁ መንጋ” ወይም “በግ” የሚባሉት ያሉበት ሁለተኛው ጎራ ነው[8]። 144ሺዎቹ ከሰማያዊ ተስፋ ጋር መንፈሳዊ እስራኤሎች ናቸው። የሚኖሩትም በጽዮን ተራራ ላይ ነው (ራእ. 14፥1)። ይህም የሰማይ ምሳሌ ነው (ዕብ. 12፥22)። “ቅቡዓን” ከምድር ነው ወደ ሰማይ

7. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፤ ገጽ 120-126
8. “Great Crowd”, in In sight on the scriptures, 1: ገጽ. 995-997



የሚወሰዱት (ራእ. 14፥4)። “ቅቡዓን” ሆኖ በምድር ላይ ወደፊት የሚኖር የለም። 144ሺዎቹ ሁሉ በሥጋ የእስራኤል ወገን መሆን የለባቸውም። አዲሱንም ዝማሬ የሚዘምሩት የእስራኤል ወገን ክርስቲያኖች ብቻ የሚሆኑበት ምንም ምክንያት የለም። ነገር ግን የአሕዛብ ክርስቲያኖችም ጭምር ናቸው። ስለዚህ 144ሺዎቹ መንፈሳዊ እስራኤል ናቸው።

“ታላቁ መንጋ” የሚባሉት እንደ “ቅቡዓን” ሰማያዊውን አካል ሳይሆን ምድርን ተስፋ የሚያደርጉት ናቸው። ታላቁ መንጋ ተስፋ የሚያደርገው በረከት (ራእ. 7፥15-17) ምድርን መውረስ ነው (ራእ. 21፥2-4)። ታላቁ መንጋ “በዙፋኑና በበጉ ፊት” ይቆማሉ (ራእ. 7፥9) ይህ ማለት ግን የታላቁ መንጋ ስፍራ ሰማይ ነው ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ሞገስ የሚያሳይ አገላለጽ ነው። ይህም አገላለጽ ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር ፊት እንደማይቆሙ ለማነጻጸር ነው (ራእ. 6፥15-17)።

ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች እንዳሉ የሚያሳየው ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል[9] (ራእ. 1፥6፤ 5፥10፤ 20፥6) ነው። ነገሥታትና ካህናት የሚሆኑት ሰዎች ከሚመሩትና በእግዚአብሔር ፊት ከሚወከሉት ሰዎች የተለዩ ናቸው። ሉቃ. 12፥32፤ ዮሐ. 10፥16 ክርስቶስ መንግሥቱን የሚሰጠው “ትንሽ መንጋ” አለው፤ ይህም መንጋ ከ“ሌሎች በጎች” የተለየ ነው [“ትንሹ መንጋ” የሚባሉት “ቅቡዓን” ናቸው። “ትልቁ መንጋ”፥ “ሌሎች በጎች” የሚባሉት ከመቶ አርባ አራት ሺው ውጪ ያሉት ናቸው]።

በእምነት ጸድቀናል ነገር ግን ጽድቃችን ጊዜያዊ ነው፤ ዘላቂነት የለውም። “ታላቁ መንጋ” በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራል። የእግዚአብሔርን ጓደኛ ለመሆን ጸድቀአል (ያዕ. 2፥23)። ለ“ታላቁ መንጋ” እንከን አልባ የመሆን ሥልጣን ወይም ደረጃ ተሰጥቶታል። ነገር ግን በሺ ዓመቱ ጊዜ የመፈተኑ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ ያለ፥ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ነው። አብርሃምም ሆነ ከክርስቶስ በፊት ለነበሩ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ተስፋ በማመናቸው በእግዚአብሔር ፊት እንከን አልባ ናችሁ ለመባል መሠረቱ ነበር (ሮሜ 4፥20-22)። “ታላቁ መንጋ”

9. ክነ ከማሁ፥ ገጽ 997። ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፤ ገጽ 165-168።
10. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፤ ገጽ 127-133 250-255
11. “Declare Righteous,” in In sight on the Scriptures, 1: 604-606

ተብለው የተቆጠሩት ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው የክርስቶስ የማዳን ሥራ እግዚአብሔር እነርሱን እንደ "ጻድቃን" እንዲመለከታቸው አድርጎታል (ማቴ. 25፥34-46)። ነገር ግን እምነታቸው ጽድቅ ሆኖ የሚቆጠርላቸው ስመልካም ሥራ ያላቸው ጥረትና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመታዘዛቸው ጋር ተያይዞ ነው (ያዕ. 2፥17-26)። የ"ታላቁ መንጋ" አባላት ጻድቅ መሆናቸው ገና አልተረጋገጠም። ጻድቅ መሆናቸው የሚረጋገጠው እስከ ሺ ዓመት መጨረሻ ድረስ በእምነት ስመታዘዝ የቀጠሉ እንደሆነ ብቻ ነው።

የክርስቲያናዊ ማኅበር አባላት ("ቅቡዓን") የእግዚአብሔር ልጅ ስመሆን ጸድቀዋል (ዮሐ. 1፥12-13) ከኃጢአት ውጪ እንዲሆኑ የተሰጣቸው ጊዜያዊ ሥልጣን በእምነት አስካሉ ጊዜ ድረስ ቋሚ ነው። እንደ "ታላቁ መንጋ" "ቅቡዓንም" ስደኅንነታቸው መልካም ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። "ቅቡዓን" የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ የሆኑት ለጊዜው ነው (ሮሜ 6፥15-16)። ነገር ግን ትክክለኛ ልጆች መሆናቸው የሚረጋገጠው በትንሣኤ መንፈስ ሆነው ከሙታን ሲነሡ ነው።

መልካም ሥራ ደኅንነትን ያመጣል። መልካም ሥራ የሚባሉት ከዚህ የሚከተሉት አራቱ ነጥቦች ናቸው[12]፦

1. በመጠበቂያ ግንብ መሪነት መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የእግዚአብሔርንና የክርስቶስን ነገር "ማወቅ" (ዮሐ. 17፥3)
2. ስእግዚአብሔር ሕግጋት መታዘዝ [እነዚህ ሕግጋት በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በኩል የተደነገጉት ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ደምን መቀበልም ሆነ መስጠት (blood transfusions)፥ የልደት በዓላትን፥ የዓመት በዓላትን ወዘተ ማክበርን ፈጽሞ የሚከስክሰው ነው]።
3. የእግዚአብሔር ድልድይ (channel) ከሆነው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጋር ኅብረት ማድረግ።
4. በይሖዋ ምስክሮች የስብከት ሥራ ላይ ተካፋይ መሆን።

"ዳግም ልደት" ለ144ሺዎቹ ብቻ ነው[13]። "ቅቡዓን" ስእግዚአብሔር መንፈስ የሚሆኑ ልጆች ናቸው። መንፈስ እንደመሆናቸውም በስማይ ሆነው ምድራዊ የእግዚአብሔር መንግሥትን ያስተዳድራሉ (1ቆሮ. 15፥50)። ዳግም ልደት ስእነርሱ ያስፈለገበትም ዓላማ በስማይ

12. The watchtower, February 15, 1983, ገጽ. 12-13.
13. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፣ ገጽ 75-78



ስስሚጠብቃቸው ሕይወት ወደ መንፈስነት ስስሚለውጣቸው ነው (ዮሐ. 3፥4-5፤ ሮሜ 6፥16-17፤ 1ጴጥ. 1፥3-4)። "ቅቡዓን" ዳግም መወስዳቸው የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል። ይህም መንፈስ ሰማያዊ ጥሪያቸውን ይገልጽላቸዋል እንዲሁም "ልባምና ታማኝ ባሪያ" የመሆን ኀላፊነታቸውን እንዲወጡ ያበረታቸዋል።

ዳግም ልደት ክርስቶስን ላመኑ ሰዎች ሁሉ አይደለም። ነገር ግን በክርስቶስ ዘመን እስራኤላዊ ሆነው ክርስቶስን የተቀበሉት ዳግም ተወልደዋል።



## የይሖዋ ምስክሮች የደኅንነት ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



ሁስት ዓይነት ክርስቲያኖች አሉ የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ሙሉ ስሙሉ የተመሠረተው ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በጣም አከራካሪና ስመረዳትም እጅግ አስቸጋሪ በሆነው በራእይ መጽሐፍ ነው (ራእ. 7 እና 14፥1-5) ። 144ሺዎቹና በራእ. 7 ላይ ያለው ታላቁ መንጋ የተለያዩ ክፍሎች ናቸው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ፍጹም ትክክል አይደለም። እንደ ድርጅቱ ትምህርት 144ሺዎቹ በቀጥታ ተተርጉሞ እስራኤላዊ ክርስቲያኖች ናቸው ሲባል፤ ታላቁ መንጋ ደግሞ ከተለያየ ነገድ ያመኑ ክርስቲያኖች ናቸው። ነገር ግን የክፍሉ መጻሕፍ ቅዱሳዊ ትምህርት 144ሺዎቹም ሆኑ ታላቁ መንጋ ሕዝበ ክርስቲያንን የሚወክሉ ናቸው። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። 144ሺዎቹ በምድር ላይ በሚመጣው ቁጣ በእግዚአብሔር ማኅተም የተጠበቁ (ራእ. 7፥1-6) እንዲሁም ቁጣው እስከ ሚያልፍ በድል የቆሙ ናቸው (ራእ. 14፥1-5)። ታላቁም መንጋ የሚወክለው ቤተ ክርስቲያንን ነው፤ ይኸውም ከታላቁ መከራ በኋላ ባለማቋረጥ ስእግዚአብሔር የሚሰጠውን አምልኮ በማሳየት (ራእ. 7፥9-17)።

አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ ያሉት በስማይ ሳይሆን በምድር ነው (ራእ. 7፥1-6)። አራቱ መላእክት ምድርንና ባሕርን ከመጉዳታቸው በፊት በእግዚአብሔር እንዲጠበቁ የታተሙ ናቸው። በተጨማሪም

144ሺው በጽዮን ተራራ ላይ ቆመው ሳለ (ራእ. 14፥1) በላይ በሰማይ መዘምራን ይዘምሩ ነበር (ቁ. 2–3)። በእርግጥ የጽዮን ተራራ ሰማያዊዋን ከተማ ሊወክል ይችላል (ዕብ. 12፥22)፤ ነገር ግን ሰማያዊዋ ከተማ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዳለች (ራእ. 21፥2)። በመንፈሳዊው አነጋገር ክርስቲያኖች አሁን በምድር እያሉ ወደ ጽዮን ተራራ መጥተዋል (ዕብ. 12፥22)። ይህ ለ144ሺዎቹ ሰማያዊውን ዝማሬ ለመማር ከሰው ዘር ውስጥ ብቸኞቹ ናቸው (ቁ. 3)። "ከምድርም ከተዋጁት" (ቁ. 3) የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው 144ሺዎቹን ነው። ነገር ግን 144ሺዎቹ በሰማይ ለዘላለም ይኖራሉ ማለት ግን አይደለም። ነገር ግን በምድር ላይ ሊመጣ ካለው ቁጣ እንዲያመልጡ ወደ ሰማይ ከተወሰዱ በኋላ ተመልሰው ወደ ምድር መመለሳቸውን ነው የሚያሳየው። አዲሲቷ እየሩሳሌም ብለን በምንጠራት "አዲስ" ምድር ላይ ይኖራሉ (ራእ. 21፥1–2)።

የተባረከው ተስፋ ለታላቁ መንጋ ነው የሚለው የይሖዋ ምስክሮች አባባል ትክክል ነው (ራእ. 7፥15–17)። በአዲሲቱ ምድርም ለመኖር ተስፋ ከተሰጣቸውም ጋር አንድ ናቸው (ራእ. 21፥2–4)። የበረከታቸውም መሠረት እግዚአብሔር በእነርሱ መካከል መኖሩ ነው። እነርሱም በእግዚአብሔር ና በበጉ ዙፋን ፊት ይቆማሉ (ራእ. 7፥9)። ምክንያቱም ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ የእግዚአብሔር ዙፋን በአዲሲቱ ምድር ስለሆነ (ራእ. 21፥3)።

የይሖዋ ምስክሮች ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች አሉ ለሚለው ትምህርታቸው ማስደገፊያ ከላይ ካየናቸው ጥቅሶች በተጨማሪ የሚጠቅሱት (ራእ. 1፥6፤ 5፥10፤ 20፥6) ነው። ነገር ግን በክፍሉ መንግሥትና ካህናት የሚሉት ቃላት አሁን በከፊል ወደፊት በሙላት ቅዱሳን በእግዚአብሔር በረከት የሚደሰቱትን ደስታ የሚያሳይ አገላለጽ ነው። እንደ "መንግሥት" ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የልጅነት ግንኙነት ያመለክታል (ራእ. 21፥7)። እንዲሁም በአዲሲቷ ምድር ላይ የሚያሳዩትን ፍትሐዊ አገዛዝ ያሳያል (ዘፍ. 1፥26–30፤ መዝ. 8፥3–8)። "ካህናት" መሆናቸውም ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው።

ሉቃ. 12፥32፤ ዮሐ. 10፥16 ክርስቶስ መንግሥትን እሰጣችኋለው ካለው "ትንሹ" መንጋ "ከሌሎች በጎች" ጋር ፍጹም ልዩነት የለውም። ከላይ ያየናቸው የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት ዐውዳቸው አብሮ የሚሄድ አይደለም። እነዚህም ክፍሎች "ታላቁ መንጋ" እና "ታናሹ መንጋ" ልዩነት አላቸው፥ ትንሹ መንጋ ትልቁን መንጋ ይመራል አይልም።



"ትንሹ መንጋ" የተባለበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ይህ ኅብረት የክርስቶስ ትንሽ ኅብረት ስለሆነ ነው። ሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን መንግሥት እስከፈለጉ ድረስ (ሉቃ. 12፥32) ለሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰጣቸዋል (ቁ. 32)። የሚፈልግም ሁሉ ያገኛልና (ማቴ. 7፥7–8)።

ዮሐ. 10፥16 ከመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ጋር ይጋጫል። ይኸውም ወደፊት በጎች ሁሉ "አንድ መንጋ" ስለሚሆኑ ነው። "ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ" የዚህ አባባል ታሪካዊ ዳራ የሚጠቁመን ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች አሕዛብ ማስትም ከእስራኤል ነገድ ውጪ የነበሩት በክርስቶስ "አንድ መንጋ" መሆናቸውን የሚያስተምር ነው።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ስለ ቅቡዓን የሚያስተምረው ትምህርት ያለው ችግር ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚደርሱትን ምድር ናፋቂ የይሖዋ ምስክሮች ያስመረ ሊያስቀራቸው ነው። እንደ ድርጅቱ ትምህርት ወደ "ቅቡዓን" የመቀላቀል ቁጥር (144ሺ) የሞላው በ1935 ዓ.ም. ነው። አሁን በምድር ላይ ያሉት የዚህ የ"ቅቡዓን" ክፍል አባላት [በሕይወት ያሉ "ቅቡዓን" "ቅሬታዎች" በመባል ይታወቃሉ] ቁጥር ከ8ሺ የሚያንስ ሲሆን ዕድሜያቸውም ከ70 ዓመት በላይ ነው። በቅርቡ እነዚህ "የቅቡዓን" "ቅሬታዎች" ሞተው ያልቃሉ፤ ድርጅቱም ያለመሪ ይቀራል።

ደኅንነት እምነትን ብቻ ሳይሆን ሥራንም ይጨምራል የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር የሚጋጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እምነት አስፈላጊ ነው ያለው ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት ስለማይቻል ነው (ዕብ. 11፥6)። እውነተኛ እምነት ደግሞ መልካምን ሥራ ፍሬው ያደረገ ነው (ያዕ. 2፥14–26)። እግዚአብሔር ደኅንነትን ያዘጋጀው ለሚያምኑ ነው እንጂ "እምነታቸውን በተግባር ላዋሉ" አይደለም። "እምነትን በተግባር ማዋል" የሚለው ቃል "ፒስቲኦ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። የቃሉም ትርጉም በአንድ ሰው ወይም ነገር መመካት ወይም ማመን ማለት ነው (ለምሳሌ፡– ዮሐ. 3፥16 18)። ትክክለኛ እምነት በሥራውና በፍሬው ይታወቃል፤ ስለዚህ እምነት እንጂ "እምነትን በተግባር በማዋል" አይደለም ለደኅንነት ቅድመ ሁኔታ (ለምሳሌ፡– ዮሐ. 3፥16, 18፤ የሐዋ. 16፥31፤ ሮሜ 1፥16–17፤ 3፥21–28፤ 2ተሰ. 1፥8–10)። መልካም ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ለደኅንነት ቅድመ ሁኔታ አይደለም። የመልካም ሥራ መጓደል ክርስቲያን

ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር እንዳያሳይ ያደርገዋል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ አጠራር ሥጋዊ ክርስቲያን ያስብለዋል (1ቆሮ. 3፥1-4)። ነገር ግን እምነት ብቻ የደኅንነት ዋስትና ነው (ቲቶ 1፥18፤ 1ጴጥ. 1፥5-10፤ 1ዮሐ. 2፥3-4፤ 3፥9-10, 14-15፤ 5፥2-3)።

በእምነት የጸደቅነው ለጊዜው ሳይሆን ለዘለቄታው (ለዘላለም) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ጓደኛ ለመሆን በጸደቁት (ያዕ. 2፥23) በ"ታላቁ መንጋ" እና የእግዚአብሔር ልጅ (ዮሐ. 1፥12-13) ለመሆን በጸደቁት "ቅቡዓን" መካከል ምንም ልዩነት የለም። ሁሉም በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ሮሜ 8፥13-14)። መጽሐፍ ቅዱስ ለሁለት ነገር መጽደቅንም ሆነ [ግምሹ፡ ስልጅነት፥ ግማሹ ጓደኛ ስመሆን] ሁለት ዓይነት ጽድቅ አለ አይልም።

እግዚአብሔር አማኞችን ጸድቀዋል ያለው ለጊዜው ወይም ወደፊት የሚጠብቃቸውን ፈተና የሚያልፋትን አይደለም። ነገር ግን ለአንዴና ለዘላለም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የጸደቅነው ላሁኑ ጊዜ ብቻ ነው፥ እንዲሁም ሺ ዓመት የፈተና ጊዜ ነው አይልም (ዕብ. 9፥27)። አብርሃምና ሌሎች ቅዱሳን ደኅንነታቸው የተረጋገጠው ወደፊት እምነታቸው ስለሚፈተን አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በማመናቸው ብቻ ነበር። አሁንም ሰው መንግሥተ ሰማይን የሚያገኘው ልክ እንደ እነርሱ ነው (ማቴ. 8፥11፤ ሉቃ. 13፥28፤ ገላ. 3፥9)። በዚህ መልኩ የጸደቀው የአብርሃም እምነት ፍጹም ነበር (ያዕ. 2፥22)። ኖኅ "በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ" (ዕብ. 11፥7)። ሁሉም ክርስቲያኖች በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት በማመናቸው ብቻ ጽድቃቸውን አውጀዋል፤ ደኅንነታቸውም የተጠበቀ ነው።

ደኅንነት የተከናወነ እውነት ነው (ሮሜ 5፥1-9) በዚህም መሠረት ነው መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ ከቁጣው እንድናለን (ሮሜ 5፥9) የሚለው። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጠን ነፃ ስጦታ መጽደቅ (ሮሜ 3፥22-24፤ 5፥15-16) እንዲሁም የዘላለም ሕይወት (ሮሜ 6፥23) ነው። ሁለቱም እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው (ሮሜ 5፥17-18)። የጸደቁም ጻድቃን ናቸው የሚከብሩት (ሮሜ 8፥20)። አማኞች ወደፊት የመክበራቸው ጉዳይ የተረጋገጠው በተከናወነው መሠረት ላይ [ይኸውም፡- በመጽደቃቸው] ነው።

የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ መሆናችን (ሮሜ 8፥15-16) ወደፊት በፈተና የሚገኝ ሳይሆን የአሁን ጊዜ እውነታ ነው። ሮሜ 8፥23 የማደጎ ልጅ መሆናችን የወደፊት ጊዜን የሚያሳይ ነው። ነገር ግን ይህ ማለት



አሁን የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ አልሆንም ማለት ሳይሆን የአሁኑ ልጅነታችን የሚገለጠው ወደፊት ነው ማለት ብቻ ነው (ቁ. 18-119፤ 1ዮሐ. 3፥1-2)። የማደጎ ልጅነታችንንም መገለጥ እየተጠባበቅን እንጂ ለማደጎ ልጅነታችን እየሠራን አይደለም (ቁ. 23-24)።

መልካም ሥራ ለደኅንነታችን ቅድመ ሁኔታ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት ትምህርቶች የሚቀዱበት፥ ደኅንነትም ሆነ መልካም ሥራ የሚገነቡበት፥ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል ነው (2ጢሞ. 3፥15-17)። የዘላለም ሕይወት የሚገኘው "ዕውቀትን በመገብየት" ሳይሆን እግዚአብሔርንና ክርስቶስ በ"ማወቅ" ነው (ዮሐ. 17፥3)። ከአብና ከወልድም ጋር ግንኙነት የሚመሠረተው በእምነት ነው። ለደኅንነት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎችን ማንበብ አለብህ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ይጋጫል። ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ ከንቱ ያደርጋል (ሮሜ 3፥21-26)።

እውነተኛ ክርስቲያን ባሕርይውን፥ ምግባሩንም ሆነ አስተሳሰቡን በእግዚአብሔር ቃል መቅረፅ አለበት። ነገር ግን መልካም ሥነ-ምግባር የደኅንነት መሠረት ሳይሆን የደኅንነት ፍሬ ነው። ዛሬ በመጠበቂያ ግንብ በኩል እየተላለፉ ያሉት ሕግጋት [ለምሳሌ፡- ደም መለጠትና ደም መቀበል [blood transfusion]፥ የልደት በዓላት፥ የሕዝብ በዓላት ወዘተ] በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠ ትምህርት አይደለም። እነዚህም ነገሮች የደኅንነትም ሆነ የቅድስና መሠረት አይደሉም።

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለል ወይም ከድርጅቱ ጋር መተባበር ለደኅንነት መሠረት ነው አይልም። እውነተኛ ክርስቲያኖች መሰሎቻቸውን መውደድ፥ ከእነርሱም ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለባቸው ያስተምራል (1ዮሐ. 3፥14፤ 4፥20፤ 5፥1)።

ደኅንነት ከእምነት በስተቀር በምንም ነገር ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ በስብከትም ሆነ በማስተማር ሥራ ላይ ተካፋይ መሆን ለደኅንነት አንገብጋቢ ጉዳይ ተደርጎ የሚሠራጨው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጭ ነው። ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ለወንጌል ሥራ ማሰማራቱም ሆነ (ማቴ. 10፥5-42፤ ሉቃ. 9፥1-8) 72ቱን መላኩ (ሉቃ. 10፥1-16) ለኛ እንደ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ክርስቲያናዊ ሕግ ልናደርገው በፍጹም አንችልም።

ክርስቲያኖችን ሰማይ ወራሽ እና ምድር ወራሽ ብሎ ለሁለት መከፈል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እስካልሆነ ድረስ የመጠበቂያ ግንብ ስለ ዳግም ልደት የሚሰጠው ትምህርት ትክክል ሊሆን አይችልም። ክርስቲያኖች መንፈስ ሳይሆን የከበሩ ሰዎች ነው የሚሆኑት (1ቆሮ. 15፥47-57)። የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዳግም ልደት አንድ ሰውን መንፈስ ወደ መሆን ሕይወት የሚያሸጋግረው ነው አይልም (ለምሳሌ ዐ፥3-5፤ ሮሜ 8፥16-17፤ 1ጴጥ. 1፥3-4)። ስለዚህ "ዳግም ልደት" እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት ለጥቂት ሰዎች ብቻ የሚሆን፥ ጥቂት ክርስቲያኖችን ሰማያዊ ጥሪ እንዳላቸው የሚጠቁም፥ ወይም በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ መሪና አለቃ እንዲሆኑ ኃይል የሚሰጥ አይደለም።

ዮሐ. 1፥12-13 "ለተቀበሉት" የሚለው ግሥ ኀላፊ ጊዜን ቢያሳይም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ዳግም አይወለዱም ማለት አይደለም። የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ብዙ ሰዎች ከእኛ መካከል ዳግም ልደትን አግኝተዋል ይላሉ። በሐዋርያው ዮሐንስ የቃል አጠቃቀም መሠረት ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ። እነርሱም፦ የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች ናቸው (1ዮሐ. 3፥10)። ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ካለ (ዮሐ. 1፥13) እንዲሁም ከእግዚአብሔር ያልተወለዱ የሰይጣን ልጆች ከሆኑ፤ አማኞች ሁሉ ዳግም ተወልደዋል ማለት ነው።

### መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት ምን ይላል?



ሁሉም ክርስቲያኖች እኩል የሆነ ሥልጣን አሁንም ሆነ ወደፊት አላቸው። ሁሉም ክርስቲያኖች በአዲሲቱ ምድር ይኖራሉ (ራእ. 21፥1-4)። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ምድር ከወረደች የቅዱሳን መኖሪያ ምድር ነው ማለት ነው። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መኖሪያ ምድር ነው ማለት ነው። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መኖሪያ ተምሳሌታዊ (ሥዕላዊ) ገለጻ ነው። ይኸውም ሕይወት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ፤ ወደፊት የከበረም አዲስ ሕይወት በምድር እንደሚሆን ነው። ዮሐንስ በመቀጠል እንዲህ ይላል፦ "እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል" (ቁ. 3)። ከፍሉ ጥቂት የተመረጡ ሰዎች



ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ይሄዳሉ አይልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ ከሰዎች ጋር ለመኖር ይመጣል፥ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ነው የሚለው። አሁን ክርስቲያኖች ወደ ሰማይ የሚሄዱት የትንሣኤን ቀን ለመጠበቅ ነው። ነገር ግን እኛ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሳይሆን የምንሄደው መንግሥተ ሰማይ ወደ እኛ ትመጣለች።

ራእ. 5፥10 ክርስቲያኖች "በምድርም ላይ ይነግሣሉ" የሚለው ዐረፍተ ነገር በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] "ከምድርም በላይ ይነግሣሉ" [over the earth] ይለዋል። ነገር ግን ይህ ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ተቀባይነት የለውም። በአዲስ ኪዳን ግሪክ "ኢፒ" የሚለው የግሪክ ቃል 63 ጊዜ "ምድር" ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ ተጠቅሶአል። ነገር ግን አንድም ቦታ ላይ ከምድር በላይ ተብሎ አልተተረጎመም። ቃሉ በራእ. 5፥10 13 ላይ የተተረጎመው በዚህ መልኩ ነው።

ክርስቲያኖች ሁሉ ትንሣኤ አግኝተው ዘላለማዊ ሕይወትን በአዲሲቱ ምድር ላይ ለዘላለም መኖር ከመጀመራቸው በፊት በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ይቆያሉ። በራእ. 7፥9-17 ላይ ያለው "ብዙ ሕዝብ" እና በሰማይ ያለው ብዙ ሕዝብ መካከል ብዙ ትይዩ እውነታዎች አሉአቸው። ይኸውም፦ በሁለቱም ክፍሎች ላይ "ብዙ ሕዝብ" የሚለው ቃል አለ (ራእ. 7፥9፤ 19፥1, 6)። በእነዚህም ክፍሎች ላይ ብቻ ነው "ብዙ ሕዝብ" የሚለው አገላለጽ በራእይ መጽሐፍ ላይ ያለው። በሁለቱም ክፍል ላይ ያሉት "ብዙ ሕዝብ" "በታላቅ ድምፅ" ይጮኻሉ (ራእ. 7፥10፤ 19፥1) የጩኸታቸውም አጀማመር አንድ ዓይነት ነው "በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው" (7፥10)፥ "ማዳንና ክብር፥ ኃይልም የአምላካችን ነው" (19፥1)። በእነዚህም ሁለት ክፍሎች ላይ ብቻ ነው "ማዳን የአምላካችን ነው" የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚገኘው። ከዚህም በኋላ ሽማግሌዎቹና አራቱ ፍጥረታት "ወድቀው" ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ፤ የመጀመሪያ ቃላቸውም "አሜን" (7፥11-12፤ 19፥4) የሚለው ነው።

ሉቃ. 23፥43 እንደ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ንስሐ የገባው ወንበዴ ለሰማያዊ ሕይወት ብቁ አይደለም። ምክንያቱም የክርስቲያናዊ ጉባዔ ተጠማቂ አባል ስላልሆነ። ነገር ግን ኢየሱስ ከእርሱ ጋር *አሁን በገነት* እንደሚሆን ቃል ገብቶለታል። ይህ የሚያሳየን አማኝ ሁሉ በሚሞትበት ጊዜ ነፍሱ ወይም መንፈሱ ንቁ ስለሆነ ከጌታ ጋር ለመሆን ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ነው።

ሁሉም ክርስቲያኖች የዘላለምን ሕይወት እኩል ይወርሳሉ። (ማቴ. 5፥3–12) የተራራው ለብከት የሚናገረው ስለ አንድ ሕዝብ እንጂ ስለተለያዩ ሁለት ክፍሎች አይደለም [የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት "ብፁዓን" ናቸው ምድርን የሚወርሱት]። ኤፌ. 4፥4 ክርስቲያን ሁሉ አንድ ተስፋ ካለው መጠበቅ ያለበት ተመሳሳይ ተስፋ ነው።

ጳውሎስ እንደሚለው ሁሉም ክርስቲያኖች "የክርስቶስ አካል" ናቸው (ኤፌ. 4፥3–4)። ክርስቲያኖች ሁሉ "አንድ አካል" ከሆኑ የዚህ አካል፥ ክፍል ያልሆነ ክርስቲያን አይደለም ማለት ነው። 1ቆሮ. 12፥12–27 ላይ ጳውሎስ የአንድ አካል ብልቶች አንዱ ከሌላው እንደሚሻል ወይም የበለጠ እንደሆነ አድርጎ ራሱን መቁጠር እንደሌለበት ያስተምራል [እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት አብዛኛው የይሖዋ ምስክር ("ታላቁ መንጋ") ጭራሹኑ የዚህ አካል ክፍል አይደለም]። ሮሜ 12፥4–8 ሌሎችን የሚያገለግሉ፥ የሚያበረታቱ፥ ምሕረትን የሚያሳዩ ወዘተ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል እንደሆኑ ሁሉ የሚያስተምሩ፥ የሚመሩና የሚተነቢዩም የክርስቶስ አካል ናቸው።

በጸጋ በእምነት በኩል የተገኘ ደኅንነት መልካም የሥራ ፍሬ ያፈራል። በእምነት ብቻ የዳንን ሰዎች ብንሆንም እንኳ የሚያድን እምነት መልካምን ሥራ ፍሬው ያደረገ ስለሆነ አማኝ የመንፈስ ፍሬ የሆነው መልካም ሥራ ይታይበታል። እምነት ብቻ ነው ደኅንነት የሚያገኙትንና የማያገኙትን የሚለየው። ለዚህም ነው ቃለ እግዚአብሔር የእምነትን አንገብጋቢነት በሰፋት የሚያስተምረው (ለምሳሌ፡– ዘፍ. 15፥6፤ ዕብ. 2፥4፤ ዮሐ. 3፥14–18፤ 20፥30–31፤ የሐዋ. 16፥31፤ ሮሜ 1፥16–17፤ 3፥22–28፤ 4፥3–5፤ 5፥1–2፤ 10፥9–11፤ ኤፌ. 2፥8፤ ቲቶ 3፥8፤ ዕብ. 4፥2–3፤ 1ጴጥ. 1፥5፤ 1ዮሐ. 3፥23–24፤ 5፥10, 13)።

እውነተኛ እምነት ታዛዥነትን የሚያፈራ፥ መልካም ሥራን የሚሠራ፥ ፍቅርን የሚያሳይ ነው (ሮሜ 1፥15፤ 16፥25–26፤ ገላ. 5፥6፤ ያዕ. 2፥14–26)። ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተገዥ ያልሆኑ ሰዎች በትክክል ያላመኑ ናቸው፤ በትክክል ያላመኑም ደኅንነት የላቸውም (1ቆሮ. 6፥9–11፤ ገላ. 5፥19–21፤ ኤፌ. 5፥5–6፤ 1ዮሐ. 1፥6፤ 2፥3–6, 9–11፤ 3፥6–15፤ ራእ. 21፥8)።

ሐዋርያት ክርስቲያን ኃጢአትን መሥራት ማቆም እንደሚገባው፥ ቅድስናን ማጎልበት እንዳለበት ማስተማራቸው እውነተኛ ክርስቲያን ከኃጢአት ጋር ዕለት በዕለት እንደሚታገል፤ ታግሎም ወደ ብስለትና



ወደ ግብረገባዊ እድገት እንደሚመጣ ያሳያል። ክርስቲያን ከኃጢአቱ ጋር መታገሉ ደኅንነቱንም ሆነ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት በጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ ሊያደርግ አይገባውም (ገላ. 5፥16–26፤ ኤፌ. 4፥25–32፤ 1ተሰ. 4፥1፤ ዮሐ. 3፥17–18)።

አንድ ኃጢአት ብቻ ሰዎችን ከዘላለም ሕይወት ያጎድላቸዋል። ይኸውም፦ እውነትን እያወቁ ለማያምኑ፥ በክርስቶስም የሚያምነውን ሰው ከክርስቶስ የሚርቁ ናቸው (ዕብ. 2፥1–3፤ 6፥4–6፤ 10፥26–29፤ 2ጴጥ. 2፥20–22፤ 1ዮሐ. 5፥16)።

ደኅንነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ እኛ ልንሠራው የምንችለው ነገር ቢኖር በእምነት መቀበል ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያለን ትክክለኛ አቋም፥ እምነታችን፥ በቅድስና ማደጋችን፥ እስከ መጨረሻው በእምነት ጸንተን መቆማችን በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል ነው (ዮሐ. 3፥16–17፤ የሐዋ. 18፥27፤ 20፥24፤ ሮሜ 3፥23–24፤ 5፥15–21፤ ኤፌ. 1፥18–19፤ 2፥4–10፤ ፊል. 1፥6፤ ቲቶ 3፥7፤ ዕብ. 4፥16፤ 1ጴጥ. 1፥5) ። ጸጋን ለማግኘት የምንሠራ ከሆነ ጸጋ ምኑን ጸጋ ሆነ? [ጸጋ ማለት የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ማለት ነው (ሮሜ 4፥2–4፤ 11፥6፤ ገላ. 2፥21)]።

ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ዮሐ. 3፥3–5)። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ማለት በሚመጣው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ላይ መኖር ከበረከቱም ተካፋይ መሆን ማለት ነው (ማቴ. 5፥19–20፤ 7፥21፤ 18፥3፤ 19፥23–25፤ 21፥31፤ ማር. 9፥47፤ 10፥23–26)። ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም ካለ ክርስቲያን ሁሉ ዳግም ሊወለድ ያስፈልገዋል ማለት ነው (ዮሐ. 3፥3–5)።

ሮሜ 8፥14–16 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና (ቁ. 14) ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ መመራት ካለባቸው፥ በመንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ ክርስቲያን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት ነው። የባርነትን መንፈስ ካልተቀበልን የተቀበልነው የልጅነት መንፈስ ነው ማለት ነው (ቁ. 15)። የልጅነት መንፈሱን የተቀበለና እግዚአብሔርን አባ የሚለው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ሁሉም ክርስቲያን እግዚአብሔርን አባት ካለው ለሁሉም ክርስቲያን እግዚአብሔር አባት ነው ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ያ መንፈስ የሚነግረን ከሆነ (ቁ. 16) አንድም የሃይማኖት ድርጅት የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም ሊለን አይችልም።

ገላ. 3፥23–4፥7 አሁን ክርስቶስን የሚያምን ሁሉ ከሞግዚት በታች (ቁ. 23–25) አይደለም። በእምነት በኩል ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን (ቁ. 26)። ከክርስቶስ ጋር የተጠመቀ ወይም እንደ ክርስቲያንነቱ ጥምቀትን የወሰደ ሁሉ ክርስቶስን ለብሶታል (ቁ. 27)። ክርስቶስንም የለበስ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ቁ. 26–27)። ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ለባርነት ከቀንበር ሥር ነበርን። አሁን ክርስቶስ መጥቶአል፤ የእግዚአብሔርም ልጆች እንድንሆን ተዋጅተናል (4፥1–5፥7)። ይህ የሚያመለክተን በክርስቶስ የተዋጀ ሁሉ የእግዚእብሔር ልጅ እንደሆነ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ እግዚአብሔርን አባ እንድንለው ያስተምረናል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ልናውቅ ይገባል (4፥6፤ ሮሜ 8፥15–16)።

1ጴጥ. 1፥3 12–23 ዳግም በመወለዳችን ሕያው ተስፋ አለን (ቁ. 3)። ይህ የሚያመለክተን ሕያው ተስፋ ያለው ሁሉ ዳግም እንደተወለደ ነው። መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት የቻልነው [ለምሳሌ፡– ፍቅር፥ ቅድስና] ዳግም ስለተወለድን ነው (ቁ. 22–23)።

1ዮሐ. 3፥9–10፤ 5፥1–2 18–19 ክርስቶስ ነው ብሎ በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል (5፥1)። በዮሐንስ አነጋገር "ከእግዚአብሔር መወለድ" ማለት የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለት ነው (5፥1፤ 3፥9–10፤ 5፥18–19፤ ዮሐ. 1፥12–13)። ዳግም መወለድ ማለት ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት ነው (ዮሐ. 3፥3–5)። ዳግም ልደት የክርስቲያንን ሕይወት ስለሚቀይር ክርስቲያን ኃጢአትን አያደርግም (1ዮሐ. 3፥9–10፤ 6፥18፤ 2ቆሮ. 5፥17) ይህም ነው ዳግም መወለድ ለክርስቲያን አንገብጋቢ ጉዳይ የሚያደርገው።

## ደኅንነትን አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. እንደ መጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መንፈሳዊ በረከቶች ለቅቡዓን ማለትም ለ144ሺዎቹ ብቻ ነው[14]።
   - ዳግም መወለድ (ዮሐ. 3፥3–8፤ ቲቶ 3፥5፤ 1ጴጥ. 1፥3፤ 1ዮሐ. 5፥1)።
   - የእግዚአብሔር የማደጎ ልጆች መሆን (ዮሐ. 1፥12–13፤ ሮሜ 8፥14–17፤ ገላ. 4፥6–7፤ ኤፌ. 1፥5)።
   - የክርስቶስ ወንድም መሆን (ሮሜ 8፥29፤ ዕብ. 2፥11–17፤ 3፥1)።

14. Robert M. Bowman, "Only for the 144,000" Fact Sheet, Christian Research Institute,



   - የክርስቶስን መልክ መምሰል (ሮሜ 8፥29፤ 2ቆሮ. 3፥18)።
   - ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግ (2ቆሮ. 5፥17፤ ኤፌ. 1፥3)።
   - ከክርስቶስ ጋር መወረስ (ሮሜ 8፥17)።
   - የአዲሱ ኪዳን አባላት መሆን (ሉቃ. 22፥20፤ ዕብ. 12፥20–29)።
   - ከክርስቶስ ሞት ጋር መጠመቅ (ሮሜ 6፥3–8፤ ፊል. 3፥10–11፤ ቆላ. 2፥12, 20፤ 2ጢሞ. 2፥11–12)።
   - የጌታን እራት መውሰድ (ሉቃ. 22፥15–20፤ 1ቆሮ. 11፥20–29)።
   - በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ (1ቆሮ. 12፥13)።
   - የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን (ሮሜ 12፥5፤ 1ቆሮ. 12፥13፤ ኤፌ. 4፥4)።
   - የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አባል መሆን (1ቆሮ. 3፥16፤ ኤፌ. 2፥20–22፤ 1ጴጥ. 2፥5)።
   - የአብርሃም ዘር አባል መሆን (ገላ. 3፥26–29፤ 6፥15–16)።
   - የንጉሥ ካህን መሆን (1ጴጥ. 2፥4–9፤ ራእ. 1፥6፤ 5፥10)።
   - በእምነት መጽደቅ (ሮሜ 3፥22–28፤ 5፥1፤ ቲቶ 3፥7)።
   - መቀደስ (1ቆሮ. 1፥2፤ 6፥11፤ ኤፌ. 1፥4፤ 1ቆሮ. 15፥50፤ 1ጴጥ. 1፥4)።
   - ከክርስቶስ ጋር መምራት (1ቆሮ. 6፥2፤ 2ጢሞ. 2፥12፤ ራእ. 20፥6)።
   - ክርስቶስንና እግዚአብሔርን የማየት ዕድል ማግኘት (ማቴ. 5፥8፤ 1ዮሐ. 3፥2)።

"ሌሎች በጎች" ዳግም ሳይወለዱ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዴት ሊወርሱ ይችላሉ (ዮሐ. 3፥3–8)? በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ከሌሉ በአሮጌው ወይም በሌላ ኪዳን ውስጥ ናቸው ማለት ነው (ሉቃ. 22፥20፤ ዕብ. 12፥20–22)? የጌታን እራት ካልወሰዱ እንዴት የዘላለም ሕይወት ይኖራቸዋል? እንዴት ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ቀን ያስነሣቸዋል (ዮሐ. 6፥52–56)? ከክርስቶስ ሞት ጋር ካልተባበሩስ እንዴት በትንሣኤ ቀን ይነሣሉ (ሮሜ 6፥3–8)? በመንፈስ ቅዱስ ሳይጠመቁ እንዴት የእርሱ ወገን ይሆናሉ (ሮሜ 8፥9፤ 1ቆሮ. 12፥13)? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አባል ካልሆኑስ እንዴት፥ እንዴትስ በዋጋ [በክርስቶስ ደም] የተገዙ ሊሆኑ ይችላሉ (1ቆሮ. 3፥16፤ 8፥19፤ ኤፌ. 2፥20–22፤ 1ጴጥ. 2፥5)?

2. ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን እንደ እረኛ ደቀ መዛሙርቱን እንደ በግ መስሎአቸው ነበር (ለምሳሌ፡- ማቴ. 10፥16)። የእርሱም ስቅላት ደቀ መዛሙርቱን እንደሚበታትናቸው እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር፡- "ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ እረኛውን እመታለሁ የምንጋውም በጎች ይበተናሉ" (ማቴ. 26፥31)። ጌታ በዚህ ስፍራ ደቀ መዛሙርቱን "በግ" ያለው በቀላሉ ስለሚደነግጡ፥ በጣም ጥቂት ስለሆኑ ወዘተ ብቻ ነው። ጌታ በሉቃ. 12፥32 ላይም የሚናገረው ስለነዚሁ ደቀ መዛሙርት ነው። ስለዚህ "ታናሽ መንጋ" በተባለውና "በግ" በተባለው መካከል ልዩነት አለ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር የተቀዳ ነውን?
3. ሉቃ. 12፥22-34 አንድ ዐውደ ንባብ ነው። ክፍሉም "ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፡-" በሚለው ዐረፍተ ነገር በመጀመር እስከ ቁጥር 34 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ያለውን ነገር ይተርካል። ይኸውም ደቀ መዛሙርት በሚባሉት፥ በሚለብሱትና በሌላም ነገር መጨነቅ እንደሌለባቸው፤ ጭንቀት የሚፈይደው ነገር እንደሌለ (ቁ. 25-26)፤ እንደውም መጨነቅ የእምነት ማጣት ችግር መሆኑን (ቁ. 29)። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንደሚያውቅ (ቁ. 30)፤ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንደሚሰጣቸው (ቁ. 32) ነው። ስለዚህ ይህ ዐውደ ንባብ ከራእይ 7 እና 14 ጋር በማያያዝ ስለ 144ሺው ነው የሚናገረው ማለት እንዴት ይቻላል?
4. የ144ሺው ቁጥር በ1935 ዓ.ም. ሞላ የሚለውስ የድርጅቱ ትምህርት ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰደ ነው? [በ1935 ዓ.ም. ስማይ እንደ ሞላ "መገለጥ" አገኘ የሚባለው የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዚዴንት ሮዘርፎርድ ነው። ድርጅቱ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል የሚከተል በምድር ላይ የሚገኝ ብቸኛ ድርጅት እኔ ነኝ እስከ አለ ድረስ ለዚህ "መገለጥ"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባዋል]።
5. እግዚአብሔር ሰማያዊ ዜግነትን ለ144ሺው ብቻ ነው የሰጠው የሚለው ክፍል የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ነው የሚገኘው? [ራእይ 7 እና 14 ላይ ሰማያዊው ዜግነት ለ144ሺው ብቻ ነው አይልም። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች ሰማያዊ ዜግነት ለ144ሺው ብቻ ነው የሚለውን ትምህርት ከየት እንዳመጡት አጥብቀን ልንጠይቃቸው ይገባል]።
6. 1ዮሐ. 5፥1 "ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ በእግዚአብሔር ተወልዶአል" ይላል። በዮሐንስ አነጋገር "ከእግዚአብሔር መውለድ" ማለት "ዳግም መወለድ" ማለት ነው (ዮሐ. 3፥3-5)። በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተወለደ ዳግም ልደት ለ144ሺው ብቻ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከየት የመጣ ነው?



7. በዮሐንስ አነጋገር "ከእግዚአብሔር መውለድ" ማለት "የእግዚአብሔር ልጅ"መሆን ማለት ከሆነ (1ዮሐ. 3፥9-10፤ 5፥1-2 18-19፤ ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥5) ከ144ሺው ውጪ ናቸው የተባሉት፥ ከ6 ሚሊዮን የማያንሱ የይሖዋ ምስክሮች ዳግም መወለድ አያስፈልጋቸውም የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር የተገኘ ነውን?
8. አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብን ጨምሮ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በምድር ነው የሚኖሩት የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት አብርሃም፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን ጨምሮ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በመንግሥተ ሰማይ ነው የሚኖሩት ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል [ለምሳሌ፡- ማቴ. 8፥11 እና ሉቃ. 13፥18] ጋር አይጋጭም?
9. "ቅቡዓን" የሚባሉት የይሖዋ ምስክሮች በሰማይ ይኖራሉ የ"ሌሎች በጎች" ክፍል የሆኑት የይሖዋ ምስክሮች ዳግም በምድር ይኖራሉ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት "አንድ መንጋ" "እረኛውም አንድ" ከሚለው ከዮሐ. 10፥16 ትምህርት ጋር አይቃረንም?
10. "ቅቡዓን" የሚባሉት የይሖዋ ምስክሮች ተስፋቸው ሰማይ ከሆነና "ሌሎች በጎች" የሚባሉት ደግሞ ተስፋቸው ምድር ከሆነ ሁላችንም የተጠራነው ለአንድ ተለፋ ነው የሚለውን የኤፌ. 4፥4 ትምህርት ድርጅቱ እንዴት ይመለከተዋል?
11. በራእይ መጽሐፍ "ፊት" የሚለው ቃል የሚያመለከተው በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ነው። 144ሺው በእግዚአብሔር ዙፋን "ፊት" እንዳሉ (14፥3)፥ መላእክትም በእግዚአብሔር ዙፋን "ፊት" እንዳሉ (7፥11)፥ 24ቱ ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ዙፋን "ፊት" እንዳሉ ሁሉ (5፥8)፥ "እጅግ ብዙ ሕዝብ" የተባሉትም በእግዚአብሔር ዙፋን "ፊት" እንዳሉ (7፥9) ይናገራል። ቃለ እግዚአብሔርን አተርጓጎማችን ወጥነት ያለው ከሆነ "እጅግ ብዙ ሕዝብ" በሰማይ ነው ያለው ወይስ በምድር? ታናሽ መንጋ በሰማይ "እጅግ ብዙ ሕዝብ" በምድር የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት እንዴት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን ይችላል?
"እጅግ ብዙ ሕዝብ" እግዚአብሔርን በመቅደሱ ቀንና ሌሊት የሚያገለግሉት ከሆነና (ራእ. 7፥15) የእግዚአብሔር መቅደስም በሰማይ ከሆነ (ራእ. 11፥19፤ 14፥17) እጅግ ብዙ ሕዝብ የሚባሉት የሚኖሩት በምድር ላይ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከየት የመጣ ነው?
12. "ሌሎች በጎች" ወይም "እጅግ ብዙ ሕዝብ" የሚባሉት የይሖዋ ምስክሮች ለዘላለም የሚኖሩት በምድር ነው፤ ለሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት እንደ ቃለ እግዚአብሔር ማስረጃ የሚወሰደው

ማቴ. 6፥10 ነው። "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" የሚባለው የድርጅቱ መጽሐፍ በገጽ 165 ላይ አምላክ ለምድር ያለው ፈቃድ ሰዎች በምድር እንዲኖሩና እንዲገዙ ለመሆኑ ከዘፍ. 1፥28 እና ከኢሳይያስ 45፥18ን ከማቴ. 6፥9–10 ጋር አያይዞ ያቀርባል። ነገር ግን የማቴ. 8፥10 ዐውደ ንባብ ከዘፍ. 1፥28 እና ከኢሳ. 45፥18 ጋር ምን ያገናኘዋል? [ከፍሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር እንዲሆን ነው እንጂ የሰዎች በምድር የመኖርና የመባዛት ጉዳይ አይደለም። ንጽጽሩ የተካሄደው በሰማይ የሆነው በምድር እንዲሆን ነው። ይኸውም ያለ ኃጢአት የሆነው የእግዚእብሔር አገዛዝ በሰማይ እንደሆነ በምድር እንዲሆን]።

13. ምድር ገነት ትሆናለች ለሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት በይሖዋ ምስክሮች የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ መዝ. 37፥9, 11, 29 ነው። ነገር ግን የምዕራፉ ዐውድ በአጠቃላይ የሚያመለክተን ዘማሪው ኃጢአተኞች ከጠፉ በኋላ ጻድቃን ስለሚኖሩበት የወደፊቷ ምድር እየተናገረ ሳይሆን ስለ ራዙ ዘመን ነው። በዕብራይስጡ መሬት የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለእስራኤ ልጆች የሰጠውን የተስፋይቱን ምድር የሚያሳይ ነበር (ዘሌ. 25፥33 ጀምሮ፤ ሆሴ. 9፥13፤ ዘዳ. 4፥38፤ 11፥13–15፤ 8፥7–9፤ ኤር. 2፥7)። ስለዚህ ምድር የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን የቃል ኪዳን ምድር እንጂ አጠቃላይ ምድርን የሚያመለክት አይደለም። ምድሪቱንም የሚወርሱ ሰዎች (ቁ. 9, 11, 22, 29) ያበድራሉ (ቁ. 21)፥ በመንገዳቸውም የቀና ነው (ቁ. 7)። የክፍሉ ትምህርት ይህ ከሆነ የመጠበቂያ ግንብ ትምህርቱን ለማጽናት እንዲህ ያሉ ጥቅሶችን ለምን ይጠቅሳል?
14. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መኖሪያ እንድትሆን የሰጠው ምድርን ከሆነ (መዝ. 115፥16) "ቅቡዓን" ለምን በሰማይ ይኖራሉ?
15. ጌታን የሚያገለግሉት ጌታ በሚኖርበት ስፍራ የሚኖሩ ከሆነ (ዮሐ. 12፥26) "ሌሎች በጎች" ከኢየሱስ ተለይተው ለዘላለም በምድር ይኖራሉ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከክፍሉ ጋር አይጋጭምን?
16. ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት ካለባቸውና (ሮሜ 8፥14–16) በእግዚአብሔርም መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ (ቁ. 14)፥ የተቀበሉትም የባርነት ሳይሆን የልጅነት መንፈስ ከሆነ (ቁ. 17) ታላቁ መንጋ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለህም፥ እግዚአብሔርንም አባት ብለህ መጥራት አትችልም ለምን ተባለ?



## 3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ

የይሖዋ ምስክሮች የሰው ነፍስ ወይም መንፈስ ቁሳዊ ከሆነው የሰው አካል የተለየ መሆኑን አያምኑም። ሰው ማለት የአካልና የ"እስትንፋስ" ጥምር (ውሁድ) ነው፤ እነዚህም ሁለቱ "ሕያው ነፍስ"ን አስገኙ። ስለዚህ አንድ ሰው በአካል ሞተ ማለት በነፍስ ወይም በመንፈስ መኖር አቆመ ማለት ነው። ሰው ሲሞት በሰማያዊም ሆነ በምድራዊ ሕይወት መኖር ያቆማል።

ለይሖዋ ምስክሮች ኢቁሳዊ የሆነ ነፍስ ወይም መንፈስ የለም። ነፍስ ማለት "ሰውዬው ራሱ ወይም አንድ እንስሳ ያለው ሕይወት ማለት ነው"[1]። መንፈስ የሚባለው ደግሞ የሚያመለክተው "የሕይወታችን[ን] ኃይል ነው"[2]። "ይህ የሕይወት ኃይል በእያንዳንዱ የሰዎችና የእንስሳት የአካል ሴሎች ውስጥ ይገኛል"[3]። ነፍስና መንፈስ አንድ አይደሉም። ነፍስ ማለት "ሕይወት" ማለት ነው። መንፈስ ማለት ደግሞ የመኖርን እውነታ እውን የሚያደርግ ኃይል ወይም ጉልበት ነው። መሞት ማለት በሥጋም ሆነ በነፍስ ወይም በመንፈስ መኖር ማቆም ማለት ነው። በሰው ተፈጥሮ ውስጥ የማይሞት ነፍስም ሆነ መንፈስ የለም። ሙታን በነፍስና በመንፈስ ንቁ ሆነው በሥጋ ስመኖር ትንሣኤን የሚጠብቁበት "የሽግግር ወቅት" የሚባል ነገር የለም።

ኃጢአተኞች ንቁ ሆነው ለዘላለም አይሰቃዩም። ሲኦል ማለት የመቃብር ስፍራ ወይም የኃጢአተኞች ለመጨረሻ ጊዜ ፈጽሞ መጥፋት ነው። ኃጢአተኞች በመከራ አይቀጡም ነገር ግን ፈጽሞ ወደ አለመኖር ደረጃ ይሄዳሉ።

1. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 374
2. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ (1991) ገጽ 79. በቅንፍ ያለውን አይጨምርም፡
3. ዝኒ ከማሁ

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች[4]

የይሖዋ ምስክሮች ሞት፥ ነፍስና ሲኦልን አስመልክቶ ያላቸውን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ለማስደገፍ ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሱአቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

ሞት የሰውን መኖር ያቆማል። ሰዎች ሲሞቱ አፈር ይሆናሉ ወይም ወደ አፈር ይመለሳሉ (ዘፍ. 3፥19)። ሞት ሐሳብን ሁሉ ይገታል (መዝ. 146፥4)። ሙታን ንቁ አይደሉም፤ ምንም አያደርጉም፥ ምንም አያውቁም (መክ. 9፥5 10)። መሞት እንደ ማንቀላፋት ነው (ዮሐ. 11፥11–14)።

ኢቁሳዊ የሆነ ነፍስ ወይም መንፈስ የለም። አዳም ነፍስ አልነበረውም (ዘፍ. 2፥7፤ 1ቆሮ. 15፥45)። በራእይ 16፥3 ላይ እና በሌላ ክፍል እንስሳት "ነፍሳት" ተብለዋል። ይህም የሚያሳየው ነፍስ ኢቁሳዊ እንዳልሆነ ነው። መንፈስ እግዚአብሔር አካልን ሕይወት እንዲኖረው ያደረገበት የሕይወት ጉልበት ነው በሰው ውስጥ ያለ የማይሞት ክፍል አይደለም።

በመክ. 3፥19–21 ላይ እንስሳትና ሰበአውያን አንድ ዓይነትመንፈስ እንዳላቸው ያስተምረናል። ይህ የሚያሳየን "መንፈስ" ኢቁሳዊ የሆነና የማይሞት የሰው ክፍል አይደለም። መክ. 12፥17 መንፈስ የሕይወት ኃይል ነው፤ ግለሰቡም ሲሞት ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል።

መሞት በሥጋ ወይም በነፍስና በመንፈስ መኖር ማቆም ማለት ነው። ከአካላዊ ሞት በኋላ ሰው በምንም መልኩ መኖር አይቀጥልም። መክ. 3፥19–21 ሰዎችም ሆኑ እንስሳት ከሞቱ በኋላ ወደ ተመሳሳይ ስፍራ ነው የሚሄዱት። እንስሳት ከሞቱ በኋላ ነፍሳቸው ንቁ እንዳልሆነ ሁሉ፤ የሰዎችም ንቁ አይደለም። ሕዝ. 18፥4 ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ የምትሞት ከሆነ ነፍስ አይሞትም ማለት አንችልም።

4. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን አስተምህሮ፡– በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ (1991) ገጽ 76–89 እንዲሁም ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 97–101 169–176 374–382 የሚባሉትን መጽሐፍት ይመለከቷል።



ለሰዎች ዘላለማዊ ቅጣት የለም። ከሞት በኋላ ዘላለማዊ የሆነ ነፍስ የለም። ሰዎች ለዘላለም የሚቀጡበት ስፍራ የለም። ኤር. 7፥31 እግዚአብሔር የሰው ልጆች በእሳት እንዲቃጠሉ አላዘዘም። ማቴ. 10፥28 በገሃነብ ያለው የፈረሰ፥ የለው አካልና ነፍስ ብቻ ነው።

ይኸውም መኖር ካቆሙ በኋላ ማለት ነው። የሐዋ. 2፥27 ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ "ሲኦል" እንደ ሄደ ይናገራል። ኢየሱስ ወደ "ሲኦል" ከሄደ ሲኦል የዘላለም የቅጣት ስፍራ አይደለም ማለት ነው። ነገር ግን የመቃብር ስፍራ ሌላ ስም ነው እንጂ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ዮሐ. 4፥8) ፍቅርና ዘላለማዊ ቅጣት አብረው የሚሄዱ ነገሮች አይደሉም። ራእ. 20፥14 "የእሳት ባሕር" ለዳግም ሞት ስዕላዊ አገላለጽ ነው። ይህም የሰዎች የመጨረሻ ወደ አለመኖር ደረጃ መሄድ ነው።



### የይሖዋ ምስክሮች በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ ያላቸው ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



ሞት የሰዎችን መኖር አያቆምም። የሰው ልጆች አፈር ናቸው (ዘፍ. 3፥19) ነገር ግን አፈር ብቻ አይደሉም። ስለዚህ ሲሞቱ አፈር ብቻ አይሆኑም ማለት ነው። መዝ. 146፥4 ሞት አስተሳሰብን ሁሉ አያቆምም። ነገር ግን የሰዎችን ዕቅድና ፍላጎት ይገታል። በመክ. 9፥5 እና 10 ላይ ሰለሞን አሁን የሚታዩትን ነገሮች ሁሉ "ከፀሐይ በታች" ይላቸዋል። ይህም የሰዎች ጥበብ የሆነው ብቻ ነው (መክ. 1፥2, 18)። ሞት ሁሉን ያቆማል የሚለው የመክብብ መጽሐፍ አገላለጽ አሁን ነገሮች እየተገለጹ ባሉበት ሁኔታ ነው እንጂ መሆን ያለባቸውን አይደለም። ዮሐ. 11፥11–14 ሞት ልክ እንደ እንቅልፍ ነው። ነገር ግን እንቅልፍ የሰዎችን መኖር ያቆማል ማለት ግን አይደለም። ሞት ከእንቅልፍ ጋር የተወዳደረው የሞተ ከእንቅልፍ ጋር የተነጻጸረበት ገጽታው የሞተም ሰው ሆነ ያንቀላፋ ሰው ለቁሳዊው ዓለም ንቁ ስላልሆነ ነው። እንቅልፍ ፍጹም ከአለመኖር ጋር ሲነጻጸር እንደማይችል ሁሉ ሞትም ሲነጻጸር አይችልም።

በዘፍ. 2፥7 እና 1ቆሮ. 15፥45 ነፍስ የሚለው ቃል [በዕብራይስጥ፡– ነፌሽ። በግሪክ፡– ሱቺ] በተለያየ በውደ ንባብ ውስጥ የተለያየ ትርጉም

አለው። በዘፍጥረትና በቆሮንቶስ መጻሕፍት ውስጥ "ነፍስ" የሚለው ቃል አዳም ሕያው ነፍስ የሆነ አካል እንደሆነ ቀርቦአል። በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ ነፍስ ሰው አንዳለው ነገር ቀርቦአል (ለምሳሌ፡- መዝ. 35፥9፤ ሉቃ. 1፥46)። በራእይ መጽሐፍ እንስሳትና ሰዎች "ሕያው ነፍስ" ተብለዋል። ነገር ግን ይህ ማለት ሰዎችና እንስሳት አንድ ዓይነት ነፍስ አላቸው ማለት አይደለም። ልብ ይበሉ "ነፍስ" የሚለው ቃል በተለያዩ ዐውደ ንባቦች ውስጥ የተለያየ ትርጉም አለው።

መክ. 3፥19-21። የመክብብ መጽሐፍ የመገለጥ እውነታ ሳይሆን ለሚታየው ወይም "ከፀሐይ በታች" ለሆነው ነገር የሚያወራ መጽሐፍ ነው። በዚህም ዐውደ ንባብ ውስጥ ነው ሰሎሞን "ነገር ሁሉ ከንቱ ነው" የሚለው (፩፥19)።

በአጠቃላይ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ እያለ ያለው የሰው ልጆች የሰው መንፈስ ወደ ላይ እንደሚወጣ የእንስሳትም መንፈስ ከአካላቸው ጋር ወደታች እንደሚወርድ በራሳቸው ሊያውቁት ያለመቻላቸውን ነው (ቁ.21)። ሰሎሞን ይህን እውነት እየካደ ሳይሆን በማየት ብቻ ይህ አውነት እንደማይታወቅ እየገለጸ ነው። ይህ ለማያዊ እውነት ሊታወቅ የሚችለው በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ብቻ ነው። የሰው ዕውቀት ሰዎችም ሆኑ እንስሳት ተመሳሳይ ስፍራ እንደሚሄዱ አድርጎ ይገምታል፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችና የእንስሳት ዕድል ፈንታ የተለያየ መሆኑን አስረግጦ ይናገራል። ሰዎች በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት ይቆማሉ፤ ነገር ግን እንስሳት እንደዚያ አይደሉም።

በሕዝ. 18፥4፥ በዚህ ዐውድ ውስጥ "ነፍስ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ሁለ መና ነው። የክፍሉም ትምህርት ኃጢአትን የሚሠራ ሰው እንደሚሞት ነው። ይኸውም፡- አንድ ሰው በአባቶቹ ኃጢአት ምትክ መሞት ይችላል የሚለውን ሐሳብ ለመቃወም ነው (ቁ. 2-4, 14-20)። እግዚአብሔር እንደሚለው ኃጢአትን የማይሠራ፥ መልካምን የሚያደርግ "በሕይወት ይኖራል"፥ "አይሞትም" (ቁ. 9, 17, 19, 21-22, 28)። በአጠቃላይ የክፍሉ ዐውድ እግዚአብሔር ከእስራኤል የሚጠብቀው ፍትሕ፥ እንዲሁም ይህን ፍትሕ ማጓደል በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ ቅጣት እንደሚያስከትል ነው። ክፍሉ ሰውን ነፍስ ብሎ ይጠራዋል። ይህም ነፍስ ኃጢአት እንዳይሠራ ይመክራል። ኃጢአት ከሠራ ግን በኃጢአቱ ይሞታል። ነገር ግን ክፍሉ ለሰው ኢቁሳዊ የሆነ፥ ከሞት በኋላም መኖር የሚችል አካል የለውም አይልም።



ኤር. 7፥31 ስለ ዘላለም ቅጣት አይናገርም። እግዚአብሔር የሰው መሥዋዕት ስለማይፈልግ ልጆቻችንን መሠዋት እንደ ሌለብን ነው የሚያስተምረው። ኃጢአተኞች የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም (ለምሳሌ፡- ዮሐ. 8፥44) ነገር ግን የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጫ ዕቃዎች ናቸው (ሮሜ 9፥22)።

በማቴ. 10፥28 እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን "ያጠፋል" ማለት አካልና ነፍስ ወደ አለመኖር ደረጃ ይሄዳሉ ማለት አይደለም። በዚህ ክፍል ላይ "ያጠፋል" የሚለው ቃል |በግሪኩ፡- አፖሎሚ| የሚያሳየው ፈጽሞ መጥፋትን ሳይሆን መሰወርን፥ መደበቅን የሚያሳይ ቃል ነው። |ለምሳሌ፡- የጠፋው በግ (በኋላ የተገኘው) ማቴ. 10፥6፤ 15፥24፤ ሉቃ. 15፥4-6፤ የጠፋው ገንዘብ (በኋላ የተገኘው) ሉቃ. 15፥9|። ሰው ነፍስን ሳይገድል አካልን ሊገድል ይችላል ማለት አካላዊ ሞት የሰውን መኖር (ነፍስን) ጨርሶውኑ ማቆም እንደማይችል የሚያስተምር ክፍል ነው። ሰው አካልን መግደል ይችላል ነፍስን ግን መግደል አይችልም ማለት ሰው ሊያጠፋው የሚችለው እና እግዚአብሔር ደግሞ ብቻ ሊያጠፋው የሚችል የሰው አካል አለ ማለት ነው።

ሲኦል የሚለውን ቃልና የእሳት ባሕርን የሚያመለክተውን ገሃነብ (ማቴ. 10፥28፤ ማር. 9፥43-48) የሚለውን ቃል ልንደባልቀው አይገባም። ለምሳሌ በሐዋ. 2፥27 ላይ ሲኦል ተብሎ መተርጎም የነበረበት ቃል ገሃነብ ተብሎ በአንዳንድ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ላይ ተተርጉሞአል። በብዙ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ሲኦል ተብሎ መተርጎም የነበረበት ቃል ገሃነብ እየተባለ ተተርጉሞአል። ሲኦል የሚለው ቃል የሚያሳየው ኃጢአተኞች ወደ ገሃነብ ከመሄዳቸው በፊት የሚቆዩበትን ስፍራ ሲሆን፤ ገሃነብ ደግሞ ኃጢአተኞች ለዘላለም የሚቀጡበትን ስፍራ ነው።

የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ሲኦል የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሁለት የተለያዩ አጠቃቀሞች እንዳሉት ይናገራሉ። አንደኛው፥ የመቃብር ስፍራን ሲያሳይ (ለምሳሌ፡- 1ቆሮ. 5፥55)፤ ሁለተኛው ደግሞ በትንሣኤና በመጨረሻ ፍርድ መካከል ያለውን የቆይታ ስፍራ ለማሳየት ገብቶአል (ሉቃ. 10፥15፤ 16፥23)። ስለዚህ በሐዋ. 2፥27 ላይ "ሲኦል" የሚለው ቃል ዘላለማዊ መቀጫ ስፍራን አያሳይም።

1ዮሐ. 4፥8 በእርግጥ እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ይናገራል። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የሚሄደውንና የማይሄደውን ጠንቅቆ ይናገራል። እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ ነው። ስለገሃነብ ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከእግዚአብሔር ፍቅርና ከእግዚአብሔር ፍትሕ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።

በራእ. 20፥14 የ"እሳት ባሕር" የሚለው አገላለጽ ሥዕላዊ ወይም ተምሳሌታዊ ነው። ነገር ግን የሚገልጸው ቀንና ሌሊት የማያቋርጥ ዘላለማዊ ቅጣትን ነው (ራእ. 20፥10) ስለዚህ የእሳት ባሕር የሚለው ቃል ሥዕላዊ (ተምሳሌታዊ) አገላለጽ ቢሆንም የሚገልጸው እውነትን እንጂ ባዶ ነገርን አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የእሳት ባሕርን "ሁለተኛ ሞት" ብሎ ይጠራዋል፤ ይኸውም የኃጢአተኞች የመጨረሻ ቅጣት ነው። የይሖዋ ምስክሮች መጽሐፍ ቅዱስ "ሁለተኛ ሞት" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ሊያብራሩልን ይችላሉ?

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሞት፥ ነፍስና ሲኦል ምን ይላል?



ሞት ማለት አሁን እየኖርን ካለንበት ዓለም ጋር ግንኙነት ማቋረጥ ማለት ነው። ሩት 1፥7 ሞት ሰዎችን ይለያያል። ማቴ. 22፥32 አካላዊ ሞት ሰዎችን ከእግዚአብሔር አይለያቸውም። ሮሜ 6፥1-2, 11 "ለኃጢአት መሞት " ሲል መኖር ማቆም ማለት ሳይሆን በኃጢአት መመላለስ መተው ማለት ነው። ኤፌ. 2 ክርስቲያን ክርስቶስን ከማመኑ በፊት መንፈሳዊ ሙት ነበር ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን መልካም ግንኙነት አቋርጦ ነበር ማለት ነው።

ኢቁሳዊ የሆነ ነፍስ ወይም መንፈስ አለ። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ተፈጥሮ ቁሳዊና ኢቁሳዊ አድርጎ ለሁለት ይከፍለዋል። አካልና ነፍስ (ለምሳሌ:- ማቴ. 10፥28)፥ አካልና አእምሮ (ለምሳሌ:- ሮሜ 12፥1-2)፥ አካልና መንፈስ (ለምሳሌ:- 1ቆሮ. 7፥34፤ ያዕ. 2፥26)፥ ሥጋና መንፈስ (ለምሳሌ:- 1ቆሮ. 5፥4-5፤ 2ቆሮ. 7፥1)፥ ሥጋና ልብ (ለምሳሌ:- ሮሜ 2፥28-29)፥ ውጫዊው ሰውና ውስጣዊው ሰው (ለምሳሌ:- 2ቆሮ. 4፥16)፥ አካልና ሥጋ በተለዋዋጭነት (ሮሜ 7፥18 23-25)፥ ውስጣዊው ሰውና አእምሮ በተለዋዋጭነት (ሉቃ. 1፥46-47)።

ሰው ከሞተ በኋላ ንቁ ነው ዕብ. 12፥9 23 [የይሖዋ ምስክሮች በአዲስቱ ዓለም ትርጉም "መንፈሳዊ ሕይወት" ብለው ዕብ. 12፥9, 23 መተርጎማቸው ክፍሉ ከአስተምህሮአቸው ጋር እንዲጣጣም አድርገውታል] በራእ. 6፥9-11 የሞቱ ሰዎች ነፍሳት እግዚአብሔር



ደማቸውን እንዲበቀልላቸው ሲጠይቁ ማየታችን ሰው ኢቁሳዊ አካል እንዳለው ያስተምረናል።

ሉቃ. 23፥43 አንድ አማኝ አሁን ቢሞት ከጌታ ጋር እንደሚሆን ክፍሉ በትክክል ይናገራል። የይሖዋ ምስክሮች "እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" የሚለውን ዐረፍተ ነገር "እልሃለሁ" በሚለው ቃልና "ዛሬ" በሚለው ቃል መካከል ያለውን ነጠላ ሠረዝ በማጥፋት "እውነት እልሃለሁ ዛሬ፥ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" እንዲል አደረጉት። ይህም አሁን (ዛሬ) እኔ ቃል እገባልሃለሁ ከእኔ ጋር ወደፊት በገነት ትሆናለህ ነው እንጂ፥ በገነት የመሆኑ ጉዳይ አሁን የሚሆን አይደለም ባዮች ናቸው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ "እውነት እልሃለሁ" የሚለው የአጽንኦት አነጋገር በወንጌላት ላይ 74 ጊዜ ተጠቅሶአል። "እውነት እልሃለሁ አሁን" የሚል ሐረግ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ጊዜ ተጠቅሶ አይገኝም።

ማቴ. 25፥46 ለኃጢአተኞች ዘላለማዊ ቅጣት እንዳለ ከሚያስተምሩ ጥቅሶች መካከል አንዱ ነው። ክፍሉ ስለ ኃጢአተኞች ዘላለማዊ ቅጣት በግልጽ ይናገራል። የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ያለምንም መሠረት በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ላይ "ይወገዳሉ" [Cutting off] የሚለውን ቃል ጨምሮበታል። የግሪኩ "ካሎሲስ" የሚለው ቃል በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ "ቅጣት"ን የሚያመለክት ቃል ነው (1ዮሐ. 4፥18፤ የሐዋ. 4፥21)። ሌላው ለኃጢአተኞች የዘላለም ቅጣት እንዳለ ከሚናገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል ራእ. 14፥9-11 እና 20፥10 ይገኙበታል። ኃጢአተኞች ወደ ዘላለም "ቅጣት" ይሄዳሉ፤ በዚያም ቀንና ሌሊት በእሳት ባሕር ይሠቃያሉ።

## ሞት፥ ነፍስንና ሲኦልን አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

?

1. ነፍስ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያየ አጠቃቀም አለው? (አዎ፡ እንዲሉ ይጠበቃል። የተለያየ አጠቃቀም እንዳለው ከላይ ያየናቸውን ማስረጃዎች ያቅርቡ) ከነዚህም አጠቃቀሞች ውስጥ ነፍስ የሚለው ቃል ውስጣዊ ሰውን ወይም ኢቁሳዊ የሆነውን ክፍል ለማሳየት ጥቅም ላይ መዋሉ ሰው ቁሳዊ ብቻ እንዳልሆነ የሚያመለክት አይደለምን?

2. እንደ መጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ነፍስ ሙሉ ሰውን ብቻ የሚያሳይ ከሆነ አካል ሲሞት ነፍስም መሞት አለበት ማለት ነው። ነገር ግን ማቴ. 28፥10 ነፍስ ሳይሞት ሥጋን ብቻ መግደል ይቻላል የሚለውን ክፍል እንዴት ይመለከቱታል?
3. ራእ. 6፥9–10 የሞቱ የሰዎች ነፍሳት ንቁ ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚነጋገሩ ይናገራል። ይህን ክፍል ሰው ሲሞት ነፍስም ወይም መንፈስም ይሞታል፥ ሰው ኢቁሳዊ የሆነ ክፍል የለውም ከሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ጋር እንዴት ይታረቃል?
4. አንድ ሰው የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎችን ከማንበቡ በፊት ሉቃ. 23፥46 ቢያነብ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢቁሳዊ የሆነውን ነፍሱን ወይም መንፈሱን ለእግዚአብሔር እንደሰጠ አይረዳም ነበር?
5. እስጢፋኖስ እየተወገረ "ነፍሴን ተቀበል" (የሐዋ. 7፥59) ማለቱ ሰው ኢቁሳዊ የሆነ ነፍስ እንዳለው አያሳይምን? እንደ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት መንፈስ የመኖር ጉልበት ከሆነ እስጢፋኖስ እየተወገረ እንዴት እንዲህ ሲል ቻለ? [የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነፍስ ሳይሆን መንፈስ ነው የሚለው። የግሪክኛውም መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ነው የሚለው]
6. በ1ተሰ. 4፥14 መሠረት ኢየሱስ ሲመጣ እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር አብሮ የሚያመጣቸው እነማን ናቸው? [አማኞች ናቸው እንዲሉ ይጠበቃል] እነዚህ አማኞች ቁሳዊ የሆነ አካል አላቸው? [የላቸውም መባል ይኖርበታል ምክንያቱም ቁጥር 16 ላይ ትንሣኤ እንዳላገኙ ለሚናገር]። ኢየሱስ አማኞችን ይዞ የሚመጣ ከሆነ (ቁ. 14) እነዚህ አማኞች ግን የትንሣኤ አካል ከሌላቸው (ቁ. 16) ኢቁሳዊ የሆነው ነፍስ ወይም መንፈስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንዳለ በትንሣኤ ቀን ከአካላቸው ጋር ኅብረት እንደሚያደርግ አያስተምረንም?
7. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው (ሉቃ. 20፥38) ሲል ሕያዋን የሚላቸው አብርሃም ይስሐቅንና ያዕቆብን አይደለምን? (አዎ እንዲሉ ይጠበቃል። ዐውዱ ይነበብ) በትንሣኤ ቀን ሕያዋን ይሆናሉ ሳይሆን የአሁን ጊዜ ግሥን መጠቀሙ ኢቁሳዊ የሆነው የሰው መንፈስ ወይም ነፍስ ንቁ መሆኑን አያሳይምን?
8. መሞት ያለመኖር ከሆነ ጳውሎስ "ሞትም ጥቅሜ ነውና" ስለዚህ "ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ" (ፊል. 1፥21–23) ለምን አለ? ያለመኖር ወይም ሞቶ መበስበስ የሚናፍቅ ነገር ነውን?



9. "ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ" (ቁ. 23) የሚለው የጳውሎስ አነጋገር የመጠበቂያ ግንብን ጽሑፍ አንብቦ ለማያውቅ ሰው በሄደበት ቅጽበት መኖር እንደሚጀምር አያስተምረውምን?
10. "ከሥጋ ተለይተን በለደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል" (2ቆሮ. 5፥8) ማለት ምን ማለት ነው?
11. የመክብብ መጽሐፍ ሰበአዊ የሆነውንና መንፈሳዊ የሆነውን ምልከት የሚያነጻጽር ከሆነና መክብብ 9፥1–10 ሰበአዊ የሆነውን ዕይታ የሚያሳይ ከሆነ ቁጥር 5 የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ዕይታ ነው ወይስ የሰበአውያንን? [የእግዚአብሔር ነው ካሉ የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቁአቸው] በቁጥር 5 ላይ ሙታን ከሞቱ በኋላ "ዋጋ የላቸውም" ይላል። ሙታን ዋጋ ከሌላቸው የይሖዋ ምስክሮች ትንሣኤን እንዴት ይጠባበቃሉ? ሙታን ከሞቱ በኋላ ዋጋ ከሌላቸው በክርስቶስ የማመናችን ጥቅም ምኑ ላይ ነው?
12. ሉቃ. 16፥22–28 ሰው ኢቁሳዊ የሆነ ነፍስ ወይም መንፈስ እንዳለው ይህም ከሞት በኋላ ንቁ እንደሆነ ይናገራል። የይሖዋ ምስክሮች ይህንን ክፍል እንዴት ይመለከቱታል? የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሐሰት ነበር ማለት ነው? ኢየሱስ ትምህርቱን ግልጽ ለማድረግ እውነተኛ ምሳሌዎችን ብቻ የሚጠቀም ከሆነ ይህንን ክፍል እንዴት እንመለከተዋለን?
13. "እውነት እልሃለሁ" [Truly, I tell you] የሚለው ሐረግ 73 ጊዜ "እውነት እልሃለሁ" ከሚለው ቃል በኋላ ነጠላ ሠረዝ ተጠቅመን አንድ ጊዜ ብቻ ይህን ሥርዓት በሉቃ. 23፥43 ላይ ባንከተል ወጥነት ባለው ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመናል ማለት ይቻላል? ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ወንበዴው በጣር ላይ ናቸው በዚያኑ ቅጽበት ቃል ካልገባለት መቼ ሊገባለት ይችላል። ስለዚህ አሁን ቃል እገባልሃለሁ ማለት ምን ትርጉም ይሰጣል?
14. ማቴ. 25፥26 ላይ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ባሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ፥ የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም "ቅጣት" የሚለውን የግሪክ ቃል "መወገድ" [cutting off] ብሎ መተርጎሙ አግባብ ነውን?
15. ኃጢአተኞች ለዘላለም ይሰቃያሉ የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ኃጢአተኞች ፈጽሞ ይጠፋሉ ከሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ጋር እንዴት አብረው ይሄዳሉ?
16. እግዚአብሔር "ዘላለማዊ" ነው ለማለት የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የተጠቀሙበትን ተመሳሳይ የግሪክ ቃል (ሮሜ 16፥26፤ 1ጢሞ. 1፥7፤ ዕብ. 9፥14፤ 13፥8፤ ራእ. 4፥9) የኃጢአተኞች ቅጣት "ዘላለማዊ" መሆኑን ለማሳየት ተመሳሳይ የሆነ የግሪክ ቃል መጠቀማቸው የኃጢአተኞች ቅጣት ዘላለማዊ መሆኑን አያስተምረንምን?

17. "ዘላለም" የሚለው የግሪክ ቃል "ለዘላለማዊ" ሕይወት የተጠቀመበትና (ማቴ. 25፥46) ለ"ዘላለም" ሞት የተጠቀመበት ተመሳሳይ መሆኑ ምን ያስተምረናል?
18. "ለዘላለም እስከ ዘላለም" (ራእ. 4፥10) የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት የሚያሳይ ከሆነ ተመሳሳይ የግሪክ ቃል፥ "ለዘላለም እስከ ዘላለም" የኃጢአተኞችን ቅጣት ለማሳየት በዚያው በራእ. 14፥11 ላይ መጠቀሱ ኃጢአተኞች ቅጣታቸው ዘላለማዊ መሆኑን እንዴት አያሳይም? ወደ ዓለመኖር ደረጃ የሄደ ሰው እንዴት ለዘላለም ይሰቃያል?

## 3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በጥቅምት 1874 ዓ.ም. ሆኖአል የሚል ትምህርት ነበረው። ብዙ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅቱ እንዲህ ዓይነት ትንቢት በፍጹም አላስተላለፈም ባዮች ናቸው። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ የክርስቶስ ምጽአት ሳይታይ በ1914 ዓ.ም. ሆኖአል የሚል ትምህርት ስላለው ነው። ብዙ የይሖዋ ምስክሮች የድርጅቱን የቀድሞ ታሪክም ሆነ አስተምህሮ አያውቁም። ይህንን ትምህርት አስመልክቶ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡ ጽሑፎችን በዋቢነት እናቅርብ፦

- "ጌታችን፥ የተሾመው ንጉሥ ከጥቅምት 1874 ዓ.ም. ድምሮ፥ አሁን ተገኝቶአል. . . ንጉሣዊ ሥራውን በጥቅምት 1878 ዓ.ም. መርቆ ሊጀምር"[1]
- "ስለዚህም የጌታ ዳግም ምጽአት በ1874 ዓ.ም. ጀምሮአል"[2]
- "መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት የጌታ ኢየሱስ ዳግም መገኘት የጀመረው በ1874 ዓ.ም. ነው"[3]
- "የጌታ ምጽአት በ1874 ዓ.ም. በኃይል እንደሆነ እስከተገነዘብንበት ጊዜ ድረስ እንድም ሰው በተገቢው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ሥራ ሊረዳ አልቻለም። ይህም በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ፍጹም ለውጥ አምጥቶአል"[4]

1. Studies in the Scriptures, Vol 4 (1997), ገጽ. 621
2. Creation (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1927), ገጽ. 289
3. Prophecy, ገጽ. 65
4. The Wathtower, 1 March 1922, ገጽ. 67



ምንም እንኳ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የቆዩ ጽሑፎች የጌታ ዳግም ምጽአት በ1874 ዓ.ም. ነው ቢሉም፤ አሁን በተሻሻለው የሥነ-ፍጻሜ ትምህርታቸው የጌታ ዳግም ምጽአት ሳይታይ በ1914 ዓ.ም ነው የሚል ነው። ይህንን ትምህርት ከሚያስተምሩት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ደግሞ ጥቂቶቹን እንመልከት፦

- "ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ መንግሥቱ የመጣው በ1914 ዓ.ም. ነው፤ ነገር ግን ለሰው ሳይታይ ነው"[5]
- "ኢየሱስ በማይታይ ሁኔታ መገኘቱን እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መቋቋም የሚጠቁሙ ብዙ ነገሮችን አስቀድሞ ተናግሮአል። የአሕዛብ ዘመን ወይም የተወሰነው የአሕዛብ ዘመን የሚያበቃው በ1914 ዓ.ም. ነው"[6]
- "መንፈሳዊ የሆነው የክርስቶስ በማይታይ ሁኔታ በመንግሥቱ መገኘት የጀመረው የአሕዛብ ዘመን በ1914 ዓ.ም. ሲያበቃ ነው"[7]

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት 1914 ዓ. የሰበአውያን አገዛዝ ማብቂያና የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ ለሙሉ መመሥረቻ ነው የሚልም ትምህርት አስተላልፎ ነበር።

- "በመጪዎቹ 26 ዓመታት ውስጥ ብቻ አሁን ያሉት መንግሥታት እየሟሙ ያልቃሉ. . . የእግዚአብሔርም መንግሥት በ1914 መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሠረታል"[8]
- "1914 ዓ.ም. የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ሙሉ ለሙሉ የሚመሠረትበት ጊዜ ነው"[9]

5. The Truth Shall Make You Free, ገጽ.300
6. "Let God Be True" ገጽ. 250
7. Man's Salvation Out of World Distress At Hand! (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1975), ገጽ. 288.
8. Studies in the Scriptures, Vol. 2 (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1888), ገጽ. 98-99
9. Studies in the Scriptures. Vol. 3 (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1891), ገጽ. 126

- "የቅዱሳን አርነት መውጣት የሚገለጸው ከ1914 ዓ.ም. በፊት ነው. . . የመጨረሻው የክርስቶስ አካል አባላት 1914 ዓ.ም. በፊት ለምን ያህል ጊዜ እንደሚከብሩ በቀጥታ የተገለጠልን ነገር የለም?? "[10]

የሰብአውያን አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ተወግዶ የእግዚአብሔር መንግሥት በ1914 ዓ.ም. ይመሠረታል የሚለው የድርጅቱ አስተምህሮ ተስፋ ቆርጦዋል። "ላይት" ["ብርሃን"] የሚባለው የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፍ ስለዚህ ተስፋ መቁረጥ እንዲህ ይላል፡– "1914 ዓ.ምን ሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች በደስታ ጠብቀውት ነበር። ነገር ግን ጊዜው መጥቶ ሲያልፍ ትልቅ ተስፋ መቁረጥ ነበር. . . በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የተሞኙ በተለይ ከእነርሱ ጋር የተባበሩ በመሳለቅ ተጠቋቁመውባቸዋል። ምክንያቱም ስለ [1914 ዓ.ም. ] ብዙ ብለው ስለነበር 1914 ዓ.ም. መጥቶ ሲያልፍ 'ትንቢታቸው' አልሞላም"[11]

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሥነ–ፍጻሜን አስመልክቶ ያወጣቸው የጊዜ ስሌዳዎች እነዚህ ብቻ አይደሉም። ነገር ግን የመጠበቂያ ግንብ መሪዎች አብርሃም፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን ጨምሮ የብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደ ልዑል ["princes"] ሆነው በ1925 ዓ.ም. በመምጣት በአሜሪካን አገር በካሊፎርኒያ ሳን ዲያጎ "ቤተ ሳሪም" (የልዑላን ቤት) በሚባለው መኖር ይጀምራሉ። ይህን አስመልክቶ "ሳልቬሽን" ("ደኅንነት") የሚባለው የድርጅቱ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡– "ያንን ዕቃ ማግኘትና ቤቱን መግዛት በምድር ላይ አሁን እንዳሉ የሚያስረግጥ የተጨበጠ ማስረጃ ሊሆን ይችላል። . . . የጥንት የእግዚአብሔር ሰዎች በጌታ ትንሣኤ በቅርቡ ትንሣኤ አግኝተው ወደ ምድር በመምጣት የሚታየውን ምድራዊ ሥራ እንደሚጀምሩ የሚያምነው ማነው"[12]። ይህንኑ ጉዳይ "ዘ ኒው ወርልድ" ["አዲስ ዓለም"] የሚባለው መጽሐፍ እንዲህ ሲል ያጸናዋል "የጥንት ታማኝ ሰዎች ከሙታን እንደሚነሡ በአሁኑ ጊዜ ምን አልባት ሊጠበቅ ይችላል። . . . ይህንንም በመጠበቅ ነው ቤቶቹ የተገዙት። . . . በባለቤትነት ተይዘው እንዲቆዩ ያደረገውም እነዚያ ልዑላን እንደሚመለሱ በማመን ነው"[13]

10. Studies in the Scriptures, Vol. 3 (Brooklyn: Watchtower Bible and Bible Society, 1913), ገጽ. 228

11. Light, Vol 1 (Broiklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1930), ገጽ. 194.በቅንፍ ያለውን አይጨምርም

12. Salvation (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1939), ገጽ. 311

13. The New World (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1942), ገጽ. 104.



በተለያዩ ጊዜያት ከድርጅቱ እየታተሙ የወጡ ጽሑፎች የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በ1925 ዓ.ም. በምድር ላይ በእርግጠኝነት እንደሚታዩ የሚናገሩ ናቸው።

- "ታማኝ የእስራኤል ሰዎች በ1925 ዓ.ም. ከሙታን እንደሚነሡ፥ ትንሣኤ እንደሚያገኙ የምንመሰክርበት ጊዜ ነው። . . . 1925 ዓ.ም. አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ እንዲሁም የብሉይ ኪዳን ታማኞች በመመለስ ምልክት የሚያደርግበት ጊዜ ነው"[14]
- "ያለምንም ስህተት . . . አብርሃም የቃል ኪዳን ተስፋ ባለቤት የሚሆንበት ዓመት 1925 ዓ.ም. ነው"[15]
- "1925 ዓ.ም. በቅዱሳን ጽሑፎች በፍጹም የተወሰነ ነው"[16]
- "1925 ዓ.ም. በቅዱሳን ጽሑፎች በእርግጠኝነትና በግልጽ የተገለጸ ዓመት ነው። እንዲሁም ከ1914 ዓ.ም. ይልቅ ግልጽ በሆነ ሁኔታ"[17]

አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና በርካታ የብሉይ ኪዳን ነቢያት በ1925 ዓ.ም. ያለመታየታቸው ለብዙ የይሖዋ ምስክሮች ተስፋ መቁረጥ ሆኖአል። በ1975 ዓ.ም. የወጣው የይሖዋ ምስክሮች ዓመታዊ መጽሐፍ ይህን ተስፋ መቁረጥ በግልጽ ያሳየ ነበር፡– "1925 ዓ.ም. መጥቶ አለፈ። የክርስቶስ ቅቡዓን ተከታዮች እንደ ክፍል [መደብ ] እስከ አሁን ድረስ በምድር ላይ ናቸው። የጥንት ጊዜ ታማኝ ሰዎች፡– አብርሃም፥ ዳዊት እንዲሁም ሌሎች ትንሣኤ በማግኘት በምድር ላይ ልዑል አልሆኑም (መዝ. 45፥16)። ስለዚህም አንግክዶናልድ እንዳስታወሰው፡– '1925 ዓ.ም. ለብዙ ወንድሞች ተስፋ መቁረጥ ነበር። አንዳንዶች ተሰናክለዋል፥ ተስፋቸው በቅጽበት ተሞአጡአል። . . . 'ሊሆን ይችላል' ተብሎ በግንዛቤ ሊያዝ ሊገባው 'በእርግጠኝነት' ተብሎ መነበብ አንዳንዶች የሚወዷቸውን [ሰዎች] ትንሣኤ በመጠበቃቸው ነው' "[18]

14. Millions Now Living Will Never Die (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1920), ገጽ 88-90

15. The Watchtower, 15 October 1917, ገጽ. 6157

16. The Watchtower, 1 April 1923, ገጽ. 106

17. The Watchtower, 15 July 1924, ገጽ. 211

18. 1975 Yearbook (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1975), ገጽ. 146 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በተደጋጋሚ ያወጡት ሐሰተኛ ትንቢቶች በዚህ ብቻ የሚያበቁ አይደሉም። ድርጅቱ ለተከታዮቹ የ6ሺ ዓመት የሰው ልጆች ታሪክ የሚጠናቀቀው በ1975 ዓ.ም. ነው የሚል ትንቢት ተንብዮ ነበር። አርማጌዶንም በዚሁ ዓመት እንደሚሆን እንዲሁም ክርስቶስ የሺ ዓመቱን መንግሥት በምድር ላይ እንደሚመሠረት።

- "በየትኛው ዓመት ነው 6000 ዓመት የሰዎች ኑሮ እንዲሁም የመጀመሪያው 6000 ዓመት የእግዚአብሔር ዕረፍት ቀን የሚጠናቀቀው? በ1975 ዓ.ም. ነው"[19] [ልብ ይበሉ ከዚህ በፊት የነበረው የመጠበቂያ ግንብ መጽሔት የ6ሺው ዓመት የሰው ልጅ ታሪክ የሚጠናቀቀው በ1873 ዓ.ም. ነው ብሎ ነበር[20]]
- "የሰው ልጆች በምድር ላይ መኖራቸው በመጠናቀቁ ከ6000 ዓመት በፊት ዘጠና ወራቶች [7 ዓመት ከ6 ወር] ብቻ ይቀራሉ. . . ምን አልባት ዛሬ የሚኖሩት አብዛኞዎቹ ሰዎች አርማጌዶን ሲጀምር ይኖራሉ"[21]

ከዚህ በፊት እንደተባለቱት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትንቢቶች 1925 ዓ.ም. ምንም ነገር ሳይሆን፥ ትንቢቱ ሳይፈጸም መጥቶ በማለፉ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በታላቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ወድቀዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ1976 ዓ.ም. እስከ 1978 ዓም. በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ የይሖዋ ምስክሮች የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን የመልቀቃቸው ምክንያት የተስፋ መቁረጡ ውጤት ነበር።

ለሠላሳ ዓመት የይሖዋ ምስክር የነበረው ዊሊያም ሽነል፡- "ለሠላሳ ዓመት ለመጠበቂያ ግንብ ባሪያ ነበርኩ" በሚለው መጽሐፉ "'መጠበቂያ ግንብ' የሚባለው መጽሔት በ1917 ዓ.ም. እና በ1928 ዓ.ም. መካከል 148 ጊዜ ባላነሰ አስተምህሮአችንን ቀያይሮብናል"[23] ብሎአል።

19. Awake! 8 October 1966, ገጽ. 19
20. The Watchtower, 15 July 1894, ገጽ. 1675
21. Our Kingdom Ministry, Mareb 1968, ገጽ.4
22. Leonard and Marjorie Chretien, Witnesses of Jehovah (Eugene, Or: Harvest House pub, 1988), ገጽ. 58
23. William J. Schenell, Thirty Years a Watchtower Slave (Grand Ra.: 9aker, 1956), ገጽ..37 citedin Ankerberd and weldon, ገጽ. 37.



የይሖዋ ምስክሮች ለዚህ ሁሉ ሐሰተኛ ትንቢት ልንተችም ሆነ በሐሰተኛ ነቢያት ጎራ ልንፈርጅ አይገባም ባዮች ናቸው። ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት ተሳስተዋል። በመሳሳታቸውም ሐሰተኛ ነቢያት ተብለው አልተወገዙም የሚል ነው። አብዛኛውን ጊዜ የይሖዋ ምስክሮች ለዚህ ስህተት መሸፈኛ የሚጠቅሱት ጥቅስ የነቢዩ ናታንን ታሪክ ነው (1ዜና 17፥2)። ንጉሥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሊሠራ ሲያስብ ናታን ለዳዊት እንደፈለክ አድርግ አለው። ነገር ግን ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን እንዲሠራ የሚፈልገው እርሱን እንዳልሆነ ተናገረ። ናታን ቢሳሳትም በእግዚአብሔር ሆነ በሰዎች እንደ ሐሰተኛ ነቢይ አልታየም። እግዚአብሔር ናታንን ደግሞ የተጠቀመበት ነገሩን እግዚአብሔር ግልጽ ባደረገለት ጊዜ በየዋህነት በማስተካከሉ ነበር የሚል ነው[24]።

በመጀመሪያ ናታን ለዳዊት የመከረው ምክር የግሉን ምክር ነበር። ናታንም የመጀመሪያውን መልእክት ከእግዚአብሔር ነው የተቀበልኩት አላለም (1ዜና 17፥2) ነገር ግን ቤቱን አትሥራልኝ "ቤቱን የሚሠራው በአንተ አይደለህም" የሚለው መልእክት ግን ከእግዚአብሔር ነበር (1ዜና 17፥3–15)።

ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች ለሐሰተኛ ትንቢቶቻቸው መሸፈኛ፥ እነርሱም በሐሰተኛ ነቢያት ጎራ እንዳይፈረጁ ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሱት ጥቅስ ፍጹም የሚያስኬዳቸው አይደለም። ይልቁንም ቃለ እግዚአብሔርን እንዴት አድርገው እንደሚያጣምሙት የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን አያጥፍም፤ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነው።

ዛሬ ሥነ-ፍጻሜን አስመልክቶ በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በስፋት የሚሰጠው ትምህርት የሚከተለው ነው፡- ክርስቶስ ሳይታይ መጥቶአል ወይም ተገኝቶአል። ወደ ምድር ዳግም ተመልሶ አይመጣም። አሁን ሳይታይ "መገኘቱ" ሳይታይ "ለመገለጡ" ዝግጅት ነው። ይህም በአርማጌዶን ወቅትና በሺው ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው ይኸውም በ1914 ዓ.ም. ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ እንደ ንጉሥ በመግዛት ላይ ስለሆነ የአሕዛብ ዘመን በ1914 ዓ.ም. ተጠናቁአል።

24. – ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፥ ገጽ 135

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከላይ ለተመለከትናቸው ትምህርቶች ማስደገፊያ ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው[25] ክርስቶስ ሳይታይ ተገኝቶአል። ክርስቶስ በማይታይ መንፈሳዊ አካል ወደ ሰማይ ስላረገ ወደ ምድር በሚታይ ቁሳዊ አካል ሊመጣ አይችልም።

"ፓሩሲያ" የሚለው የግሪክ ቃል በአብዛኛው የተተረጎመው "ምጽአት" ተብሎ ነው። ነገር ግን መተርጎም የነበረበት "መገኘት" ተብሎ ነበር። "ፓሩሲያ" ማለት "መገኘት" ማለት እንጂ "ምጽአት" ማለት አይደለም። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በፊል. 2፥12 እና በ2ቆሮ. 10፥10 "ፓሩሲያ" የሚለውን ቃል "መገኘት" ብለው ነው የተረጎሙት።

በማቴ. 24፥37 ላይ "ፓሩሲያ" የሚለው ቃል የተነጻጸረው "ከኖኅ ዘመን" ጋር ነው። ይኸውም የብዙ ዘመን ቆይታን እንጂ አንድ የተወሰነ የጊዜ ነጥብን ለማሳየት አይደለም። ስለዚህ ይህ የሚያሳየን "ፓሩሲያ" የሚለው ቃል የጊዜን ርዝማኔ ይኸውም ክርስቶስ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ጊዜ ለማሳየት አይደለም።

ክርስቶስ ሳይታይ "መገኘት" የጀመረው በ1914 ዓ.ም. ነው[26]። መጽሐፍ ቅዱስ የጊዜ ቅደም ተከተል የሚያሳየው 1914 ዓ.ም. "የአሕዛብ ዘመን" ማብቅያ ወይም "የተቀጠረውን የአሕዛብ ዘመን" ነው (ሉቃ. 21፥24)። ክርስቶስ የተነበያቸው የፍጻሜ ዘመን ምልክቶች ከ1914 ዓ.ም. ጀምሮ መታየት ጀምረዋል። ጦርነቶች፥ የምድር ነውጦች፥ ድርቅ፥ ወንጀሎች፥ በሽታዎች በዓለም ዙሪያ እየጨመሩ መጥተዋል (ማቴ. 24፥3-7 12፤ ማር. 13፥7-8፤ ሉቃ. 21፥10-11) "የመንግሥት ወንጌል" ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል እንደመጣ ለዓለም ሁሉ ይነገራል ማቴ. 24፥14። ይህም ዜና በይሖዋ ምስክሮች አማካኝነት በዓለም ሁሉ እየተሰበከ ነው።

25. - በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፡ ገጽ 142-149።
- ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፡ ገጽ 340-344። Insight on the Scriptures, 2; 676-679 . Appendix 5 B, in New World Translation of the Holy Scriptures; with References (1984), 1576-1577 ይመለከቷል

26. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፡ ገጽ 134-141 ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፡ ገጽ 94-97 232-240



አሥራ ዘጠኝ መቶ አሥራ አራት ዓመተ ምሕረት እጅግ ወሳኝ (ማለትም ለይሖዋ ምስክሮች) ዓመት ነው። 1914 ዓ.ም. ከመሆኑ ከ30 ዓመት በፊት የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች [ከ1931 ዓ.ም. በፊት የነበሩት የይሖዋ ምስክሮች የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በመባል ይታወቁ ነበር] የአሕዛብ ዘመን በ1914 ዓ.ም. እንደሚያበቃ ጠቁመው ነበር። የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በ1914 ዓ.ም. መጀመሩ "ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች" የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በእግዚአብሔር እየተመራ እንዳለ አረጋግጦላቸዋል። 1914ን አስመልክቶ "የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች" የጠበቋቸው አንዳንድ ነገሮች ትክክል አለመሆናቸው እውነት ነው። ነገር ግን ይህ ስህተታቸው መልእክታቸውን ውድቅ አያደርገውም። የይሖዋ ምስክሮች ሥነ-ፍጻሜን አስመልክተው የሚተነቢዩት ትንቢት የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል እስካልሆነ ድረስ ስህተታቸው እንደ ሐሰተኛ ነቢያት አያስቆጥራቸውም። በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ቃለ እግዚአብሔርን የጻፉት ሰዎች እንኳን ትንቢታቸው መቼና እንዴት እንደሚፈጸም ቀኑን ለይተው አያውቁም ነበር (ምሳ. 4፥18፤ ዮሐ. 3፥4 10፤ 21፥22-23፤ 1ቆሮ. 13፥9-10፤ 1ጴጥ. 1፥10-11)።

ክርስቶስ በምድር ላይ መግዛት የጀመረው በ1914 ዓ.ም. ነው። ከ33 ዓ.ም. - 1914 ዓ.ም. ድረስ ክርስቶስ መንግሥት ነበረው። ነገር ግን የሚገዙለት 144ሺዎቹ ብቻ ነበሩ (ዕብ. 10፥13፤ መዝ. 110፥1-6)።



## የይሖዋ ምስክሮች በክርስቶስ ምጽአት ላይ ያላቸው ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



ኢየሱስ ክርስቶስ የከበረ አካል ቢኖረውም ቁሳዊ በሆነ የሰው አካል ከሙታን ስለመነሣቱ የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በሚለው ርዕስ ሥር ተመልክተናል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል ከሙታን ተነሥቶ እየታየ ሳላረገ ምጽአቱም በአካል እየታየ ይሆናል።

በእርግጥ "ፓሩሲያ" የሚለው የግሪክ ቃል "መገኘት" በሚለው ትርጉም በፊል. 2፥12 እና 2ቆሮ. 10፥10 ላይ ተተርጉሞአል። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ደግሞ መምጣት ወይም መድረስ ተብሎ

የተተረጎመ ሲሆን ይህ ቃል (ማለትም "ፓሩሲያ") "ፓሪሚያ" ከሚለው ቃል ጋር በተጓዳኝነት ገብቶ ይገኛል (የሐዋ. 12፥20፤ ገላ. 4፥20፤ ፊል. 1፥26)። "የኖኅ ዘመን" "ፓሩሲያ" ከሚለው ቃል ጋር ማለትም ከጥፋት ውኃ በፊት ካለው ጊዜ ጋር ሳይሆን የተነጻጸረው የክርስቶስ "ምጽአት" ("ኤርኪታይ" ቁ. 42) ድንገተኛ መሆን ከጥፋት ውኃው ድንገተኛነት ጋር ነው። በዚህ ዐውድ ውስጥ "ፓሩሲያ" የሚለው ቃል እና "ኤርኪቻይ" የሚለው ቃል ተመሳሳይ ናቸው።

1ቆሮ. 5፥3 ላይ ጳውሎስ በመንፈስ አብሩአቸው እንደሚገኝ ተናግሮአል። ጳውሎስ እገኛለሁ ("ፓሪሚ") ያለው በመንፈስ ነው ነገር ግን ኢየሱስ እገኛለሁ ያለው በአካል (በዓይን በሚታይና በእኛ በሚዳሰስ መልኩ) ነው። እግዚአብሔር አምላክ ከእስራኤል ጋር የነበረው በመንፈስ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ በአካል እየታየ በሰዎች መካከል ተገኝቶአል። እግዚአብሔር በመንፈስ ነበር የተገኘው ስለዚህም የኢየሱስ መገኘት እንደ እግዚአብሔር በመንፈስ ነው የሚለው ማስረጃ ትክክል አይደለም።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል አይመጣም ለሚለው ትምህርቱ የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች በምንም ዓይነት መልኩ ትምህርቱን የሚደግፉለት አይደሉም። ዮሐ. 14፥19 "ገና ጥቂት ዘመን አለ። ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ" ኢየሱስ "ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም" ማለቱ ከአሁን በኋላ ለዘላለም ለዓለም መታየቱን አቆማለሁ ማለቱ አይደለም። ነገር ግን በአገልግሎቱ ዘመን እየታየ በሰዎች መካከል እንደሚመላለስ አሁን እንደማይታይ ለማሳየት ብቻ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ "ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግምሞ ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም" (ዮሐ. 16፥16) ብሎአልና። ዓለም ኢየሱስን ማየት ሲያቆም ደቀ መዛሙርቱ ግን ያዩታል፤ ይህም ከትንሣኤው በኋላ እንደሚያዩት እንጂ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር እንደሚለው የሚያዩት ከ2ሺ ዓመት በኋላ አይደለም።

ከማቴ. 24፥3 ጋር በተጓዳኝነት ያሉት ክፍሎች፥ ማር. 13፥4 እና ሉቃ. 21፥7 የሚያመለክቱት ወደፊት ስለሚሆነው "ምልክት" እንጂ በሰማይ ከዚህ በፊት ስለሆነ ነገር አይደለም። የደቀመዛሙርቱን ጥያቄ ለመመለስ ኢየሱስ "ምልክት" ያለው ከ"ሰው ልጅ መምጣት" (24፥30) በፊት የሰዎች ልጆች ሁሉ ስለሚያዩት፥ በሰማይ ስለሚከናወን ምልክት ነው። "ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ እንዲሁ እናንተ ደግሞ



ይህን ሁሉ ሲታዩ በደጅ እንደቀረበ እወቁ"። (ማቴ. 24፥ 32–33) "ምልክት" ያስፈለገው የኢየሱስ ምጽአት የማይታይ ስለሆነ አይደለም፤ ነገር ግን መቅረቡን ለማሳየት ነው። የበለስ ጫፍ ሲለሰልስና ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ የበጋ መቅረብ እንደሚታወቅ ሁሉ፤ ፀሐይ ስትጨልም፥ ጨረቃም ብርሃንዋን መስጠት ስታቆም፥ ከዋክብት ከሰማይ ሲወድቁ፥ የሰማይም ኃይላት ሲናወጡ (ቁ. 29) የጌታ ምጽአት እንደቀረበ እናውቃለን። ይኸውም ምድራዊው ምልክት ምድራዊውን ነገር እንደሚያሳይ ሰማያዊውም ምልክት ሰማያዊውን ነገር ያሳያል። በአጠቃላይ "ምልክት" ያስፈለገው የጌታ ምጽአት የማይታይ ስለሆነ ሳይሆን ምልክቱ የጌታ ምጽአት እጅግ መቅረቡን ለማሳየት ነው።

በማቴ. 24፥37–39 ከምጽአቱ ጋር የተነጻጸረው ከጥፋት ውኃው በፊት የነበረው የኖኅ ዘመን አይደለም። ነገር ግን ንጽጽሩ የተካሄደው ከጥፋት ውኃው ድንገተኝነት ጋር ነው። የጥፋት ውኃው እስከ መጣ ጊዜ ድረስ ውኃው ይመጣል ብሎ የጠበቀ አልነበረም። ስለዚህ የኖኅ ዘመን የሚያሳየው ፍርድ በምድር ላይ ድንገት እንደሚመጣ ነው። ይህም የሰው ልጅ ለፍርድ እንደሚመጣ የሚያመለክት ነው። ከጥፋት ውኃው በፊት የረጅም ጊዜ "ምልክት" አልነበረም፤ እንዲሁም የፍርድ ቀን እስከሚመጣ ጊዜ ድረስ የረጅም ጊዜ ምልክት የለም። የሐዋ. 1፥9–11 እንደሚያመለክተው ኢየሱስ እየታየ ነበር ያረገው፤ ከዚያም "ደመና" ሰወረው (ቁ. 9)። መሳእክት እንዲሁ ተመልሶ ይመጣል ማለታቸው ከደመና ወጥቶ እየታየ እንደሚመጣ ማለተማራቸው ነው (ቁ. 11)።

በራእ. 1፥7 ላይ "ደመና" የሚለው ቃል የኢየሱስ ክርስቶስን ለፍርድ መምጣት የሚያመለክት ሲሆን ከዳን. 7፥13 ላይ የተወሰደ አገላለጽ ነው። "የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ" (ራእ. 1፥6–7 13–14፤ ዳን. 7፥9 13–14፤ ራእ. 14፥14–16)። (ማቴ. 24፥30፤ 26፥64፤ ማር. 13፥26፤ 14፥62፤ ሉቃ. 21፥27) የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ለማሳየት በራሱ በኢየሱስ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት መታየቱ በመንፈስ የሚሆን፥ በታላቅ ጥረት የሚታወቅ ጉዳይ አይደለም። "የወጉት ሁሉ" የሚያዩት እውነታ ነው፤ (ዕብ. 6፥6) ይህ ማለት ኢየሱስን ያልተቀበሉት እንኳ ማየት እንደሚችሉ ነው።

ኢየሱስ በማይታይ ሁኔታ መገኘቱ (ፓሩሲያ) ከ"መገለጡ" (አፓካሉፕሲስ) ይለያል የሚለው የመጠበቂያ ግንድ ድርጅት አስተምህሮ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱን ድርጊቶች አይለያያቸውም። በሉቃስ ወንጌል የሰው ልጅ የሚገለጥበት ቀን [አፓካሉፕቲታይ] (ሉቃ. 17፥30) የተነጻጸረው ድንገተኛ ከሆነው

ከጥፋት ውኃ ፍርድ ጋር (ቁ. 26-27) እንዲሁም ድንገተኛ ከሆነው የሰዶም ፍርድ ጋር (ቁ. 28-29) ነው። በማቴዎስ ወንጌል የሚገኘው የክፍሉ ትይዩ የሰው ልጅን ድንገተኛ ምጽአት (ማቴ. 24፥37, 39) ከጥፋት ውኃ ጋር ነው ያነጻጸረው። በአዲስ ኪዳን ክፍሎች እነዚህ ሁለት ቃላት በተለዋዋጭነት ገብተው ይገኛሉ።

ክርስቶስ ሳይታይ መገኘት የጀመረው በ1914 ዓ.ም. ነው የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ምጽአት አሀዛዊ ቀመር እንድናበጅ አይፈልግም። ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የሥነ-አፈታት መርህ በመጠቀም የክርስቶስ ምጽአት በ1914 ዓ.ም. ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ፍጹም ትክክል አይደለም[27]። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 1914 ዓ.ም. ስለሌለ ክርስቲያንም ሊያምን በፍጹም አይገባውም።

የመጠበቂያ ግንብ የመጨረሻ ዘመን "ምልክቶች" ናቸው የሚባሉት ምልክቶች ትክክል አይደሉም። በዓለም ላይ የተለያዩ ችግሮች መኖራቸው፥ ይህም ችግር እኛ ባለንበት ዘመን የበለጠ እየጨመረ መምጣቱ ትክክል ነው። ነገር ግን የይሖዋ ምስክሮች የስብከት ሥራ ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች አንዱ ነው የሚለው ግን ፍጹም ትክክል አይደለም (ማቴ. 24፥14)። ምክንያቱም በጥንት ክርስቲያኖች የተሰበከው "የመንግሥት ወንጌል" እና አሁን መሰበክ ያለበት ወንጌል ፍጹም አንድ ዓይነት መሆን አለበት እንጂ ከ1914 ዓ.ም. ወዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል መጥታለች በሚል፥ ከቀድሞ ክርስቲያኖች ስብከት ፈጽሞ የተለየ መሆን የለበትም (የሐዋ. 8፥12፤ 20፥24-25፤ 28፥23-31)።

"የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች" [ከ1931 ዓ.ም. በፊት የነበሩት የይሖዋ ምስክሮች የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በመባል ይታወቁ ነበር] ስለ 1914 ዓ.ም. የነበራቸው ግምት ትክክል ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን እነርሱ ካስቡት የተገላቢጦሽ መሆኑ ነው። ራስልና "የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች" ፓሩሲያ ("ምጽአት") በ1874 ዓ.ም. ጀምሮ በ1914 ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ ነበር ያስተማሩት። በእነርሱ እምነት የኢየሱስ "መገኘት" በ1914 ዓ.ም. ይበቃ ነበር። በአሁኑ ዘመን እንዳሉት የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ የኢየሱስ መገኘት የጀመረው በ1914 ዓ.ም. ነው [ወይም መገኘቱ (ፓሩሲያ) እስከ 1914 ዓ.ም አልጀመረም ነበር]

27. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1914 ዓ.ም. ነው ለሚለው ትምህርቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀሳቸውን ጥቅሶችና የስሌቱን አወቃቀር፦ ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር ገጽ 92-96 የሚለውን የድርጅቱን መጽሐፍ፥ በተለይ ገጽ 96ን ልብ ብለው ይመርምሩት።



የሚል ነው። ስለዚህ ዛሬ የመጠበቂያ ግንብ እያስተማረ ያለው የ1914 ዓ.ም. ጠንሳሾች መገኘቱ ያበቃል ባሉበት ጊዜ መገኘቱ ጀምሮአል እያሉ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ጳውሎስ ኢየሱስ በሌለበት ጊዜ አለ ስለሚሉ ሰዎች ግልጽ የሆነ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ አስተላልፈዋል (ማቴ. 24፥23-27፤ 2ተሰ. 2፥1-2)።

የክርስቶስን ምጽአት አስመልክቶ በሚሰጡት የሐሰት ትንቢቶች መጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ማስጠንቀቂያ አለው (ማቴ. 24፥23-27፤ ሉቃ. 21፥8፤ 2ተሰ. 2፥1)። ስለዚህ የክርስቶስን ምጽአት አስመልክቶ የሚሰነዘሩት መላምቶችና ትንቢቶች በመጽሐፍ ቅዱስ በቸልታ የሚታለፉ ነገሮች አይደሉም። እርግጥ ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትና ሐዋርያት የተነበዩአቸውን አንዳንድ ትንቢቶች አልተረዱአቸውም ነበር (1ቆሮ. 13፥9-10፤ 1ጴጥ. 1፥10-11)። ስለ ወደፊቱም አንዳንድ ግምቶች ነበሩአቸው ' (ዮሐ. 21፥22-23)። ነገር ግን የሐሰት ትንቢቶችን አልተነበዩም።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት አስተምህሮዎቹንና ትንቢቶቹን ማሻሻልና መቀየር ሲፈልግ የሚጠቅሰው ጥቅስ ምሳ. 4፥18 ነው። የክፍሉ ዐውድ እንደሚጠቁመን ክፍሉ በትክክለኛው ኑሮ ስለማደግ እንጂ ስለ ትንቢትና አስተምህሮ ለማሻሻልና መቀየር አይደለም። ዮናስን በተመለከተ (ዮና. 3፥4 10)፦ ዮናስ እግዚአብሔር ተናገር ያለውን ነገር ነው የተናገረው (ዮና. 3፥2-3, 5, 10)። በእርግጥ የይሖዋ ምስክሮች የሚያስተላልፍዋቸውን የሐሰት ትንቢቶች ሁሉ ተንቢዩ ያላቸው ወይም ትንቢቱን የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ነውን? የዮናስ ትንቢት ነነዌ ንስሐ ካልገባች እንደምትጠፋ የማስጠንቀቂያ ትንቢት እንጂ የሐሰት ትንቢት አልነበረም።

ኢየሱስ ምድርን መግዛት የጀመረው ከ33 ዓ.ም. [ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣበት ጊዜ] ጀምሮ እንጂ በ1914 ዓ.ም. አይደለም። ዕብ. 10፥13 ክርስቶስ መግዛት ለመጀመር በቆይታ ላይ ነበር ወይም ነው አይልም። ነገር ግን ጠላቶቹን እስከሚገዛ ድረስ መቆየቱን ብቻ ነው። መዝ. 110፥1-6 ክርስቶስ "በጽዮን" እንደሚገዛ ይናገራል፤ ይህም በ33 ዓ.ም. ነው የተጀመረው። ቀጣይነቱም እስከ መጨረሻው የፍርድ ቀን ድረስ ነው (መዝ. 2)።

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ምጽአት ምን ይላል?



መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በአካል፣ እየታየ ወደ ምድር እንደሚመጣ ያስተምራል። "ፓሩሲያ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሌላ የክርስቶስን ምጽአት የሚገልጹ ብዙ ቃላቶች አሉ። ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን እንመልከት፦ "ኢፒፋኒያ" የቃሉ ትርጉም "መገለጥ"፣ "መታየት " እንዲሁም "መምጣት" ማለት ነው (2ተሰ. 2፥8፤ 1ጢሞ. 6፥14፤ 2ጢሞ. 4፥1 8፤ ቲቶ 2፥13)። ይህ የግሪክ ቃል መለኮት በሰው ሁኔታ መገሥጥን ለማሳየት በግሪክ ቋንቋ በሰፋት ጥቅም ላይ ውሎአዋል። ራሳቸውን እንደ አምላክ ይቆጥሩ የነበሩ የጥንት ነገሥታት፣ "እኛ አማልክት ነን ነገር ግን በሰው ሁኔታ 'ታይተናል' ወይም 'ተገልጠናል' " ለማለት ሲፈልጉ "አፒፋነስ" በሚለው ስም ይጠሩ ነበር። "ፋኔሮ" የቃሉ ትርጉም "መታየት" ወይም "መገለጥ" ማለት ነው (ቆላ. 3፥14፤ 1ጴጥ. 5፥4፤ 1ዮሐ. 2፥28፤ 3፥2)። ይህ ቃል "ኢፒፋኒያ" ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ትርጉም አለው። ይኸውም የአንድ ነገር መገለጥ ወይም መታየት ማለት ነው። "ኤርኮማይ" የቃሉ ትርጉም "መምጣት" ማለት ነው (ማቴ. 16፥27–28፤ 24፥30, 42, 44፤ 25፥13, 31፤ 26፥64፤ ማር. 13፥26፤ 14፥62፤ ሉቃ. 9፥26፤ 12፥40፤ 21፥27፤ የሐዋ. 1፥11፤ 1ቆሮ. 4፥5፤ 11፥26፤ 2ተሰ. 1፥10፤ ራእ. 1፥7፤ 22፥7, 12, 20) ይህ ቃል መምጣት ለሚለው የቃል ትርጉም የተለመደ የግሪክ አጠቃቀም ነው።

የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ለማሳየት "አፖካሉብሲስ"፣ "ኤርኮማይ"፣ "አፒፋኒያ" እና "ፓሩሲያ" የሚሉት ቃላት በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ክርስቲያኖች የክርስቶስን "መገለጥ" ("አፖካሉብሲስ" ወይም "ኢፒፋኒያ") ይጠባበቃሉ፣ ተስፋም ያደርጋሉ (1ቆሮ. 1፥7፤ 1ጴጥ. 1፥13፤ ቲቶ 2፥13)። እስከ ምጽአቱም ("ፓሩሲያ") ሲታገሡ ይገባል (ያዕ. 5፥7–8)። "አፖካሉብሲስ" እና "ፓሩሲያ" የሚሉት ቃላት "የጌታን ቀን" ለማሳየት ሥራ ላይ ውለዋል (1ቆሮ. 1፥7፤ 2ተሰ. 2፥1፤ 2ጴጥ. 3፥4, 8–12)። "አፖካሉብሲስ"፣ "ኢፒፋኒያ"፣ "ኤርኮማይ" እና "ፓሩሲያ" የሚሉት ቃላት ክርስቶስ በኃጢአተኞች ላይ ሊፈርድ እንደሚመጣ ለማሳየት ጥቅም ላይ ውለዋል (ማቴ. 24፥50–51፤ 25፥31–46፤ 2ተሰ. 1፥7–10፤ 2፥8)። የክርስቶስ "ምጽአት"



("ኤርኮማይ" ወይም "ፓሩሲያ") በኃጢአተኞች ላይ "እንደ ሌባ" ሲመጣ ስላለው የጌታ ቀን፥ (የፍርድ ቀን) ለማሳየት በጥቅም ላይ ውለዋል (ማቴ. 24፥42–44፤ ሉቃ. 12፥36–40፤ 1ተሰ. 5፥1–4፤ 2ጴጥ. 3፥10፤ ራእ. 16፥15)። ኢየሱስ የእርሱን "መገለጥ" እና "ምጽአት" ("አፒፋኒያ"፥ "ፓሩሲያ") በቅድስናና ነቀፋ በሌለበት ሕይወት መጠበቅ እንዳለብን አስተምሮአል (1ተሰ. 3፥13፤ 5፥23፤ 1ጢሞ. 6፥11–14፤ 2ጢሞ. 4፥1–5፤ 2ጴጥ. 3፥9–12፤ 1ዮሐ. 2፥28)። ኢየሱስ "ሲመጣ" ("ኤርኮማይ"፥ "ፓሩሲያ") አማኞች ከእርሱ ጋር ለመሆን ይሰበሰባሉ (ማቴ. 24፥31፤ 1ተሰ. 4፥16–17፤ 2ተሰ. 2፥1)።

ኢየሱስ የሚመጣው በአካል እየታየ ነው። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ እንደመጣ ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ዳግም ምጽአቱንም ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሎአል፦ ኤርኮማይ "መምጣት" (ዮሐ. 1፥9፤ 3፥31፤ 8፥14፤ 9፥39፤ 18፥28፤ 1ጢሞ 1፥15፤ 1ዮሐ. 4፥2–3፤ 2ዮሐ. 7)። "ኢፒፋኒያ"፦ "መገለጥ" ወይም "መታየት" (2ጢሞ. 1፥10)፥ "ፋኔሮ"፦ "መታየት" ወይም "መገለጥ" (1ጢሞ. 3፥16፤ ዕብ. 9፥26፤ 1ጴጥ. 1፥20፤ 1ዮሐ. 1፥2፤ 3፥8)። እነዚህ ቃላት ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ በአካል መገለጡን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውለዋል፦ "ኤርኮማይ" (ዮሐ. 20፥19, 24, 26፤ 21፥13) "ፋኔሮ" (ዮሐ. 21፥1, 14)። ኢየሱስ በአካል ከሙታን ስለ ተነሣ በአካል እየታየ መምጣቱ አይቀሬ ነው።

እስከ አሁን ካየናቸው ማስረጃዎች በተጨማሪ ክርስቶስ በአካል እየታየ እንደሚመጣ የሚያስተምሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ማቴ. 23፥39 የእስራኤል ነገዶች ንስሐ ገብተው ኢየሱስን እስከሚባርኩበት ጊዜ ድረስ ኢየሱስን አያዩትም። ይህ የሚያሳየን ወደፊት ዳግም የማየት ዕድል እንዳላቸው ነው። የሐዋ. 3፥20–21 እግዚአብሔር ኢየሱስን ዳግም ልኮት እንደሚመጣ ያስተምረናል። 1ተሰ. 4፥16 "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና" "ጌታ ራሱ" የሚለው የአጽንኦት ቃል እየታየ ወደ ላይ የወጣው ራሱ እንደሚመጣ የሚያሳይ እንጂ ትርጉም የሌለው ድግግሞሽ አይደለም። ዕብ. 9፥26–28 በመጀመሪያ ክርስቶስ የተገለጠው ስኃጢአተኞች ለመሞት ነበር። አሁን ግን ዳግም የሚታየው የዳኑትን ለመሰብሰብ ነው።

የኢየሱስ መንግሥት መግዛት የጀመረው በዕርገቱና በትንሣኤው ጊዜ ነው። የሐዋ. 4፥25–27 መዝ. 2፥1–2 ኢየሱስ በዕብራውያንና በሮማውያን ስሞት አሳልፎ ተሰጠ። ኢየሱስ በክብር በእግዚአብሔር

ቀኝ የተቀመጠው በ33 ዓ.ም. ነው (የሐዋ. 13፥22-33፤ ዕብ. 1፥3-5፤ 5፥5፤ መዝ. 2፥7)። ኢየሱስ በትንሣኤ ከሙታን መነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ገልጾዋል (ሮሜ 1፥4)። ኢየሱስ ሥልጣን ተቀብሎአል። ይህም ሥልጣን "እስከ ዓለም ፍጻሜ" ነው (የሐዋ. 1፥8፤ ራእ. 2፥28-27፤ መዝ. 2፥8-9። ማቴ. 28፥18-20) ለኢየሱስ ሥልጣን በሰማይና በምድር ተሰጥቶታል። ይህም የኢየሱስን ዓለማቀፋዊ ሥልጣን የሚያሳይ ነው። ለንጉሣዊ ቃሉም ሰዎች እንዲታዘዙ እናስተምራለን።

የንጉሡ መልካም ዜና የደኅንነት መልእክት ነው። ይህ መልካም ዜና በመጀመሪያ በሐዋርያት ተሰብኩአዋል (የሐዋ. 8፥12፤ 20፥25፤ 28፥23, 31)። በክርስቲያኖች መሰበክ ያለበት የደኅንነት መልካም ዜና ወይም ወንጌል አንድ ብቻ ነው (ገላ. 1፥6-8፤ 2ቆሮ. 11፥4)። የደኅንነት መልካም ዜና የመዳን ምልክት ነው። ይኸውም ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት ትክክለኛ ግንኙነት ማድረግ ነው (ሮሜ 1፥16-17)። የምሥራቹም መሠረት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው እንጂ በ1814 ዓ.ም. ሆነ የሚባለው ነገር አይደለም (1ቆሮ. 15፥3-4)። የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅ፥ ሰላም፥ ደስታ በመንፈስ ቅዱስ ማድረግ ነው (ሮሜ 14፥17)። በረከትን በእምነት የምንቀበለው ከሞተውና ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣው ኢየሱስ ነው (ሮሜ 5፥11)።

## የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች ?

1. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት 1674 ዓ.ም.ን፥ 1925 ዓ.ም.ን፥ 1975 ዓ.ም.ን አስመልክቶ ያስተላለፋቸው ትንቢቶች ትክክል ካልነበረ ድርጅቱ በምድር ላይ የሚገኝ የአምላክ ብቸኛ ወኪል፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መንፈሳዊ ምግብ የሚያወርድበት ብቸኛ ድልድይ እንዴት ሊሆን ይችላል?
2. በአሁኑ ጊዜ በድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡት ጽሑፎች የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1814 ዓ.ም. ነው እያሉ የጥንቶቹ ጽሑፎች ደግሞ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1674 ዓ.ም. ነው ይሉ የነበረው ለምንድን ነው? እውነተኛ የአምላክ ነቢይ ትንቢቶቹን እንዲህ አድርጎ ሊቀያይር እንዴት ይችላል?



3. የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ ለሙሉ የሚመሠረተውና የሰበአውያን አገዛዝ የሚያከትመው በ1914 ዓ.ም. ነው ይል የነበረው የድርጅቱ ትንቢት ለምን ተፈጻሚነት አላትገኘም? ትንቢቱ ተፈጻሚነት ያለማግኘቱ ድርጅቱንና የድርጅቱን ነቢያት ሐሰተኞች አያደርጋቸውምን?
4. በ1925 ዓ.ም. አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ እንዲሁም የብሉይ ኪዳን ነቢያት "ንጉሥ" ሆነው በምድር ላይ መኖር ይጀምራሉ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትንቢት ለምን ተፈጻሚነት ሳያገኝ ቀረ? እግዚአብሔር ሐሳቡን ቀይሮ ነው? እግዚአብሔር ሐሳቡን የማይቀይር ከሆነ ይህን ትንቢት የተነበየው ድርጅት ሐሰተኛ ነቢይ ሊባል አይገባውም?
5. የ6000 ዓመት የሰው ልጆች ታሪክ የሚጠናቀቀው በ1873 ዓ.ም. ነው የሚለው የድርጅቱ ትንቢት ወደ 1978 ዓ.ም. ተሸጋግሮ ነበር። ነገር ግን በሁለቱም ጊዜ የመጠበቂያ ግንብ ትንቢት ትክክል ሆኖ አልተገኘም። ይህ ጉዳይ ድርጅቱን ሐሰተኛ ነቢይ አያደርገውም?
6. የሰው ልጆች ታሪክ የሚጠናቀቀው በአርማጌዶን ጦርነት በ1975 ዓ.ም. ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትንቢት ትክክል ያለመሆኑ ስለ ድርጅቱ ምን ያስተምረናል?
7. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት 1874 ዓ.ም.፥ 1914 ዓ.ም. 1825 ዓ.ም. እና 1975 ዓ.ም. አስመልክቶ ያስተላለፋቸው ትንቢቶች ፍጹም ሐሰተኛ መሆናቸው ድርጅቱን መንፈሳዊ ምግብ እንደሚያወርድ የአምላክ ብቸኛ ድርጅት አድርገን እንድንቀበለው ያደርገናል?
8. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከመሆኑ በፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ከማቴ. 24፥28-30 እናነባለን፦ "ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃል፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል" የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1914 ዓ.ም. ከሆነ በ1914 ዓ.ም. ወይም በ1874 ዓ.ም. የሚከተሉት ነገሮች ሆነው ነበር፦
    - ፀሐይ ጨልሞ ነበር?
    - ጨረቃም ብርሃንዋን አልሰጥም ብላ ነበር?
    - ከዋክብትስ ከሰማይ ወደ ምድር ወድቀው ነበር?
    - የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ብለው ነበር?
9. ክርስቶስ ቢያርግ ደመና እንደተቀበለው አመጣጡም ከመሄዱ ጋር አንድ ዓይነት መሆኑ ("እንዲሁ") የኢየሱስ ዕርገት በአካል እየታየ መሆኑን አያስተምረንም?

10. በሐዋ. 1፥9 "ደመና" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች የሚያዩትን የእግዚአብሔር ክብር የሚያሳይ (የሚያመለክት) ነው (ማቴ. 17፥5፤ 24፥30፤ 26፥64)። በብሉይ ኪዳንም እንደዚሁ ነው (ዘጸ. 16፥10፤ 40፥34–35፤ 1ነገ. 8፥10–11) ። "ደመና" የሚለው ቃል የሚታየውን የእግዚአብሔር ክብር የሚያመለክት ከሆነ፤ ኢየሱስ ሲያርግም ሆነ ዳግም ሲመጣ "በደመና" መሆኑ በክብር እየታየ መምጣቱን አያመለክትም?

11. ራእ. 1፥7 ያለ ምንም የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ወይም ጽሑፍ ረዳትነት ለመጀመርያ ጊዜ ብናነበው ኢየሱስ በጠላቶቹ እንኳ እየታየ እንደሚመጣ የሚያሳየን አይሆንም ነበር? በ1914 ዓ.ም. የምድር ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ብለው ነበር?

12. ነቢያት ትንቢታቸው ሐሰተኛ ሆኖ ሐሰተኛ ነቢያት አይደላችሁም ሊባሉ ይችላሉ? [የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ራሱ በርካታ ትንቢቶቹ ትክክል እንዳልነበሩ ያምናል]።

13. ነቢያት "የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል. . . " ብለው ትንቢታቸው ግን ሐሰት መሆኑ የተረጋገጠባቸው ነቢያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ? አንድ ማስረጃ እንኳ ካቀረቡ በቂ ነው [ዮናስ 3፥1 እንዲሁም 1ዜና 17፥2 ቢጠቅሱ እነዚህ ጥቅሶች ነቢያቶቹ ሐሰተኛ ትንቢት እንዳላስተላለፉ ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይከልሱ]

14. በነቢያት አፍ ቃሉን የሚጨምር እግዚአብሔር ከሆነ (ዘዳ. 18፥18፤ 2ሳሙ. 23፥2፤ የሐዋ. 4፥24–25፤ 1ቆሮ. 2፥13) ነቢያት ሐሰት ሊናገሩ ይችላሉ? ሐሰት ከተናገሩ ግን ትንቢታቸው ከእግዚአብሔር ነው ማለት እንችላለን? እነርሱንስ ሐሰተኛ ነቢያት የማንልበት ምክንያት ምንድን ነው?

15. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት እንዲህ ይላል፡– "ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው" ( ዘዳ. 18፥22) "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችው በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን፥ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?



እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል" (ማቴ. 7፥15–17) ከዚህ ምን እንማራለን?

16. "ፓሩሲያ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሌላ የክርስቶስን በአካል እየታየ መምጣትን የሚያስተምሩ ብዙ የግሪክ ቃላት አሉ። ለምሳሌ ከላይ የተመለከትናቸው "ኤፒፋኒያ"፥ "ፋኒሮ"፥ "ኤርኮማይ"፥ "አፖካሉብሲስ" ወዘተ። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ እንደመጣ ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋሉት እነዚሁ ቃላት ዳግም ምጽአቱንም ለማሳየት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህስ ምን ያስተምረናል?

17. በቀድሞ ክርስቲያኖች የተሰበከው የደኅንነት መልእክት እና በአሁኑ ዘመን ክርስቲያኖች መስበክ ያለበት መልእክት የተለያየ ነው (የሐዋ. 8፥12፤ 20፥25፤ 28፥23, 31፤ ገላ. 1፥6–9፤ 2ቆሮ. 11፥4)? የተለያየ መሆን ከሌለበት ከ1914 ዓ.ም. ወዲህ በመስበክ ያለበት ወንጌል ከቀድሞው የተለየ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል?

18. የክርስቶስ ምጽአት አስመልክቶ የሚተነበዩት ትንቢቶች ሐሰት መሆን ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያስከትል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን (ማቴ. 24፥23–27፤ ሉቃ. 21፥8፤ 2ተሰ. 2፥1)። እነዚህ ክፍሎች ስለ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት ምን ያስተምሩናል?

19. "ኪንግደም ሚኒስትሪ" [Kingdom Ministry, May 1974, ገጽ. 3]የሚባለው የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፍ የኃጢአተኞች ዓለም ከመጥፋቱ በፊት ቤታችሁንና ንብረታችሁን በመሸጥ በአቅኚዎች አገልግሎት ውስጥ ለመግባት 1974 ዓ.ም. አጭሩና መልካሙ መንገድ ነው ብሎ ነበር። ይህም ለብዙ ይሖዋ ምስክሮች ተስፋ መቁረጥና ድርጅቱን ለቆ ለመውጣት ምክንያት ሆኖ ነበር። በዚያን ዘመን የይሖዋ ምስክር ብትሆንና ይህን የመሰለውን የድርጅቱን ጥሪ አክብረህ ቤትህንና ንብረትህን ሸጠህ የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ("አቅኚ") ብትሆን 1975 ዓ.ም. ሲያልፍ ትንቢቱ ሐሰት መሆኑን ብታውቅ ምን ይሰማሃል? እንዲህ አድርጎ ያታለለህንስ የሃይማኖት ድርጅት የእግዚአብሔር ብቸኛ የሆነ ምድራዊ ወኪል ነው ለማለት ትደፍራለህ?

# ምዕራፍ አራት

## ሰዎችን ከመናፍቃን እንዴት እንጠብቅ?

4.1 ሰዎች መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ? .... 151
4.2 ሰዎች መናፍቃንን እንዳይከተሉ እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን? ........ 155
4.3 የይሖዋ ምስክሮችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ተመካሪ አቀራረብ ........................................ 160



## 4.1 ሰዎች መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ[1]?

### I. አጠቃላይ እሰሳ

### 1. የግል ፍላጎት

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች የራሳቸው የሆነ ችግር አለባቸው። መናፍቃን ደግሞ ይህን ችግር እንደሚፈቱላቸው ቃል ይገቡላቸዋል። እንዲያውም ለችግሩ አማራጭ የማይገኝለት ብቸኛው መፍትሄ በእነርሱ ዘንድ ብቻ እንደሚገኝ ይናገራሉ። መናፍቃን የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ሰጥቂት ጊዜ ሊያሙአሉ ይችሉ ይሆናል። ይሁን እንጂ ለችግሮቹ የሚሰጡት መፍትሄ ዘላቂነት የለውም። ምክንያቱም ለሰዎች ችግር ትክክለኛ መፍትሄ ሊሰጥ ከሚችለው እውነተኛው ወንጌል ስለራቁ። ከዚህም የተነሣ የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ማሙአላት ይሳናቸዋል። ቋሚና ዘላቂ በሆነ መንገድ የሰዎችን ጥያቄ መመለስና የውስጥ ፍላጎታቸውን ማርካት የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።

ክሩት ቫን ጎርደን የሚባለው የሥነ መለኮት ሊቅ "መናፍቃንን በወንጌል መድረስ" በተሰኘው መጽሐፉ ላይ ሰዎች መናፍቃንን በመከተል ሊያረኩት የሚፈልጉትን ፍላጎት በአራት ክፍል መድቦታል። ይኸውም አእምሮአዊ ፍላጎት፥ ስሜታዊ ፍላጎት፥ ማኅበራዊ ፍላጎትና፥ መንፈሳዊ ፍላጎት ናቸው[2]። እነዚህ ፍላጎቶች በራሳቸው መጥፎነት የላቸውም ማንኛውም ሰው በተለያየ መጠን እነዚህ ፍላጎቶች አሉት። እነዚህን ፍላጎቶች በእግዚአብሔር ቃል እውነት አለማርካት ሰዎችን በመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገቡ ሊያስገድዳቸው ይችላል።

### 2. የአስተምህሮ ምክንያት ሊሆን ይችላል

ሰዎች ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ከተረዱ በኋላ የተረዱትን እውነት ትተው በመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ አይገቡም ብሎ ማሰብ ትክክል ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በአንጻራዊነት ሲታይ በዚህ መልኩ መናፍቃንን የሚከተሉ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው።

---

1. ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው Alan W. Gomes. Unmasking the Cults በሚል ርዕስ ከጻፈው መጽሐፍ ላይ ነው። (Grand Rapids: Zondervau, 1995) ገጽ. 81-85
2. Kurt Van Gorden, "Unity School of Christianity" in Evangelizing the Cults, ገጽ. 140. Cited in Alan W. Gomes. ገጽ. 81

## 3. ቤተ ክርስቲያን ማሙአላት ያሰባትን ሳታሙአላ ስትቀር

ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንድታሙአላላቸው የሚፈልጉት ሳይሙአላላቸው ሲቀር መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ሊጀምሩ አልያም በተጀመረው እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ሦስት አራተኛ የሚሆኑት የሞርሞንስ አባሎች በአንድ ወቅት የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አባላት[3] የመሆናቸው ጉዳይ ይህንኑ እውነት የሚያጠናክር ነው።

ቫን ባለን መናፍቅነትን "ያልተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ[4]" ብሎ ይጠራዋል። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መሙላት ያቃታትን ባዶነት መናፍቃን እየሞሉ ብዙዎችን በማሳሳት ላይ ስላሉ ነው። የመናፍቃን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት የቤተ ክርስቲያንን ጉድለት ያሳያል። በሌላ አነጋገር የቤተ ክርስቲያን መድከም ለመናፍቃን መበራከት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጎአል። እንዲህ ሲባል ግን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ረገድ ያከናወነችው ምንም ነገር የለም ማለት አይደለም። ይብዛም ይነስ ቤተክርስቲያን ለነገሩ ቦታ ሰጥታ የምትችለውን ሁሉ ስታደርግ ቆይታለች። ባንጻሩም ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ማርካት የምትችለው የግለሰቦቹ ጥረትና ፈቃደኝነት ሲታከልበት ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን የአባሎቹአን መንፈሳዊ፥ አእምሮአዊ፥ ማኅበራዊና፥ አካላዊ ፍላጎት በእግዚአብሔር ቃል እውነት ዘወትር የምታረካበት መንገድ ሊኖር ይገባል።

3. Josh Mc Dowell and Don Stewart, Assisted by Kurt Van Gorden. The Deceivers: What Cults Believe, How They Lure Followers. (San Bernardino, Calif: Here's Life Publishers, 1992). ገጽ. 16

4. Van Baalen. Chaos of the Cults. ገጽ. 390



## II. ሰዎች መናፍቃንን በመጠጋት ሊያሙአሉ የሚፈልጉት ፍላጎት

### 1. ፍቅር

ሰዎች መናፍቃንን ከሚጠጉበት ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ፍቅርና እንክብካቤ ፍለጋ ነው። ይህን በበቂ ሁኔታ ካገኙ ባገኙበት ስፍራ እስከ መጨረሻው ለመቆየት ይገደዳሉ። መናፍቃንን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በጣም አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ይህ ነው።. ሰዎች "ዩኒቲ እስኩል ኦፍ ክርስቲያኒቲ" በሚባለው የመናፍቃን ድርጅት እንዲሳቡ የሚያደርጋቸው ድርጅቱ ለፍቅር ከፍተኛ ስፍራ ስለሚሰጥ ነው[5]።

### 2. ቤተሰብ

ወጣቶች መናፍቃንን ከሚከተሉበት ምክንያቶች አንዱ ለጊዜውም ሲሆን የሚያስጠጋቸው ቤተሰብ ለማግኘት ነው። የቤተሰብ መፍረስና በወላጆችና በልጆች መካከል የማያቋርጥ ጠብ መኖር እንዲሁም አግባብ ባልሆነ መንገድ ልጆችን መቅጣት፥ ወጣቶች አዲስ ቤተሰብ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል።

### 3. ተፈላጊነትና ክብሬታን ማግኘት

ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ካጡ ወይም ቤተሰባዊነት የማይሰማቸው ከሆነ በአደገኛ ሁኔታ ለመናፍቃን እንቅስቃሴ ይጋለጣሉ። ተፈላጊነትን፥ ተቀባይነትንና ክብሬታን እናገኝበታለን ብለው ወደሚያስቡት ስፍራ ለመሄድ አያቅማሙም። ብዙ መናፍቃን ደግሞ ተፈላጊነትን፥ ተቀባይነትንና ክብሬታን ያለገደብ እንደሚሰጡ ያውጃሉ። ታዲያ እነዚህ ነገሮች አጥብቆ ይፈልጋቸው የነበረውም ሰው በቀላሉ ይወሰዳል።

መናፍቃን ለተራው አባል እንኳ ትልቅ የሆነ የአገልግሎት ስፍራ ይሰጣሉ። ይህም የእያንዳንዱን አባል አስፈላጊነት ከፍ ያደርገዋል። ሞርሞኖች "ክህነታዊ ሥራ" ያሚሉትን አገልግሎት ትኩረት ይሰጡበታል። ወጣቶቻቸው የሁለት ዓመት ሚሲዮናዊ ሥራ ይሠራሉ። የይሖዋ ምስክሮች አባሎቻቸውን ሁሉ በማንቀሳቀስ ቤት ለቤት በመሄድ እንዲሁም በየመንገድ ዳሩ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ወንጌልን እንዲሰብኩ ጽሑፍን እንዲያሠራጩ ያደርጉአቸዋል።

5. Mc Dowell and stewart. The Deceivers. ገጽ. 18.

### 4. አካላዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ መናፍቃን ሰናይ ምግባርን ሲያከናውኑ ይታያል። ይኸውም የተራበን ያበላሉ፥ የታረዘን ያለብሳሉ፥ ቤተሰብ የሌላቸውን ልጆች በማደጎ ወስደው ያሳድጋሉ። ለትምህርት ያላቸው ዕቅድ እንዲሁም ድርጅቶቻቸውን ለማስተዋወቅ የሚጠቀሙበት መንገድና ዘዴ እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀማቸው ከኛ እጅግ ብዙ ርቀው እንዲሄዱ አድርጎአቸዋል።

### 5. መንፈሳዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት መንፈሳዊ ረሀባቸውን ለማጥገብ ነው። መንፈሳዊ ረሃብ በማጥገብ ረገድ "የእምነት እንቅስቃሴ" በሚል ስም በመዲናችን እየተንቀሳቀሰ ያለው ትምህርት እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል። ብዙ ወጣቶችን በአምልኮ አቀራረባቸው በመማረክ ከየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዲፈልሱ አድርጎአቸዋል። የሚያሳዝነው ግን ይህ እንቅስቃሴ የአምልኮ አቀራረቡን አሳምሮ ወጣቶችን እየመገበ ያለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የትምህርቱን ሰንኮፍ ከተነደፉት ወጣቶች ላይ መንቀል እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ ነው[6]። መናፍቃን የእነርሱን ሥርዓተ አምልኮ መከተልና ፕሮግራማቸውን በተከታታይ መካፈል ለመንፈሳዊ እርካታ አምብርት እንደሆነ ይናገራሉ።

### 6. ለአእምሮአዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

ሰዎች በተለይም ወጣቶች መናፍቃንን የሚፈልጉት ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለማግኘት ነው። በዚህ ረገድ የይሖዋ ምስክሮችን እንደ አብነት ልንጠቅስ እንችላለን። የይሖዋ ምስክሮች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት ያለምንም ገደብና ቅድመ ሁኔታ እንደሚያምኑ ይናገራሉ። ሆኖም የግሪክና የዕብራይስጥ በኩረ ጽሑፋትን እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ታሪክን አጣመው ያቀርባሉ። እውቀት ፈላጊው ሰው በዚህ ሁኔታ በቀላሉ ይታለላል።

6. እዚህ ላይ ተሾመ ነጋሽ እስከመጣ ድረስ በሚል ርዕስ እንዲሁም ግርማ ቡሾ የእምነት እንቅስቃሴ የዘመኑ ወንጌል በሚል ርዕስ የጻፍዋቸውን መጻሕፍት ማንበብ ጠቃሚ ነው።



### 7. ሁለገብ የሆነ አኗኗር

አንዳንድ ሰዎች መናፍቃንን የሚጠጉት በአኗኗር ዘይቤአቸው ፈጣን ለውጥ ወይም መሻሻል ስለሚያሳዩ ነው። ለምሳሌ፦ በሲጋራ፥ በመጠጥና፥ በአደንዛዥ ዕጾች ሱስ የተለከፈ ሰው በመናፍቃን ሥነምግባር ሊሳብ ይችላል። ምክንያቱም በርካታ መናፍቃን ቅድስናን አድርግና አታድርግ ከሚሉት ሕጎቻቸው ጋር ብቻ ስለሚያያይዙት ሁለገብ አኗኗር [Wholesome Lifestyle] ሊያሳዩ ይችላሉ። እንዲሁም እንደ ሞርሞንስ የመሳሰሉት እምነቶች ከማጨስ፥ ከመጠጣትና ከመደነስ በተጨማሪ እንደ ቡናና ለስላሳ መጠጦች መራቅ ለቅድስና እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አጠንክረው ስለሚናገሩ በእኩይ ምግባር የተቸገረ ሰው በቀላሉ ሊሳብ ይችላል።

## 4.2 ሰዎች መናፍቃንን እንዳይከተሉ እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን[1]?

ሰዎች መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ከመንፈቃቸው በፊት ወደዚያ የሚወስዳቸውን መንገድ ማጠር ጠቀሜታው ታላቅ ነው። ሰዎች በመናፍቃን ተታለው ከመወሰዳቸው በፊት ልንወስዳቸው የሚገቡ መሠረታዊ እርምጃዎች አሉ። ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን ዘዴዎች መጠቀም አስፈላጊ ቢሆንም እነዚህ ዘዴዎችን እንኳን ተጠቅመን ሰዎች መናፍቃንን ሊከተሉ ይችላሉ። በእርግጥ ሰዎች መናፍቃንን እንዲከተሉ የሚያስገድዳቸውን ሁኔታዎች ማጥበብ ይቻላል፤ ነገር ግን ፈጽመን መዝጋት ወይም ማጠር አይቻልም።

### I. መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለቤተ ክርስቲያንህ ማሳየት

### ሀ. ቤተ ክርስቲያን ከመናፍቃን ልትማር ያስፈልጋታል

መናፍቃን መናፍቅ ወይም ሐሰተኞች ስለሆኑ "ከእነርሱ የምንማረው አንዳች ነገር የለም" ብሎ ማሰብ ፍጹም አግባብ አይደለም። መናፍቃን ሰዎችን የሚስቡት ሰዎች የሚፈልጉት ነገር [እውነት ባይሆንም እንኳ] እነርሱ ዘንድ ስላለ ነው። መናፍቃን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት በቤተ ክርስቲያን ደካማ ጎኖች ላይ ስለሆነ ለእነርሱ እድገት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በመመርመር ቤተ ክርስቲያን ድካሙአን አሻሽላ መቅረብ አለባት።

1. ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው፦ Alan W. Gomes, Unmasking the Cult. (Grand Ra.: Zondervan 1995) ገጽ. 86-90 በሚል ርዕስ ከጻፈው መጽሐፍ ላይ ነው።

ብዙ ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት በሕይወታቸው ለሚገጥማቸው ተገቢ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እስከሆነ ድረስ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ፍላጎቶች በማጥናት ቃለ እግዚአብሔር እነዚህን ፍላጎቶች በሚመልስበት መልኩ ልትመልስ ይገባታል። "ለምንድነው ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ከመናፍቃንና ከሌሎች የሃይማኖት ቡድኖች ለተገቢ ጥያቄዎቻቸው መልስ ያገኙት?" የሚለውን ጥያቄ ነው ቤተ ክርስቲያን ራሷን ልትጠይቅ የሚገባት። ቤተ ክርስቲያን መናፍቃን ለሰዎች ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ልትሰማ እንዲሁም እነዚህን ጥያቄዎች ጌታ በመስሰበት መንገድ ልትመልስ ይገባታል።

ሰዎች መናፍቃን የሚሆኑት ተገቢ ከሆነው አእምሮአዊ፥ ማኅበራዊ፥ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማርካት ከሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍላጎቶች በሚያረካበት መንገድ በማርካት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትናን በቤተ ክርስቲያን ማጎልበት አለብን።

## ለ. የአባሎቻችንን አእምሮአዊ ፍላጎት ማርካት አለብን

ክርስቲያን የሚያምነውን እንዲሁም ለምን ማመን እንዳለበት ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው ብዙ ሰዎች የሚያምኑትን ያውቃሉ፤ ነገር ግን ለምን እንዳመኑ በጭራሽ አያውቁም። እንዲያውም የበለጠ ቁጥር ያላቸው ምን እንደሚያምኑም ሆነ ስምን በዚህ መልኩ ማመን እንዳስፈለጋቸው ጨርሶ አያውቁም።

ክርስቲያን በእምነት እውነት ላይ ሊተከል ይገባዋል። ማንኛውም ክርስቲያን አስተምህሮተ ሥላሴን፥ የክርስቶስን ፍጹም ሰብአዊነትና አምላክነት፥ የክርስቶስን የአካል ትንሣኤ፥ እንዲሁም ደኅንነት በእምነት አማካኝነት በጸጋ መሆኑን ከቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

ክርስቲያን ምን እንደሚያምንና ለምን እንደሚያምን መከላከያ ነጥብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማቅረብ ካልቻለ ለመናፍቃን ትምህርት የተጋለጠ ነው። ማርቲን እንደሚለው "ከመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ለዘጠና ቀን የቆየ የይሖዋ ምስክር አማካይ [average] ክርስቲያንን በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ እምነታቸውን ሊያስጥል ወይም ሊያደናግራቸው ይችላል"።

እውነት የገባው አማኝ በማስረጃ ተብዬዎች አይሞኝም የባንክ ሠራተኞች ከጤናማው ብር ጋር የዕለት ተዕለት ቅርርብ ስላላቸው



ሐሰተኛ ኖቶችን ወዲያውኑ ያውቁአቸዋል። እንደዚሁም ክርስቲያኖች የመናፍቃንን ስህተት ለማወቅም ሆነ ለጥያቄአቸው በቂ መልስ ለመስጠት እውነተኛውን አስተምህሮ እንደሚገባው ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ክርስቲያን ከፀሐይ በታች ያሉትን የመናፍቃን አስተምህሮ ሁሉ ማወቅ አያስፈልገውም። ነገር ግን ዋና ዋና መናፍቃንንና የመናፍቃንን ተመላሳይ ባሕርይ ማወቅ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ለትሰጥና በመናፍቃን ለተጎዱት ሰዎች የማገገሚያ ትምህርት ስታስተምር፥ ጊዜዋንና ጉልበቱአን በከንቱ ለታባክን ኑፋቄ የብዙዎችን እምነት ሲብሮ መግባቱ ብዙ ሳያስደንቅ ይችላል።

ሰዎች እምነታችንን በተመለከተ የሚጠይቁንን አእምሮአዊ ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መመለስ ካልቻልን ከባድ አጣብቂኝ ነው የሚገጥመን። ለምሳሌ፦ አንዲት እኅት ለአንድ እስላም ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ልትነግረው ፈለገች እንበል። እስላሙ አምላኳ እንዴት አንድም ሦስትም እንደሆነ እንድታብራራለት ፈለገ። እሷም "ሥላሴ ልታምነው የሚገባህ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህ ትምህርት እንዲገባህ በጾም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ስትወድቅ እግዚአብሔር ራሱ ይገልጽልሃል" አለችው።

ከዚህ ውይይት ብዙ ነገር መመልከት ይቻላል። አንደኛው የሥላሴ ትምህርት ስሜት የማይሰጥ፥ በሥነ መስኮትም ሆነ በአመክንዮ መሠረት የሌለው፤ ነገር ግን ዕውር በሆነ እምነት የሚታመን ነው ልጅት ያደረገችው። ሌላው "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ስሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ"። (1ጴጥ. 3፥15) የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ አልኖረችበትም።

ቤተ ክርስቲያን ስለ መናፍቃን ልታስተምር ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን ቅድሚያ በመስጠት የመናፍቃንን መሠረተ እምነት እንዲሁም የተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ምን እንደሚያምኑና ለምን እንደሚያምኑ ማስተማር ይገባል። ይህም ትምህርት ክርስቲያኖችን ስምስክርነት ብቁ ያደርጋቸዋል። ተቃውሞአቸውንም ስመመለስ የምናጠናው ጥናት እምነታችንንም ሆነ እውቀታችንን ያጠነክረዋል።

ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ የሚረዳቸውን ትምህርት ልታስተምር ይገባታል [ለምሳሌ፦ ሥነ አመክንዮ (Logic)]። ክርስቲያኖች ምን ማመን እንዳለባቸውና የትኛውን ማመን እንደሌለባቸው ማስተማር ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን

እውነቱን ከውሸት የሚለዩበትን ዘዴ ማሳወቅ አግባብ ነው። ክርስቲያን እውነትን የሚገመግምበትንም ሆነ ሐሰት የሆነውን ነቅሶ የሚያወጣበትን እውቀት ካላገኘ "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ"። የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ተግባራዊ ያደርገዋል? "እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ እየተንሳፈፍን ሕጻናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም" (ኤፌ. 4፥14)።

## ሐ. የሕዝባችንን ማኅበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ማርካት አለብን

ልብንና አእምሮን ሊነካ የሚችል የአምልኮ መንፈስ መፍጠር ወይም ማዳበር አለብን። መናፍቃን ቅናት [Zeal] አላቸው። ነገር ግን ቅናታቸው ያለ እውነተኛ እውቀት ነው (ሮሜ 10፥2)። በተቃራኒው እውነተኛ ክርስቲያኖች እውነትን ይዘው ሳለ መጠነኛ ቅናት ነው ያላቸው። በሚዛናዊነት የተሞላው የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ግን ቅናት ከእውቀት ጋር ነው (2ጴጥ. 1፥3–8)።

የቤተ ክርስቲያን አባሎችን መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት የቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነቶችን አጠንክረን ልናስተምር ይገባል (1ጴጥ. 2፥2፤ 2ጢሞ. 3፥16)። በተጨማሪም አእምሮንና ስሜትን ሊነካ የሚችል አምልኮ መፍጠር አለብን።

## II. መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለልጆችህ ማሳየት

## ሀ. ጠንካራ ቤተሰብ ልጆቹን ከመናፍቃን በመከላከል ቁልፍ ሚና ይጫወታል

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በማንኛውም ጉዳይ ላይ በግልጽ መወያየትን ባህል ካደረጉ መንፈሳዊውን ነገር ለመወያየት አዳጋች አይሆንባቸውም። በእርግጥ ልጆች ስለተለያዩ መናፍቃንም ሆኑ ሃይማኖቶች የመስማት ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን መልካም ግንኙነት ለውይይት መሠረት ነው።

ስለ እምነትህ ከልጆችህ ጋር በግልጽነት ተወያይ። ወላጆች ልጆቻቸውን በተመመለከተ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ የማስተማርም ሆነ መመሪያ የመስጠት ተቀዳሚ ኀላፊነት አለባቸው (ኤፌ. 6፥4)። ስለዚህ ተቀዳሚ ኀላፊነታቸውን በሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ትከሻ ላይ መጣል አግባብ አይደለም።



## ለ. እንደማንኛውም ግለሰብ ልጆችህን አክብር

እንደማንኛውም ግለሰብ ልጆች እንዲከበሩ ይፈልጋሉ። ከቤተሰቦቻቸውም የተለየ ማንነት አላቸው። ወላጆች ልጆቻቸው ማንነታቸውን ሊገልጹ የሚፈልጉበትን ተገቢውን ነጻነት ሊነፍጉአቸው አይገባም። ይህን ማጣት ልጆች ወደ መናፍቃን እንዲሄዱ ሊገፋፉቸው ይችላል። መናፍቅም በመሆን ከቤተሰቦቻቸው የተለየ ማንነት እንዳላቸውና የተለየ የአኗኗር ዘይቤ እንደሚከተሉ ማሳያ መንገድ አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የመናፍቃንን የአኗኗር ዘይቤ በመከተልም ከቤተሰቦቻቸው ራሳቸውን ሊለዩ ይችላሉ።

ብልኀ ወላጆች የልጆቻቸውን ማንነት መግለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ለምሳሌ እንደ አለባበስ፥ አበጣጠር፥ ወዘተ ያሉትን እንዲያደርጉ ይፈቅዱላቸዋል። በነገር ሁሉ ስኬታማ የሚሆኑበትን መንገድ ያመቻቻሉ። ብዙ መናፍቃን የስኬታማነትን አጭር መንገድ እናሳያለን ስለሚሉ ልጆች በዚህ ማነቆ ተጠምደው መናፍቃንን ሊከተሉ ይችላሉ።

## ሐ. የልጆችህን ጥያቄ በአንክሮ ልትመለከተው፥ አጥጋቢ መልስም ልትፈልግለት ይገባሃል

አንዳንድ ልጆች ለመንፈሳዊ ጥያቄዎቻቸው መልስ ፍለጋ መናፍቃንን ሊከተሉ ይችላሉ። ልጆች ጥያቄዎቻቸው በአጥጋቢ ሁኔታ ካልተመለሰ ጥያቄአቸውን ሊመልሱ ወደሚችሉት መልስ ሰጪዎቻቸው እምነትና የአኗኗር ዘዴ መሄዳቸው አይቀሬ ነው። ወላጆች የማያውቋቸውን ሥነ መለኮታዊ ጥያቄዎች ያለማወቃቸውን በግልጽ በመናገር ለጥያቄዎቻቸው መልስ መፈለግ ወይም በበቂ ሁኔታ ሊመልስላቸው ወደሚችለው ሰው ዘንድ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

ልጆች አስደንጋጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጥያቄዎችን እንኳ ቢጠይቁ ልንቆጣቸውም ሆነ ልናስደነግጣቸው በፍጹም አይገባም። እግዚአብሔር የት ነው የሚኖረው? እሱን ማን ፈጠረው? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በምን አውቃለሁ? ብለው ልጆች ሊጠይቁ ይችላሉ። ነገር ግን ከምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በጣም የከፋው ልጆችን ማስደንገጥና ጥያቄዎቻቸውን ማጣጣል ነው።

ወጣቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ የሚያስቡበትን ሥነ መለኮታዊና ሥነ አመክንዮአዊ መንገዶችን ልናስተምራቸው ይገባል።

### መ. ወጥንት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ ከልጆችህ ጋር ኑር

ልጆች ግብዝነትን ከሩቅ ነቅሰው የማውጣት ታላቅ ችሎታ አላቸው። በእርግጥ ወጥንት ያለውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ከልጆችህ ጋር በጋራ የማትኖር ከሆነ ልጆችህ ክርስትናን ቢያወግዙ አትደነቅ!

ወጥንት ስንል ፍጹምነት ማለት አይደለም። ልጆች ችግርን እንዴት እንደምትፈታ ሊማሩ ይገባቸዋል። ለምሳሌ፡- ልጆችህ ሲበድሉህ ወይም ሲያጠፉ ለእነርሱ ያለህ ይቅርታ። አንተ ስታጠፋ ጥፋትህን በማመን እንዴት ይቅርታ እንደምትጠይቅ የእምነትህን እውነታ በኃይል ይገልጠዋል።

### ሠ. ልጆች እውነታዎችን የሚመዝኑበት ጥሩ ዘዴ ስጣቸው

ልጆች እውነቱን ከውሸት እኩይን ከሰናይ የሚለዩበትን ዘዴ አስተምራቸው። ዘዴዎች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ከውሸት ልንለይባቸው የምንችልባቸው መሣሪያዎች ናቸውና። ምንም እንኳ በእያንዳንዱ አስተምህሮ ሐሰቱንና እውነቱን ጠልቀን ባንናገርም በሚገጥሙን አጋጣሚዎች ሁሉ ዘዴዎች ማንኛውንም ነገር የምንመዝንባቸው መሣሪያዎች ናቸው።

## 4.3 የይሖዋ ምስክሮችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ተመካሪ አቀራረብ መሠረታዊ እውነታ[1]

የይሖዋ ምስክሮች ሰዎች ናቸው። ማንኛውም ሰው በሃይማኖቱ ለመቀየት ያለውን ፍላጎት አላቸው። እንደማንኛውም ሰው ስሜት ስላላቸው ሊከበሩ፥ "ትክክል" እንደሆኑ ሰዎች እንዲያውቁላቸው ይፈልጋሉ።

የይሖዋ ምስክሮች እርስ በእርሳቸው የተለያዩ ናቸው። ሁሉም የይሖዋ ምስክር አንድ ዓይነት አይደለም! አንዳንዱ ለራሱ ራሱ እንዲያስብ ይፈልጋል! አንዳንዱ ሁሉን ሰዎች እንዲነግሩት ይሻል። አንዳንዶቹ ጥሩ አድማጮች ናቸው! ሌሎቹ ደግሞ ጥሩ አድማጭ አይደሉም።

1. Bowman Jehovah's Witnesses ገጽ. 71-74



የይሖዋ ምስክሮች እንደ ማንኛውም ኃጢአተኛ ሰው ስለሆኑ ትዕቢት፥ ጉራ፥ ቁጣ አለባቸው። እንዲሁም እግዚአብሔርን የመፈለግ ፍላጎት ያላቸው ይመስላሉ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ካልረዳቸው በስተቀር ልባቸውን በመቀየር ወደ እውነት ሊመጡ በፍጹም አይችሉም።

. የይሖዋ ምስክሮች በየሳምንቱ በርካታ ትምህርቶችን ይማራሉ። ስለዚህም በየአገሩ ያሉ ሁሉ ተመሳሳይ አመለካከት አላቸው። በአማካኝ ስልሳ ገጽ የድርጅቱን ጽሑፍ ከአራት ገጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር በማያያዝ በየሳምንቱ ማንበብ ይጠበቅባቸዋል[2]።

የይሖዋ ምስክሮች ከመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በስተቀር የማንኛውንም የሃይማኖት ድርጅት ጽሑፎችን ማንበብ አይፈቀድላቸውም። በተለይ "አፈንጋጮች" ["apostates"] በሚሉአቸው ድርጅቱን በለቀቁ ሰዎች፥ እንዲሁም "ተቃዋሚዎች" በሚባሉት በድርጅቱና በአስተምህሮቱ ላይ ሂስ የሚሰነዝሩ ሰዎች የተጻፉ ጽሑፎችን ማንበብ አጥብቆ የተከለከለ ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ለድርጅታቸው ታማኞች መሆን እንደሚገባቸው ይማሩሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ያለመጠበቂያ ግንብ ጽሑፍ አንብቦ መረዳት በጥብቅ የተከለከለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ያለመጠበቂያ ግንብ መረዳት በፍጹም አይቻልም።

### ጠቃሚ ምክሮች

የይሖዋ ምስክሮችን አክብራቸው [እነርሱ ባያከብሩህ እንኳን]። መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ መሠረተ እምነትህን ጠንቅቀህ እወቅ። [የይሖዋ ምስክሮች ከእነርሱ በስተቀር ሌላ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቅ፥ እንደነርሱም የተማረ ያለ አይመስላቸውም]።

የይሖዋ ምስክሮች እምነት ከአንተ ጋር በሚስማማበት ነጥብ ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእነርሱ ጋር ተስማማ። ለምሳሌ፡- የሰዎች ብቸኛ ተስፋ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሆነ እመን (ተስማማ)፤ ነገር ግን ለምን የእግዚአብሔር መንግሥት በ1914 ዓ.ም. እንዳልመጣ ግስጽላቸው። የሰው ልጆች አዲሲቱን ምድር እንደሚወርሱ እመን፤ ነገር ግን ለሰው ልጆች ሁለት ተስፋ እንደሌለ፥ ታላቁ መንጋ ምድር፥ ቅቡዓን ሰማይ ይወርሳሉ የሚለው ትምህርት ትክክል እንዳልሆነ አስተምራቸው።

2. David A Reed. How to Rescue Your Loved One from the Watchtower (Grand Rapids: Baker, 1989), ገጽ. 9

## መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ጠይቃቸው

የይሖዋ ምስክሮች "በተቃዋሚ" ["opposer"] ጎራ ፈርጀውህ ካንተ ጋር መወያየታቸውን እንዳያቆሙ ወይም ልባቸውን እንዳይዘጉ ወሳኝ የሆኑ፥ ቁልፍ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ራሳቸውን መልሱን እንዲመልሱት እርዳቸው። ለምሳሌ፦ ለቅቡዓን ብቻ የተሰጡ በረከቶችን አስመልክቶ፦ "ክርስቶስን የማየት ዕድል ያላቸው ቅቡዓን ብቻ ናቸው ወይስ ሁሉም ክርስቲያን?" "እንደ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል የሚኖራቸው ቅቡዓን ብቻ ናቸው ወይስ ክርስቲያኖች ሁሉ?" በዚህ ርዕስ ላይ ይህንን የመሳሰሉ በርካታ ጥያቄዎችን ከጠየካቸው በኋላ፥ "እውነቱ እንዲህ ከሆነ አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጻፈው ለቅቡዓን ብቻ ነው ማለት ነው?"[3]

የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮአቸው ምን ያህል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደሚቃረን አሳያቸው። ለምሳሌ፦ ዮሐ. 2፥19-22 "ኢየሱስ በቁጥር 19 ላይ 'ይህን ቤተ መቅደስ' ሲል የትኛውን ቤተ መቅደስ ለማመልከት ፈልጎ ነው?" ምናልባት "የክርስቶስ መንፈሳዊ አካልን ማለቱ ነው" ይሉን ይሆናል። ቀጠል አድርገህ እንዲህ በማለት ጠይቃቸው፦ "ኢየሱስ 'እንሣዋለሁ' የሚለው ቤተ መቅደስ ከሚፈርሰው ቤተ መቅደስ ጋር አንድ ዓይነት ነው ወይስ አይደለም?" አንድ ዓይነት አይደለም በሚለው አቋማቸው ከጸኑ በቁጥር 19 ላይ "ይህን" [this] የሚለውን አመልካች ቃል አሳያቸው። ምናልባት አሁንም "ቤተ መቅደስ" የሚለው ቃል የክርስቶስን መንፈሳዊ አካል እንጂ ቁሳዊ አካሉን አያመለክትም ካሉ፦ "በኢየሱስ ጠላቶች የፈረሰው ቁሳዊ አካል የት ሄደ?" ብለህ ጠይቃቸው። ድርጅታቸው "የክርስቶስ ቁሳዊ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል" የሚል ትምህርት ስላለው ይህንኑ ይነግሩን ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ እንበላቸው፦ "ታዲያ ቤተ መቅደሱ ወደ ጋዝነት ከተቀየረ ፈርሶ ነው የቀረው? ዳግም አልተነሣም ማለት ነው?"

ምናልባት "ቤተ መቅደስ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ክርስቲያናዊ ጉባዔን ነው" ካሉ እንዲህ ጠይቃቸው፦ "ቁጥር 21 ላይ ዮሐንስ፦ 'እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር' ሲል 'ሰውነት' የሚለውን ቃል በቀጥታ ነው የወሰደው ወይስ በተምሳሌታዊ ገለጻው [figuratively]?"። በተምሳሌታዊ ገለጻው ነው ካሉን "በቁጥር 22 ላይ ደቀ መዛሙርትን የክርስቶስ ትንቢት እውነት ነበር እንዲሉ ያደረጋቸው

3. በትምህርቶቹ መጨረሻ ላይ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች የሚለው። ርዕስ ለዚሁ ጥቅም የተዘጋጀ ነው።



ምንድን ነው?"። "ኢየሱስ በቁጥር 19 ላይ 'እንሣዋለሁ' ያለው እና በቁጥር 22 ላይ ያስነሣው አንድ ዓይነት ነገርን ወይም ሰውን ነው ወይስ የተለያየ?"። በፍጹም የተለያየ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም የተነሣው የፈረሰው ነው። ቁጥር 22 "ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሳቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ" የሚለው ገለጻ ቤተ መቅደስ የተባለው ቃል የክርስቶስን አካል እንደሚያሳይ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የይሖዋ ምስክሮችን እንዳሳታቸው በብልኀት አሳያቸው። የይሖዋ ምስክሮች እምነታቸውን ሙሉ በሙሉ በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ላይ ስላደረጉና የሌሰውን ሰው አስተምህሮአዊ አመለካከት ስለማይቀበሉ የድርጅቱን ሐሰተኛነት አጥርተው እንዲመለከቱ እርዳቸው። ለምሳሌ፦

ሀ. እንዲህ ብለህ ጠይቅ፦ "ድርጅቱ ወይም ፓስተሮቼ ካታለሉኝ፥ ስህተታቸውንም ለማመን ፈቃደኛ ባይሆኑ ከእነርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ይኖርብኛል?" (አይኖርብህም በሚለው ይስማማሉ)

ለ. "የሃይማኖት ድርጅታቸው ያታለላቸውን ሰዎች ባውቅ መታለላቸውን መናገር ያለብኝ ይመስልሃል?" (አቅጣጫችን ሊገባቸው ይችል ይሆናል ነገር ግን ይስማሙበታል)።

ሐ. "በታላቅ አክብሮት የምገልጽልህ ነገር ቢኖር በርካታ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ተከታዮቹን እያታለላቸው ነው። ከተሳሳትኩ ልትመልሰኝ ትችላለህ፤ ነገር ግን ትክክል ከሆንኩ ይህ እውነታ እንዲገባህ ያስፈልጋል። በዋቢነት ማቅረባቸው ማስረጃዎች ሁሉ የድርጅቱን ጽሑፎች ነው እንጂ። "በአፈንጋጭ" ወይም "በተቃዋሚ" የተዘጋጀ አይደለም። በዚህ መልኩ መነጋገር እንችላለን?"[4]

4. በዚህ ቅድመ ሁኔታ የሚስማሙ ከሆነ ውይይታችሁን ከመጀመራችሁ በፊት በተለይ ድርጅቱ ሥነ-ፍጻሜን አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያት ያወጣቸውን ሐሰተኛ ትንቢቶች በዋቢነት ለመጥቀስ መዘጋጀት ያስፈልጋል። ፎቶኮፒ የተደረጉ ዶክመንቶች (ማስረጃ ጽሑፍ) በሚከተለው አድራሻ መጻፍ ማስመጣት ይቻላል፦

Witness Inc.
P. O. Box 597, Clayton, Ca 94517
USA

ወይም፦ "የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት" በሚለው ርዕስ ሥር ያሉትን የግርጌ ማስታወሻዎች በማቅረብ መወያየት ይቻላል። [ከላይ የጠቀስነው አድራሻ በመናፍቃን ላይ የሚሠራ ክርስቲያናዊ ድርጅት ነው። ደብዳቤዎችን በእንግሊዝኛ ይጻፉ]

**ለይሖዋ ምስክሮች የመጠበቂያ ግንብ ትንቢቶች ሐሰት መሆናቸውን አሳያቸው። ድርጅቱ ተከታዮቹን አለቶአቸዋል የሚለውን አቀራረብ በዚህም ለፍሬ መጠቀም ጥሩ ነው። ይኸውም፦ በመጀመሪያ ጥያቄህን ከድርጅቱና ከተከታዮቹ አርቀው (በእነርሱ አትጀምር) ከዚህም ወደ ድርጅታቸው መልሰው። ሐሰተኛ ትንቢት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙን እንዲነግሩህ ጠይቃቸው። መሠረታዊ ነጥቡን ከዘለሉት በትሕትና አስረቅደህ አስተካክል ወይም ጨምር። የሐሰተኛ ትንቢት ትርጉሙና መሠረታዊ ነጥቡ የሚከተሉትን ይጨምራል፦**

- **ስለ ወደፊቱ የተተነበየው ትንቢት ሐሰት መሆኑ ከተረጋገጠ።**
- **ሃይማኖታዊ ድርጅቱ እንደ ሥልጣን ምንጭ ከታየ።**
- ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል ከታየ።
- ትንቢቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተጋጨ።

ከዚያም እንዲህ ብለህ ጠይቅ፦

ሀ. "እኔ አባል የሆንኩበት ሃይማኖታዊ ድርጅት ሐሰተኛ ትንቢትን ቢተነብይ ድርጅቱን መልቀቅ ያለብኝ አይመስልህም"?

ለ. "የአንድ ሃይማኖታዊ ድርጅት አባል የሆኑ ሰዎች ድርጅታቸው ሐሰተኛ ትንቢት ቢተነብይ ተከታዮቹን ላስጠንቅቃቸው አይገባም?"

ሐ. "በታላቅ አክብሮት የምገልጽልህ ነገር በእጄ ያሉ በርካታ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ድርጅቱ ባለፉት ጊዜያት ሐሰተኛ ትንቢቶችን ማስተላለፉን ይናገራሉ። ከተሳሳትኩ ልታስተካክለኝ ትችላለህ። ነገር ግን ማስረጃዎቹ ትክክል ከሆኑ ስለ ድርጅቱ ሐሰተኛ ትንቢቶች እንድታውቅ እፈልጋለሁ"



## የይሖዋ ምስክሮችን ወደ ክርስቶስ ስማምጣት ማስወገድ ያለብን አቀራረብ

### ሀ. የተሳሳተ ግንዛቤ

የይሖዋ ምስክሮች መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያውቁ አድርገህ አታስብ። የይሖዋ ምስክሮች የራሳቸውን አስተምህሮአዊ ዘዴ እንዲሁም ይደግፉናል የሚሉአቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያውቃሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚገባ አያውቁም። የይሖዋ ምስክሮች ላገኙት ሰው ሁሉ በድፍረት የሚመሰክሩት ይደግፉናል የሚሉአቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጥንተው ነው። ይህም የይሖዋ ምስክሮች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ እውቀት ያላቸው ያስመስላቸዋል። በተለይ ከክርስቲያኖች ጋር መነጋገር ሲፈልጉ ሙሉ በሙሉ የሚደገፉት "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" በሚባለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሐፍ ላይ ነው።

የይሖዋ ምስክሮችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት የሚያስችለው ዘዴ አንድ ብቻ ነው ብለህ አታስብ። ነገር ግን በፍቅር፥ በትሕትና፥ በየዋህነትና ራስን በመግዛት የምታውቀውን እውነት ንገራቸው። መናፍቅ መሆን እውቀት የማጣት ችግር ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ችግርም ስለሆነ ለለ እነርሱ 'እንደምታጠና ሁሉ አጥብቀህ ጸልይላቸው። ወደ እውነት ሁሉ ሰዎችን የሚመራው የእግዚአብሔር መንፈስ ነውና።

### ለ. ጠቃሚ ያልሆኑ ባሕርያት

እኔ ክርስቲያን ነኝ ብሎ የይሖዋ ምስክሮችን ማባረር አግባብ አይደለም። 2ዮሐ. 10–11 ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ጋር መወያየትን አይከለክልም። ቁጥር 10 በቤታችሁ አትቀበሉት ሲል ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በቤታችሁ እያሳረፉችሁ ሌሎችን እንዲሰብኩ አታድርጓቸው ማለቱ ነው። ይህም የጥንት ክርስቲያኖች ልማድ ነበር ማቴ. 10፥11። ሌላው ቤት የሚለው ቃል የጥንት ክርስቲያኖች ያመልኩባቸው የነበረውን የቤት ቤተ ክርስቲያናትን ሊያመለክት ይችላል። እውነቱ እንዲህ ከሆነ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን የቤተ ክርስቲያንን መድረክ መስጠት እንደሌለብን የሚያስተምረን ነው።

የይሖዋ ምስክሮች መሳሳታቸውን እንዲቀበሉ አታስገድድ ሰዎች ትዕቢት ስላለባቸው መሳሳታቸውን እያወቁ ተሳስቻለሁ ላይሉ ይችላሉ። ወደ ቤታቸው ሄደው እንዲያስቡበት ፍቀድላቸው። ብዙውን ጊዜ

የይሖዋ ምስክሮች ሁለት ሁለት ሆነው ስለሚሄዱ አንደኛው የተናገርከውን እንኳ ቢቀበል ጓደኛውን ስለሚፈራ ችግርም ስለሚደርስበት መቀበሉን ላይገልጽ ይችላል።

የማታውቀውን ነገር አትናገር። በመጀመሪያዎቹ ቅጂዎች ማለትም በግሪኩና በዕብራይስጡ ላይ ያለህ እውቀት ጠንካራ ካልሆነ ጠለቅ ባሉ ስዋስዋዊ ጉዳዮች ላይ አትነጋገር። እርግጠኛ ባልሆንክባቸው አስተምህሮአዊ ርዕሶች ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ላይ አትወያይ። የይሖዋ ምስክሮች የጠየቁህን ጥያቄ የምታወቀው ከሆነ እንደማታውቀው ነገር ግን ጥያቄውን ወስደህ መልስ እንደምትፈልግለት በየዋህነት ንገራቸው።

## ዋቢ መጻሕፍት
## በክርስቲያን ጸሐፊያን የተጻፉ መጻሕፍት


- Bowman, Robert M. Jehovah's Witnesses Grand Rapids: Zondervan, 1995.
  _________ Jehovah's Witnesses, Jesus Christ, and the Gospel of John. Grand
- Rapids: Baker Book House, 1989.
  _________ Understanding Jehovah's Witnesses. Grand Rapids: Baker Book House, 1991.
  _________ Why You shoud Believe in the Trinity: An Answer to Jehovah's Witnesses. Grand Rapids: Baker Book House, 1989.
- Pinnerty, Robert U. Jehovah's Witnesses on Trial: The Testimony of the Early Church Fathers.
  Phillipsburg, N. J.: Preshyterian & Reformed, 1993.
- Gomes, Alan W. Unmasking the cults. Grand Rapids: Zondervan Publishing House,1995.
- Gruss, Edmond C. The Jehovah's Witnesses and Prophetic Speculation, Zd ed. Notley, N.J.: Preshyterian & Reformed, 1975.
- Hoekema, Anthony A. The Four Major Cults. Grand Rapids: Eerdmans, 1978.
- Magnani, Dvane, and Arthur Barrett. The Watchtower Files: Dialogne with a Jehovah's Witness. Minneapolis; Bethany House, 1985.
- Martin, Walter. The Kingdom of the Cults. Minneapolis, MN: Bethany House Publishers, 1982.
- Reed, David. How to Rescue Your Loved One from the Watchtower. Grand Rapids: Baker Book House, 1989.
- Rhodes, Ron. Reasoning from the Scriptures with the Jehovah's Witnesses. Eugene, Ore.: Harvest House, 1993.
- Tucker, Ruth. Anoter Gospel. Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1989.


## የሥነ-መለኮት መጻሕፍት


- Basic Christian Doctrines, ed. Carl F. Henry. Grand Rapids; Baker Book House, 1983.
- Berkhof, Lovis. Manual of Christian Doctrine. Grand Rapids: Wm. B Eerdmans Publishing Co., 1983
- Erickson, Millard J. Christian Theology. Grand Rapids: Baker Book House, 1987.
- Ryrie, Charles C. Basic Theology. Wheaton, IL: Victor Books, 1986.

## ማብራሪያዎች [አንድምታዎች]


- Bible Knowledge Commentary, Old Testament. Eds. John F. Walvoord and Roy B. Zuck. Wheaton, IL: Victor Books, 1985.
- Bruce, F. F. The Book of Acts. Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1986
- Bruce, F. F. The Epistle to the Hebrews. Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1984
- Cole, R Alan Exodus: An Introduction and Commentary. Downers Grove, IL: Inter Varsity Press, 1973.
- Eadie, John. A Commentary on the Greek Text of Epistle of Paul of the Colossians. Grand RApids: Baker Book House, 1979.
- Morris, Leon. The First Epistle of Paul to the Corinthians, Tyndale New Testament Commentaries. Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1976.
- ____________ The Gospel According to St. Luke. Grand Rapids: Wm B. Eerdmans Publishing Co., 1983.
- Robertson, A.T. Word Pictures. Nashville: Broadman Press, 1930.


## ማጣቀሻ መጻሕፍት


- Archer, Gleason. Encyclopedia of Bible Difficulties. Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1982.
- Arndt, William and Gingrich, Wilbur. A Greek English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature. Chicago: The University of Chicago Press, 1957.
- Geisler, Norman and Howe, Thomas. When Critics Ask. Wheaton, IL: Victor Books, 1992.
- New Bible dictionary. Ed. J. D. Douglas. Wheaton, IL: Tyndal House Publishers, 1982.
- New International Dictionary of New Testament Theology. Ed. Colin Brown. Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1979.


## በመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የታተሙ መጻሕፍት


- Aid to Bible Understanding. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1971.
- God's Kingdom of a Thousand Years Has Apprached. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1973.
- The Great Man Who Ever Lived. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1991.
- Holy Spirit – The Force Behind the Coming New Order! Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1976.
- "The Kingdom Is At Hand" Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1944.
- "Let Your Name Be sanctified" Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1961.
- Man's Salvation Out of World Distress At Hand! Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1961.
- Millions Now Living Will Never Die. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1920.
- New World Translation. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Scociety, 1981
- Prophecy. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1929.
- Qualified to Be Ministers. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1955.
- Reasoning from the Scriptures. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 19
- Should You Believe in the Trinity? Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1989
- Theocratic Aid to Kingdom Publishers. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1989.
- The Truth That Leads to Eternal Life. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1968.
- Year book of Jehovah's Witnesses, 1952-1997. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1952-1997.
- You Can Live Forever in paradise on Earth. Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1982.
- "Your Will Be Done On Earth". Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1958.


## በድርጅቱ የተዘጋጁ አማርኛ መጻሕፍት


- በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ። Brooklyn: Watchtower Bible aod Tract Society, 1991.
- በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነውን? Brooklyo: Watchtower Bible and Tract Society, 1993.
- ከቅዱሳን መጽሐፎች እየጠቀሱ ማመራመር። Brooklyn: Watchtower Bible aod Tract Society, 1994.


## መናፍቃንን አስመልክቶ
## በጸሐፊው እየተዘጋጁ ያሉ መጻሕፍት

1. "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን
2. የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ? ያልተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ
3. በሥላሴ ማመን ለምን ተገባህ? ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለምን? መልስ ለይሖዋ ምስክሮች

## ምሁራን ስለዚህ መጽሐፍ ምን ይላሉ?

" 'የይሖዋ ምስክሮችና አለተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን' የተባለው መጽሐፍ የይሖዋ ምስክሮችን ትምህርትና የመጽሐፍ ቅዱስ መልስን በማስደገፍ ጥሩ ግንዛቤን ያስጨብጣል። መጽሐፍ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፥ በግል እንብበው ለመረዳት ለሚፈልጉ ሁሉ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው።"

**መጋቢ ለሊሺ ከበደ**
በወንጌላውያን ሥነ-መለኮት ኮሌጅ መምህር

"በእርግጥ 'የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን' የተሰኘው መጽሐፍ በአለተምህሮተ ሥላሴ ላይ ያለንን እምነት ከመናፍቃን ለመጠበቅ የተሳሳቱትንም በእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ለመመለስ እንዲያስችል ተደርጎ የተዘጋጀ ምሁራዊ መጽሐፍ ነው። በማንኛውም አገልግሎት የተሠማሩና ጌታን በእውነት የሚወዱ ክርስቲያኖች ሊገዙት ብቻ ሳይሆን ደግመው ደጋግመው፥ መልሰው መላልሰው ሊያነቡት የሚገባ መጽሐፍ ነው።"

**አቶ መሐሪ ታደሰ**
ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን

**ሌሎች ምሁራን ያሉትን በመጽሐፉ ጀርባ ይመልከቱ።**